# የመጨረሻው ትንቅንቅ

ሪክ ጆይነር እንደጻፈው

ትርጉም በሰሎሞን አሰፋ

ናዝሬት 2004

አሳታሚ፡- ሰሎሞን አሰፋ

የመጀመሪያ ዕትም ጥቅምት 2004/October 2011 ታተመ።

ትርጉም፡- በሰሎሞን አሰፋ

የገጽ ቅንብር ቄስ ተድላ አሰፋ

የኮምፒውተር ትየባ ማርታ አፈወርቅ

ይህንን መጽሐፍ ያለ አሳታሚው ፈቃድ በየትኛውም ዓይነት የማባዛት ዘዴ ተጠቅሞ በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ ማባዛት በሕግ የተከለከለ ነው። ይሁንና ለቅኝት፣ ለሂሳዊ አስተያየት፣ በአጭሩ መጥቀስ ግን ይቻላል።

በተለይ ካልተገለጸ በስተቀር ሁሉም ጥቅሶች የተወሰዱት በ1954 ዓ.ም ከታተመው መጽሐፍ ቅዱስ እትም ነው።

# ማውጫ

ገጽ

ምስጋና. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . I
መግቢያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . II
አስተያየት. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .III

**ክፍል አንድ**
የሲኦል ኃይላት እየተመሙ ናቸው. . . . . . . . . . . . .1

**ክፍል ሁለት**
የተቀደሰው ተራራ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .25

**ክፍል ሦስት**
የንስሮቹ መመለስ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . .44

**ክፍል አራት**
ነጩ ዙፋን. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .64

**ክፍል አምስት**
ድል ነሺዎቹ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .109

# አስተያየት

. . .ወቅቱ ከአስራ ሁለት ዓመት በፊት የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ የነበርኩበት ጊዜ ነው። የምዝገባው ቀን ስላለቀ ብዙ ተማሪዎች የሴሚስተር ክፍያው የመጨረሻው ቀን እንዳያልፍብን ለመክፈል ክፍሉን አጨናንቀነዋል። ተራዬ ደርሶ ገንዘቡን ለመክፈል በእጄ ይዤው የነበረውን አንድ መጽሐፍ ጠረጴዛው ላይ አስቀምጬ ወደ ኪሴ ስገባ ትመዘግበን የነበረች አንዲት አሜሪካዊት ሚሲዮናዊ ዓይኗን ጠረጴዛው ላይ ወዳስቀመጥኩት እንግሊዝኛ መጽሐፍ ላይ ጣል በማድረግ "ይህ መጽሐፍ የአንተ ነው?" አለችኝ። የእኔም መልስ "አዎን" ነበር። "ብዙጊዜ ደጋግሜ አንብቤዋለሁ" አለችኝ። "እኔ ደግሞ አራት ጊዜ ያህል አንብቤዋለሁ" አልኳት። "እኛ ሚሲዮናውያን በጣም የምንወደው ድንቅ መጽሐፍ ነው" አለችኝ ያቺ አሜሪካዊ ሚሲዮናዊት። ይህን ንግግራችንን ያደመጡ ተማሪዎች ስወጣ ጠብቀው ዙሪያዬን ከበቡኝ። ብዙዎቹም ፎቶ ኮፒ እያስነሱ ወሰዱት። ይህ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ዛሬ ወንድማችን ስሎሞን "የመጨረሻው ትንቅንቅ" ብሎ የተረጎመው The Final Quest የተሰኘው መጽሐፍ ነበር።

በመሆኑም ይህ መጽሐፍ በመጨረሻው ዘመን ለምትገኘው ቤተ ክርስቲያንና አገልጋዮቿ ልዩ፣ ልዩ ችግሮቿ መንስኤዎቻቸውና መፍትሄዎቻቸውንም ጭምር የያዘች እግዚአብሔር በጊዜው የሰጠን በረከት በመሆኗ ክርስቲያኖች፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች የግድ ሊያነቡት ይገባል እላለሁ። ወንድማችን ስሎሞን አሰፋም በጥሩ ሁኔታ ወደ አማርኛ መልሰህ ለምድራችን ለንባብ በማብቃትህ ከልቤ እግዚአብሔር ይባርክህ ለማለት እወዳለሁ።

መጋቢ ታደሰ ንጋቱ



# ራዕዩን የተቀበልኩበት መንገድ

ይህንን ራዕይ በተመለከተ ይደርሱኝ ከነበሩ እጅግ የተለመዱ ጥያቄዎች መካከል አንዱ "ራዕዩን እንዴት ተቀበልከው?" የሚለው ነው። እኔም ጥያቄው አስፈላጊ እንደሆነ ስለማምንበት መልሱን ከዚህ በታች በዝርዝር ለመስጠት እሞክራለሁ። አስቀድሜ ግን ራዕይና "ትንቢታዊ ልምምዶች" ስል ምን ማለቴ እንደሆነ ላብራራው።

"ትንቢታዊ ልምምዶች" ያልኳቸው ቁጥራቸው በርካታና የተለያዩ ሲሆኑ ጌታ በቅዱሳት መጻህፍቱ ለህዝቡ የተናገረባቸውን የመጀመሪያዎቹን መንገዶችንም ሁሉ የሚያካትቱ ናቸው። ጌታ ዛሬም እንደ ትናንት ያው በመሆኑና ለህዝቡ መናገሩን ፈጽሞ ስላላቋረጠ እነዚህ ልምምዶች ወደፊትም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ሁሉ በተመሳሳይ መንገድ የመታየታቸው ነገር ይቀጥላል። ሐዋርያው ጴጥሮስ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ምዕራፍ አንድ ላይ በሰበከው ስብከቱ እንዳስረዳው ህልሞች፣ ራዕዮችና ትንቢቶች የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስና የመጨረሻው ዘመን ዋነኛ ምልክቶች ናቸው። እኛም ወደ መጨረሻው ዘመን መገባደጃ ላይ በእጅጉ እየተቃረብን በመሆናችን እነዚህ ምልክቶች በዘመናችን የመለመዳቸው ነገር እየጨመረ መጥቷል።

እነዚህ ምልክቶች በእጅጉ እየተለመዱ የመጡበት አንዱ ምክንያት ግቦቻችንን ወደ ፍጻሜ ለማምጣት በዚህ ዘመን አስፈላጊ በመሆናቸው ነው። አሳዛኙ ነገር ግን ቅዱሳት መጻህፍትንና እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር ባለው ኅብረት ውስጥ ያሉትን የትንቢታዊ መገለጦችን አስፈላጊነት ከአብዛኛው ክርስቲያን ይልቅ ሰይጣን በተሻለ ሁኔታ የሚያውቅ መሆኑና የሃሰት ስጦታዎቹን ለአገልጋዮቹ እጅግ በላቀ መጠን የማፍሰሱ እውነት ነው። ሆኖም እውነተኛው የብር ኖት ከሌለ ሃሰተኛ የብር ኖት የሚባል እንደማይኖር ሁሉ ትክክለኛው እውነታም ከሌለ ሃሰተኛው አይኖርም።

ጌታን አዳኜና መድሃኒቴ አድርጌ የተቀበልኩት በ1922 ዓ.ም ሲሆን ከዚያም ብዙ ሳልቆይ ወዲያውኑ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ምዕራፍ ሁለት ላይ የተጻፈውን መልዕክት አንብቤ "የመጨረሻው ዘመን" የሚባሉት ክስተቶች እነዚህ ከሆኑ እግዚአብሔር እኛን የሚናገርባቸውን እነዚህን መንገዶች መረዳቴ አስፈላጊዬ እንደሆነ ተረዳሁ። በመጀመሪያ ደረጃ እነዚህን ልምምዶች ከጌታ ለመቀበል ስለ መጸለዬ የማስታውሰው ነገር ባይኖርም ስለ እነርሱ ለማወቅና በይበልጥም ኃይሉን ለመቀበል ግን መጸለይ ጀመርኩ።

ከዚያን ጊዜ አንስቶም በተለያዩ ጊዜያት በተደጋጋሚ ባየኋቸው ራዕዮች ውስጥ አልፌያለሁ። እነዚህን መሰል መንፈሳዊ ልምምዶችን ያላየሁባቸውና ያልተቀበልኩባቸው ረዥም ጊዜያትን ያሳለፍኩ ብሆንም በኋላ ላይ ግን ከዚህ በፊት ያየኋቸው አንድም ተደጋግመው ወይም ይበልጥ በኃይለኛ ሁኔታ ተመልሰው እየመጡ ይታዩኝ ጀመር። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በሁሉቱም መንገድ ይታዩኝ ጀመር። ስለ ትንቢታዊ ስጦታ ልምምዶችና ስለ ትንቢት ጠቃሚ ትምህርትን ስለ ተማርኩኝ እነዚህን ሁኔታዎች በሙሉ በቅርቡ በሚታተመው መጽሐፌ ላይ በይበልጥ በዝርዝር እጠቅሳቸዋለሁ።

ትንቢታዊ መገለጦች በርካታ ደረጃዎች አሏቸው። የመጀመሪያው "አግራሞትን" (መደነቅን) ያካተተው እውነተኛው ትንቢታዊ መገለጥ ሲሆን ይህ መገለጥ ትክክለኛው ልምዱ ባላቸውና መንፈሳዊ ነገርን ለመረዳት ፈጣን በሆኑ ሰዎች ከተተረጎመ ጠቀሜታው የተለየ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ በዚህ ደረጃ ላይ "መገለጦች" ከገዛ ራሳችን ስሜቶች፣ ሚዛናዊነትን ከመሳትና ከአስተምህሮቶቻችን ተጽዕኖ ሊደርስባቸው ስለሚችል በዚህኛው ደረጃ ላይ የትኛውም መገለጥ ቢመጣ "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" የሚለውንና ሌሎች ይህን መሰል ቃሎችን ላለመጠቀም ወስኛለሁ።

ራዕዮች በአግራሞት (በመደነቅ) ደረጃ ሲመጡ ስለሚችሉ ረጋ ብለን "በልቦናችን ዓይኖች" መለየት ነው ያለብን። በተለይም ጳውሎስ በኤፌሶን 1:18 ላይ እንደተናገረው "የልቦናችን ዓይኖች" ይበልጥ በተከፈቱ መጠን እነዚህ ነገሮች የበለጠ ኃይለኛና ጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለሆነም ይህን ዓይነቱን ራዕይ በመቀበል ልምምዱ ያላቸው ሰዎች ራዕዩን በሚቀበሉበት ወይም በሚተረጉሙበት ጊዜ በጣም የተለየና ትክክለኛም ሊሆን ይችላል።

ቀጣዩ የመገለጥ ደረጃ ለልባችን ልዩ አብርሆት የሚሰጠውን የመንፈስ ቅዱስን ቅባት ወይም የጌታን ጎልዎት መገኘትን መረዳት ነው። ይህ ዓይነቱ መገለጥ አብዛኛውን ጊዜ ወደ እኔ የሚመጣው ስጽፍ ወይም ንግግር ሳደርግ ሲሆን ስለምናገረው ርዕሰ ጉዳይ ትክክለኛነት ወይም አስፈላጊነት እጅግ የላቀ በራስ የመተማመን ስሜትን የሚሰጠኝ ነው። ምናልባትም ሐዋርያት የአዲስ ኪዳን መልዕክቶቻቸውን በጻፉበት ወቅት የተለማመዱት ምሪት ይሄንን እንደሆነ ነው የማምነው። ይህ መገለጥ ትልቅ በራስ የመተማመንን መንፈስ ቢሰጠንም እንኳን አሁንም ድረስ አግባብነት በሌላቸው ጥላቻዎቻችንና አስተምህሮቻችን ወዘተ. ተጽዕኖ ሊደርስበት የሚችል የመገለጥ ደረጃ ነው። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ በመልዕክታቱ ውስጥ በተወሰኑ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ አስተያየቱን ሲሰጥ የጌታ መንፈስ ከእርሱ ጋር እንደሚስማማ



የሚናገረው። በአጠቃላይ ከትንቢት ጋር ስንገናኝ ከቀኖናዊነት (ከግትረኝነት) ይልቅ ትህትና ይበልጥ አስፈላጊ ነው።

ከአግራሞት (መደነቅ) ይበልጥ ላቅ ባለ ደረጃ ላይ የሚከሰቱት ደግሞ "ግልጽ ራዕዮች" ናቸው። የጌታ ጎልዎት ወይም የቅባቱ መገኘት በሚሰማን ጊዜ እኛ ካለን መረዳት የበለጠ ነው ግልጽነትን የሚሰጡን። በግልጽ የሚታዩ ራዕዮች ውጫዊ ሲሆኑ፣ የሚታዩትም ልክ ፊልም እንደምንመለከተው በግልጽ ነው። እነዚህን ራዕዮች በራሳችን ቁጥጥር ስር ማዋል ስለማንችል በዚህ መገለጥ ውስጥ ሊመጣ የሚችለው መዘበራረቅ በጣም አናሳ እንደሆነ ነው የማምነው።

ሌላው የትንቢታዊ ልምምድ ከፍተኛው ደረጃ፣ ጴጥሮስ ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት እንዲሄድና ወንጌልን ለመጀመሪያ ጊዜ ለአህዛብ እንዲሰብክ በታዘዘበት ወቅት የተመለከተውና፣ ጳውሎስም በሐዋርያት ሥራ 22:17 ላይ በቤተ መቅደስ ሲጸልይ እንደመጣበት ዓይነት ያለው ተመስጦ ነው። ቅዱሳት መጻህፍትን በጻፉልን ነቢያት ዘንድ የተለመዱ ልምምዶች እነዚህ ተመስጦዎች ነበሩ። ተመስጦ አዕምሯችሁ ንቁ ሆኖ እያለ እንደምታዩት ህልም የምታዩት መንፈሳዊ ልምምድ ነው። ራዕይ በግልጽ ስታዩ "የፊልም ስሌዳን" ከማየትም በበለጠ ባልተለመደ መንገድ እያያችሁ እንዳላችሁ ነው የሚሰማችሁ። ራዕዩን በተመስጦ ውስጥ ሆናችሁ በምታዩበት ቦታ እያላችሁ በአካባቢያችሁ በመከናወን ላይ ያለውን እንቅስቃሴ እያያችሁና እንዲያውም በዚያ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፎ ማድረግ መቻላችሁ እየጨመረም ሊሄድ ይችላል። ይህ ማለት ሕዝቅኤል ብዙጊዜ የተመለከተውንና ምናልባትም ዮሐንስ በራዕይ መጽሐፉ የዘገባቸውን ዓይነት ራዕዮች ማለት ነው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት ራዕዮች ሁሉም የጀመሩት ከህልም ሲሆን፣ አንዳንዶቹን ታላቅ የጌታ ጎልዎት መገኘት በተሰማኝ ጊዜ፣ አብዛኞቹን ግን በተመስጦ ደረጃ ያየኋቸው ናቸው። አብዛኞቹን ያየኋቸው በዙሪያዩ እየተካሄደ ያለውን እንቅስቃሴ እያየሁና እንዲያውም ስልክ ሲደወልልኝ እንኳ አንስቼ ማነጋገር በምችልበት ሁኔታ ውስጥ ነበር። በዚህ መካከል የሆነ ነገር ጣልቃ ሲገባ ወይም ነገሮች እየከበዱ ሲመጡ ተነስቼ በአካባቢው በእግሬ ወዲያና ወዲህ እያልኩ ስመላለስ እቆይና ተመልሼ ስቀመጥ ራዕዩን ወዲያውኑ እንደገና ካቋረጥኩበት ማየት እጀምር ነበር። ልምምዱ አንዱ እየከበደ ከመጣ ተነስቼ የጌታን ፊት ወደምፈልግበት ተራራ ላይ ወደሚገኘው የጸሎት ክፍሌ እሄድና ከዚያም ተመልሼ ወደ ቤቴ እመጣለሁ። ከሳምንት ቆይታ በኋላ ደግሞ ተመልሼ እወጣና ወዲያውኑ ካቆምኩበት እጀምር ነበር።

እነኚህን ልምምዶች እንዴት አድርጌ "እንደማበራቸው" በፍጹም ባላውቅም ሁልጊዜ በፈቃዴ የማጥፋት ነጻነቱ ግን ነበረኝ። የዚህ ራዕይ ሰፊው ክፍል ወደ እኔ የመጣው ሁለት ጊዜ በጣም አመቺ አይደለም ብዬ በማስበውና አስፈላጊ የሆነውንና የመጨረሻ ማስረከቢያ ቀኑ የደረሰብኝን ሥራዬን ለመስራት ወደ ክፍሌ ከገባሁ በኋላ ነበር። ከዚህ የተነሳም ሁለቱ ጋዜጦቻችን መውጣት ከነበረባቸው ጊዜ ትንሽ ዘግየት ብለው ወጡ። ያሰራጨሁትን የመጨረሻ መጽሐፌን አጠናቅቀዋለሁ ብዬ ተስፋ ያደረኩት ከጥቂት ወራት በፊት ቢሆንም ጌታ ግን ስለ እኔ የመጨረሻ ማስረከቢያ ቀን ግድ ያለው አይመስልም ነበር!

በህልምና በተመስጦ ውስጥ እጅግ የላቁ ስጦታዎች ናቸው ብዬ የምላቸው መናፍስትን መለየትና የዕውቀት ቃል ናቸው። አንዳንድ ጊዜ አንድን ሰው ስመለከት ወይም ስለ አንድ ቤተ ክርስቲያን፣ ወይም ስለ አንድ የወንጌል አገልግሎት (ሚኒስትሪ) ስጸልይ ስለ እነርሱ በተፈጥሮ ዕውቀት የማላውቃቸውን ነገሮች ማወቅ እጀምራለሁ። በእነዚህ ትንቢታዊ ልምምዶች ወቅት እነዚህ ስጦታዎች በግል "እውነተኛ ሕይወቴ" ተለማምጄው በማላውቅበት ሁኔታ በቅደም ተከተል ይሰሩ ነበር። ለዚህም ነው በዚህ ራዕይ ውስጥ የክፋት ሠራዊቱን ስልትና አቅማቸውን ሁሉ በአንድ ጊዜ ማየት የቻልኩትና፣ ያወቅሁት። ይህ ዕውቀት ወደ እኔ እንዴት እንደሚመጣ ባላውቅም የማውቀው ግን እጅግ ብዙ ዝርዝር ርዕሰ ጉዳዮችን ይዞ ሲመጣ ነው። አንዳንድ ጊዜ ወደ አንድ ነገር ወይም ወደ አንድ ሰው እመለከትና የዚያን ሰው ያለፈ፣ የአሁንና የወደፊት ህይወቱን በሙሉ በአንድ ጊዜ እረዳለሁ። የዚህን መጽሐፍ ጊዜና ቦታ ለመቆጠብ ስል ይህንን ዕውቀት እንዴት እንደ ተቀበልኩት ዝርዝር ማብራሪያ ውስጥ ሳልገባ አካትቼዋለሁ።

## ትንቢታዊ መገለጦችን መጠቀም

የትኛውም ዓይነት ትንቢታዊ መገለጥ፣ አስተምህሮን (ዶክትሪንን) ለመመስረት በሚል ዓላማ ጥቅም ላይ መዋል አለበት ብዬ እንደማላምን ይህንን አስቀድሜ በአጽንዖት መግለጽ ይኖርብኛል። አስተምህሮን ለመመስረት ቅዱሳት መጻህፍቱ ምሉዕ እና በቂ ናቸው። ትንቢታዊ መገለጦች ሁለት መሠረታዊ ጠቀሜታዎች አሏቸው። የመጀመሪያው በተወሰኑ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ አሁን ያለውን ወይም የወደፊቱን የጌታን ፈቃድ መግለጥ ነው። ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን ጳውሎስ ወደ መቄዶንያ እንዲሄድ የተገለጠለት ህልምና ኢየሩሳሌምን በፍጥነት ለቆ እንዲወጣ የተቀበለው ተመስጦ ነው። ለዚህ ትንቢታዊ መገለጥ ለእኛ ምሳሌ ከሚሆኑን አንዱ በአጋቦስ አገልግሎት



የተገለጠውና በመላው ዓለም ላይ ሊደርስ ያለው የርሃብ አደጋ ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ ከጳውሎስ የኢየሩሳሌም ጉብኝት ጋር የተገናኘው ነው።

እነዚህን የመሳሰሉ መገለጦች በግልጽ ባይታዩም በቅዱሳት መጻህፍቱ ውስጥ ለተሰጡት አስተምህሮዎች አብርሆትን ሲሰጡ ግን እንመለከታለን። ለምሳሌ ያህል የጴጥሮስ ተመስጦ የእግዚአብሔርን ፈቃድና ቅዱሳት መጻህፍቱ በጣም በግልጽ ስለሚናገሩት (አህዛብ ወንጌልን መቀበል ስለመቻላቸው) ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች፤ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ገና ስላልደረሰችበት እውነት ስለ ሁለቱም አብርሆትን የሚሰጡ ናቸው።

በዚህ መጽሐፍ የቀረቡት ራዕዮች አንዳንድ ስልታዊ መገለጦችን የያዙ ሲሆኑ፤ እውነቱን ለመናገር ከአሁን በፊት ፈጽሞ አይቼ የማላውቃቸውን፤ ነገር ግን አሁን በግልጽ በተመለከትኳቸው አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎች ላይ አብርሆትን የሚሰጡ ናቸው። ይሁን እንጂ በእነዚህ ልምምዶች ያወቅኋቸውን አብዛኞቹን አስተምህሮቶች በሕይወት ኖሬያቸዋለሁ ብዬ መናገር ባልችልም እንኳን የበሩልኝ ግን ነበሩ። ጳውሎስ ብዙጊዜ ለራሱና ለሚያስተምረው ትምህርት እንዲጠነቀቅ ለጢሞቴዎስ ስለሰጠው ማሳሰቢያ አስባለሁ። በዚህ ልምምዴ ውስጥ ከተነገሩኝ አብዛኞቹ ቃሎች ብዙጊዜ የጠቀሙኝን ትምህርት አግኝቼባቸዋለሁ። እኔው ራሴ ሳስተምራቸው የነበሩ ትምህርቶችን እንኳን አንዳንዶቹን ተግባራዊ ማድረግ በሚገባኝ መንገድ ከማድረግ ጎድዬ እንደነበርም ተረድቻለሁ፡ በዚህም ምክንያት እነዚህን አብዛኞቹን እንደ ተግሳጽ ስቀበላቸው በሌል በኩልም ለሁሉም ሰው የሚሆኑ መልዕክቶች እንደሆኑ ስለተሰማኝ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ጠቅሻቸዋለሁ።

አንዳንድ ሰዎች ይህንን መጽሐፍ *የመናኝ ጉዞ* እንደተባለው መጽሐፍ በሦስተኛ ሰው አድርጌ እንድጽፈው አበረታተውኝ ነበር። እኔ ግን ከብዙ ምክንያቶች የተነሳ እንደዚያ አድርጌ ላለመጻፍ ወሰንኩ። በመጀመሪያ የፈጠራ ግኝቱ ባለቤት መሆንን ብወደውም የተቀበልኳቸው ራዕዮች ባለቤት ባለመሆኔ ግን አንዳንድ ሰዎች የግል የፈጠራ ውጤቴ አድርገው ይወስዱብኝና ስህተት ይሆናል ብዬ ተሰማኝ። ሌላው ምክንያት ይበልጥ ትክክል ልሆን እችላለሁ ብዬ ስለተሰማኝ እነዚህን ልምምዶች ልክ እንደ ተቀበልኳቸው በተግባር በሕይወቴ ላዛምዳቸውና በተቀበልኳቸው መንገድም ለማስተላለፍ የተቻለኝን ሁሉ አድርጌያለሁ። ይሁንና ትልቁ ድክመቴ ግን ዝርዝር ነገሮችን ማስታወስ አለመቻሌ መሆኑን ተረዳሁ። አንዳንዴ በዚህ ራዕይ ውስጥ በተወሰኑ ዝርዝር ጉዳዮች ዙሪያ የራሴን የማስታወስ ችሎታ ጥያቄ ውስጥ እከተዋለሁ።

ስለዚህ ስህተት የሌለባቸው ቅዱሳት መጻህፍት ብቻ በመሆናቸው የትኞቹንም ይህን መሰል መልዕክቶችን በቃሉ ብርሃን መመርመር ትክክል እንደሆነ ነው የማምነው። ስለሆነም ይህንን መጽሐፍ በምታነቡበት ጊዜ የጌታ መንፈስ ወደ እውነት እንዲመራችሁና የትኛውንም ገለባ ከስንዴው እንዲለይላችሁ ልባዊ ጸሎቴ ነው።



# ክፍል አንድ

# የሲኦል ኃይላት

# እየተመሙ ናቸው



# ክፍል አንድ
# የሲኦል ኃይላት እየተመሙ ናቸው

አጋንንታዊ ሠራዊቱ በዓይኔ ማየት እስኪሳነኝ ድረስ እጅግ ብዙ ሲሆን እያንዳንዳቸውም የተለያዩ ሰንደቅ ዓላማዎችን ተሸክሞ በተሰለፈ ክፍለ ጦር ስር ተከፋፍለው ተሰልፈው ነበር። ትላልቆቹ ክፍለ ጦሮች ትዕቢት፣ ራስን ማጽደቅ፣ ስምን ማስጠራት፣ ራስ ወዳድነት፣ ያለ አግባብ (በጭፍን) መፍረድና ቅናት የሚሉ ሠንደቅ ዓላማዎችን በያዘ ጦር ስር ተሰልፈው ነበር። በዓይኔ ማየት ከምችላቸው ከእነዚህም ሌላ እጅግ በርካታ ሌሎች ክፍለ ጦሮችም ተሰልፈው ነበር። ይሁንና ከገሃነም እየወጣ ከመጣው ከዚህ አስፈሪ መንጋ ፊት በግንባር ቀደምነት የተሰለፉት ግን እጅግ ኃያላን ይመስሉ ነበሩ። የዚህ ሠራዊት መሪ ደግሞ የወንድሞች ከሳሽ የሆነው ራሱ ሰይጣን ነበር።

ይህ መንጋ ሠራዊት የታጠቃቸው የጦር መሳሪያዎች በላያቸው ላይ ስሞቻቸው ተጽፎባቸው ነበር። ሰይፎቹ ዛቻ፣ ጦሮቹ ክህደት፣ ቀስቶቹ ሃሰት፣ ክስና ስም ማጥፋት ይባሉ ነበር። መራርነት፣ ርኩሰት፣ አለመቀባበል፣ ትዕግስት ማጣት፣ ይቅር አለማለት የተባሉ ስሞች ያሏቸው ጥቂት የአጋንንቱ ቡድን አባላትም ለዋናው ውጊያ ከዚህ ሠራዊት ፊት ቀድመው እንዲጓዙ ተልከው ነበር።

እነዚህ የአጋንንቱ ቡድን አባላት ቁጥራቸው አናሳ ቢሆንም ኃይላቸው ግን ከኋላቸው ተሰልፎ ከሚገሰግሰው በርካታ ክፍለ ጦር የሚተናነስ አልነበረም። ቁጥራቸው አናሳ የሆነው ደግሞ ስልታዊ ምክንያት ብቻ ነበር። እነዚህ ጥቂት አጋንንታዊ ቡድኖች ልክ ዮሐንስ መጥምቁ ህዝቡን በጥምቀት ለጌታ ለማዘጋጀት ብቻውን የተለየ ቅባት እንደተሰጠው ሁሉ "ብዙሃኑን ህዝብ ለማጥመቅ" ልዩ አጋንንታዊ ኃይልን የለበሱ ነበሩ። አንዱ የመራርነት አጋንንት በህዝብ ወገን ሁሉ ወይም ባህሎች ላይ እንኳን ሳይቀር መርዙን መርጨት ይችል ነበር። የርኩሰት አጋንንቱ ራሱን ከአንድ የትያትር፣ የፊልም ወይም የንግድ ምርት አስተዋዋቂ ተዋንያን ጋር እንኳን በማቆራኘት ቁጥሩ እጅግ በርካታ የሆነን ህዝብ እንደ ኤሌክትሪክ ያለ ኃይል እየላከ በመምታት "ያፈዛቸውና ያደነዝዛቸው" ነበር። ይሄ ሁሉ ደግሞ ቀጥሎ ለሚመጣው ለታላቁ የክፋት መንጋ መንገድ ጠርጎ ለማዘጋጀት ነበር።



ይህ ሠራዊት እየገሰገሰ ያለው በተለይ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥቃት ቢሆንም ጥቃቱን ግን በተቻለው ሁሉ በመንገዱ ባገኘው ሁሉ ላይ ይሰነዝር ነበር። ይሄ ደግሞ ብዙ ህዝብን በንስሃ ወደ ቤተ ክርስቲያን መልሶ ለማፍሰስ የተወሰነውን መጪውን የእግዚአብሔርን ሥራ አስቀድሞ ለማስናከል የተደረገ ጥረት እንደሆነ ነው የተረዳሁት።

የዚህ ሠራዊት ቀዳሚ ስልቱ በየትኛውም የግንኙነት ደረጃ ላይ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትን እርስ በርሳቸው፣ ማለትም ማህበረ ምዕመናንን ከመጋቢዎቻቸው፣ ባሎችን ከሚስቶቻቸው፣ ልጆችን ከወላጆቻቸው ማጣላትና ማበጣበጥ ነበር። የዚህ ሠራዊት ቡድን አባላት ግለሰቦችን በመራርነት፣ በርኩሰት፣ ሰውን በማግፋት፣ ወዘተ. መንፈስ በመሙላት በተቻላቸው መጠን በየአብያተ ክርስቲያናቱ ወይም በቤተሰብ ውስጥ ያለውን ክፍተት ለማስፋት የሚላኩ ነበሩ። ከዚያም ቀጣዮቹ ክፍለ ጦሮች የዚህን ጦርነት ሰለባዎችን ሙሉ በሙሉ በቁጥጥራቸው ስር ለማዋል በተከፈተላቸው ክፍተት ሁሉ አልፈው ይገባሉ።

የዚህ ራዕይ እጅግ አስደንጋጩ አካል ደግሞ ይህ የክፋት መንጋ የሚጋልበው በፈረስ ሳይሆን በክርስቲያኖች ላይ መሆኑ ነበር። እነዚህ ክርስቲያኖች አብዛኞቹ ጥሩ፣ ጥሩ ልብስ የለበሱ፣ የተማሩ፣ ጸባየ ሸጋዎችና ከየትኛውም ዓይነት የሕይወት ምልልስ የተወከሉ ናቸው። እነዚህ ወገኖች የክርስትና እውነቶችን በአንደበታቸው እየተናገሩ ህሊናቸውን የሚሸነግሉ ስመ-ክርስቲያኖች ናቸው። ከዚህ የተነሳም ሕይወታቸው ለጨለማው ኃያላት ተስማሚ በመሆኑ ለእነርሱ የተመደቡት አጋንንት ይበልጥ እያደጉ ተልዕኳቸውን በቀላሉ ይፈጽሙባቸው ነበር።

ከእነዚህ ስመ-ክርስቲያኖች መካከል አብዛኞቹ ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ አጋንንትን የሚያስተናግዱ ሲሆኑ ሙሉ በሙሉ የሚቆጣጠራቸው ግን አንዱ እርሱም በሰልፍ ወደ ውስጣቸው ዘልቆ በመግባት ፍላጎቱን በኃይል የሚፈጽምባቸው የየትኛውም ክፍለ ጦር አጋንንት ነበር። ምንም እንኳን ሁሉም ክፍለ ጦሮች በአንድ ላይ በሰልፍ እየተመሙ ቢሆኑም በተመሳሳይ ሁኔታ ሠራዊቱ በሙሉ ትርምስምሱ የወጣ ነው። ለምሳሌ ያህል ጥላቻን የሚዘሩት አጋንንት ክርስቲያኖቹን የሚጠሏቸውን ያህል ሌሎቹንም አጋንንት ይጠሏቸው ነበር። የቅናትን መንፈስ የሚዘሩት አጋንንት ሁሉም እርስ በርሳቸው የሚመቀኛኙ ነበሩ። የዚህ መንጋ መሪዎች አጋንንቱ እርስ በርሳቸው እንዲጣሉ የሚያደርጉበት ብቸኛው መንገድ ደግሞ በሚጋልቡባቸው ስመ-ክርስቲያኖች ላይ ጥላቻን፣ ቅናትን፣ ወዘተ. በመርጨት ነበር። ቅዱሳት

መጻህፍቱ በእስራኤል ላይ በተቃውሞ ተነስቶ የነበረው የጠላት ሠራዊት በእስራኤል ላይ ያለው ክፉ ዓላማው ሲጨናገፍበት ቀጣውን መግታት ተስኖት እርስ በርሱ እየተዋጋ ራሱን ለማጥፋት መብቃቱን እንደነገሩን እነዚህም ህዝቦች በዚጊዜ እርስ በርሳቸው እየተጣሉ ይጨራረሱ ነበር።

አጋንንቱ በእነዚህ ስመ-ክርስቲያኖች ላይ ይጋልቡባቸው እንጂ፤ ክርስቲያን ባልሆኑት ሰዎች ውስጥ እንደሚያደርጉት በእነርሱ ውስጥ እንደማያድሩባቸው ግን ልብ ብያለሁ። እነዚህ አማኞች ማድረግ ያለባቸው ነገር ቢኖር፤ ከአጋንንቱ ጋር ያላቸውን ስምምነት ማቆም ብቻ እንደሆነ ግልጽ ነው። ለምሳሌ ያህል አንድ የቅናት መንፈስን የሚረጭ አጋንንት የሚጋልብበት ስመ-ክርስቲያን፤ የቅናት መንፈስን መቃወም ሲጀምር ያ አጋንንት በእርሱ ላይ ያለውን ኃይሉን በጣም በፍጥነት ያጣል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ አጋንንቱ ጨኸቱን ማሰማት ይጀምራል፤ ያንጊዜ የዚያ አጋንንት ክፍለ ጦር አዛዥ ያንን ክርስቲያን በመራርነት መንፈስ፣ ወዘተ. እንደገና እስኪቆጣጠረው ድረስ ጥቃት እንዲሰነዝሩበት አጋንንቱን ሁሉ ያዛቸዋል። ይህ ካልሰራለትም አጋንንታዊ መናፍስቱ የመራርነት፣ የክስ፣ ወዘተ. ክፉ ሥራቸውን እንዲያጸድቁላቸው የቅዱሳት መጻህፍቱን ጥቅስ አጣመው መጥቀስ ይጀምራሉ።

የአጋንንቱ ኃይል ሙሉ በሙሉ ስር የሰደደው በማሳት መሆኑ ግልጽ ሲሆን በተለይ እነዚህን ክርስቲያኖች እግዚአብሔር እየተጠቀመባቸው እንደሆነ አድርገው እስኪያስቡ ድረስ ያስታቸው ነበር። ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ ሁሉም ራስን የማጽደቅ መንፈስን ሠንደቅ ዓላማዎች ተሸክመው ስለነበር፤ እየገሰገሰ ያለው ሠራዊት በሙሉ የእነዚህን ክፍለ ጦሮች እውነተኛ ማንነት የሚገልጹትን ሠንደቅ ዓላማዎችን ማየት እንኳን እንዳይችሉ ከልለዋቸው ስለነበር ነው።

ከዚህ ጦር በስተጀርባ የተሰለፈው ማን እንደሆነ ለማወቅ ከርቀት ስመለከት ያየሁት የራሱን የወንድሞች ከሳሽ የሆነውን አጃቢዎች ነበር። ጠላት እየተጠቀመበት ያለው ስልቱ በጣም ቀላል እንደሆነ መረዳት ስጀምር እየሆነ ባለው ነገር ተደነቅሁ። ይህ ሠራዊት እርስ በርሷ የምትለያይ ቤት እንደማትጸና ስለሚያውቅ፤ ቤተ ክርስቲያን ሙሉ በሙሉ ከጸጋው ትጎድል ዘንድ በመካከሏ ይህን የመሰለውን መለያየት ለማምጣት ይተጋል። ይህንን ሊያደርግ የሚችልበት ብቸኛ ዘዴው ደግሞ ክርስቲያኖች በገዛ ወንድሞቻቸው ላይ በጠላትነት እንዲነሱባቸው እነርሱን መጠቀም እንደሆነ ግልጽ ነው። እናም በክፍለ ጦሩ የፊት ረድፍ ላይ የተሰለፉት ሁሉም ክርስቲያኖች ወይም ቢያንስ ስመ-ክርስቲያኖች የነበሩት ለዚህ ነው። እነዚህ የሳቱ አማኞች ለከሳሹ በመታዘዝ የሚወስዱት እያንዳንዱ ርምጃ በእነርሱ ላይ ያለውን ኃይሉን



ሲያጠናክርለት፤ ይህ ደግሞ ሠራዊቱ ወደፊት ሲገሰግስ የእርሱንም ሆነ የአዛዦቹን በራስ የመተማመን መንፈስን ያሳድግለት ነበር። የዚህ ሠራዊት ኃይል የተመሠረተው እነዚህ ስመ-ክርስቲያኖች ከክፉው አካሄድ ጋር አብረው በመስማማታቸው መሆኑ ግልጽ ነው።

## ምርኮኞቹ

በመጀመሪያው ረድፍ ላይ ከተሰለፉት ከእነዚህ ክፍለ ጦሮች ኋላ ደግሞ የዚህ ጦር ምርኮኛ የሆኑ ሌሎች ብዙ ክርስቲያኖች ይጓዙ ነበር። እነዚህ ክርስቲያኖች ሁሉም የቆሰሉና የፍርሃትን መንፈስ በሚረጩ ትናንሽ አጋንንቶች ጥቃት ስር የወደቁ ነበሩ። በአጋንንቱ ሠራዊት ቁጥጥር ስር የወደቁት ሌሎች ምርኮኞች ቁጥራቸው ከአጋንንቱ ቁጥር የሚበልጥ ነው የሚመስለው። እነዚህ ምርኮኞች ሰይፍና ጋሻቸውን እንደታጠቁ ቢሆኑም እስካሁን ድረስ በእነዚህ የጦር ዕቃዎቻቸው አለመጠቀማቸው ግን የሚገርም ነው። ቁጥሩ እጅግ በርካታ የሆነ ክርስቲያን ሠራዊት የፍርሃትን መንፈስ በሚረጩ በጣም በጥቂት ትናንሽ አጋንንት ቁጥጥር ስር እስረኛ ሆነው ሲጠበቁ መቻላቸውን ማየት አስደንጋጭ ነገር ነበር። እነዚህ ክርስቲያኖች የታጠቁትን የጦር ዕቃ ተጠቅመውበት ቢሆን ኖሮ ራሳቸውን ከጠላቶቻቸው በቀላሉ ነጻ ማውጣት በቻሉ፣ ምናልባትም በክፉት መንጋው ሁሉ ላይም ከፍተኛ ውድመትን ባደረሱበት ነበር። በዚህ ፈንታ ግን ተማርከው አብረው እየተጓዙ ናቸው።

ከእነዚህ ምርኮኞች አናት በላይ ያለውን ሰማይ፤ ክፉ ቀን የተባሉ ጥንብ አንሳዎች ስለጋረዱት ሰማዩ እንደ ጨለማ ጠቁሮ ነበር። እነዚህ ጥንብ አንሳዎች አንዳንድ ጊዜ በምርኮኞቹ ትከሻ ላይ እያረፉ ያስታውኩባቸው ነበር። ይህ ትውከትም ኩነኔ ነበር። ምርኮኛው ትውከቱ ሲተፋበት ለጥቂት ጊዜ ዝሎ ይደክምና፣ ከዚያም ቀጥ ብሎ ከተጓዘ በኋላ ከበፊት ይልቅ እየደከመ ሄዶ ይወድቅ ነበር። ምርኮኞቹ እነዚህን ጥንብ አንሳዎች በያዙት ሰይፍ በቀላሉ መግደል ሲችሉ ለምን እንዳልገደሏቸው ግን ደንቆኛል።

አንዳንዴ ደካሞቹ ምርኮኞች ተሰናክለው በሚወድቁ ጊዜ ደግሞ ሌሎቹ ምርኮኞች በእነዚህ በወደቁት ላይ ይሳለቁባቸው፣ ያንቋሽሿቸውና በያዙት ሰይፍም ይወጓቸው ነበር። ከዚያም የወደቁት ምርኮኞች ከመሞታቸው በፊት ጥንብ አንሳዎቹ መጥተው ሲቀለጣጥሟቸው ሌሎቹ ክርስቲያን ምርኮኞች ግን ይህን ትዕይንት ዝም ብለው ቆመው ይመለከቱ ነበር። እንዲያውም አንዳንዴ ደክመው የወደቁትን እንደገና መልሰው በያዙት ሰይፍ ይወጓቸው ነበር።

ይህንን እያየሁ ሳለሁ እነዚህ ምርኮኞች የኩነኔ ትውከቱ ከእግዚአብሔር

ዘንድ የመጣ እውነትና፣ እነርሱም ከእግዚአብሔር ሠራዊት ጋር አብረው እየተጓዙ እንደሆነ አድርገው ያስቡ እንደነበር ተገነዘብኩ። ምርኮኞቹ የፍርሃት መንፈስ የሚረጩትን እነዚህን ትናንሽ አጋንንት ወይም ጥንብ አንሳዎች ያልገደሏቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላኩ መልዕክተኞች አድርገው ስላሰቡ ነበር። ነገሩን በጣም አስቸጋሪ ያደረገው ደግሞ የጥንብ አንሳዎቹ መንጋ ሰማዩን መጋረዱና የወደቀባቸው ጨለማ ያደረሰባቸው ነገርም ሁሉ፤ ከጌታ ዘንድ የመጣ አድርገው በገርነት ሲቀበሉ ማየቱ ነው። የወደቁት ምርኮኞች በዚህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች እንደወደቁ ሲሰማቸው፤ ጥቃቱን የሰነዘሩባቸውን አጋንንትም እግዚአብሔር የላካቸው አድርገው ነበር ያሰቡት።

ምርኮኞቹ ይቀርብላቸው የነበረው ብቸኛ ምግብ የጥንብ አንሳዎቹ ትውከት ነበር። ይህን ትውከት ለመብላት እምቢተኛ የሆኑት ዝለው እስኪወድቁ ድረስ በርሃብ ሲጠቁ፤ የቀረበላቸውን ትውከት የሚመገቡት ግን ለጊዜው የከፋትን ኃይል በመልበስ ብርታት ያገኙ ነበር። በመቀጠል ደግሞ ያለ ማቋረጥ የሚጠጡት መራራ ውሃ ይሰጣቸው ነበር። ይህን መራራ ውሃ የማይጠጡትም ይደክሙ ነበር። መራሩን ውሃ የሚጠጡትም፤ ውሃውን ጠጥተው እንደጨረሱ በሌሎቹ ላይ ማስታወክ ይጀምራሉ። ከምርኮኞቹ አንዱ ማስታወክ ሲጀምር ከአጋንንቱ አንዱ ይወጣበትና ፊት ለፊት ወደ ተሰለፉት ክፍለ ጦር ይጋልብበት ነበር።

ከዚህ ከጥንብ አንሳዎቹ ትውከት የሚከፋው ደግሞ እነዚህ አጋንንቶች በሚጋልቧቸው ክርስቲያኖች ላይ የሚሸኑትና የሚጸዳዱት አጸያፊ የሆነ ዝልግልግ ነገር ነበር። ይህ ዝልግልግ ነገር የአጋንንት ክፍለ ጦሩ ባህርይ የሆነው ትዕቢት፣ ራስ ወዳድነት፣ ክፉ ምኞት፣ ወዘተ. ነበር። ይሁንና ምርኮኛ ክርስቲያኖቹ ግን ይህ ዝልግልግ ነገር የመንፈስ ቅዱስ ቅባትና ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነ ፍርድ እንደሆነ አድርገው ከመረዳታቸው በላይ አጋንንቶቹንም የእግዚአብሔር መልዕክተኞች እንደሆኑ አድርገው ነበር የሚያስቡት።

እኔም በክፋት ሠራዊቱ በጣም በመጠላቴ ሞቴን እየተመኘሁ ሳለሁ እንዲህ የሚል የጌታ ድምጽ ወደ እኔ መጣ። *"የጠላት የመጨረሻው ዘመን የመጀመሪያው ሠራዊት ይሄ ሲሆን ይህም የሰይጣን የመጨረሻው መሳት ነው። የመጨረሻ የጥፋት ኃይሉም ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው እንዲጣሉ ሊጠቀምባቸው ተለቋል። ጠላት ይህንን ሠራዊት ለዘመናት ለክፋት ዓላማዎቹ የተጠቀመበት ቢሆንም እንዲህ ያሁኑን ያህል ግን ብዙዎችን መጠቀም ተችሎት አያውቅም። አንተ ግን አትፍራ! እኔም ጦር አለኝ። ከዚህ ጦርነት የምትሰወርበት ሌላ ስፍራ ስለሌለ አሁን ስለ መንግስቴ፣ ስለ እውነትና ስለሳቱት በጽናት መዋጋት አለብህ"።*



ይህ ከጌታ ዘንድ የመጣው ድምጽ በጣም ስላጽናናኝ ወዲያውኑ ስተው የነበሩት ክርስቲያን ምርኮኞች ይሰሙኛል ብዬ በማሰብ ወደ እነርሱ መጮህ ጀመርኩ። ይህንን ባደረግሁ ጊዜ ሠራዊቱ በሙሉ እኔን ለማየት ፊቱን ወደ እኔ አዞረ። በዚህን ጊዜ በክርስቲያኖቹ ምርኮኞች ላይ የወደቀው ፍርሃትና ተስፋ መቁረጥ ወደ እኔም መምጣት ጀመረ። ክርስቲያኖቹ እየደረሰባቸው ያለው ነገር ምን እንደሆነ ይነቁና ይገነዘቡ እንደሆን ብዬ በማሰብም ጩኸቴን ማሰማት ቀጠልኩ። ይሁንና ከመካከላቸው አብዛኞቹ ምርኮኞች ግን ጥሩራቸውን ወደ እኔ ለመወንጨፍ ቀስትና ደጋናቸውን አንስተው ደገኑብኝ። ሌሎቹ ደግሞ ምን እንደሚያደርጉኝ ስላላወቁ አመነቱ። ከዚያም እኔም ያለጊዜው መጮኼን ተረዳሁ። ይሄ ደግሞ ሞኝ ሰው እንኳን የማይሰራው በጣም ስህተት የሆነ ነገር ነበር።

## ጦርነቱ ተጀመረ

ከዚያም ወደ ኋላዬ ዘወር ስል የጌታ ሠራዊት ከኋላዬ ተሰልፎ ቆሞ አየሁ። የዚህ ሠራዊት ቁጥር በጥቂት ሺህዎች የሚቆጠር ቢሆንም በኃይሉ ግን ከጠላት ጦር ሁሉ በእጅጉ የሚበልጥ ነበር። ይሁንና ከጌታ ሠራዊት ወገን ከተሰለፉት ክርስቲያኖች ቁጥር ይልቅ ከክፉው ወገን የተሰለፉና ጠላት የሚጠቀምባቸው ክርስቲያኖች ግን እጅግ በርካታ መሆናቸውን ባየሁኝ ጊዜ ደነገጥኩ፣ ተስፋም ቆረጥኩ። አስቃቂ ከሆነው ከዚህ እልቂት በስተጀርባ የተሰለፉትን ኃይላት የሚረዱ እውነተኛ ክርስቲያኖች በጣም ጥቂት መሆናቸው፤ ሊጀመር ያለው ጦርነት ክርስቲያኖች እርስ በርስ የሚዋጉት ታላቅ ጦርነት እንደሆነ ተረዳሁ።

የጌታን ሠራዊት ይበልጥ ቀርቤ ስመለከተው ሙሉ የጦር ዕቃቸውን የለበሱት ክርስቲያኖች ቁጥራቸው ጥቂት ብቻ ነበርና ሁኔታው ይበልጥ ተስፋ አስቆራጭ ሆነብኝ። አብዛኞቹ የታጠቁት አንድ ወይም ሁለት ዓይነት የጦር ዕቃ ብቻ ሲሆን አንዳንዶቹ እንዲያውም ጨርሶ መሳሪያ የሚባል ያልያዙና ከመካከላቸውም በርካቶቹ የቆሰሉ ነበሩ። ሙሉ የጦር ዕቃቸውን ከለበሱት መካከል አብዛኞቹ በእጃቸው የያዙት ጋሻ፤ እየመጣ ካለው ኃይለኛ እልቂት ሊከላከልላቸው የማይችል በጣም ትናንሽ እንደሆነ ተረዳሁ። ይበልጥ ያስደነገጠኝ ነገር ደግሞ ከእነዚህ ወታደሮች መካከል አብዛኞቹ ሴቶችና ህጻናት መሆናቸው ሲሆን፤ ሙሉ የጦር ዕቃቸውን ከታጠቁት መካከልም ስለያዙት የጦር መሳሪያ አጠቃቀም በቂ ስልጠና የወሰዱት በጣም ጥቂቶቹ ብቻ ነበሩ።

የከፋት መንጋው ምርኮኞች ይከተሉት እንደነበረው ይህንንም ሠራዊት ከኋላ የሚከተለው ህዝብ ነበር። ይሁንና እነዚህኞቹ ግን ባህርያቸው ከእነዚያ

በጣም የተለዩ ነበሩ። በተለይ እኔን ያሳሰበኝ ከሠራዊቱ ኋላ ተሰልፎ ይጓዝ የነበረው የክርስቲያኑ ህዝብ ነገር ስለነበር በአካባቢው ይሰማ ከነበረው የሁከት ድምጽ በላይ ድምጹን ከፍ አድርጌ ጦርነቱ ሊጀመር መሆኑን ላስጠነቅቃቸው ሞከርኩ። ሆኖም ሊሰሙኝ የቻሉት ግን በጣም ጥቂቶች ብቻ ነበሩ። የሰሙኝም ቢሆኑ በጦርነት እንደማያምኑና ጌታም ምንም ዓይነት ክፉ ነገር እንዲደርስባቸው እንደማይፈቅድ ሁለት ጣቶቻቸውን ከፍ በማድረግ "የሰላም ምልክት" አሳዩኝ። ይሁን እንጂ ጌታ የጦር ዕቃውን ያልለበሰውን ሰው ሊመጣ ላለው ፍልሚያ እንደማይፈልግ ላስረዳቸው ብሞክርም፤ እንደዚያ ያለ ነገር ሊሆን ወደማይችልበት የሰላምና የደስታ ስፍራ እንደደረሱና ዝም እንድላቸው በቁጣ መለሱልኝ። ሆኖም ጌታ ለጦርነት ላልተዘጋጁት ለእነዚህ የሚዋጉበትን የጦር ዕቃ እንዲሰጣቸውና ራሳቸውን ይከላከሉ ዘንድ እንዲረዳቸውም ወደ እርሱ መጸለይ ጀመርኩ።

ከዚያም አንድ መልዓክ ወደ እኔ ቀርቦ ቀንደ መለከት ከሰጠኝ በኋላ ፈጥኜ እንድነፋው ነገረኝ። እኔም መልዓኩ እንደ ነገረኝ ቀንደ መለከቱን ስነፋው፤ የጦር ዕቃ ታጥቀው የነበሩት አንዳንዶቹ ለሰሙት የመለከት ድምጽ ምላሽን ሰጡ። በዚህን ጊዜ ፈጥነው የሚለብሱት በርካታ የጦር ዕቃ መጣላቸው። ከመካከላቸው በተለያዩ የጠላት ቀስቶች ተወግተው ቆስለው የነበሩት የጦር ዕቃውን በቁስላቸው ላይ ሲለብሱ አስተዋልሁ። ይሁንና ስለዚህ ጉዳይ ምንም ነገር መናገር ከመቻሌ በፊት ግን ጠላት ፍላጻዎቹን በእኛ ላይ ያዘንብብን ጀመር። በዚህም ምክንያት የጦር ዕቃውን ያልለበሰ ሰው ሁሉ እየተወጋ ሲቆስል፣ የበፊት ቁስላቸውን ያልሸፈኑትም በዚያው ቁስላቸው ላይ እንደገና እየተወጉ ወደቁ።

በአጋንንት የስድብ ቀስት ተወግተው የነበሩትም ወዲያውኑ ያልተወጉትን መሳደብ፤ በሃሜት ቀስት የተወጉትም ሌላውን ማማት ጀመሩ። ከዚህ የተነሳ በገዛ ራሳችን ሰፈር ትልቅ መለያየትና ትርምስ ተፈጠረ። ልክ በቅዱሳት መጻህፍቱ ውስጥ እንደተጠቀሱትና እርስ በርሳቸው ለመጠፋፋት እንደ ተነሱት አንዳንድ የአህዛብ ሠራዊት እኛም እርስ በርሳችን ለመጠፋፋት አፋፍ ላይ ደርሰን እንደነበር ተሰማኝ። ራስን መከላከል አለመቻል ምንኛ አስጨናቂ ነገር ነው! ከዚያም ጥንብ አንሳዎቹ ቆስለው የወደቁትን አንስተው ለመውሰድና በየጦር ሰፈራቸው ላጎሯቸው እስረኞቻቸው ለመስጠት ወደ ታች እየበረሩ መጡ። እነዚህ ቆስለው የወደቁት አሁንም ድረስ ሰይፋቸውን በእጃቸው እንደያዙ ቢሆንም ጥንብ አንሳዎቹን በቀላሉ መምታት ሲችሉ ያንን ሳያደርጉ ግን ቀሩ። እንደ እነርሱ ቆስለው ባልወደቁት በሌሎቹ ወገኖቻቸው በጣም አዝነውባቸውና ተቆጥተውባቸው ስለነበርም በገዛ ፈቃዳቸው በጥንብ አንሳዎቹ



እየተያዙ ተወሰዱ።

እኔም ከሠራዊቱ በስተኋላ የተሰለፈው ህዝብ ሁኔታ ስላሳሰበኝ የደረሰባቸውን ጉዳት ለማየት ፈጥኜ ወደ እነርሱ ሮጥኩ። ነገሩ ሊሆን የማይችል ይመስል ይሆናል። ሆኖም በመካከላቸው የነበረው ሁኔታ ግን ከዚህም በባሰ የከፋ ነበር። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩት የጠላት ቀስት ባደረሰባቸው ጉዳት ቆስለው በወደቁበት ቦታ ሆነው እያቃሰቱ ነበር። ከራሳቸው በላይ ያለው ሰማይም የጠላት እስረኛ ሊያደርጓቸውና አንስተው ሊወስዷቸው ካሰፈሰፉት ጥንብ አንሳዎች ብዛት የተነሳ ጠቁሮ ነበር። ካልቆሰሉት መካከል ብዙዎቹ ደግሞ ራሳቸውን በመጠራጠር አስተው ስለነበር፤ እነዚህም ቢሆኑ በቀላሉ በጥንብ አንሳዎቹ ተወሰዱ። ጥንብ አንሳዎቹን ለመዋጋት ሙከራ ማድረግ የጀመሩት ጥቂቶች ቢሆኑም፤ እነርሱም አስፈላጊውን የጦር ዕቃ ያልለበሱ ስለነበሩ ጥንብ አንሳዎቹ ምንም ዓይነት ትኩረት አልሰጧቸውም ነበር። የቆሰሉት ደግሞ በጣም በቁጣ ተሞልተው ሊረዳቸው ይቀርባቸው የነበረውን አማኝ ሁሉ ሲዝቱበትና ሲያባርሩት፤ ለጥንብ አንሳዎቹ ግን ተገዢዎች ሆኑ።

ካልቆሰሉትና ጥንብ አንሳዎቹን ለመዋጋት ሞክረው ከነበሩት መካከል ጦርነቱ ይካሄድበት ከነበረበት ስፍራ በሩጫ መሸሽ ጀመሩ። ከጠላት ጋር የተካሄደው ይህ የመጀመሪያው ፍልሚያ እጅግ አውዳሚ ስለነበር እኔም አብሬያቸው እስክሸሽ ድረስ ተፈትኜ ነበር። በአስደናቂ ፍጥነት ከሸሹት ከእነዚያ መካከል አንዳንዶቹ እንደገና ሙሉ የጦር ዕቃቸውን ለብሰውና ረዣዥም ጋሻዎቻቸውን ይዘው ተመልሰው መምጣት ጀመሩ። ካየሁት ሁሉ የመጀመሪያው አደገኛ ነገር ይሄ ነበር።

እነዚህ ተመልሰው የመጡት ተዋጊዎች ከዚህ በኋላ ቆራጥ ውሳኔ እንጂ በሳቅ የታጀበ ደስታ አልነበራቸውም። እነዚህ በጠላት አንድ ጊዜ ተታለው የወደቁ ከዚህ በኋላ ግን ዳግመኛ በቀላሉ እንደማይታለሉ አወቅሁ። እንዲያውም የወደቁትን ሰዎች ቦታ ተክቶ ለመሸፈንና ከኋላ፣ ከግራና ከቀኝ የተሰለፉትን ለመከላከል አዲስ ሥልጣን መስጠትም ጀመሩ። በሠራዊቱ ውስጥ የሚገኘው እያንዳንዱ ሰው እንደገና በጽናትና በቆራጥነት ለመዋጋት መነሳት ይጀመር ዘንድ ይህ ትልቅ ብርታትንና መነሳሳትን ነበር የፈጠረው። ከዚያም ወዲያውኑ እምነት፣ ተስፋ፣ ፍቅር የተባሉ ሦስት ታላላቅ ቅዱሳን መላዕክት መጡና ከሠራዊቱ በስተጀርባ ቆሙ። እኛም ወደ እነዚህ መላዕክት በምንመለከትበት ጊዜ የያዝናቸው ጋሻዎች ቁመታቸው ያድግ ጀመር። የነበረው ተስፋ መቁረጥ እንዲህ ፈጥኖ ወደ እምነት መለወጡ አስደናቂ ሲሆን፤ ይህ እምነት ደግሞ በጣም በልምድ የተፈተነ ጠንካራ እምነት ነበር።

## አውራ ጎዳናው

አሁን ሁሉም ሰው የእግዚአብሔር ቃል የተባሉ ሰይፎችንና በተለያየ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች የተሰየሙ ቀስቶችን እንደ ያዘ ነው። ቀስታችንን በመወንጨፍ አፀፋዊ ምላሽን መስጠት ብንፈልግም የጠላት ሠራዊትን አጋንንቶቹ ይጋልቡባቸው ከነበሩት ክርስቲያኖች ነጥለን መምታቱን ግን ሳናውቅበት ቀረን። ከዚህ የተነሳ እነዚህን ክርስቲያኖች በእውነት ቀስት ብንወጋቸውና ከወደቁበት ድንዛዜ ቢነቁ ፊታቸውን ወደ አስጨናቂዎቻቸው በመመለስ እንደሚወጓቸው ገባንና አንዳንዶች እንዳደረጉት እኔም ጥቂት ቀስቶችን ወደ እነርሱ ወነጨፍኩ። ይሁንና የወነጨፍኳቸው ቀስቶች በሙሉ ማለት ይቻላል አጋንንቱን ሳይሆን ክርስቲያኖቹን ነበር የወጉት። ክርስቲያኖቹም በእነዚህ የእውነት ቀስቶች ሲወጉ በቁጣ ተሞሉ እንጂ ቆስለው አይወድቁ ወይም አይነቁም ነበር። ከዚህ የተነሳ የሚጋልብባቸው አጋንንት የበለጠ ያድግ ነበር።

ይህ ሁኔታ ሁላችንንም አስደነገጠን፣ ጦርነቱንም ማሸነፍ እንደማንችል ተሰማን። ቢያንስ የገዛ ራሳችንን ቦታ ይዘን መቆየት ለመቻል በእምነት፣ በተስፋና በፍቅር ላይ ብንደገፍም እንኳን ጥበብ የተባለ ሌላ ታላቅ መልዓክ ተገልጦ ከጀርባችን ባለው ተራራ ላይ ሆነን እንድንዋጋ አዘዘን።

በተራራው ላይ ዓይናችን ማየት እስከሚችለው ድረስ በተለያየ ከፍታ ላይ የሚገኙ አምባዎች ነበሩ። በእያንዳንዱ ከፍታ ላይ ያሉት አምባዎች ወደ ላይ በሄድን ቁጥር እየጠበቡ የሚሄዱና ለመቆም ይበልጥ አዳጋች ነበሩ። እያንዳንዱ ከፍታ በአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ስም የተሰየመ ሲሆን የታችኞቹ "መዳን"፣ "ቅድስና"፣ "ጸሎት"፣ "እምነት"፣ ወዘተ. ባሉ መሠረታዊ እውነቶች፣ የላይኞቹ ደግሞ ጥልቅ በሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች የተሰየሙ ነበሩ። ወደ ላይኞቹ ከፍታ በወጣን ቁጥር ጋሻዎቻችንና ሰይፎቻችን ሁለቱም የበለጠ እያደጉ ሲሄዱ ጠላት የሚወነጭፍብን ቀስቶችም እኛ ወዳለንበት ስፍራ መድረስ አይችሉም ነበር።

## አሳዛኙ ስህተት

ታችኛው ከፍታ ላይ ከነበሩት ክርስቲያኖች መካከል አንዱ፤ ጠላት ወንጭፈቸው የነበሩ ቀስቶችን ከመሬት እያነሳ መልሶ ወደ እነርሱ መወንጨፍ ጀመረ። በዚህ ጊዜ አጋንንቶቹ የሚወነጨፍባቸውን ቀስቶች በቀላሉ ዘወር እያሉ እያሳለፉ በእነርሱ ቁጥጥር ስር ያሉ ክርስቲያኖችን እንዲወጓቸው አደረጉ። ክርስቲያኖቹ ከሰሯቸው በጣም ከባድ ስህተቶች አንዱ ይሄ ነበር።



ክርስቲያኑ በክስ ወይም በስም ማጥፋት ቀስት ከእነዚህ በአንዱ ሲወጋ የመራርነት ወይም የቁጣ አጋንንቱ በርሮ በዚያ ቀስት ላይ ያርፍና በክርስቲያኑ ላይ ሽንቱን መሽናትና ሰገራውን መጸዳዳት ይጀምራል። አንድ ክርስቲያን ቀደም ሲል ከነበሩት ከትዕቢት ወይም ራስን ከማጽደቅ በተጨማሪ በእነዚህ ሁለት ወይም ሦስት በሚሆኑ አጋንንቶች ቁጥጥር ስር ሲወድቅ ደግሞ የፊቱ ገጽታ ወደ አስቀያሚው የአጋንንቱ ገጽታ ይለወጥ ነበር።

እኛ ይህንን ማየት የቻልነው ላይኛው ከፍታ ላይ ስለሆንን ሲሆን፤ ታችኛው ከፍታ ላይ ያሉትና የጠላትን ቀስት እያነሱ መልሰው ይወነጭፉ የነበሩት ግን ማየት አይችሉም ነገር። ከዚህ የተነሳ ገሚሶቻችን ወደ ላይ መውጣቱን መቀጠል እንዳለብን፣ የተቀሩት ደግሞ ታችኛው ደረጃ ላይ ምን እየተከናወነ እንዳለ በዚያ ላሉት ለማስረዳት ወደ ታች ተመልሰው እንዲወርዱ ወሰንን። ከዚያም እያንዳንዱን ከፍታ በግላቸው ለመጠበቅ ከወሰኑት ከጥቂት አርበኞች በቀር የቀሩት በሙሉ ወደ ላይ መውጣታቸውን እንዲቀጥሉ እንጂ ያንን ከማድረግ እንዳያቋርጡ ማስጠንቀቂያ ተሰጣቸው።

## ድነት

"የወንድሞች ኅብረት" ወደተባለው ከፍታ ላይ ስንደርስ አንዳቸውም የጠላት ቀስቶች ሊያገኙን አልቻሉም። እኛ ሰፈር ውስጥ ካሉት ብዙዎቹ መውጣት የሚፈልጉት እዚህ ደረጃ ድረስ እንደሆነ ወስነው ነበር። እኔ ግን የእያንዳንዱ አዲስ ከፍታ የእግር መረገጫ አዳልጦ የሚጥል አደገኛ እንደሆነ ብረዳም፣ የጦር መሳሪያዎቼን ታጥቄ ወደ ላይ በወጣሁ ቁጥር ብዙ ብርታትና ጥበብ ይሰማኝ ስለነበር ግን ወደ ላይ መውጣቴን ቀጠልኩ።

ወደ ላይኛው ከፍታ በወጣሁ ቁጥርም ክርስቲያኖቹን ሳልነካ አጋንንቶቹን ነጥዬ በቀስት ወንጭፌ ለመውጋት በቂ ችሎታ አገኘሁ። ከዚህ የተነሳ ከጠላት ሠራዊት በስተጀርባ የተሰለፉትን ዋነኞቹን የክፋት መንጋ መሪዎቹን መውጋት እንደምችል ተሰማኝ። በጣም በርካታ ክርስቲያኖች ደህንነታቸው በተጠበቀበት፣ ነገር ግን ጠላትን ወንጭፈው መውጋት በማይችሉበት ታችኛው ከፍታ ላይ ቆመው በማየቴ ሃዘን ተሰማኝ። ወደ ላይኛው ከፍታ በመውጣት ላይ ያሉት ግን እያደገ ያለው ብርታታቸውና ስብዕናቸው ታላቅ ባለ ድል ስላደረጋቸው እያንዳንዳቸው የጠላት ወገን የሆኑትን ብዙዎቹን ማጥፋት ተችሏቸው ነበር።

በነበሩበት በእያንዳንዱ ከፍታ ላይ የወደቁ፤ ብዙዎቹ ክርስቲያን ተዋጊዎች እንዳጣሏቸው የተረዳኋቸው በየቦታው የተበታተኑ የእውነት ቀስቶች ነበሩ። እነዚህ ቀስቶች ሁሉም የዚያ ከፍታ እውነት ስም የተሰጣቸው

ነበሩ። ከእኛ መካከል አንዳንዶቹ እነዚህን ቀስቶች ለማንሳት ፈቃደኞች ባይሆኑም ከስር የተሰበሰበውን ያንን ታላቅ መንጋ ለመደምሰስ ግን ማግኘት የቻልነውን ያህል ሁሉ መውሰድ እንደሚያስፈልገን ተረዳሁ። እናም አንድ ቀስት አንስቼ ብወነጭፍ አንዱን አጋንንት በጣም በቀላሉ ወጋሁት። ይህን ጊዜ ሌሎቹም እያነሱ መወንጨፍ ጀመሩ። በዚህም ብዙውን የጠላት ክፍለ ጦር መደምሰስ ቻልን። ከዚህ የተነሳም ድል እንደ ተቀናልን ያየው የክፋት ሠራዊቱም በሙሉ ትኩረቱን ሙሉ በሙሉ በእኛ ላይ በማድረግ ጥቃቱን ይበልጥ በእኛ ላይ ሰነዘረብን። ምንም እንኳን ተልዕኮችን ማብቂያ የሌለው ቢመስልም ይህ ድል ግን አነቃቅቶን ነበር።

ጠላት በላይኛው ከፍታ ላይ የምንገኘውን እኛን በቀስቱ ሊያገኘን ስላልቻለ የጥንብ አንሳዎቹ መንጋ እኛ ላይ ለማስታወክ ወይም የእግር መረገጫ ደረጃዎቹ አዳልጠው እንዲጥሉን ለማድረግ በዚያ ደረጃ ላይ ሽንታቸውን የሚሸኑትን ወይም ሰገራቸውን የሚጸዳዱትን አጋንንቶችን በመሸከም በእኛ ላይ ያንዣብቡ ጀመር።

## መልህቁ

ወደ እያንዳንዱ ከፍታ አምባ ላይ በወጣን ቁጥር ሰይፎቻችን ያድጉ የነበረ ቢሆንም፤ ወደ ላይኛው ከፍታ ላይ እየወጣሁ ስሄድ ግን የያዝኩት ሰይፍ አስፈላጊ መስሎ ስላልታየኝ ወደ ኋላዬ ጣልኩት። ይሁንና ሰይፉ የተሰጠኝ ለአንድ ሁነኛ ምክንያት መሆን አለበት ብዬ በማሰብ እንደገና አነሳሁት። ከዚያም የቆሙኩበት የእግር መረገጫ ደረጃ በጣም ጠባብና የሚያዳልጥ ስለነበር ሰይፌን አጠገቤ መሬቱ ውስጥ ጠግቼ ከቀረቀርኩት በኋላ ያንን ተደግፌ ቀስቴን በጠላት ላይ መወንጨፌን ተያያዝኩት። በዚህ ጊዜ *“ብዙዎቹ ራሳቸውን አጽንተው ለመቆም ሰይፋቸውን በአግባቡ ባለመጠቀማቸው ምክንያት ሲወድቁ፤ አንተ ግን ወደ ከፍታ መውጣት የሚያስችልህን ጥበብ ተጠቅመሃል”* የሚል የጌታ ድምጽ ወደ እኔ መጣ። ይህንን ድምጽ ከእኔ በቀር ሌላ ማንም የሰማው ያለ አልመሰለኝም። ይሁንና ብዙዎቹ ግን እኔ ያደረኩትን በማየት ተመሳሳዩን ርምጃ ወሰዱ።

ጌታ ይህንን ፈጥኜ እንዳደርግ ለምን እንዳልተናገረኝ ቢደንቀኝም ቀደም ብሎ ባልታወቀ ሁኔታ ተናግሮኝ እንደነበር ግን ተረዳሁ። ይህንን በሃሳቤ እያወጣሁና እያወረድኩ እያለሁ በቀደመው መላ የሕይወቴ ዘመን የጌታን ድምጽ በመስማትና በመታዘዝ ለዚህ ወቅት ስልጠና እየወሰድኩ እንደነበር መረዳት ጀመርኩ። በዚህ ጦርነት ላይ እያለሁም አሁን ያለ'ና ጥበብና ማስተዋል ከአንዳንድ ምክንያቶች የተነሳ ሊያድግ ወይም ሊወሰድብኝ



እንደማይችል ሳውቅ በሕይወት ዘመኔ ሁሉ ገኘመውኝ ስለነበሩት እያንዳንዱ የሕይወት ፈተና ላቅ ያለ ምስጋናዬን ለጌታ አቀረብኩ። በወቅቱ በደረሰብኝ ጊዜ ባለማመስገኔም አዘንሁ።

ወዲያውኑ አጋንንቶቹን እያነጣጠርን መውጋት ስንጀምር፤ ከጠላት ሠራዊት ዘንድ ልክ እንደ እሳትና ዲን የነደደ ቁጣ ወረደብን። በጠላት ሠራዊት ወጥመድ ውስጥ የወደቁት ክርስቲያኖችም የዚህ የቁጣ እሳት ንዳድ እየተሰማቸው እንደሆነም ተረዳሁ። በዚህም ምክንያት አንዳንዶቹ በጣም ስለተበሳጩ በቁጣ እርስ በርሳቸው ይጠጉ ጀመር። ይሄ ለእኛ በጣም አበረታች ቢሆንም፤ ከማንም በበለጠ እየተሰቃዩ ያሉት ግን እነዚህ በጠላት ሰፈር የነበሩ ክርስቲያኖች ነበሩ። ይህ ራሱ ክርስትና ለዓለም እንደገና ቀልጦ መሰራት የማይችል ወርቅ ሆኖ እንደሚታይም ተረዳሁ።

ሰይፎቻቸውን እንደ መልህቅ መሬት ውስጥ ያልቀረቀሩት አንዳንድ ክርስቲያኖች ብዙዎቹን ጥንብ አንሳዎች በሰይፋቸው እየወጉ መጣል ቢችሉም ቆመው ባሉበት የእግር መወጣጫ ደረጃ ላይ እንዳሉ በቀላሉ እየተመቱ ይወድቁ ነበር። ከዚህ የተነሳ አንዳንዶቹ ታችኛው ደረጃ ላይ ሲወርዱ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ታችኛው የመጨረሻው ደረጃ ላይ በመውደቃቸው ጥንብ አንሳዎቹ መጥተው አንስተው እየተሸከሙ ወሰዷቸው። እያንዳንዷን ደቂቃ ሰይፌን በእግር መወጣጫ ደረጃው ላይ በጥልቀት መቀርቀር ወይም ከእጄ ላለመለየት ጥረት ሳደርግ ቆየሁ። ይህንን በማንኛውም ሰዓት ሁሉ አደርግ የነበረ ሲሆን ጥበብም አጠገቤ መቆሙ በጣም አስፈላጊ እንደነበር ተገነዘብኩ።

## አዲስ የጦር ዕቃ

የወነጨፍናቸው የእውነት ጥሩሮች ጥንብ አንሳዎቹን እምብዛም ዘልቀው ባይጎዷቸውም ወደ ኋላ እንዲያፈገፍጉ ግን አድርገዋቸው ነበር። አንዳንዶቻችን ወደሚቀጥለው ከፍታ እንወጣ ዘንድ፤ እነዚህ ጥንብ አንሳዎች ሁልጊዜ በበቂ ርቀት ወደ ኋላ እንዲያፈገፍጉ ለማድረግ “ገላትያ ሁለት ሃያ” በተባለውና እነርሱ ሊደርሱበት በማይችሉት ከፍታ ላይ ወጣን። በዚህ ከፍታ ላይ እያለን ከእኛ በላይ ያለው ሰማይ ውበቱ አንጸባራቂ ስለነበር ብርሃኑን በዓይናችን ማየት ተሳነን። በዚህ ጊዜ ከዚህ በፊት ተሰምቶኝ የማያውቅ ሰላም ተሰማኝ።

እዚህ ደረጃ ላይ እስከ ደረስኩበት ጊዜ ድረስ አብዛኛው የውጊያ መንፈሴ ለመንግስቱ፣ ለእውነትና ለምርኮኞቹ የነበረኝ ፍቅር በጠላት ላይ ባለኝ ፍርሃት፣ ጥላቻና ጥርጥር ላይ ለበቀል ተነሳሳ። እዚህ ደረጃ ላይ ስወጣም በፊት ከርቀት ብቻ ማየት እችላቸው ለነበሩት ለእምነት፣ ለተስፋና ለፍቅር

ቅርብ ሆንኩ። በዚህ ለእምነት፣ ለተስፋና ለፍቅር ክብር ብሸነፍም እነርሱን መቅረብ እንደምችል ግን ተሰማኝ። አጠገባቸው ስደርስም ፊታቸውን ወደ እኔ በማዞር የጦር ዕቃዬን ማደስና መወልወል ጀመሩ። ወዲያውኑም የጦር ዕቃዬ ከእምነት፣ ከተስፋና ከፍቅር ይወጣ በነበረው ክብር እየተሰወለ ሄዶ በጣም አንጸባራቂ ሆነ። ሰይፌን ሲነኩትም ታላቅ የመብረቅ ብርሃን ማንጸባረቅ ጀመረ። ከዚያም ፍቅር "እዚህ ከፍታ ላይ የደረሱ ሰዎች ወደፊት ከሚመጣው ዘመን ኃይላት ጋር የሚቀመጡ ናቸው" አለ። በመቀጠልም ወደ እኔ ዘወር ብሎ ስቅስቅ ብሎ እያለቀሰ "እነዚህን የጦር ዕቃዎች እንዴት እንደምትጠቀምባቸው አሁንም ማስተማር አለብኝ" አለኝ።

"የገላትያ ሁለት ሃያ" መወጣጫ ደረጃ በጣም ሰፊ ሲሆን ምንም ዓይነት የመውደቅ አደጋ ያለበት አይመስልም። በዚያም ተስፋ የሚል ስም የተጻፈባቸውና ስፍር ቁጥር የሌላቸው ቀስቶች ነበሩ። ከእነዚህ ጥቂቶቹን እያነሳን እታች በሚገኙት ጥንብ አንሳዎች ላይ ስንወነጭፋቸው እየወጉ ገደሏቸው። በዚህ መወጣጫ ደረጃ ላይ ከወጡት ክርስቲያኖች ገሚሱ እነዚህን ቀስቶች ታችኛው መወጣጫ ደረጃ ላይ  ለሚገኙት ወገኖች ወስደው ለመስጠት እያነሱ መሸከም ሲጀምሩ ገሚሶቹ ደግሞ መወንጨፋቸውን ቀጠሉ።

ጥንብ አንሳዎቹ ወደ ታችኞቹ መወጣጫ ደረጃዎች እየተምዘገዘጉ ቢመጡም፤ በዚያ ያሉት ግን ቁጥራቸው ከፊት ይልቅ አነስተኛ ነበር። "በገላትያ ሁለት ሃያ" ደረጃ ላይ ሳለን ከዕይታችን ውጪ ከሆኑት የጠላት መሪዎች በቀር ሌላውን የጠላትን ሠራዊት በሙሉ መምታት ቻልን። ይህ የጠላት ሠራዊት ያፈሰሰብንን የተስፋ መቁረጥ ደመና፤ እውነትን ውጤታማ እንዳይሆን ስላደረገው ጥንብ አንሳዎቹን በሙሉ እስክንደመስሳቸው ድረስ የእውነትን ቀስቶች ላለመጠቀም ወሰንን። ይሄ ውጊያ በጣም ረዥም ጊዜ ቢወስድብንም ድካም የሚባል ነገር ግን አልተሰማንም ነበር። በመጨረሻም ከተራራው በላይ ያለው ሰማይ ሙሉ በሙሉ ከጥንብ አንሳዎቹ ጸዳ።

አሁን በእያንዳንዱ መወጣጫ ደረጃ ላይ የጦር ዕቃዎቻችን ያድጉ እንደነበረው እምነት፣ ተስፋና ፍቅርም በጣም ስለገዘፉ ጦርነቱ ከሚደረግበት አካባቢ ርቀው ያሉ ህዝቦች እንኳ ሲያዩዋቸው እንደሚችሉ አወቅሁ። ክብራቸውም በጥንብ አንሳዎቹ ታላቅ ደመና በጠቆረው የምርኮኞቹ ሰፈር ላይ እንኳን ያንጸባርቅ ስለነበርና መታየት ስለቻለም በጣም ተበረታታሁ። ምናልባትም ጠላት የሚጠቀምባቸውና በእርሱ ቁጥጥር ስር የዋሉት ክርስቲያን ምርኮኞች በዚህ ጊዜ እኛ ጠላታቸው እንዳልሆንን፤ ጠላት ግን እየተጠቀመባቸው መሆኑን ይረዱት ይሆናል።



ሆኖም በጠላት ሰፈር ያሉትና የእምነት፣ የተስፋና የፍቅርን ብርሃን ማየት የጀመሩት፤ እነዚያ ደካሞች ወይም መረዳት የተሳናቸው ያስቷቸው ዘንድ የተላኩባቸውን አጋንንቶች "የብርሃን መላዕክት" እያሉ ይጠሯቸው ጀመር። ከዚህ የተነሳም አጋንንቶቹ እነዚህን ወገኖች ማሳታቸውና በባርነት ስር ማሰራቸው እኔ ከተረዳሁት በላይም እጅግ የላቀ እንደነበር ተረዳሁ።

ይሁንና የሁለቱም ሠራዊት አካል ያልነበሩና ክርስቲያን ያልሆኑ ወገኖች የእምነት፣ የተስፋና የፍቅርን ክብር ሲመለከቱ የተሻለ ዕይታ በመፈለግ ወደ ተራራው እየቀረቡ መምጣት ጀመሩ። እነዚህ ክብራቸውን ለማየት የቀረቡትም ውጊያው በማንና በማን መካከል የተካሄደ እንደሆነ በትክክል መረዳት ጀመሩ። ይሄ ደግሞ ለእኛ ትልቅ ማበረታቻ ነበር።

ድሉ ያስገኘው መነቃቃትም በእኛና በምርኮኞቹ ዘንድ እየጨመረ መሄዱን ቀጠለ። በዚህ ውጊያ ውስጥ ተካፋይ መሆኔ በየትኛውም ዘመን ከተካሄዱ ታላላቅ ተጋድሎዎች በአንዱ ላይ የተካፈልኩ ያህል ነበር የተሰማኝ። ተራራችንን ያጠቁ የነበሩትን ብዙዎቹን ጥንብ አንሳዎች ከደመሰስናቸው በኋላ በመቀጠል ደግሞ ጥንብ አንሳዎቹ ጋርደዋቸው የነበሩትን ምርኮኞች ከወደቁበት ማንሳት ጀመርን። ጨለማው ሲገፈፍና ጸሐይ ብርሃኗን በምርኮኞቹ ላይ ማንጸባረቋን ስትጀምር ምርኮኞቹ ከወደቁበት ታላቅ እንቅልፍ መንቃት ጀመሩ። ወዲያውኑም እየተነሱ አስጠያፊ ከሆነውና በተለይም አሁንም ድረስ ሁለንተናቸውን ከሸፈነው ትውከት ራሳቸውን ማጸዳዳት ጀመሩ። ከዚያም እምነትን፣ ተስፋንና ፍቅርን እንደዚሁም ተራራውን ሲያዩ እየሮጡ ወደዚያ ሄዱ።

የክፋት መንጋው ከጀርባቸው ሆኖ የክስና የስም ማጥፋት ቀስቶቹን ቢወነጭፍባቸውም ቀድሞ ምርኮኛ የነበሩ እነዚህ ክርስቲያኖች ግን ወደፊት መገስገሳቸውን አላቆሙም ነበር። ብዙዎቹ ልክ ተራራው አጠገብ እንደ ደረሱ ከደርዘን ወይም ከዚያም በላይ የሆኑ የተወነጨፉ ቀስቶች ቢቀረቀሩባቸውም እነርሱ ግን የሆነባቸውን የተረዱ አይመስሉም ነበር። ተራራው ላይ መውጣት እንደጀመሩም ቁስላቸው ወዲያውኑ ይፈወስ ጀመር። አሁን የተስፋ መቁረጥ ደመናው በመገፈፉ ሁሉም ነገር ይበልጥ ቀለል ያለ ይመስል ነበር።

## ወጥመዱ

ቀድሞ ምርኮኛ የነበሩት እነዚህ ክርስቲያኖች አሁን ከጥፋት በመዳናቸው ታላቅ ደስታ ሆኖላቸዋል። ስለ እነዚያ እውነቶች ታላቅ መደነቅ የፈጠረብንን ተራራውን መውጣት እንደጀመሩም ስለ እያንዳንዱ መወጣጫ ደረጃ  በምስጋና

የተሞሉ ይመስሉ ነበር። እነዚህ የቀድሞ ምርኮኞች በውስጣቸው ጠላትን አምርሮ የመዋጋት ውሳኔ ወዲያውኑ ስለተቀሰቀሰባቸው የተሰጣቸውን የጦር ዕቃ በመታጠቅና ተምልሰው በመሄድ እስከ ዛሬ ድረስ ምርኮኛ አድርጎ በመያዝ ባሰቃያቸው ጠላታቸው ላይ ጥቃት መሰንዘር እንዲችሉ ይፈቀድላቸው ዘንድ ለመኑ። እኛም በጉዳዩ ከተወያየን በኋላ ሁላችንም ለመዋጋት በተራራው ላይ መቆየት እንዳለብን ወሰንን። ከዚያም የጌታ ድምጽ እንደገና *"ሁለተኛ ጊዜ ጥበብን መርጠሃል። ጠላትን በገዛ ራሱ መሬት ላይ ሆነህ ልትወጋው የምትሞክር ከሆነ ልታሸንፈው አትችልም። ስለዚህ በተቀደሰው ተራራዬ ላይ መቆም አለብህ"* አለኝ።

ይህን የመሰለውን ትልቅ ውሳኔ አስበንና በዝርዝር ተወያይተን በመወሰናችን እጅግ ተደንቄ ስለነበር፣ ከዚህ በኋላ ሌላ የትኛውንም ዓይነት ውጤታማ ውሳኔን አስቀድመን ሳንጸልይበት ላለመወሰን የተቻለኝን ሁሉ ለማድረግ ወሰንኩ። ሆኖም ጥበብ ፈጥኖ ወደ እኔ በመምጣትና ሁለቱን ትከሻዎቼን አጥብቆ በመያዝ ትኩር ብሎ ዓይን ዓይኔን እየተመለከተ *"ይህንን ማድረግ አለብህ"* አለኝ።

ጥበብ ይህን ካለኝ በኋላም ከአንድ እኔ ካላየሁት የጠላት ጥቃት የሚያድነኝ በሚመስል ሁኔታ ወደ ፊት ጎትቶ ወሰደኝ። የቆምኩት "በገላትያ ሁለት ሃያ" ሰፊ ሜዳ ላይ ቢሆንም ዘወር ብዬ ወደ ኋላዬ ስመለከት ግን ለካስ በጣም አፋፉ ላይ በመቆሜ ሳላውቅ ከተራራው ላይ ለመውደቅ በጣም ተቃርቤ ነበር። ከዚያም ጥበብን ዓይኖቹን ስመለከታቸው *"ከዚህ የሕይወት ደረጃም ሆነ ከየትኛውም ደረጃ ላይ ልትወድቅ ስለምትችል፣ የቆምክ ሲመስልህ እንዳትወድቅ ተጠንቀቅ"* አለኝ።

ከተገኘው ድል መነቃቃት የተነሳ ሥራችን ከተሳካልን በኋላ ግን ለወንድሞች ኅብረት ግድ የለሽ ሆንኩኝ። በግድ የለሽነት ከመውደቅ የበለጠም በጠላት ጥቃት ተመትቶ ለመውደቅም ይበልጥ የተመቻቸ ሰው ሆንኩ። እናም ስለዚህ ጉዳይ ለጥቂት ጊዜ ያህል አሰብ አደረኩ።

## እባቦቹ

ጥንብ አንሳዎቹን መግደላችንንና በክርስቲያኖቹ ይጋልቡ የነበሩትን አጋንንትንም እየለቀምን ማንሳታችንን ለረዥም ጊዜ ያህል ቀጠልን። የወነጨፍናቸው የተለያዩ የእውነት ቀስቶችም በተለያዩ አጋንንቶች ላይ ከፍተኛ ጫና እንደ ፈጥሩባቸው አስተዋልን። ውጊያው ረዥም ጊዜ ይወስድ እንደነበር ብናውቅም ከእንግዲህ ግን በጦርነት በሚደርስ ጉዳት ስለማንሰቃይ



"የትዕግስት" ደረጃን አልፈን ወደ ተራራው ጫፍ መውጣታችንን ቀጠልን። ሆኖም እነዚህ የጠላት ምርኮኛ የነበሩ ክርስቲያኖች አጋንንቶቹ ከውስጣቸው ቢባረሩላቸውም ወደ ተራራው የወጡት ግን ጥቂቶቹ ነበሩ። ብዙዎቹ አጋንንቱ ቢወጡላቸውም የአጋንንቱን ባህርያት አውልቀው የጣሉ ስላልነበሩ መዘላበዳቸውን አላቆሙም ነበር። የአጋንንቱ ጨለማ እንደ ተወገደም እነዚህ ክርስቲያኖች የቆሙበት መሬት ሲሽከረከር ማየት ቻልን። ከዚያም እኔ እግሮቻቸውም በእባቦች ተተብትበው ታስረው አየሁ። እባቦቹን ሳያቸውም ሁሉም ተመሳሳይና በላያቸው ላይ "ውርደት" የሚል ስም የተጻፈባቸው ነበሩ።

በእነዚህ እባቦች ላይ የእውነትን ጥሩር ብንወነጭፍባቸውም ውጤቱ ግን ያን ያህል አመርቂ አልሆነም። በመቀጠልም የተሰፉን ጥሩሮች ብንሞክር እነርሱም ምንም የተለየ ውጤት አላመጡም። ሁላችንም እርስ በርስ በመረዳዳታችን "ከገላትያ ሁለት ሃያ" ደረጃ በላይ ከፍ ብሎ መውጣት በጣም ቀላል ብሎልን ነበር። አሁን ጠላትን በመቃወም ማድረግ የምንችለው ነገር ትንሽ ቢመስልም እንኳ በእባቦቹ ላይ ጥቃት የምናደርስበትን አንድ ነገር እስከምናገኝ ድረስ መውጣት እስከምንችለው ከፍታ ድረስ ወደ ላይ ለመውጣት ጥረት ለማድረግ ወሰንን።

ከዚያም በጣም በፍጥነት የእውነትን መወጣጫ ደረጃን አልፈን ወጣን። በእባቦቹ ላይ በግልጽ የሚሰራ መሳሪያ ባይኖርም እንኳን፣ በአብዛኞቹ ደረጃዎች ላይ ቆመን ዙሪያችንን ለመመልከት ግን አልተቸገርንም ነበር። እምነት፣ ተስፋና ፍቅር ከእኛ ጋር ቢሆኑም ጥበብን ከኋላ በርቀት ትተነው እንደመጣን ግን አላስተዋልኩም ነበር። ይህ እንዴት የከፋ ስህተት እንደሆነ ሳልረዳ ብዙ ቆየሁ። ጥበብ ከፍታው ጫፍ ላይ ቢደርስብንም እርሱን ወደ ኋላ ትተን በመምጣታችን ግን በክፋት መንጋው ላይ የተቀዳጀነው ፈጣንና ቀላል ድል ዋጋ አስከፍሎናል።

ያለ ምንም ማስጠንቀቂያ ማለት ይቻላል ወደ ኤደን ገነት የአትክልት ስፍራ በሚያደርስ መወጣጫ ደረጃ ላይ ወጣን። ይህ ስፍራ ከአሁን በፊት በሕይወቴ አይቼ ከማውቃቸው ስፍራዎች ሁሉ እጅግ የተዋበ ስፍራ ነበር። በዚህ የአትክልት ስፍራ መግቢያ በር ላይ "ምንም ዓይነት ቅድመ ሁኔታን የማይጠይቅ የአብ ፍቅር" የሚል ጽሁፍ ተጽፎበታል። ይህ መግቢያ በር እጅግ የከበረና ከመግባት ወደ ኋላ ማለት እስከማንችል ድረስ አልፈን ለመግባት የሚያጓጓ ነበር። ልክ በሩን አልፌ እንደ ገባሁ የሕይወት ዛፍ እንደሆነ የተረዳሁትን አንድ ዛፍ አየሁ። በዚህ አትክልት ስፍራ ማዕከላዊ

ስፍራ ላይ የሚገኘው ይህ ዛፍ፤ አስደናቂ ኃይልና ሥልጣን ባላቸው መላዕክት የሚጠበቅ ነበር። መላዕክቱን ስመለከታቸው እነርሱም መልሰው ተመለከቱኝ። ሰውን ለማየት የናፈቁና የእኛን መምጣት የሚጠባበቁ ነበር የሚመስሉት። በአትክልት ስፍራው ሆኜ ወደ ኋላዬ ስመለከት ደግሞ ሌሎች ተዋጊ ሠራዊቶችን አየሁ። ይሄ ሁላችንንም ስላበረታታን ወደ ዛፉ ልናልፋቸው ወሰንን። ይህን ጊዜ ከመላዕክቱ አንዱ፡- "ከዚህ ፍሬ መብላት የሚችሉት እዚህ ደረጃ ላይ የደረሱና የአብን ፍቅር ያወቁት ናቸው" አለን።

እርቦኝ እንደ ነበር በፍጹም አልተሰማኝም ነበር። ሆኖም የዛፉን ፍሬ ስቀምሰው ግን ከዚህ በፊት ከቀመስኳቸው ምግቦች ሁሉ የሚበልጥ ጣፋጭ ጣዕም ያለው፤ ነገር ግን የተለመደ ምግብ ነበር።

ይህ የቀመስኩት ምግብም የጸሐይ ብርሃንን፣ ዝናብን፣ የለመለሙ መስኮችን፣ ከውቅያኖሱ አድማስ በስተጀርባ በመጥለቅ ላይ ያለችውን የጸሐይ ጀምበርን፣ ከዚያም በበለጠ የምወዳቸውን ሰዎች እንዳስታውስ አረገኝ። በምንርሰው በእያንዳንዱ ጉርሻም ሰውንና ሁሉንም ነገር የበለጠ መውደድ ጀመርኩ። ከዚያም የምጠላቸው ሰዎች ወደ አዕምሮዬ መምጣት ሲጀምሩ እነርሱንም ወደድኳቸው። በዚህ ወቅት የተሰማኝ ስሜት፤ "የገላትያ ሃያ ሁለትን" መወጣጫ ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ ስንወጣ ከተሰማን ሰላም እንኳን የሚበልጥ ነበር። በመቀጠልም የጌታ ድምጽ *"አሁን ይሄ የዕለት እንጀራህ በመሆኑ በፍጹም ከአንተ አይወሰድብህም። በፈለግኸው ጊዜና መጠን ተመገብ። ለፍቅሬ ፍጻሜ የለውም"* ሲለኝ ሰማሁት።

ይህ ድምጽ ከወዴት እንደ መጣ ለማየት አንጋጥጬ ወደ ላይ ወደ ዛፉ ስመለከት ዛፉ ፍፁም ንፁህ በሆኑ ነጫጭ ንስሮች ተሞልቶ አየሁ። ንስሮቹ ከዚህ በፊት አይቼ የማላውቀው እጅግ የተዋበና ወደ ውስጥ ዘልቆ የመግባት ኃይል ያላቸው ዓይኖች ያሏቸው ነበሩ። እነርሱም እኔ የምሰጣቸውን ትዕዛዝ በመጠባበቅ ወደ እኔ ተመለከቱ። ከንስሮቹም አንዱ "እነዚህ ንስሮች እባቦቹን የሚበሉ ናቸውና አንተ የምትሰጣቸውን ትዕዛዝ ለመፈጸም እየተጠባበቁ ነው" አለኝ። እኔም "ሂዱና እነዚያን ወንድሞቻችንን ተብትቦ ያሰራቸውን ውርደት ብሉት" አልኳቸው። እነርሱም ለመብረር ክንፎቻቸውን መዘርጋት ሲጀምሩ ታላቅ ነፋስ መጣና ወደ ላይ እየነጠቀ ወሰዳቸው። ንስሮቹ ሲበርሩ ሰማዩን ዓይንን በሚያጥበረብር ክብር ሞሉት። ንስሮቹ ወደ ላይ ሲወጡ እኛም ካለንበት ከፍታ ላይ ሆነን ከጠላት ሰፈር የሚሰማን የፍርሃትና የዋይታን ድምጽ መስማት ቻልን።



## ንጉሡ ተገለጠ

ከዚያም በተራራው ከፍታ ጫፍ ላይ በመድረሳችን ጌታ ኢየሱስ ራሱ በመካከላችን ተገለጠና እያንዳንዳችንን እንኳን ደስ አላችሁ የሚል የደስታ መግለጫና ሰላምታ አቀረበልን።

በመቀጠልም *"ወደ ሰማይ ከወጣሁ በኋላ በዚያ ከሚገኙት ወንድሞቻችሁ ጋር የተካፈልኩትን የመንግስቴን መልዕክት ከእናንተም ጋር መካፈል አለብኝ። እጅግ ኃያል የሆነው የጠላት ሠራዊት ሽሽ እንጂ ጨርሶ አልጠፋም። አሁን የመንግስቴን ወንጌል ይዘን በመውጣት ዘመቻ የምናደርግበት ሰዓት ነው። ንስሮቹ ስለ ተለቀቁ ከእኛ ጋር ይሄዳሉ። በእያንዳንዱ የተራራው መወጣጫ ደረጃ ላይ ቀስቶችን ብታገኙም ሰይፋችሁና የጦር መሳሪያችሁ ግን እኔ ነኝ። አሁን የጌታ ሰይፍ ከዓይኖቹ የሚመዘዝበት ሰዓት ነው"* አለን።

ከዚያም ዘወር ስል ፍፁም በሆነ አንድነት እያንዳንዳቸው የየራሳቸውን ስንደቅ ዓላማ የሚያውለበልቡ ከዘር፣ ከነገድ፣ ከቋንቋና ከህዝብ ሁሉ የተወጣጡ ወንዶች፣ ሴቶችና ህጻናት ያሉበት የጌታ ሠራዊት በዚያ የአትክልት ስፍራ ቆመው አየሁ። ከዚህ በፊት በምድር ላይ እንደዚህ ያለ ሠራዊት ታይቶ እንደማያውቅም ተረዳሁ። ጠላት በምድር ሁሉ ላይ በርካታ ሠራዊትና ምሽጎች እንደነበሩት ባውቅም አንዳቸውም ግን በዚህ ታላቅ ሠራዊት ፊት ሊቆሙ የሚችሉ አልነበሩም። እኔም ትንፋሽ እያጠረኝ "ይህቺ ቀን የጌታ ቀን መሆን አለባት" ስል በዚያ የነበረው መላው ሠራዊት ደግሞ "የሠራዊት ጌታ ቀን ደረሰች" ብለው በታላቅ ድምጽ መለሱ።

## ማጠቃለያ

ከወራት ቆይታ በኋላም ይህንን ህልም ቁጭ ብዬ በሃሳቤ ሳወጣና ሳወርድ ነበር። ከገሃነም የወጣው የክፋት መንጋ ሠራዊት መዝመት ሲጀምር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የማያቸው የተወሰኑ ክስተቶችና ሁኔታዎች በአሳሳቢ ሁኔታ አይቼው ከነበረው ህልም ጋር አብረው የሚሄዱ ይመስሉ ነበር። በዚህ ጊዜ አብርሃም ሊንከን "ነጻ አውጪ" መሆን የቻሉበትንና የአሜሪካንን አንድነት ያስጠበቁበት ትልቁ መንገድ የእርስ በርስ ጦርነቱን ለመዋጋት ፈቃደኛ መሆናቸው፣ መዋጋት ብቻም ሳይሆን ጦርነቱ በድል እስከሚጠናቀቅ ድረስም ባለማመቻመች መዋጋታቸው እንደነበር አስታወስኩ። አብርሃም ሊንከን በታሪካችን ደም አፋሳሽ የሆነውን ይህንን ጦርነት ጠላትን በፕሮፓጋንዳ

"አጋንንታዊ" አድርገው ሳያቀርቡ ለመዋጋት ጸጋው ሊኖራቸው ይገባ ነበር። ያንን አድርገው ቢሆን ኖሮ ፈጣን ወታደራዊ ድልን መቀዳጀት ቢቻላቸውም ከጦርነቱ በኋላ ግን ኅብረቱን የበለጠ አስቸጋሪ ያደርገው ነበር። እርሳቸው ግን ኅብረቱን ለመጠበቅ ከልባቸው ይዋጉ ስለነበር ፍጹም ጠላታቸው ያደረጉት የደቡቡን ግዛት ወንዶችና ሴቶችን ሳይሆን እነርሱን ምርኮኛው አድርጎ አስሮ የያዛቸውን ክፋውን ነበር።

በተመሳሳይም በአሁኑ ሰዓት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ታላቅ መንፈሳዊ የእርስ በርስ ጦርነት ሲካሄድ እየታየ ነው። ብዙ ሰዎች ይህንን ጦርነት ለማስወገድ የተቻላቸውን ሁሉ እያደረጉ ናቸው። ይሄ ሁሉም ሰው በቀላሉ የሚረዳው ግልጽ እውነት ነው። ይሁን እንጂ እውነትን ማመቻመቹ የመጨረሻ ፍጥጫውን ይበልጥ አስቸጋሪ ያደርገው እንደሆን እንጂ በፍጹም ዘለቄታዊ ሰላምን አያመጣም።

ጌታ አሁን ሰዎችን ነጻ ለማውጣት ይህንን መንፈሳዊ የእርስ በርስ ጦርነት ለመዋጋት ፈቃደኛ የሆነ አመራርን እያዘጋጀ ነው። የጦርነቱ ዋነኛ ጉዳይም ባርነት ከነጻነት ጋር የሚያደርገው ፍልሚያ ይሆናል። ሁለተኛው ጉዳይ ለአንዳንድ ሰዎች ዋነኛ የሆነው የገንዘብ ጉዳይ ነው። ልክ በአንድ ወቅት በአሜሪካ ተነስቶ የነበረው የእርስ በርስ ጦርነት መላ አገሪቱን የሚያጠፋ እንደመሰለ ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ላይ የመጣውም ፍጥጫ በጊዜው የቤተ ክርስቲያን ፍጻሜ ሆኖ ይገለጣል። ይሁንና አሜሪካን ከእርስ በርስ ጦርነቱ መትረፍ ብቻም ሳይሆን በምድር ላይ ኃያል አገር ሆና እንደ ወጣች ሁሉ ቤተ ክርስቲያንም እንዲሁ ኃያል ሆና ትወጣለች። የሚጠፉት ሰዎችን በመንፈሳዊ ባርነት አስረው የያዙ አስተምህሮዎችና ተቋማት እንጂ ቤተ ክርስቲያን አትጠፋም።

ከዚህ በኋላም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ፍጹም የሆነ ፍትህ በአንዲት ጀምበር አይመጣም። አሁንም የሴቶችን መብት ለማስከበርና ቤተ ክርስቲያንን ከዘረኝነትና ከብዝበዛ ነጻ ለማውጣት የሚካሄዱ ትግሎች ይኖራሉ። እነዚህ ሁሉ ፊት ለፊት ልንጋፈጣቸው የሚገቡን ጉዳዮች ናቸው። ይሁንና ወደፊት በሚመጣው መንፈሳዊ የእርስ በርስ ጦርነት መካከል እምነት፣ ተስፋና ፍቅር እንደዚሁም እነርሱ የቆሙበት የእግዚአብሔር መንግስት ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ መታየት ይጀምራሉ። ይሄ ደግሞ ሰዎችን ሁሉ ወደ መንግስቱ ማፍለስ የሚጀምር ይሆንና የእግዚአብሔር መንግስት ከየትኛውም የሥጋ ለባሽ መንግስት በላይ ሆና ትገለጣለች።



**መቼም ቢሆን በጌታ ዘንድ "ሺህ ዓመት እንደ አንድ ቀን" እንደሆነ እንርሳ። ሺህ ዓመት ይወስድብናል ብለን የምናስበውን ሥራ እግዚአብሔር በአንድ ቀን ሊሰራው ስለሚችል ነጻ የማውጣት ሥራና የቤተ ክርስቲያን መክበር እኛ ከምናስበው በበለጠም ፈጥኖ የሚከናወን ሥራ ነው የሚሆነው። ይሁንና እየተነጋገርን ያለነው ግን በሰው ሊሰራ ስለሚችል ነገር አይደለም።**

# ክፍል ሁለት

# የተቀደሰው ተራራ



## ክፍል ሁለት
## የተቀደሰው ተራራ

በእግዚአብሔር ኤደን ገነት በምትገኘው የሕይወት ዛፍ ስር ቆመን ሳለን በዚያ መሳው ሠራዊት ያለ ነበር የሚመስለው፡፡ ብዙዎቹ በጌታ ፊት ተንበርክከው ነበር፡፡ በዚህን ጊዜ ጌታ አሁንም ድረስ የጠላት ምርኮኛ ሆነው ስለተያዙ ወንድሞቻችንና እርሱ ስለወደደው ዓለም ስንል ተመልሰን ወደ ጦርነቱ እንድንሄድ አዘዘን፡፡ ይሄ ለእኛ አስጨናቂ፣ አስደናቂ፣ ሁለቱንም ነበር፡፡ አስጨናቂነቱ አሁን ፊት ለፊት ተገልጦልን የታየንን ጌታና ከዚህ በፊት ከኖርንባቸው ከየትኛውም አካባቢ ይልቅ እጅግ አብልጦ ውብ የሆነውን ይህንን ገነት ትተን እንድንሄድ መታዘዛችን ሲሆን፤ አስደናቂነቱ ደግሞ ከእርሱ የመጣ ትዕዛዝ መሆኑ ነበር፡፡ እዚህ ያለውን ነገር ሁሉ ትቶ እንደገና ወደ ጦርነት ውስጥ መግባቱም ለአዕምሮ የሚመች ነገር አልነበረም፡፡

ጌታም *"መንፈሳዊ ስጦታና ኃይል እንዲሁም ቃሌንና መንግስቴን የምታስተውሉበትን እየጨመረ የሚሄድ ማስተዋልን የሰጧችሁ ቢሆንም ከሁሉ የሚበልጥ የተሰጣችሁ የጦር ዕቃ ግን የአብ ፍቅር ነው፡፡ በዚህ በአባቴ ፍቅር እስከ ተመላለሳችሁ ጊዜ ድረስ በፍጹም አትወድቁም፡፡ በእኔ ውስጥ የተገለጠው የአብ ፍቅር የዚህ ዛፍ ፍሬ ሲሆን በውስጤ ያለው ይህ ፍቅርም የዕለት እንጀራችሁ ሊሆን ይገባል"* ሲል አበረታታን፡፡

ጌታ ይህን በመሰለ ውብና የከበረ ስፍራ በክብሩ የተገለጠ አይመስልም ነበር፡፡ በእርግጥ መገለጡ የተለመደ ነገር ቢሆንም አሁን የተናገረበት ጸጋ ግን ከዚህ በፊት በፍጹም አይቼ የማላውቀው እጅግ ማራኪ አደረገው፡፡ እርሱ በክብርም ሆነ በታላቅነት ከሰው ማንነት ያለፈ ስለሆነ አብ ለምን እንደ ወደደውና እንዳከበረው ሁሉን ነገር መረዳት ቀላል ነበር፡፡ መቼም ጸጋና እውነት ከምንም ነገር የሚበልጡ በመሆናቸው እርሱ በእውነትም ጸጋና እውነት የሞላበት ነው፡፡

ይህን የሕይወት ዛፍ ፍሬ በበላሁ ጊዜም ስለ መልካም ነገር በፍጹም አስቤ የማላውቀው ሰው፤ ነፍሴ በመልካም ሃሳብ ሁሉ ተሞላች፡፡ ኢየሱስ በተናገረኝ ጊዜ የሆነው ነገር ደግሞ ከዚህ ላቅ ብሎ ብቻ ይታይ እንደሆነ እንጂ ይኼው ነበር የሆነው፡፡ የእኔ ፍላጎት የነበረው በዚህ ስፍራ መቆየትና እርሱ የሚናገረውን ሁሉ መስማት ነበር፡፡ አንድ ወቅት ላይ ዙፋኑ ፊት ሆነው

ሳያቋርጡ ከማምለክ በቀር ሌላ ምንም ሥራ ስለ ሌላቸው መላዕክት ሳስብ አምልኮ እንዴት አሰልቺ ይሆንባቸው ይሆን እያልኩ አስብ እንደነበር አስታውሳለሁ:: አሁን ግን ሁልጊዜ እርሱን ዝም ብሎ ከማምለክ ሌላ ከዚህ የሚበልጥ አስደናቂ ወይም አስደሳች ሥራ እንደሌለ ተረድቻለሁ:: የተፈጠርነው እርሱን ለማምለክ ሲሆን በዚህም በእርግጠኝነት የመንግስተ ሰማይ ምርጥ አካል እንሆናለን:: በአምልኮው ላይ የመንግስተ ሰማያት መዘምራን ሁሉ ተገኝተው ቢሆኑ ኖሮ ምን ያህል አስደናቂ እንደሚሆን መገመት አልችልም:: በአምልኮ ፕሮግራሙ ወቅት ከመሰላቸት ጋር በጣም እታገል ነበር ብሎ ማመኑ ከባድ ነው:: ይህ የሆነውም በእነዚያ ጊዜያት ሙሉ በሙሉ ከእውነታው ስለወጣሁ እንደሆነ ብቻ ነው የማውቀው::

በዚያ የአምልኮ ጊዜ አዕምሮዬ በሌሎች ነገሮች ሲጠመድ ወይም ሃሳቤ ሲባዝን መልሼ ማስተካከል ፈለግሁ:: ለእርሱ ያለኝን አድናቆት የመግለጥ ፍላጎቴም የበለጠ እየጨመረ ሄደ:: ማመስገን ነበረብኝና ሳመሰግነው አፌን ስከፍት ከሠራዊቱ ፈንድቶ በወጣውና በሰማሁት ድንገተኛ የአምልኮ ኅብረ ዝማሬ ድምጽ ደነገጥኩ:: ሌላ ሰው መኖሩን እንኳን እስከምዘነጋ ድረስ ሁላችንም ፍጹም በሆነ አንድነት ውስጥ ነበርን:: ቀጥሎ የመጣው የከበረ አምልኮም በሰው ቋንቋ ሊገለጽ የሚችል አልነበረም::

እያመለክን እያለም ከጌታ ዘንድ ወርቃማ ብርሃን እየፈነጠቀ መውጣት ጀመረ:: በወርቁ ብርሃን ዙሪያም ብር ይታይ ነበር:: ከዚያም ሁላችንንም በሥጋ ዓይኔ አይቼው የማላውቀው የተለያዩ ኅብረ ቀለማት ድምቀት ከበበን:: ከዚህ ክብር የተነሳም ከዚህ በፊት ተለማምጀው ወደማላውቀው የስሜት ዓለም ውስጥ ገባሁ:: ይህ ክብር ከመጀመሪያም በዚያ እንደነበር ብረዳም፤ ትኩረታችንን በአምልኮ ውስጥ እንዳደረግነው በጌታ ላይ ስናደርግ ግን ክብሩን የበለጠ ማየት ጀመርን:: ጌታን የበለጠ እያመለክነው በሄድን መጠንም ክብሩ ይበልጥ እየጨመረ ሲመጣ አየን:: ይህ ክብር ስለ መንግስተ ሰማያት አልመው ከነበረው በብዙ የሚበልጥ ክብር ነበር::

## ማደሪያው

በእንዲህ ዓይነቱ ክብር ውስጥ ጊዜን ማስላት የምንችልበት ምንም ዓይነት መንገድ ስላልነበረ ይህ አምልኮ ለምን ያህል ጊዜ እንደ ዘለቀ ሃሳቡ የለኝም:: አምልኮው ለጥቂት ደቂቃዎች ወይም ለብዙ ወራት የቆየ ሊሆን ይችላል:: በግሌ እመለከተው የነበረው ክብር ግን በሥጋ ዓይኖቼ ከማየው እጅግ ታላቅ ስለነበር ዓይኔን ጨፈንኩ:: ሆኖም ዓይኖቼን እንደገና ስገልጥ ጌታ በዚያ ስፍራ አለመኖሩን ስረዳ ደነገጥኩ:: ይሁንና እርሱ በነበረበት ቦታ ላይ



ግን የመላዕክት ሠራዊት ቆመው ነበር:: ከመላዕክቱም አንዱ ወደ እኔ ቀረበና "ዓይኖችህን እንደገና ጨፍን" አለኝ:: ስጨፍን የጌታን ክብር አየሁ:: አሁን ከተለማመድኩት ካለዚህ ክብር መኖር እንደማልችል ተረዳሁ:: ይሄ ለእኔ ቀላል ዕረፍት አልነበረም::

ከዚያም መልዓኩ "በሥጋ ዓይኖችህ ካየኸው ይልቅ በልቦናህ ዓይኖች ያየኸው የበለጠ እውነተኛ ነው" አለኝ:: ይህንን የእውነት ቃል ከዚህ በፊት ብዙጊዜ ራሴው ተናግሬው የነበረ ቢሆንም በህይወት የኖርኩት ግን በጥቂቱ ነው! መልዓኩም ቀጠለና "ጌታ ለመጀመሪዎቹ ደቀ መዛሙርት እርሱ ቢሄድና መንፈስ ቅዱስ ቢመጣ እንደሚሻል የነገራቸው ምክንያቱ ይህ ነበር:: ጌታ የሚያድረው በአንተ ውስጥ ነው:: አንተ ይህን ለብዙጊዜ ያህል ስታስታምረው ኖረሃል:: አሁን ግን ከሕይወት ዛፍ ወስደህ በልተሃልና የተናገርከውን በሕይወት ልትኖረው ይገባል" አለኝ::

በመቀጠልም መልዓኩ መልሶ ወደ በሩ እየመራ ሲወስደኝ፤ እኔ ግን ይህን ስፍራ ለቀቄ መሄድ ባለመፈለግ እምቢታዬን ገለጽኩ:: መልዓኩም ትከሻዬን አቅፎ ዓይን፣ ዓይኔን በመገረም እያየኝ "ፈጣሪ ራሱ ያለው በአንተ ውስጥ በመሆኑ ምክንያት ይህ የአትክልት ስፍራ በልብህ ውስጥ አለ:: ይህን የአትክልት ስፍራ በፍጹም ትተኸው አትሄድም:: ጌታን ማምለክና እርሱ በሚገኝበት በዚያ ለዘላለም መኖርን እጅግ የተወደደውን ምርጫ መርጠሃልና ከአንተ ፈጽሞ አይወሰድብህም:: ይሁንና ከዚህ ቦታ ይልቅ እጅግ ወደሚፈለግበት ስፍራ ልትወስደው ግን ይገባል" አለኝ:: ለካስ ይህ መልዓክ ጥበብ ራሱ ነበር::

መልዓኩ ትክክል መሆኑን ሳውቅ አሻግሬ ወደ ሕይወት ዛፍ ተመለከትኩ:: ይህንን ስፍራ ለቅቄ ከመሄዴም በፊት የቻልኩትን ያህል ፍሬውን የመያዝ ግዴታ ነበረብኝ:: ጥበብም የልቤን ሃሳብ አውቆብኝ ትከሻዬን ነቅንቅ አደረገኝና "አይሆንም! ይህ ፍሬ በፍርሃት የሚሰበሰብ ከሆነ ይበላሻል:: ጌታ ያለው በአንተ ውስጥ በመሆኑ ይህ ዛፍና ይህ ፍሬ ያሉትም በውስጥህ ነው:: ይህንን ማመን አለብህ" አለኝ::

ዓይኖቼን በመጨፈን ጌታን እንደገና ለማየት ብሞክር አልቻልኩም:: ዓይኖቼን ስገልጥ ጥበብ አሁንም አትኩሮ እያየኝ ነበር:: ከዚያም በታላቅ ትዕግስት እንዲህ ሲል ንግሩን ቀጠለ:: "ሰማያዊውን ዓለም ቀምሰኸል:: ይህንን የቀመሰ ሁሉ ደግሞ የተገለጠውን የጌታን ኅልዎት ትቶ ተመልሶ ወደ ጦርነቱ መሄድን በፍጹም አይፈልገውም:: ሐዋርያው ጳውሎስ ወደዚህ ወደ ሦስተኛው

*ሰማይ በመጣ ጊዜ ተመልሶ ወደ ምድር በመሄድ ቀሪ የምድር ህይወት ዘመኑን በቤተ ክርስቲያን የወንጌልን ሥራ ለመስራት ወይም እዚህ ወዳለው ሰማያዊ ርስቱ ለመግባት ውስጡ ሲታገል ነበር የኖረው። በምድር ላይ ቆይቶ ባገለገለ ቁጥርም ይህ ሰማያዊ ርስቱ እየሰፋ ይሄድ ነበር። አሁን አንተም እውነተኛ የአምልኮ ልብ ስላለህ ሁልጊዜ በዚህ መሆንን ፈልገሃል። ይሁንና ይህን መሆን የምትችለው ግን ወደ እውነተኛ አምልኮ ውስጥ ስትገባ ነው። የትም ቦታ ብትሆን ትኩረትህን በእርሱ ላይ ባደረግህ ቁጥር ክብሩን የበለጠ ታያለህ"።*

በመጨረሻም ጥበብ የተናገረኝ ይህ ቃል እንድረጋጋ አደረገኝ። ጌታን ስለዚህ አስደናቂ ልምምድና ስለ ሰጠኝም ሕይወት ለማመስገን እንደገና ዓይኖቼን ስጨፍን ክብሩን ማየት ጀመርኩ። ቀደም ሲል የነበረው የአምልኮ ልምምድ ስሜትም ነፍሴን ወረራት። ጌታ "አልተውህም ከቶም አልጥልህም" ሲል የተናገረኝ ቃል ግልጽና የጎላ ነበር፣ እንደሚሰማም እርግጠኛ ነበርኩ።

እኔም "ጌታ ሆይ አለማመኔን ይቅር በል፣ እባክህ አንተን እንዳልተውህ ወይም ጥዬህ እንዳልሄድ እርዳኝ" ስል ለመንኩት። ይህ "ገሃዱ ዓለም" እውነተኛ አይደለም፣ መንፈሳዊው ዓለም ግን ወደ ሌላው ተመልሼ መሄድ ማሰብ እስከማልችል ድረስ እጅግ እውነተኛ ነበር። ስለዚህም በማንኛውም ሰዓት ላይ እነቃና ህልም ሆኖ አገኘው ይሆናል በሚል አስጨናቂ ፍርሃትና መደነቅ በሁለቱም ተይዤ ስለነበር ይህ ጊዜ ለእኔ አስደናቂ እና የሚያበሳጭ፣ ሁለቱንም ነበር።

ጥበብ በውስጤ ይመላለስ የነበረውን ነገር በመረዳት *"ህልም እያየህ ነው። ይህ ህልም ደግሞ እውነተኛ ነው ብለህ ከምታስበውም በላይ እውነት ነው። አብ ሰዎች ወደ እርሱ ማደሪያ ስፍራ የሚያስገባውን በር ያዩ ዘንድ ህልምን ነው የሚሰጣቸው። እርሱ የሚኖረው በሰዎች ልብ ውስጥ ብቻ ሲሆን ህልሞች ደግሞ ወደ እርሱ የሚያደርሷችሁ የልባችሁ በሮች ሊሆኑ ይችላሉ። ለዚህ ነው የእርሱ መላዕክት ብዙጊዜ ለሰዎች በህልም የሚገለጡትና በሃጢአት የወደቀውን ሰው ሃሳብ አልፈው በቀጥታ ወደ ልቡ መግባት የሚችሉት"* አለኝ።

ዓይኖቼን ገለጥ ሳደርግ ጥበብ ሁለቱንም ትከሻዎቼን አጥብቆ እንደ ያዘኝ *"ለምትሰራው ሥራ የተሰጠሁህ ዋና ስጦታ እኔ በመሆኔ መንገዱን ባሳይህምና በዚያ ላይ እንድትጓዝ ባደርግህም ታማኝ የሚያደርግህ ግን ፍቅር ነው። የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ሲሆን ትልቁ ጥበብ ግን እርሱን መውደድ ነው"* አለኝ።



ከዚያም ትቶኝ ወደ በሩ መሄድ ሲጀምር እኔም እያመነታሁ ተከተልኩት። ስለ ጦርነቱ መነቃቃት እና ተራራውን ስለ መውጣት ባስብምና በዚያ ውስጥ ማለፍ የግድ ቢሆንም ይህን ከመሰለው የጌታ ኅልዎት መገኘትና ከተለማመድኩት አምልኮ ጋር የሚነጻጸር ነገር ግን አልነበረም። ለእኔ ይህንን ትቶ መሄዱ ከዚህ በፊት ከፍዬ የማላውቀውን እጅግ ከፍተኛ መስዋዕትነትን መክፈል ነው የሆነብኝ። ከዚያም ሁሉም ነገር በውስጤ እንደነበር ባስታውስም ይህንን ፈጥኜ መርሳት በመቻሌ ተደነቅሁ። ይሄ ደግሞ በሥጋ ዓይኔ ባየሁትና በልቤ ባየሁት ዕይታ መካከል በውስጤ የሚካሄድ ትልቅ ጦርነት ያለ ነበር የሚመስለው።

ከጎኔ ሆኖ ይራመድ ወደ ነበረው ወደ ጥበብ ጠጋ አልኩና "ላለፉት ሃያ አምስት ዓመታት እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሦስተኛው ሰማይ ለመነጠቅ ስጸልይ ኖሬያለሁ። ታዲያ ይህ ያለንበት ስፍራ ሦስተኛው ሰማይ ነውን?" ስል ጠየቅሁት።

*"የእርሱ አካል ነው፣ ነገር ግን ከዚህ የሚበልጥ ሌላም ብዙ አለ"* ሲል መለሰልኝ።

"ያንንስ ለማየት ይፈቀድልኛልን?" ስል ደግሜ ጠየቅሁት።

*"ገና የሚበልጠውን ታያለህ፣ አሁን የምወስድህም ያንን ወደምታይበት ስፍራ ነው"* አለኝ።

ድንገትም ስለ ዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ ማሰብ ጀመርኩና "ዮሐንስ ያየው ራዕይ የሁለተኛው ሰማይ አካል ነው ወይ?" ስል ጠየቅሁት።

*"ዮሐንስ በራዕዩ ያየው የሦስተኛውን ሰማይ አካል ቢሆንም አብዛኛው ግን የሁለተኛው ሰማይ አካል ነው። የመጀመሪያው ሰማይ ከሰው ልጅ ውድቀት በፊት የነበረው ሲሆን፣ ሁለተኛው ሰማይ ክፉው በምድር ላይ በነገሠበት ወቅት ያለው መንፈሳዊው ዓለም፣ ሦስተኛው ሰማይ ግን የአብ ፍቅርና እንደገናም እርሱ በንጉሡ አማካይነት በምድር ላይ የሚያሸንፍበት አገዛዙ ነው"* አለኝ።

"የመጀመሪያውስ ሰማይ ምን ይመስላል?" ብዬ በጠየቅሁት ጊዜ ለየት ያለ ቀዝቃዛ ነፋስ ተሰማኝ።

ጥበብም ይህ ጥያቄዬ አስደነገጠው መሰለኝ *"አሁን ስለዚያ አለመጨነቅ ጥበብ ነው። ቀደም ሲል እንደ ተናገርከው ሦስተኛውን ሰማይ መፈለግ ጥበብ*

*ነው:: ስለ ሦስተኛው ሰማይ በምድር ሕይወትህ ማወቅ ከምትችለው በላይ ገና ልታውቀው የሚገባህ ሌላም ነገር አለ:: እሱም በዚህ ምድር በሕይወት ሳለህ ልትሰብከው ስለሚገባህ ስለ ሦስተኛው ሰማይ መንግስት ነው:: በሚመጣው ዘመን ስለ መጀመሪያው ሰማይ ይነገርሃል፣ ይሁንና አሁን ግን ስለ መጀመሪያው ሰማይ ማወቁ ምንም አይጠቅምህም"* ሲል ቆጣ ብሎ መለሰልኝ::

የሚሰማኝን የዚህን ቀዝቃዛ ነፋስ ማንነት አስታወስኩ:: ጥበብም የልቤ ሃሳብ ትክክል መሆኑን በመቀበል ራሱን በመነቅነቅ አረጋገጠልኝ:: ይህ መልዓክ እንዴት የተወደደ ስጦታ እንደሆነ ስለተገነዘብኩም "በእርግጥም አንተ በትክክለኛው መንገድ ላይ እንድሄድ የምትጠብቀኝ ታላቅ ወዳጅ ነህ" ማለት ስለነበረብኝ ይህንኑ አልኩት::

እርሱም *"አዎን በእርግጥ እጠብቅሃለሁ"* ብሎ መለሰልኝ::

ከዚህ በፊት ከሌሎች መላዕክት በፍጹም ተሰምቶኝ የማያውቅ የተለየ ፍቅር ከዚህ መልዓክ ውስጥ ሲወጣ እንደ ተሰማኝ እርግጠኛ ነበርኩ:: ብዙጊዜ መላዕክት የሚሰማቸውን የኃላፊነት ስሜት ከፍቅር ሳይሆን ከተግባራቸው አንጻር ነው የሚገልጹት:: ጥበብ የልቤን ሃሳብ በአንደበቴ አውጥቼ የነገርኩት ይመስል በቀላሉ በሚገባኝ መንገድ በአጽንዖት እንዲህ አለኝ::

*"ፍቅር ጥበብ ነው:: አንተን ባልወድህ ጥበብ መሆን አልችልም ነበር:: የእግዚአብሔርን ደግነትና ቁጡነት ማየትም ጥበብ ነው:: እርሱን መውደድና መፍራትም ጥበብ ነው:: ከዚህ የተለየ የምታደርግ ከሆነ ግን ያለኸው በስህተት መንገድ ላይ ነው:: መማር ያለብህም ቀጣዩ ትምህርት ይኼው ነው"* አለኝ::

ጥበብ በደንብ አላወቀኝ ይሆናል ብዬ ስለተሰማኝ ለመጀመሪያ ጊዜ "ያንን አውቃለሁ፣ ለሌሎችም ብዙጊዜ አስተምሬዋለሁ" ስል መለስኩለት::

ጥበብም *"ከረዥም ጊዜ አንስቶ ወዳጅህ ስለነበርኩ ታስተምር የነበረውን ትምህርት አውቀዋለሁ:: የጽድቅ ውጤት የሚወጣህ በአዕምሮ ዕውቀት ሳይሆን በልብህ በማመን ስለሆነ ያስተማርካቸው አንዳንዶቹ ትምህርቶችህ ምን ማለት እንደሆኑ አሁን አንተ ራስህ ልትማራቸው የሚገቡህ ናቸው"* አለኝ::

ጥበብን በጥያቄ በማፋጠጤ ሃፍረት ስለተሰማኝ ይቅርታ ጠየቅሁት:: እርሱም ጥያቄዬን በጸጋ ተቀበለው:: እኔም እርሱን በጥያቄ የምሞግተው አብዛኛውን ጊዜ በሕይወቴ ጉዳት ሲደርስብኝ እንደሆነ የተገነዘብኩት ከዚህ በኋላ ነበር::



## ሌላው የፍቅሩ አጋማሽ

ጥበብም ንግግሩን በመቀጠል *"ለመትከል ጊዜ፣ ለማጨድም ጊዜ እንዳለ ሁሉ ጌታን በታላቅ ፍርሃትና አክብሮት የምናከብርባቸውና የምናወድስባቸው ጊዜያት አሉ:: እያንዳንዱን ጊዜ ለይቶ ማወቁ ጥበብ ነው:: እውነተኛ ጥበብ የእግዚአብሔርን ጊዜና ሰዓት ያውቃል:: አሁን አንተን ወደዚህ ስፍራ ያመጣሁበት ምክንያቱ ጌታን በፍቅሩ ክብር የምናመልክበት ሰዓት ስለሆነ ነው:: ያንን ከመሰለ የጦርነት ፍልሚያ በኋላ ከምንም ነገር በላይ የሚያስፈልግህ ነገር ይህ በመሆኑ አሁን ፍርዱን በመፍራት ታመልከው ዘንድ ወደ ሌላ ስፍራ እወስድሃለሁ:: እነዚህን ሁለቱን እስከምታውቅ ድረስ ግን ልንለያይ የምንችልበት አደጋ አለ"* አለኝ::

እኔም ንግግሩን በመጠራጠር "በዚያ በከበረ አምልኮ ውስጥ ብቆይ ኖሮ አንተን እንደማጣህ ነው ወይ የምትነግረኝ?" ስል ጠየቅሁት::

*"አዎን፣ መምጣት በምችልበት ጊዜ ዘወትር ወደዚህ ስፍራ እየመጣሁ እጎበኝሃለሁ:: ይሁንና መንገዶችን አብረን የምንሻገረው ግን እምብዛም ነው:: ይህን የመሰለውን ክብርና ሰላም ትቶ መሄድ ከባድ ቢሆንም ይህ ግን የንጉሡ ሙሉ መገለጥ አይደለም:: እርሱ የበግ ጠቦትና አንበሳ ሁለቱንም ነው:: ለመንፈሳዊ ህጻናቱ የበግ ጦቦት ሲሆን ለበሰሉት ደግሞ አንበሳ እንዲሁም የበግ ጠቦትም ነው:: አንተ ይህንን እንደምታውቅ ብረዳም ያወቅከው ግን በአዕምሮህ ነው:: በቅርቡ በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ስትቆም ያንጊዜ በልብህ ታውቀዋለህ"* አለኝ::

## ወደ ጦርነቱ መመለስ

የኤደን ገነት የአትክልት ቦታ በርን ከኋላችን ትተን ከመውጣታችን በፊት ጥበብን እስካሁን ያየሁትን በሙሉ ለጥቂት ጊዜ ያህል ቆም ብዬ ማሰላሰል እችል እንደሆነ ጠየቅሁት:: እርሱም *"አዎን ይህን ማድረግ አለብህ:: ሆኖም ይህን ለማድረግ ግን ከዚህ የተሻለ ስፍራ አለ"* አለኝና ይዞኝ ሄደ::

ጥበብን በበሩ በኩል ተከትዬው በመውጣት ከተራራው ከፍታ ወደ ታች መውረድ ጀመርን:: በዚህ ወቅት ጦርነቱ አሁንም ድረስ እየተካሄደ መሆኑን ስመለከት ደነቀኝ:: ሆኖም የአሁኑ ግን ወደ ተራራው ስንወጣ የነበረውን ያህል ከባድ አልነበረም:: በተራራው ታችኛው መወጣጫ ደረጃዎች ላይ አሁንም የሚወነጨፉ የክስና የስም ማጥፋት ፍላጻዎች ነበሩ:: አብዛኛው ከሞት የተረፈው የጠላት መንጋ በታላቆቹ ነጫጭ ንስሮች ላይ እጅግ አመርሮ ጥቃት

ቢሰነዝርባቸውም ንስሮቹ ግን በቀላሉ እያየሉበት ነበር።

እስከ ተራራው ስር ድረስም ወደ ታች ወረድን። "ከደህንነት" እና "ከቅድስና" መወጣጫ ደረጃዎቹ በላይ ያለው ደረጃ "የምስጋናና የውዳሴ" ነበር። ገና በጦርነቱ መጀመሪያ ላይ በዚህ ደረጃ ለመውጣት ስሞክር ጠላት ከሰነዘራቸው እጅግ የከፉ ጥቃቶች መካከል አንዱ አግኝቶኝ ስለነበር ይህንን ደረጃ በደንብ አስታውሰዋለሁ። አንዴ እዚህ ደረጃ ላይ ከደረስን ቀሪውን ደረጃ መውጣቱ ከፊተኞቹ ይልቅ በጣም ቀላል ነበር። ከዚያም ድንገት አንድ ከጠላት የተወነጨፈ ፍላጻ የጦር ዕቃችንን ዘልቆ ወጋው። ሆኖም ግን የጌታ ፈውስ ወዲያውኑ መጣ።

እዚህ ደረጃ ላይ እንደ ወጣን የጠላት ሠራዊት በእኔ ላይ ትኩረት ቢያደርግብኝም አብሮኝ የነበረውን ጥበብን ግን ማየት አይችልም ነበር። ስለዚህም ፍላጻቸውን እንደ ዝናብ አወረዱብኝ። እኔ ግን በቀላሉ በጋሻዬ እየመከትኩ አከሸፍኳቸው። በኋላ ግን የሚወረውሩት ፍላጻ ስላለቀባቸው መወንጨፋቸውን አቆሙ።

በዚህ ደረጃ ላይ ሆነው እሁንም ድረስ በትጋት ይዋጉ የነበሩ ወታደሮች እንዲህ አይበገሬ ያደረገኝን ልዩነት በማየት ተደንቀው ተመለከቱኝ። በዚህ ጊዜ ነበር የጌታ ክብር ከጦር ዕቃዎቼና ከጋሻዬ ላይ ሲፈነጠቅ ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተዋልኩት። ወታደሮቹ ያለ ማቋረጥ ወደ ተራራው ጫፍ ቢወጡ፣ እነርሱም እንደ እኔ በዚያ ጌታን እንደሚያዩት ነገርኳቸው። ለመሄድ ፈቃደኛ ሲሆኑም ወዲያውኑ ጥበብን አዩት። በዚህ ጊዜ እርሱን ለማምለክ መሬት ላይ መውደቅ ጀመሩ። እርሱ ግን አጥብቆ ከለከላቸው፣ መንገዳቸውንም እንዲሄዱ አዘዛቸው።

## ታማኞቹ

አብዛኞቹ ሴቶችና፣ ህጻናት ለነበሩት ለእነዚህ ወታደሮች ልቤ በፍቅር ተሞልቶ ነበር። የጦር ዕቃቸው የተዝረከረከና በደም የተበከሉ ቢሆኑም ለሽንፈት እጃቸውን ያልሰጡ ግን ነበሩ። የጦርነቱን እጅግ ትልቁን ሸክም የተሸከሙና ስፍራቸውንም ያልለቀቁ በመሆናቸው ከእኔ የበለጠ ክብር እንደሚገባቸው ነገርኳቸው። ይህንን ስላቸው ያመኑኝ ባይመስሉም ያንን በመናገሬ ግን ለእኔ ያላቸውን አድናቆታቸውን ገለጹልኝ። እኔም ይህ አድናቆታቸው ከልባቸው እንደሆነ ተሰምቶኛል።

ተራራው ላይ ያሉትን እያንዳንዱን መወጣጫ ደረጃዎች ፈጥነን በቁጥጥራችን ስር ማድረግ አለብን። አለበለዚያ ከሞት የተረፉት ጥንብ



እንሳዎች እየመጡ ለመርገጥ አስቸጋሪ እስከሚሆን ድረስ ደረጃው ላይ ሊያስታውኩበትና ዓይነ-ምድራቸውን ሊጥሉበት ይችላሉ። አብዛኞቹ ከፍታዎች ተከላክለው በጠበቋቸውና የደረጃውን እውነት በአጽንዖት በሚናገሩ ከተለያዩ ቤተ እምነቶች እንደመጡ በተገነዘብኳቸው ወታደሮች ቁጥጥር ስር ተይዘው ነበር። እነዚህን ቡድኖች ከእምነት ወደ ኋላ የተመለሱ አድርጌ አስብ ስለነበር ለአንዳንዶቹ በነበረኝ ጥሩ ያልሆነ አመለካከት ሃፍረት ተሰማኝ። ይሁንና እነርሱ ግን እዚህ ላይ ሆነው ከጠላት የሚሰነዘርባቸውን ኃይለኛ ጥቃት በታማኝነት እየተዋጉ ነበር። ምናልባትም እኔ የተራራውን ደረጃ መውጣት የቻልኩት እነርሱ እነዚህን ይዞታዎች በርትተው ስለ ተከላከሉልኝ ነው።

ከእነዚህ ደረጃዎች መካከል አንዳንዶቹ ለተራራውና ለውጊያ ሜዳው ጥሩ ዕይታ ቦታ ላይ የሚገኙ ቢሆንም አንዳንዶቹ ደረጃዎች ግን በጣም የተነጠሉ ስለነበሩ በዚያ ያሉት ወታደሮች ማየት ይችሉ የነበረው የገዛ ራሳቸውን ስፍራ ብቻ ነበር። እነዚህ ወታደሮች ደግሞ ስለ ተጧጧፈው ጦርነት ወይም ጦርነቱን ይዋጋ ስለ ነበረው የወገን ሠራዊት የማያውቁ ነበር የሚመስሉት። እነዚህ ወታደሮች ከነበሩበት ከተራራው ዝቅተኛ ደረጃ እነርሱ ወዳሉበት ከፍተኛ ደረጃ ይወጡ ዘንድ ለማበረታታትና ለመርዳት ወደ ታችኛው ደረጃ ወርዶ የሚመጣውን ማንኛውንም ሰው ይቃወሙ በነበሩ ወታደሮች በክስና በስም ማጥፋት ቀስት ተወግተው ክፉኛ የቆሰሉ ነበሩ። ይሁንና አንዳንዶቹ የጌታን ክብር እያብለጨለጩ ከላይ ወደ ታች መውረድ ሲጀመሩ ግን ታችኛው ደረጃ ላይ የነበሩት አብዛኞቹ ታላቅ የደስታ ድምጽ በማሰማት በቆራጥነት ወደ ላይ መውጣት ጀመሩ። ይህን ሁሉ እየተመለከትኩ እያለሁ ጥበብ ብዙም አልተናገረም። ሆኖም እኔ በሰጠሁት ምላሽ ግን በጣም ነው ደስ ያለው።

## እውነቱ ተገኘ

በዚህን ጊዜ ተራራው ጫፍ ላይ ደርሰው የነበሩና በእነዚያ እውነቶች ላይ አቋም በመውሰድ ከታች ወደሚገኙት ሁሉም ደረጃዎች ወርደው መርዳት የጀመሩ በርካታ ሠራዊትን አየሁ። እያንዳንዳቸው ይህንን በሚያደርጉበት ጊዜ በላያቸው ከተሸከሙት ክብር የተነሳ የረገጡት ደረጃ ያንጸባርቅ ጀመር። በመቀጠልም ተራራው በሙሉ ከሞት የተረፉትን ጥንብ አንሳዎችና አጋንንቶችን ዓይን የሚያሳውር ክብርን ማንጸባረቅ ጀመረ። ከጥቂት ጊዜ በኋላም በተራራው ላይ እጅግ ታላቅ ክብር ከመወረዱ የተነሳ ልክ እንደ ኤደን ገነት የአትክልት ስፍራ ያለ ተመሳሳይ ስሜት ይሰማን ጀመር።

ጌታን ስለዚህ ክብሩ ማመስገንና ማወደስ እንደ ጀመርኩ እንደገና በእርሱ ኅልዎት መገኘት ውስጥ ገባሁ። በዚህ ልምምድ ውስጥ የተሰማኝን ስሜትና

ክብር በውስጤ መያዝ እየከበደኝ ሲመጣም አቆምኩ። በዚህ ጊዜ ጥበብ ከጎኔ ቆመና እጆቼን ትከሻዬ ላይ ጣል አድርጎ *"በምስጋና ወደ ደጆቹ በውዳሴም ወደ አደባባዮቹ ግብተሃል"* አለኝ።

እኔም "እንደገና በኤደን ገነት እንዳለሁ ነው የሚሰማኝ። ሆኖም የበፊቱ ግን በጣም እውነት ነበር!" ስል መለስኩለት።

ጥበብም *"በዚያ ነበርክ፣ እንዲህ እውን ሆኖ ባያውቅም፣ ለአንተ ግን ሆኗል። ልክ ጌታ በመስቀል ላይ አጠገቡ ተሰቅሎ ለነበረው ወንበዴ 'ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ' እንዳለው አንተም በማንኛውም ጊዜ ወደ ገነት መግባት ትችላለህ። ጌታ ያለው በውስጥህ በመሆኑ ምክንያት እርሱ፣ የእርሱ ገነትና ይህ ተራራ ሁሉም በውስጥህ ነው ያሉት። ተራራውን ስለወጣህ ቀድሞ የነበረውና ከዚህ በፊት የቀመስከው አሁን ለአንተ እውነት ሆነዋል። አንተ እኔን ማየት ስትችል ሌሎች ያልቻሉበት ምክንያቱ እኔ ወደ አንተ ግዛት በመግባቴ ሳይሆን አንተ ወደ እኔ ግዛት በመግባትህ ነው። ነቢያቱ በጠላት ሠራዊት ፊት ብቻቸውን በቆሙ ጊዜ እንኳን ትልቅ ድፍረትን የሰጣቸው ይህ የተረዱት እውነት ነው። በእነርሱ ላይ የተሰለፈባቸውን ምድራዊውን ሳይሆን የጌታ ወገን የሆኑትን የሰማይ ሠራዊትን በማየታቸው ነው"* ሲል መለሰልኝ።

## ገዳዩ ወጥመድ

በመቀጠል ከላይ ሆኜ ወደ ታች ወደ ጦርነቱ እልቂትና ወደ ኋላው ያፈገፍግ የነበረውን የአጋንንት ሠራዊቱን ተመለከትኩ። ከኋላዬ ክብር የሞላባቸው ብዙ ተዋጊዎች በተራራው ላይ ስፍራቸውን እንደያዙ ነበሩ። በዚህን ጊዜ ከዚህ የጠላት መንጋ የተረፈውን ለመደምሰስ ኃይሉና ብርታቱ እንዳለን አወቅሁ። ጥበብ ግን *"አሁን ጊዜው አይደለም። እዚያ ማዶ ተመልከት"* ሲለኝ ወዳመለከተኝ አቅጣጫ ተመለከትኩ። ሆኖም ከገዛ ራሴ የጦር ዕቃ እያንጸባረቀ የሚወጣው የብርሃን ነጸብራቅ ማንኛውንም ነገር ለማየት ስለከለከለኝ ያንን ለመከላከል ዓይኖቼን በእጄ ጋረድኩኝ። ከዚያም በውልብታ በትንሽ ሸለቆ ውስጥ ያለን እንቅስቃሴ አየሁ።

ከጦር ዕቃዬ እየወጣ ያንጸባርቅ የነበረው ክብር ጨለማው ውስጥ ያለውን ለማየት አስቸጋሪ ስላደረገብኝ የማየው ነገር በትክክል ምን እንደሆነ መረዳት አልቻልኩም። ነገሩን ማየት እችል ዘንድ የጦር ዕቃዬን መጋረድ የምችልበት ነገር ካለ ብዬ ጥበብን ብጠይቀው እለብሰው ዘንድ አንድ በጣም መናኛ የሆነ መጎናጸፊያን ሰጠኝ። መጎናጸፊያውን ሳየው ለዓይን ደስ



የማይል ስለነበር "ይሄ ደግሞ ምንድነው?" ስል ጠየቅሁት። እርሱም *"ትህትና ነው። ይህን ካልደረብክ በቀር በደንብ ማየት አትችልም"* አለኝ። እኔም መጎናጸፊያውን እየተጠየፍኩ ለበስኩት። በዚህን ጊዜ ከዚህ በፊት ማየት ያልቻልኳቸውን ብዙ ነገሮችን ማየት ጀመርኩ። ወደ ሸለቆውና በዚያ አይቼው ወደ ነበረው እንቅስቃሴም ተመለከትኩ። ተራራው ላይ ሆኖ ያገኘውን ሁሉ መትቶ ለመጣል አድፍጦ ይጠባበቅ የነበረ አንድ የጠላት ክፍለ ጦር መንጋ በዚያ መኖሩን ስመለከት ደነቀኝ።

"ያስ የምን ሠራዊት ነው? ከውጊያው ጥቃትስ እንዴት አመለጠ?" ስል ጥበብን ጠየቅሁት።

ጥበብም *"ትዕቢት ነው። ወደ እግዚአብሔር ክብር ውስጥ ከገባችሁ በኋላ የሚከተላችሁ እጅግ ክፉው ጠላት እርሱ ነው። ያ አሳች ጠላት ይህንን መጎናጸፊያ ለመደረብ ፈቃደኛ የማይሆኑ ሰዎችን ብዙ ችግር ያደርስባቸዋል"* ሲል አብራራልኝ።

ወደ ኋላዬ ወደ ተራራው ዘወር ብዬ ስመለከት በርካታ የከበሩ ተዋጊዎች የጠላትን መንጋ ቅሬታዎችን ለማጥቃት ሜዳውን ሲያቋርጡ አየሁ። አንዳቸውም የትህትና ካባ ስላልለበሱ ከጀርባቸው ሆኖ ጥቃት ሊሰነዝርባቸው አድፍጦ ቆሞ የነበረውን ጠላት አላዩትም ነበር። እኔም ላስቆማቸው ብዬ ወደ እነርሱ መሮጥ ስጀምር ጥበብ *"ሥልጣንህን የሚያውቁልህ ይህንን ካባ የደረቡ ወታደሮች ብቻ በመሆናቸው እነርሱን ማስቆም አትችልም። ሊመጣ ያለውን ታላቅ ጦርነት መምራት ከመቻልህ በፊት ግን ማየት ያለብህ አንድ ነገር አለና ተከተለኝ"* ሲል ከለከለኝ።

## የክብሩ መሠረት

ጥበብ በጣም የመጀመሪያ ወደሆነውና "ድነት" ወደ ተባለው የተራራው ታችኛው ደረጃ እየመራ ወሰደኝና *"አንተ የተራራው የመጨረሻ ዝቅተኛ ደረጃ ይሄ እንደሆነ ነው የምታስበው። ይሁንና ይህ ደረጃ ግን የተራራው ሁሉ መሠረት ነው። ለየትኛውም ጉዞ እጅግ አስፈላጊው ነገር የመጀመሪያው ርምጃ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ እጅግ አስቸጋሪውም እርሱ ነው። ያለ 'ድነት' ከፍታ የሚባል ነገር የለም"* አለኝ።

በዚህኛው ደረጃ ላይ በደረሰው እልቂት ተደናግጬ ነበር። እያንዳንዱ ወታደር እጅግ ክፉኛ ቢቆስሉም አንዳቸውም ግን አልሞቱም። ብዙዎቹ ለመውደቅ የቀረቡ ቢመስሉም አንዳቸውም ግን አልወደቁም። ከሞት

የተረፉትም በተራራው ጠርዝ ላይ ሳመል ያህል ተንጠልጥለው ነው። መላዕክት እነዚህን ወታደሮች ለማገልገል በታላቅ ደስታ በሁሉም በታ ተገኝተው ስለነበር "ለምንድነው እንዲህ ሲበዛ ደስ ያላቸው?" ብዬ መጠየቅ ነበረብኝ።

*"እነዚህ መላዕክት እነዚህን ወታደሮች በሕይወት ጠብቆ ለማቆየት ከፍተኛ ጀግንነትን አሳይተዋል። ብዙ ገፍተው አልሄዱ ይሆናል። ይሁንና ተስፋ ግን አልቆረጡም። ሲፈወሱ ወዲያውኑ የቀራቸውን የተራራውን ከፍታ ክብር ለማየት መውጣት ይጀምራሉ። እነዚህ ሊመጣ ላለው ጦርነት ታላቅ ተዋጊዎች ይሆናሉ"* አለኝ።

አሁን ያሉበትን ሁኔታ በማየትም "ተራራውን ከቀረነው ጋር አብረውን ቢወጡ አይሻልም ነበርን?" ስል ተቃውሞዬን አቀረብኩኝ።

*"ይሄ የተሻለ የሚሆነው ለአንተ ሳይሆን ለእነርሱ ነበር። ሌሎች ወደ ተራራው ከፍታ ላይ እንዲወጡ ለመርዳት በጣም ጥቂት ሰዎች ከነበሩበት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ወርደው መጥተው ባያውቁም እነዚህ ግን ይህንን አድርገዋል። እነዚህ ራሳቸው በተራራው ጠርዝ ላይ ተንጠላጥለው የነበሩ ቢሆኑም እንኳን ሌሎችን ጎትተው ለማዳን ግን የደረሱ ናቸው። በእርግጥም ብዙዎቹ ኃያላን ተዋጊዎች ተራራው ጫፍ ላይ የደረሱት በእነዚህ በታማኞቹ እገዛ ነው። የእነዚህ ጀግንነት ተራራው ጫፍ ላይ ከደረሱት ጀግንነት የሚተናነስ አይደለም። በሰማይ ታላቅ ደስታ ይሆን ዘንድ ሌሎችን ወደ ተራራው የድነት ደረጃ በማምጣት ረገድ ትልቅ አስተዋጽዖን አበርክተዋል። ከዚህ የተነሳ በሰማይ ያሉ መላዕክት በሙሉ መጥተው ሊያገለግሏቸው ቢፈልጉም የተፈቀደላቸው ግን እጅግ ለከበሩት ብቻ ነው"* አለኝ።

ብዙዎቻችን ወደ ላይኛው የተራራው ከፍታ እየወጣን ሳለን በእነዚህ ታላላቅ ቅዱሳን ላይ የነቀፋ ቃል ስንሰነዝርባቸው ስለነበር በእነርሱ ላይ ስለነበረኝ በጎ ያልሆነ አመለካከት እንደገና ሃፍረት ተሰማኝ። እነርሱ ግን ተግቶ በመዋጋትና ነፍሳትን በመናጠቅ የእረኝነት ልብ እንዳላቸው አሳይተውናል። ጌታ ዘጠና ዘጠኙን ትቶ የጠፋውን አንዱን ፍለጋ እንደ ሄደ እነርሱም የጠፉትን ሊደርሱ በሚችሉበት ስፍራቸው ላይ ጸንተው በመቆም አሁንም ድረስ ውድ ዋጋን እየከፈሉ ናቸው። እኔም እነርሱን መርዳት ብፈልግም ከየት እንደምጀምር ግን አላወቅሁም።

ከዚያም ጥበብ *"እነርሱን ለመርዳት መፈለግህ ትክክል ነው። ይሁንና የበለጠ የምትረዳቸው ግን ትሰራው ዘንድ በተጠራህበት ጥሪ ስትሄድ ነው።*



*እነዚህ ሁሉ የሚፈወሱና ወደ ተራራው የሚወጡ ናቸው። አሁን ከአንተና ከእነርሱ በፊት ከወጡት ከሌሎች ከሁለቱም የተነሳ ጠላትን በመደምሰስና መንገድን በማመልከት ፈጥነው መውጣት ይችላሉ። ጠላትን ፊት ለፊት ከመጋፈጥ ፈጽሞ ወደ ኋላ ያላፈገፈጉ ደፋሮች ስለሆኑም እንደገና በጦርነቱ ውስጥ ከጎንህ ይሰለፋሉ"* አለኝ።

## የትዕቢት ኃይል

ከጦርነቱ ሜዳ የሚሰማው ድምጽ ትኩረቴን በወሰደው ጊዜ ተራራውን ስወጣ እንደተማርኩት ስወርድም እንዴት እየተማርኩ እንደ ነበር በሃሳቤ አወጣና አወርድ ነበር። በአሁኑ ሰዓት በሺህዎች የሚቆጠሩ ኃያላን ተዋጊዎች በጠላት መንጋ ላይ ጥቃት ለመሰንዘር ሜዳውን ተሻግረው ሲሄዱ ትዕቢት ከተባለው የጠላት ኃይል አንዱ ክፍለ ጦር በቀር ሌላው የጠላት ኃይል በሙሉ ሽሽቱን በየአቅጣጫው ተያያዘው። በዚህን ጊዜ ትዕቢት ሙሉ በሙሉ ሳይደመሰስ ከቀረውና ወደ ፊት እየገፋ ከነበረው ተዋጊ ኃይሉ ጀርባ ሆኖ የፍላጻዎችን መዓት ሊያዘንብ ተንቀሳቀሰ። በዚህን ጊዜ ነበር ኃያላኑ ተዋጊዎች ከጀርባቸው በኩል ለሚሰነዘርባቸው የጥሩር ፍላጻ ሙሉ በሙሉ የተጋለጡትና ይህንንም ጥቃት የሚከላከሉበት የጦር ዕቃ እንዳልነበራቸው የተገነዘብኩት።

ከዚያም ጥበብ *"ከበስተጀርባ ለተሰለፈው ጦር መከላከያ የሚሆን የጦር መሳሪያ የለም ብለህ አስበሃል። ከጠላት ፊት ሸሽተህ መሮጥ ማለት ለጥቃት መጋለጥ ማለት ነው። ይሁንና በትዕቢት መፍጠንም ምን ያህል ለጥቃት እንደሚያጋልጥህ ፈጽሞ አላየህም"* ሲል አስተያየቱን ሰነዘረ።

እኔም ለዚህ ንግግሩ ስምምነቴን መግለጽ የቻልኩት ራሴን በመነቅነቅ ብቻ ነበር። ነገሩን መታገስ ባይቻለኝም ምንም ነገር ለማድረግ በጣም በመዘግየቴ ግን ጥበብ ያንን መታገስ እንዳለብኝ ተናገረ። ከዚህ በፊት ሃዘን ተሰምቶኝ አውቃለሁ። ሆኖም አሁን የእግዚአብሔር መንግስት ትልቅ ሽንፈት ሊደርስበት እንደሆነ ሳውቅ የተሰማኝ ዓይነት ሃዘን ግን ፈጽሞ ተሰምቶኝ አያውቅም።

ጠላት የትዕቢት ቀስቱን እየወነጨፈ አርበኞቹን ሲወጋቸው እነርሱ ግን መወጋታቸውን ያለማወቃቸውና ጠላትም ፍላጻዎቹን መወንጨፉን አለማቋረጡ ደነቀኝ። አርበኞቹ ደም እየፈሰሳቸውና እየደከሙ ቢሆኑም እነርሱ ግን ያንን አላወቁም። ወዲያውኑም ጋሻቸውንና ሰይፋቸውን መሸከሙ በጣም ስለከበዳቸው የጦር ዕቃዎቹ ከዚህ በኋላ እንደማያስፈልጓቸው በመግለጽ እያወላለቁ ይወረውሯቸው ጀመር።

ከዚያም "ብርቱው አሳች" የተባለው ሌላው የጠላት ክፍለ ጦር ፈጥኖ ተገለጠ። መላው የዚህ ክፍለ ጦር አባላትም የቀስት መዓታቸውን እንደ ዝናብ በማውረድ ዒላማቸውን የመቱ መሰሉ። ትናንሽና ደካማ የሚመስሉት ጥቂት አሳች አጋንንቶች አንድ ወቅት ታላቅና የከበረ ሠራዊት የነበሩትን እነዚህን አርበኞች እየነዱ በምርኮ ወሰዷቸው። ሁሉም የተለያየ የአጋንንት አስተምህሮ ስሞች ወደ ተሰጧቸው የተለያዩ እስር ቤቶች ተወረወሩ። ይህ ታላቅ የጽድቅ ሠራዊት እንዴት እንዲህ በቀላሉ እንደ ተሸነፈና እስካሁን ድረስም ጥቃት ያደረሰበት ማን እንደሆነ እንኳን ባለማወቁ ተገረምኩ።

"እነዚያ ተራራው ጫፍ ድረስ ወጥተው የነበሩና ጌታን ያዩ ብርቱዎቹ እንዴት እንዲህ ለሽንፈት ሊጋለጡ ቻሉ?" ስልም ድንገት የልቤን ሃሳብ አውጥቼ ዘከዘኩት።

ጥበብም *"እጅግ ከፉና ሁልጊዜ ከጀርባችሁ አድብቶ ሊጥላችሁ የሚፈልግ ጠላት ቢኖር ትዕቢት ነው። በአንዳንድ መንገዶች እጅግ ታላቅ ወደሚባሉ ከፍታዎች ላይ የወጡ ሰዎች በታላቅ የውድቀት አደጋ ውስጥ ነው የሚወድቁት። መቼም ቢሆን በዚህ ሕይወት በማንኛውም ሰዓት ከየትኛውም ደረጃ ላይ ልትወድቅ እንደምትችል ማስታወስ አለብህ"* ሲል አዝኖ ነገረኝ።

እኔም ለራሴ "የቆምክ የሚመስልህ እንዳትወድቅ ተጠንቀቅ" አልኩና "እነዚህ የቅዱሳት መጻህፍት ቃሎች ለእኔ አሁን እንዴት አስፈሪ መሰሉ" በማለት መለስኩለት።

ጥበብም *"ለውድቀት ጥቃት ከተጋለጡት ሰዎች ታናሹ አንተ መሆንክህን የምታውቀው ለውድቀት እጅግ የተጋለጥክ መሆንህ ሲታሰብህ ነው። ብዙ ሰዎች የሚወድቁት ከትልቅ የድል ስኬት በኋላ ነው"* ሲል በሃዘን ገለጸልኝ።

እኔም "ታዲያ ራሴን ይህን ከመሰለ ጥቃት መጠበቅ የምችለው እንዴት ነው?" ስል ጠየቅሁት።

*"ወደ እኔ ቅረብ፣ በሕይወትህ ትላልቅ ውሳኔዎችን ከመወሰንህ በፊት በዚያ ጉዳይ ላይ የጌታ ፈቃድ ምን እንደሆነ እርሱን ጠይቅ፣ ያንን የትህትና መጎናጸፊያህንም ልበስ። ያንጊዜ ጠላት የእነዚያን ሠራዊት ዓይኖች እንዳሳወረ የአንተን በቀላሉ ማሳወር አይችልም"* አለኝ።

መጎናጸፊያዬን ስመለከተው በጣም መናኛና የማይረባ የሚመስል ሲሆን እኔም ከአንድ ተዋጊ አርበኛ ይልቅ አንድ ምስኪን በረንዳ አዳሪ እንዳስመሰለኝ



ነበር የተሰማኝ። ጥበብ ግን ድምጼን ከፍ አድርጌ የተናገርኩ ይመስል እንዲህ ሲል መለሰልኝ።

*"ጌታ ከነገሥታት ይልቅ ለበረንዳ አዳሪዎች ቅርብ ነው። ጸጋውን የሚሰጠው ለትሁታን በመሆኑ እውነተኛ ብርታት የሚኖርህ በእግዚአብሔር ጸጋ በተመላለስክበት መጠን ብቻ ነው። ከጸጋው ሊበልጥ የሚችል ኃይል ስለሌለ የትኛውም የክፋት መሳሪያ ይህንን መጎናጸፊያ አልፎ ሊወጋህ አይችልም። አንተም ይህንን መጎናጸፊያ እስከለበስክ ድረስ ከዚህ ዓይነቱ ጥቃት የተጠበቅህ ነህ"*።

ከዚያም በተራራው ላይ ስንት ተዋጊ አርበኞች እንደ ቀሩ ለማየት ወደ ላይ አንጋጥጬ መመልከት ጀመርኩ። የቀሩት ጥቂት መሆናቸውን ባየሁ ጊዜም ደነገጥኩ። ይሁን እንጂ ሁሉም ተመሳሳይ የሆነ የትህትና መጎናጸፊያ ለብሰው በማየቴ ግን "ያ እንዴት ሆነ?" ስል ጥበብን ጠየቅሁት።

ጥበብም *"አንተ የመሰከርከለትን ጦርነት ባዩ ጊዜ ሁሉም የእኔን ርዳታ ፈልገው ወደ እኔ መጡ። እኔም መጎናጸፊያቸውን ሰጧቸው"* ሲል መለሰልኝ።

"ግን እኮ ያንን ወቅት በሙሉ ከእኔ ጋር እንደ ነበርክ ነው ይሰማኝ የነበረው?" አልኩት።

እርሱም *"እኔ የአባቴን ፈቃድ ለመፈጸም ወደፊት ከሚጓዙት ሁሉ ጋር እገኛለሁ"* ሲል መለሰልኝ።

እኔም በዚህን ጊዜ "ጌታ ነህ እንዴ ለካ!" ብዬ ጮኽኩኝ።

እርሱም *"አዎን! ፈጽሞ እንደማልተውህ፣ እንደማልጥልህ ይህን ነግሬሃለሁ። ከአንተ ጋር እንደሆንኩ ሁሉ ከሌሎቹም ተዋጊዎች ሁሉ ጋር እሆናለሁ። ፈቃዴን ለመፈጸም በምትፈልግበት ቦታ ሁሉ በዚያ ከአንተ ጋር እሆናለሁ። ጥበብም ያስፈልግሃል"* አለኝና ተሰወረብኝ።

## በመንግስቱ ውስጥ ያለው ማዕረግ

"በድነት" ደረጃው ላይ የቆሙትንና የቆሰሉትን ያገለግሏቸው በነበሩት ታላቅ የመላዕክት ሠራዊት መካከል እንደ ቆምኩ ነበር። በመላዕክቱ መካከል እየተራመድኩ ማለፍ እንደ ጀመርኩም በጉልበታቸው በርከክ በማለት ለእኔ ያላቸውን አክብሮት በታላቅ በሰላምታ ገለጹልኝ። በመጨረሻም ከእኔ ይልቅ

በኃይል የበረቱ ሆነው ሳለ ለምን እንዲህ እንዳደረጉ ከመካከላቸው እጅግ ታናሽ የሆነውን አንዱን መልዓክ ጠየቅሁት። እርሱም "ከለበስከው መጎናጸፊያ የተነሳ ነው። በመንግስቱ ውስጥ እጅግ ትልቁ ማዕረግ ደግሞ እርሱ ነው" ሲል መለሰልኝ።

እኔም "ይሄ እኮ መናኛ መጎናጸፊያ ነው" አልኩት።

መልዓኩም "አይደለም! የለበስከው የእግዚአብሔርን ጸጋ ነው። ከዚያ የሚልቅ ታላቅ ኃይል ደግሞ የለም!" ሲል ተቃወመኝ።

"ይሁንና መጎናጸፊያውን በሺዎች የምንቆጠር ነን የለበስነው። ታዲያ እንዴት ነው መጎናጸፊያው ማዕረግን ሊወክል የሚችለው?" ስል ጠየቅሁት።


"እናንተ ታላቅ ፍርሃት ያደረባችሁ ድል አድራጊ የንጉሡ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ናችሁ። እርሱ በዚህ ምድር ይመላለስ በነበረበት ሰዓት ላይ ተመሳሳዩን መጎናጸፊያ ለብሶ ነበር የተመላለሰው። ያንን መጎናጸፊያ እስከለበሳችሁ ድረስ በሰማይም ሆነ በምድር በፊታችሁ ሊቆም የሚችል ኃይል አይኖርም። ያንን መጎናጸፊያ መንግስተ ሰማይም ሆነ ሲኦል ያሉት ሁሉ ያውቁታል። በእርግጥ እኛ የእርሱ አገልጋዮች ብንሆንም እርሱ ግን በእናንተ ውስጥ ነው የሚኖረው። እናንተም የለበሳችሁት የእርሱን ጸጋ ነው" አለኝ።

መጎናጸፊያውን ባልለብስና የከበረውን የጦር ዕቃዬንም ጥዬው ቢሆን ኖሮ ይህ የመልዓኩ ንግግርና መሳዕከቱም ለእኔ ያሳዩኝ አክብሮት በትዕቢት ይሞላኝ እንደነበር ተረዳሁ። ይህን የመሰለ መናኛ መጎናጸፊያ ለብሶ እንዲህ በቀላሉ በትዕቢት ወይም በእብሪት መሞላት የማይቻል ነበር። ይሁን እንጂ በመጎናጸፊያው ላይ ያለኝ እምነት ግን በፍጥነት እያደገ ሄደ።



# ክፍል ሦስት

# የንስሮቹ መመለስ



# ክፍል ሦስት

# የንስሮቹ መመለስ

ከአድማስ ማዶ አቅጣጫ ታላቅ ነጭ ደመና ወደ እኛ እየመጣ እንደሆነ ስመለከት በውስጤ የሆነ ተስፋ ተቀሰቀሰ:: የጸሐይዋ መውጣት የሌሊቱን ጨለማ ሲገፈው ወዲያውኑ አካባቢው በተስፋ ተሞላ:: ደመናው እየቀረበ በመጣ ጊዜም ከሕይወት ዛፍ ላይ እየተነሱ የሚበሩ ታላላቅ ነጫጭ ንስሮችን አየሁ:: ንስሮቹም በእያንዳንዱ የተራራው ደረጃ ላይ ከተሰለፉት አርበኞች ጎን ቦታ ቦታቸውን በመያዝ ተራራው ላይ ማረፍ ጀመሩ::

የንስሮቹ በዚያ ቦታ መገኘት በጣም ስላስደነቀኝ አጠገቤ መጥቶ ያረፈውን ንስር ትኩር ብዬ በጥንቃቄ ተመለከትኩት:: ንስሩም በሚዋጉ ዓይኖቹ በጥልቀት ሲመለከተኝ ከእርሱ ምንም ነገር መደበቅ እንደማልችል ተረዳሁ:: ዓይኖቹን ሳያቸው ብርድ እንደ ያዘው ሰው እስክንቀጠቀጥ ድረስ በጣም ቁጡና አስፈሪ ነበሩ:: ንስሩም ከአፌ ቃል አውጥቼ ጥያቄ መጠየቅ ከመቻሌ በፊትም እንዲህ አለኝ::

"እኛ ማን መሆናችንን ማወቅ ትፈልጋለህን? እኛ ለዚህ ሰዓት ተጠብቀን የተሸሸግን ነቢያቶች ነን:: መለኮታዊ ኃይል ያላቸው የጦር መሳሪያዎች ለተሰጣቸው ሰዎችም ዓይኖች ነን:: ጌታ ያደረጋቸውን ነገሮችና ጠላትም በእናንተ ላይ ሊያደርገው ያቀደባችሁን ሁሉ እንድናይ ተደርገናል:: ሁላችንም ምድርን በሙሉ አሰስናት፣ ስለ ጦርነቱ ማወቅ የሚያስፈልገውንም ነገር ሁሉ አውቀናል"::

እኔም በጣም በቁጣ ሆኜ "ታዲያ የተካሄደውን ጦርነት አላያችሁምን? ተማርከው የተወሰዱትን እነዚያን የእምነት አርበኞችንስ እንዴት ልትረዷቸው አልቻላችሁም?" ስል ጠየቅሁት::

"በእርግጥ ሁሉንም ነገር አይተናል:: ርዳታ እንድናደርግላቸው ቢጠይቁን ኖሮ ልንረዳቸው እንችል ነበር:: ወደ ኋላ እንዲያፈገፍጉ፣ እንዲረጋጉና አርፈው እንዲቀመጡም በመንገር እንረዳቸው ነበር:: ይሁንና ጦርነቶቹ ውስጥ ገብተን መዋጋት የምንችለው ግን አብ ሲያዘን ነው:: ልንረዳቸው የምንችላቸውም በእኛ የሚያምኑትን ብቻ ነው:: የነቢይን ወይም የእኛን አገልግሎት ጥቅም ማግኘት የሚችሉት እኛን እንደ ነቢይ የተቀበሉን ብቻ



ናቸው:: እነዚህ አርበኞች እናንተ የለበሳችሁትን መጎናጸፊያ ገና አላገኙም:: መጎናጸፊያው ስለሌላቸውም የእኛን ማንነት ማወቅ አይችሉም:: እዚህ ቆስለው ያሉትን ጨምሮ ገና ያላወቅሃቸው ሌሎች ሁላችንም አንዳችን ለአንዳችን እናስፈልጋለን" አለኝ::

## የንስሩ ልብ

ከንስሩ ጋር እየተነጋገርኩ እያለሁ እንደ እርሱ ማሰብ ጀመርኩ:: ከዚህ አጭር ውይይት በኋላም የንስሩን ልብ ጠልቄ ማየትና እርሱ እኔን እንዳወቀኝ፤ እኔም እርሱን ማወቅ ቻልኩ:: ንስሩም ይህን ተገንዝቦት ስለ ነበር እንዲህ አለኝ::

"ምንም እንኳን በጣም ያደጉ ባይሆኑም አንዳንድ የእኛ ዓይነት ስጦታዎች አሉህ:: ይሁንና ብዙም አልተጠቀምክባቸውም:: እኔ በዚህ የተገኘሁት በአንተና ሌሎች አንተን በመሰሉ ሰዎች ውስጥ ያሉትን እነዚህን ስጦታዎች ለመቀስቀስና እንዴት እንደምትጠቀሙባቸውም ላስተምርህ ነው:: ግንኙነታችንም በዚህ መንገድ እውን ይሆናል:: ሁላችንም ለድል የሚያበቁንን በርካታ ታላላቅ ዕድሎች እንዳጣናቸው ላለመጥቀስ እርግጠኛ መሆን አለብን:: አለበለዚያ አላስፈላጊ ለሆኑ ጥፋቶች ሰለባ እንሆናለን"::

እኔም "ከየት ነው የመጣኸው?" ስል ጠየቅሁት::

ንስሩም "የምንበላው እባቦችን ሲሆን ምግባችንም ጠላት ነው:: ምግባችን የሚመጣው የዲያቢሎስን ሥራ ማፈራረስ የሆነውን የአብን ፈቃድ ከማድረግ ነው:: የምንበላው እያንዳንዱ እባብ ራዕያችን እንዲጨምር ሲረዳን፤ የምናፈራርሰው እያንዳንዱ የጠላት ምሽግም ይበልጥ ከፍ ብለን እንድንበርና ረዘም ላለ ጊዜም በአየር ላይ እንድንቆይ የሚያበረታን ነው:: የመጣነው የሃፍረት እባቦች ከሚበሉበትና ብዙዎቹን ወንድምና እህቶችህን አስሮ ከያዛቸው ድግስ ላይ ነው:: እነዚህ ወንድሞችህና እህቶችህ መንገዱን እንዲመሯቸውና ከጠላትም የመልሶ ማጥቃት ጥቃት እንዲጠብቋቸው ከኋላ ትተናቸው ከመጣናቸው ንስሮች ጋር እየመጡ በመሆናቸው በቅርቡ እዚህ ይደርሳሉ" አለኝ::

እነዚህ ንስሮች ስለ ራሳቸው እርግጠኞች ቢሆኑም ትምክህተኛ ግን አልነበሩም:: ማን እንደነበሩና ምን ያደርጉ ዘንድ እንደተጠሩ ያውቁ ነበር:: እኛ ጋና ወደፊት ሊሆን ያለውንም ያውቁ ነበር:: በራስ መተማመናቸው እኔን፣ ከእኔ በበለጠም አሁን በዙሪያችን የተገኙትንና የቆሰሉትን ሁሉ የሚያጽናና ነበር:: በጣም የደከሙት ከንስሩ ጋር ያደረኩትን ውይይት በቅርበት ሆነው

ያዳምጡ ነበር:: የጠፉ ልጃቸውን ያገኙ ወላጆች ልጃቸውን በስስት እንደሚያዩት ይመለከቱኝ ነበር::

## የመንፈሱ ነፋስ

ንስሩ ጠላት ያቆስላቸውን ሲመለከት ፊቱ ተለዋወጠ:: ክንፎቹንም ዘርግቶ በማራገብ በቆሰሉት ላይ ቀዝቀዝ ያለ የሚያነቃቃ ለስላሳ ነፋሻማ የነፋስ ሽውታ በእርጋታ ያራግብላቸው ጀመር:: ይህ ነፋስ ከሌላው የነፋስ ሽውታ የተለየና በፍጹም ከዚህ በፊት ተሰምቶኝ የማላውቀው ነፋስ ነበር:: በዚህ በእያንዳንዱ የነፋስ ሽውታም ኃይልና የአዕምሮ ብሩህነትን እሳበስ ነበር:: የቆሰሉትም ወዲያውኑ ፍጹም ትህትና በተሞላ አኳኋን ቆመው እግዚአብሔርን ሲያመልኩ ሳይ እንባዬ ፈሰሰ::

እንደገናም እነዚህ በዚህ ደረጃ ላይ ተወስነው የቀሩት ወገኖች ተራራውን እየወረድን ላለነው ለእኛ በጣም ደካማና ሞኝ ቢመስሉንም በመከራ ውስጥ አልፈው የዳኑና ከእኛ በበለጠ ታማኝነታቸውን የጠበቁ ነበሩ:: እግዚአብሔር ከከፋው ጥቃት ስለጠበቃቸው እነርሱም በታላቅ ፍቅር ወደውታል:: ስለዚህም እነርሱን አንቋሽሼ በማየቴ ከባድ ሃፍረት ተሰማኝ::

አንጋጥጬ ወደ ተራራው ጫፍ ስመለከት ሁሉም ንስሮች ክንፎቻቸውን በእርጋታ ያራግቡ ነበር:: ተራራው ላይ ያለው እያንዳንዱ ሰው እነርሱ በክንፋቸው በሚያራግቡት ለስላሳ ነፋስ እየተነቃቃ ጌታን ማምለክ ጀመረ:: መጀመሪያ ላይ በተለያየ የተራራው ደረጃ ላይ የነበሩት ሰዎች በሚያቀርቡት አምልኮ መካከል የሚሰማው የሕብረ ዝማሬው ድምጽ የተዘበራረቀ ነበር:: ይሁንና ከጥቂት ቆይታ በኋላ ግን በእያንዳንዱ ደረጃ ላይ የሚገኘው ሰው ፍጹም በሆነ የድምጽ ውህደት ይዘምር ጀመር:: በምድር ላይ ፈጽሞ እንደዚያ ያለ የተዋበ ሕብረ ዝማሬ ሰምቼ ስለማላውቅ ይህ ዝማሬ እንዲቆም በፍጹም አልፈለኩም ነበር:: ወዲያውኑም ይህ አምልኮ በኤደን ገነት የአትክልቱ ስፍራ አውቀው ከነበረው ዓይነት አምልኮ ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ ተገነዘብኩ:: ይሁንና ይህኛው ግን ከዚያኛው በበለጠ ሙሉና የበለጸገ ሃሳብ ያለው ነበር:: እንዲህ ይበልጥ የተዋበ የመሰለበት ምክንያትም ተራራውን ከብበው በያዙት ጠላቶቻችን ፊትና ይህን በመሰለ ጨለማና ክፋት ተከበን እናመልክ ስለነበረ እንደሆነ ነው የተረዳሁት::

ይህ አምልኮ ለምን ያህል ሰዓት እንደ ቆየ ባላውቅም መጨረሻ ላይ ግን ንስሮቹ ክንፎቻቸውን ማራገባቸውን ሲያቆሙ አምልኮውም ቆመ:: በዚህን ጊዜ ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረውን ንስር "አምልኮውን ለምን አቆማችሁት?" ስል



ጠየቅሁት:: እርሱም እጁን ቆስለው ወደነበሩትና አሁን ፍጹም ጤነኛ ወደሆኑት እያመለከተኝ "እነርሱ በመፈወሳቸው ነው:: እውነተኛ አምልኮ የትኛውንም ዓይነት ቁስል መፈወስ ይችላል" ሲል መለሰልኝ::

እኔም "እባክህ እንደገና ዘምሩ" ብዬ ለመንኩት::

"ይህን ዝማሬ እንዘምረዋለን:: ሆኖም መቼ እንደምንዘምረው ግን ውሳኔው የእኛ አይደለም:: ተሰምቶህ የነበረው ቀዝቃዛ ነፋስ እርሱ መንፈስ ቅዱስ ነው:: መሪያችን እርሱ እንጂ እኛ እርሱን አንመራውም:: እርሱ የቆሰሉትን ፈውሷቸዋል፣ ወደፊት ለምናካሂደው ጦርነትም አስፈላጊውን አንድነት ማምጣት ጀምሯል:: እውነተኛ አምልኮ ራስ በሆነው በኢየሱስ ላይ የከበረውን ዘይት ያፈስሰዋል:: ከዚያም እኛን ከእርሱ ጋርና እርስ በእርሳችንም አንድ እያደረገን በአካሉ ሁሉ ላይ ይፈስሳል:: ከእርሱ ጋር አንድ የሆነ ማንም ሰው እንደ ቆሰለ ወይም እንደ ረከሰ አይኖርም:: ደሙ ንጹህ ሕይወት ያለው ስለሆነ ከእርሱ ጋር ስንጋጠም ወደ እኛ ይፈስሳል:: ከእርሱ ጋር ስንጋጠም ከሌላውም አካሉ ጋር እንጋጠማለን:: ያንጊዜ ደሙ በሁላችንም ውስጥ ይፈስሳል:: የሰውነታችሁን ቁስል የተፈወሳችሁት ደሙ ለቆሰሉት ብልቶች እንደገና ሕይወትን ማምጣት ይችል ዘንድ በመፍሰሱና ቁስሉን በማልበሱ አይደለምን? ሁላችንም አንድ አካል ነንና አንዱ የአካሉ ክፍል ሲቆስል ያ ክፍል ጤንነቱ ሙሉ ለሙሉ እስከሚመለስለት ድረስ ከዚያ አካል ጋር አንድ ላይ መጋጠም አለብን" አለኝ::

በአምልኮ ውስጥ ያለው የዚህ ታላቅ ደስታ ዝርዝር ትምህርት፣ ለመረዳት ከባድ ወይም ምስጢር ቢመስልም በጣም መሠረታዊ እንደሆነ ግን አወቅሁ:: መንፈስ ቅዱስ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ እያንዳንዱ ቃል ምንም ያህል ቀላል ቢመስል እጅግ የከበረ ስለነበር በጣም በፍቅር በመሞላቴ ብርቱዎቹን ያረጁ ንስሮችን ጨምሮ ሁሉንም ሰው እቅፌ ለመሳም ፈለግሁ::

ከዚያም ተማርከው የነበሩትን ኃያላን አርበኞቹን አስታወስኳቸው:: ንስሩ ይህንን ቢያውቅም ምንም አልተናገረም:: በመጨረሻም በጥንቃቄ አትኩሮ ሲመለከተኝ "የጠፉትን መመለስ እንችላለን ወይ?" ስል ጠየቅሁት::

## የንጉሡ ልብ

በመጨረሻም ንስሩ "አዎን! ለአንተ የተሰማህን ነገር ማድረጉ ትክክል ነው:: መላው አካል እስካልዳነ ድረስ ፍጹማን አይደለንም፣ አምልኳችንም ፍጹም አይሆንም:: እጅግ በከበረው አምልኮ ውስጥና በንጉሡ ኅልዎት መገኘት

ውስጥ እንኳን ብንሆን የወንድሞቻችን ምርኮኛ መሆን ንጉሣችንን ስለሚያሳዝነው ሁላችንም አንድ እስክንሆን ድረስ ይሄው ባዶነት ይሰማናል። ሁላችንም በእስራት ውስጥ ሳሉት ወንድሞቻችን ብናዝንም ይበልጥ ያዘንነው ግን ለንጉሣችን ልብ ነው። ልጆቻችሁን ሁሉ ብትወዷቸውም የበለጠ የምትራሩት ግን ለቆሰለው ወይም ለታመመው ልጃችሁ ነው።ንጉሣችንም ሁሉንም ልጆቹን ቢወዳቸውም ይበልጥ ትኩረቱን የሚስቡት ግን የቆሰሉት ናቸው። የቆሰለ እስካለ ድረስ እርሱም ስለሚቆስል፣ የቆሰሉት ሁሉ እስኪድኑ ድረስ ስለ ስሙ ስንል የጠፉትን ከመመለስ ማቋረጥ የለብንም" አለኝ።

## ተራራን የሚያናውጥ እምነት

ንስሩ አጠገብ ተቀምጬ እርሱ የተናገራቸውን ቃሎች አሰላስል ጀመር። በመጨረሻም "አሁን አንተ ስትናገር የጥበብን ድምጽ ሰማሁ። ጥበብ በአንተ ውስጥ ሆኖ እንደተናገረኝ ነው የተረዳሁት። ከዚያ ከመጨረሻው ጦርነት በፊት ስለ ራሴ እርግጠኛ ነበርኩ። ይሁንና እነርሱ በተወሰዱበት ተመሳሳይ ቅድሚያ ግምት እኔም ተወስጄ ስለነበር ጥበብ ባያቆመኝ ኖሮ በጣም በቀላሉ ልማረክ እችል ነበር። ወንድሞቼን ነጻ ለማውጣት ካለኝ ፍላጎት ይልቅ ጠላትን በመጥላት ይበልጥ ተነሳስቼ ነበር። በታላቁ ጦርነት ውስጥ የተዋጋሁና ወደዚህ ተራራ ጫፍ ላይ የወጣሁ የመጀመሪያው ሰው በመሆኔም አሁን ያደረኳቸው ትክክለኛ ነገሮች አብዛኞቹ በተሳሳቱ ምክንያቶች ከንጹህ ልቤ አስቤ ያደረኳቸው ስህተቶች እንደሆኑ ነው የማስበው። አሁን ግን ይበልጥ እየተማርኩ በሄድኩ ቁጥር ስለ ራሴ የበለጠ እርግጠኛ አለመሆኔ ነው የተሰማኝ" አልኩት።

ንስሩም "ከጥበብ ጋር አብረህ ለረዥም ጊዜ የቆየህ መሆን አለብህ" አለኝ።

"እርሱ ከእኔ ጋር እንደነበረ ማወቅ ከመጀመሬ ከረዥም ጊዜ በፊት አንስቶ ከእኔ ጋር ነበር። ይሁንና በእነዚያ ጊዜያት እቃወመው ነበር ብዬ እሰጋለሁ። አሁንም ተመልሼ ወደ ጦርነቱ ከመግባቴ በፊት ሊኖረኝ የሚገባና አሁንም ድረስ በጣም አስፈላጊ የሆነ፣ ሆኖም ምን እንደሆነ የማልረዳው አንድ የሆነ ነገር እንደ ጎደለኝ ግን ተረድቻለሁ" አልኩት።

ታላቁ ንስርም "የጥበብ ድምጽ ስለብህ ሲናገርህ አንተም ታውቃለህ። መጎናጸፊያው ስላለህ ጥሩ ተምረሃል። አሁን የሚሰማህም ስሜት እውነተኛ እምነት ነው" ብሎ በተናገረኝ ጊዜ ዓይኖቹ ይበልጥ ዘልቀው በጥልቀት ወደ ውስጤ ይገቡ ነበር።



"እምነት? እየተናገርኩ ያለሁት እኮ ወደ ኋላ ስለማፈግፈግ አሳሳቢ ጥርጣሬ እኮ ነው!" አልኩት።

"አንተ ራስህን የምትጠራጠር ብልህ ሰው ነህ። ሆኖም እውነተኛ እምነት ግን በእግዚአብሔር ላይ እንጂ በራስህና በእምነትህ ላይ የሚደገፍ አይደለም። አንተ ይህንን ተራራ ማናወጥ ለሚችለው እምነት ቅርብ ስለሆንክ እናውጠው፣ እኛም ማናወጥ አለብን። እምነትን ከዚህ በፊት ወዳልሄደባቸው ቦታዎች የምንወስድበት ጊዜው አሁን ነው። ይሁንና አንተ ግን ልክ ነህ። አሁንም አንድ በጣም አስፈላጊ የሆነ ነገር አጥተሃል። ምንም እንኳን ተራራው ጫፍ ላይ የወጣህና በመንገድህም ላይ የትኛውንም እውነት የተቀበልህ፣ ወደ እግዚአብሔር ገነት የገባህ፣ ምንም ዓይነት ቅድመ ሁኔታን የማይጠይቀውን ፍቅሩን የቀመስህና ብዙጊዜም ልጁን ያየኸው ብትሆንም፤ አሁን ግን ከእግዚአብሔር ምስክሮች በሙሉ የተረዳኸው ከፊሉን ብቻና ያም ቢሆን ጥልቀት የሌለው በመሆኑ መገለጥ ሊኖርህ ይገባል" አለኝ።

ይሄ በጣም እውነት ስለሆነ ሲሰሙት እንደሚያጽናና ተረዳሁ። "በስህተት በጣም በብዙ ሰዎችና ሁኔታዎች ላይ ፈርጃለሁ። ጥበብ ግን ሕይወቴን ብዙጊዜ አድኗታል። አሁን ግን በውስጤ ያለው የጥበብ ድምጽ ትንሽ ሲሆን፤ የገዛ ራሴ የሁከት ሃሳቦችና ስሜቶች ግን ከሩቅ ሲጮሁ ነው የሚሰሙት። ጥበብን በገዛ ልቤ ውስጥ ከምሰማው ይልቅ በአንተ ውስጥ ሆኖ በጎላ ድምጽ ሲናገር ስለሰማሁት አብዝቼ ወደ አንተ መቅረብ እንዳለብኝ አውቄያለሁ" አልኩት።

ንስሩም "እኛ እዚህ የተገኘነው አንተ ስለምትፈልገን፣ እኛም ስለምንፈልግህ ነው። እኔ የሌሉኝ ስጦታዎች ተሰጥተውሃል። አንተ የሌሉህ ስጦታዎች ደግሞ እኔ አሉኝ። እኔ ያልተለማመድኳቸውን ተለማምደሃቸዋል፣ አንተ ያልተለማመድካቸውን እኔ ተለማምጃቸዋለሁ። ንስሮቹ እስከ መጨረሻ ተሰጥተውሃል፣ አንተም ለእኛ ተሰጥተኸናል። ለጊዜው ከአንተ አልለይም፤ ከዚያም በእኔ ቦታ ሌሎች ንስሮችን መቀበል አለብህ። እያንዳንዱ ንስር የተለያየ ቢሆንም የጌታን ምስጢራት ማወቅ ግን በግል ሳይሆን በኅብረት ታስጥቶናል" አለኝ።

## የእውነት በሮች

ከዚያም ንስሩ ካረፈበት ቋጥኝ ላይ ተነሳና እኛ ቆመንበት በነበረው ደረጃ ጠርዝ ላይ አንዣበበ። "ወደዚህ ና" ብሎ ጠራኝና ወደ እርሱ ስቀርብ ወደ ታችኛው መሠረትና ወደ ትንሹ በር የሚያደርሱ ደረጃዎችን አሳየኝ።

“ይህንን ከዚህ በፊት ያላየሁት ለምንድነው?” ስል ጠየቅሁት፡፡

“መጀመሪያ ወደ ተራራው ላይ በወጣህ ጊዜ ዙሪያውን ለመመልከት እዚህ ደረጃ ላይ ለረዥም ጊዜ ስላልቆየህ ነው” ሲል መለሰልኝ፡፡

እኔም “ያንን እንዴት አወቅህ? መጀመሪያ ላይ ወደ ተራራው ስመጣ በዚህ ነበርክን?” ስል ጠየቅሁት፡፡

“ይህንን በር ያጡ ሁሉ በተመሳሳይ ምክንያት ይህንኑ ያደረጉ በመሆናቸው እዚህ ባልሆንም አውቅ ነበር፡፡ ሆኖም በዚህ ግን ነበርኩ፡፡ ወደ ተራራው በምትወጣበት ወቅት ላይ በመንገድህ ላይ ፈጥነህ ካለፍካቸው ወታደሮች አንዱ እኔ ነበርኩ” ሲል መለሰልኝ፡፡

በዚህን ጊዜ ነበር ንስሩ ከተለወጥኩ በኋላ አግኝቼው ጥቂት ያነጋገርኩት ሰው መሆኑን የተገነዘብኩት፡፡ እርሱም እንዲህ ሲል ንግግሩን ቀጠለ፡፡ “ከዚህ በኋላ አንተን መከተል አለብኝ፡፡ እዚህ ደረጃ ላይ በጣም ለረዥም ጊዜ ያህል ስለቆየሁ ለውጥ ያስፈልገኛል፡፡ እስካሁን ድረስ ወደዚህ ስፍራ ልመራቸው ጥረት እያደረግሁ ያለኋቸውን የጠፉ ነፍሳትን ሁሉ ልተዋቸው አልችልም፡፡ መጨረሻ ላይ ባለሁበት ቦታ ለመቆየትም ይሁን ትቼ በመሄድ ራሴን የጌታን ፈቃድ ለማድረግ ስሰጥ ጥበብ ወደ እኔ መጣና ይህንን በር አሳየኝ፡፡ ይህ በር ወደ ተራራው ጫፍ የሚያደርስ አቋራጭ መንገድ ስለነበረው ከእናንተ ቀድሜ ደረስኩ፡፡ በዚያም ወደ ንስርነት ተለወጥኩ” አለኝ፡፡

ከዚያም በአንደኛውና በሁለተኛው ደረጃዎች ላይ እንደዚህ ያሉ በሮችን አይቼ እንደነበር፣ ከበሮቹ በአንዱ ወደ ውስጥ አጮልቄ መመልከቴንና ባየሁት ነገር እንዴት ተደንቄ እንደነበርም ትዝ አለኝ፡፡ ትኩረቴ ሁሉ የጦርነቱን ውጊያ አልፎ ተራራው ጫፍ ላይ መውጣት ስለነበር በጣም አርቄ ለመመልከት አልደፈርኩም፡፡ “ከእነዚያ በሮች በአንዱ አልፎ መግባትና በቀጥታ ወደ ተራራው ጫፍ መውጣት እችል ነበር ወይ?” ስል ጠየቅሁት፡፡

ንስሩም በጥቂቱ ቆጣ ብሎ “እንደምትለው ቀላልማ አይደለም፡፡ እያንዳንዱ በር ወደ ተራራው ጫፍ የሚወስዱ መተላለፊያ መንገዶች አሉት፡፡ ሌሎቹ በሮች ተራራው ላይ ወደሚገኙት ወደ ሌሎቹ መወጣጫ ደረጃዎች የሚመሩ ሲሆኑ አብ ይህንን እያንዳንዱን መተላለፊያ መንገድ ያዘጋጀው እያንዳንዱ ሰው የመንፈሳዊ ጉልምስና ደረጃ የሚጠይቀውን የሚያሟላበትን እንዲመርጥ ነው?” አለኝ፡፡



“እንዴት ያንን ያደርጋል? ይሄ የማይመስል ነገር ነው!” እያልኩ በውስጤ እያሰብኩ እያለሁ ንስሩ ይህንን የተሰወረውን የልቤን ሃሳብ አወቀ፡፡

ከዚያም ንስሩ ድምጼን አውጥቼ ሃሳቤን የነገርኩት ይመስል “ቀላል ነው” ሲል ንግግሩን ቀጠለ፡፡ “መንፈሳዊ ጉልምስና የሚወሰነው ሁልጊዜ የገዛ ራሳችንን ፍላጎቶች ለመንግስቱ ጥቅም ወይም ስለ ሌሎች ሰዎች ስንል መስዋዕት ለማድረግ ባለን ፈቃደኝነት ላይ ነው፡፡ ለመግባት እጅግ ትልቁን መስዋዕትነትን የሚጠይቀው በር ሁልጊዜ የሚወስደን ወደ ላይኛው መወጣጫ ደረጃ ነው” አለኝ፡፡

ንስሩ የተናገረኝን ነገር በሙሉ ለማስታወስ ሞከርኩ፡፡ በፊቴ ያለውን በር አልፎ መግባትና ወደ ተራራው ጫፍ የሚያደርሰውን ትክክለኛውን በር ከመረጠውና ከእኔ በፊት ቀድሞ ከሄደው ሰው የቻልኩትን ያህል መማሩ ብልህነት እንደሆነም አወቅሁ፡፡

ንስሩም ንግግሩን በመቀጠል “በቀጥታ ወደ ተራራው ጫፍ አልሄድኩም፣ ወደዚያም የሄደ ማንንም ሰው አላገኘሁም፡፡ ነገር ግን እዚህ በድነት ደረጃ ላይ ሆኜ እየተዋጋሁ እያለሁ ራስን መስዋዕት ስለማድረግ ብዙ ተምሬ ስለነበር ከማንም በላይ ፈጥኜ ወደዚያው ሄድኩ፡፡ አንተ መጎናጸፊያውን ስለለበስክ ይህንን በር አሳይቼሃለሁ፡፡ ጊዜው አጭር በመሆኑ ግን እዚህ የተገኘሁት ፈጥነህ እንድትጎለምስ ልረዳህ ነው” አለኝ፡፡

ንግግሩን በመቀጠልም “በእያንዳንዱ መወጣጫ ደረጃ ላይ በሮች አሉ፡፡ እያንዳንዱ በርም ማስተዋል ከምትችሉት በላይ ወደሆኑ መዝገቦች ነው የሚመሯችሁ፡፡ በእጃችሁ የያዛችሁት እያንዳንዱ መዝገብ በልባችሁ ውስጥ ልትሸከሙት የምትችሉት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአካል ሊገኙ የሚችሉ ግን አይደሉም፡፡ የእግዚአብሔር ቤት መዝገብ ማለት ልባችሁ ነው፡፡ እንደገና ተራራው ጫፍ ላይ በደረሳችሁ ጊዜ ልባችሁ በምድር ላይ ካሉት ሃብቶች ሁሉ ይልቅ እጅግ ጠቃሚ ዋጋ ያላቸውን ሃብቶች ይይዛሉ፡፡ እነዚህ ለዘላለም የእናንተው ስለሆኑም በፍጹም አይወሰዱባችሁም፡፡ አሁን የአውሎ ነፋሱ ደመናዎች እየተሰበሰቡና ሌላ ታላቅ ውጊያ እየመጣ በመሆኑ ፈጥናችሁ ሂዱ” አለኝ፡፡

እኔም “አብረኸኝ ሂድ” ስል ለመንኩት፡፡

“አሁን ስፍራዬ እዚህ በመሆኑ አልሄድም፡፡ እነዚህን የቆሰሉትን መርዳት ስላለብኝ እዚህ እቆያለሁ፡፡ ነገር ግን ተመልሰህ ስትመጣ እዚሁ እንገናኛለን፡፡

ወደዚህ እንደገና ተመልሰህ ከመምጣትህ በፊትም ወንድምና እህት የሆኑ ብዙ ንስሮችን ታገኛለህ። እነርሱም በምታገኛቸው ቦታ ሁሉ ላይ ከእኔ በተሻለ ሊረዱህ ይችላሉ" አለኝ።

## የሰማይ መዝገቦች

ንስሩን ትቼው መሄድ እስኪሳነኝ ድረስ በጣም ወደድኩት። ይሁንና እንደገና እንደማገኘው ስረዳ ግን ደስ አለኝ። አሁን በሩ ልክ ማግኔት ብረትን እንደሚስብ የእኔንም ትኩረት ስለሳበው ከፍቼ ገባሁ።

ስገባም በዚያ ያየሁት ክብር በጣም የሚያምር ስለነበር ወዲያውኑ በጉልበቴ ወድቄ ተንበረከኩ። ወርቁ፣ ብሩና የከበሩ ድንጋዮች በቃላት መግለጽ ከሚቻለው በላይ እጅግ ውብ ነበሩ። እንደ እውነቱ ከሆነ ከሕይወት ዛፍ ክብር ጋር የሚወዳደሩ ነበሩ። ክፍሉ መጨረሻ የሌለው እስከሚመስል ድረስ በጣም ሰፊ ነበር። ወለሉ ብር፣ ቋሚ ምሰሶዎቹ ወርቅና ኮርኒሱም ከዚህ በፊት ፈጽሞ አይቼ የማላውቃቸውን የተለያዩ ኅብረ ቀለማትን የሚያንጸባርቅ ንፁህ አልማዝ ነበር። ዙሪያችንንም ምድራዊ ያልሆነ ልዩ የደንብ ልብስ የለበሱ ስፍር ቁጥር የሌላቸው መላዕክት ከበውን አየሁ።

በክፍሉ ውስጥ ወዲያና ወዲህ እያልኩ መራመድ ስጀምር መላዕክቱ እጅ እየነሱ ሰላምታ ሰጡኝ። ከእነርሱም አንዱ ወደ እኔ ጠጋ ብሎ ስሜን በመጥራት "እንኳን ደህና መጣህ" ብሎ ተቀበለኝ። ከዚያም በሩን አልፈው ለሚገቡ ሰዎች ምንም የሚከለከል ነገር ስላልነበረ በክፍሉ ውስጥ መሄድ ወደምፈልግበት ቦታ ሁሉ መሄድና ማየት የምፈልገውን ማንኛውንም ነገር ማየት እንደምችል ነገረኝ።

ውበቱን በቃላት መግለጽ በማልችለው በዚህ ክፍል በጣም ተደንቄ ስለነበር ከኤደን ገነት የሚበልጥ ውብ ስፍራ አድርጌ አየሁት። መልዓኩም ተገርሞ "ይሄ እኮ ገነት ነው! አባታችሁ ቤት ውስጥ ካሉት ክፍሎች አንዱ ይሄ ሲሆን እኛም አገልጋዮቻችሁ ነን" አለኝ።

ወደፊት እየተራመድኩ እያለሁም ታላቅ የመላዕክት ሠራዊት ሲከተሉኝ አየሁ። ዘወር ብዬም ለምን እንደሚከተሉኝ መሪያቸውን ጠየቅሁት። እርሱም "የምንከተልህ ከደረብከው መጎናጸፊያ የተነሳ ነው።
እኛ በዚህና ሊመጣ ባለው ጦርነትም ላይ እናገለግልህ ዘንድ ለአንተ የተሰጠን ነን" አለኝ።



መላዕክቱን ምን እንደማደርጋቸው ስላላወቅሁ መንገዴን ዝም ብዬ ቀጠልኩ። ከዚያም መልኩ ሰማያዊ የሆነ አንድ ትልቅ ድንጋይ ትኩረቴን ሳበው። ይህ ድንጋይ በውስጡ ጸሐይንና ደመናዎችን የያዘ ነበር የሚመስለው። ቀርቤ በእጄ ስነካው የሕይወትን ዛፍ ፍሬ በበላሁ ጊዜ ተሰምቶኝ የነበረው ዓይነት ተመሳሳይ ስሜት በውስጤ እንደ ጎርፍ ፈሰሰ። ኃይል፣ ምድራዊ ያልሆነ የአዕምሮ ብሩህነት፣ ለሰው ሁሉና ጎልቶ ለሚታየው ፍጥረተ ዓለም ሁሉ ፍቅር ተሰማኝ። የጌታንም ክብር ማየት ጀመርኩ። ድንጋዩን ለረዥም ጊዜ በነካሁት ቁጥር ክብሩ የበለጠ እየጨመረ ነበር የሚሄደው። እጄን ከድንጋዩ ላይ ለማንሳት በፍጹም አልፈለኩም ነበር። ይሁንና ክብሩ በጣም እየከበደ ሲመጣ ግን መጨረሻ ላይ እጄን ማንሳት ነበረብኝና አነሳሁ።

ከዚያም ዓይኖቼ በአንድ ውብ አረንጓዴ ድንጋይ ላይ ሲያርፉ አጠገቤ ቆሞ የነበረውን መልዓክ "ይህ ድንጋይ በውስጡ የያዘው ነገር ምንድነው?" ስል ጠየቅሁት።

- "እነዚህ ድንጋዮች በሙሉ የመዳን መዝገቦች ናቸው። አሁን ሰማያዊውን ዓለም እየዳሰስከው ሲሆን ያም አንዱ የሕይወት መታደስ ነው" አለኝ።

ልክ አረንጓዴውን ድንጋይ ስነካው ምድርን በበለጸገና በጣም አስደናቂ በሆነ ቀለማት ተሸፍና አያት ጀመር። እጄን ድንጋዩ ላይ ለረዥም ጊዜ ባስቀመጥኩ ቁጥርም የቀለማቱ ብልጽግና እያደገ ይሄድ ነበር። በዚህ ጊዜ ለማየው ነገር ሁሉ ያለኝ ፍቅር አደገ። በአንድ መወጣጫ ደረጃ ላይ ሕይወት ባላቸው ነገሮች መካከል ያለን ከዚህ በፊት በፍጹም አይቼ የማላውቀውን ኅብረት ማየት ጀመርኩ። ከዚያም በፍጥረት ውስጥ ያለውን የጌታን ክብር አየሁ። ከኃይሉ የተነሳም ይህን ቦታ ለቅቄ እስከሄድኩበት ጊዜ ድረስ ክብሩ እየጨመረ መሄድ ጀመረ።

እዚያ ቦታ ላይ ምን ያህል ጊዜ እንደቆየሁ ምንም ሃሳቡ እንደሌለኝ ተገነዘብኩ። እነዚህን ድንጋዮች ሁሉ ስነካቸው ስለ እግዚአብሔርና እርሱ ስለ ፈጠረው ፍጥረተ ዓለሙ ያለኝ ዕውቀት ማደጉን ተረዳሁ። በዚያ አንድ ክፍል ውስጥ ብቻ አንድ ሰው በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ሊያገኘው ከሚችላቸው በላይ የሆኑ ሌሎችም በጣም በርካታ ነገሮች ነበሩ። ወደ መልዓኩ ዘወር ብዬ "ከዚህ በኋላ ስንት ክፍሎች ይቀሩናል?" ስል ጠየቅሁት።

"በወጣህባቸው በእያንዳንዱ የተራራው መውጫ ደረጃ ላይ እንደዚህ ያሉ ተመሳሳይ ክፍሎች አሉ" አለኝ። እኔም "አንድ ሰው ከሁሉ በሚያንስ በእነዚህ

ክፍሎች በአንዱ ውስጥ ብቻ እንኳን ያለውን ይህንን ሁሉ እንዴት ነው መለማመድ የሚችለው?" ስል ጠየቅሁት።

እርሱም "አንተ ይህንን ማድረግ የምትችልበት ዘላለም ተሰጥቶሃል። እጅግ መሠረታዊ በሆኑት በጌታ ኢየሱስ እውነቶች ውስጥ ያሉትን መዝገቦች መቁጠር ከምትችሉት በላይ ለሕይወት ዘመናችሁ በቂ ናቸው። በአንድ የሕይወት ዘመን ብቻ ሊያውቅ የሚገባውን ማንኛውንም ነገር ሁሉ ማወቅ የቻለ ማንም ሰው የለም። ይሁንና የምትፈልጉትን ነገር መውሰድና ወደ ፍጻሜያችሁ የምታደርጉትን ጉዞ መቀጠል ነው ያለባችሁ" አለኝ።

እንደገናም በቅርቡ ስለተካሄደው ጦርነትና ተማርከው ስለ ተወሰዱት ምርኮኞች ማሰብ ጀመርኩ። ይህን በመሰለ የከበረ ስፍራ ላይ እንዲህ ያለውን ሃሳብ ማሰብ ደስ አያሰኝም። ይሁንና ወደዚህ ክፍል ተመልሼ ለመምጣት ዘላለም እንዳለኝ አወቅሁ። ተመልሼ ወደ ተራራው ጫፍ የምደርስበትን መመለሻ መንገዴን ለማግኘትና ከዚያም እንደገና ጦርነቱ ወደሚካሄድበት ሜዳ ተመልሼ ለመሄድ ያለኝ ጊዜ አጭር ብቻ ነበር።

ከዚያም ወደ መልዓኩ ዘወር ብዬ "ወደ ተራራው ጫፍ የሚመራኝን በር እንዳገኝ ልትረዳኝ ይገባል" አልኩት።

መልዓኩም ግራ በመጋባት ተመለከተኝና "እኛ የአንተ አገልጋዮች ስለሆንን እኛን መምራት ያለብህ አንተ ነህ። ይህ ተራራ ለእኛ ምስጢር ነው። ሁላችንም ይህንን ታላቅ ምስጢር ማየት እንፈልጋለን። ይሁንና በጥቂቱም ቢሆን ያወቅነውን ይህንን ክፍል ለቀን ከወጣን በኋላ ግን በበለጠ ከአንተ እንማራለን" አለኝ።

እኔም "በሮቹ በሙሉ የት እንዳሉ ታውቃላችሁን?" ስል ጠየቅሁት።

"አዎን እናውቃለን! ይሁንና ወዴት እንደሚያደርሱ ግን አናውቅም። አንዳንዶቹ በጣም የሚያንጉ፣ አንዳንዶቹ ግልጽ፣ ሌሎቹ ደግሞ በእውነቱ የሚከብዱ ናቸው። እንዲያውም አንዱማ በጣም አስፈሪ ነው" አለኝ።

"እዚህ ቦታ ላይ በጣም የሚያስፈሩ በሮች አሉ? እንዴት ሊሆን ይችላል?" ስል በጥርጣሬ ጠየቅሁት።

"እንዴት ሊሆን እንደቻለ አናውቅም። ይሁንና ላሳይህ ግን እችላለሁ" አለኝ።

እኔም "እባክህ አሳየኝ" አልኩት።



አልፈናቸው ለመሄድ አስቸጋሪ የነበሩና በቃላት ሊገለጽ የማይችል ክብር ያለባቸውን መዝገቦችን ለጥቂት ጊዜያት ያህል አልፈን ሄድን። በዚያ በእያንዳንዳቸው ላይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች የተጻፉባቸው ብዙ የተለያዩ በሮችን አገኘን። እያንዳንዱን በር አልፌ ለመግባት አጥብቄ ፈልጌ የነበረ ቢሆንም ስለ "አስፈሪው በር" ለማወቅ የነበረኝ ጉጉቴ ግን ይበልጥ ወደዚያው እንዳመራ ገፋፋኝ።

## ጸጋና እውነት

ልክ አስፈሪ ነው የተባለው በር ላይ ስንደርስ በፍጥነት ወደ ኋላዬ አፈገፈግሁ። ዘልዬ በእጄ አፈፍ አድርጌ ልይዘው የቃጣኝ አንድ የተዋበ ቀይ ድንጋይ አጠገቤ ስለነበረ ነካሁት። ወዲያውኑም በጌቴሰማኒ የአትክልት ቦታ ተገኘሁና ጌታን ሲጸልይ አየሁት። ፊቱ ላይ አይቤት የነበረው ጭንቀት ቀደም ሲል ካየሁት በር የባሰ አስፈሪ ስለነበር ደነገጥኩ። ፈጥኜ እጄን ከድንጋዩ ላይ ባነሳሁ ጊዜ በእግሮቼ መቆም ተሳነኝና ወለሉ ላይ ተዘረርኩ። ቀደም ሲል ወዳየኋቸው ሰማያዊና አረንጓዴ ድንጋዮች ለመመለስም አጥብቄ ፈለግሁ። መላዕክቱ በዙሪያዬ ሆነው እያገለገሉኝ ስለነበር በፍጥነት እንድነቃቃ ያደረገኝን አንድ የሚጠጣ ነገር ሰጥተውኝ እንደጠጣሁ ወዲያውኑ በእግሮቼ ቆምኩ። እንደገናም ክፍሎቹ ውስጥ ወደሚገኙት ድንጋዮች ለመሄድ ጥሩ ስሜት መሰማት ቢጀምረኝም መጨረሻ ላይ የጌታ ጸሎት ራዕይ ግን ባለሁበት ስፍራ እንድቆም በተደጋጋሚ ግድ አለኝ።

"እዚያ ከበሩ ጀርባ ያለው ነገር ምን ነበር?" ስል መልዓኩን ጠየቅሁት።

መልዓኩም "ድንጋዮቹን ስትነካቸው አንተ ያየኸውንና፣ የተሰማህን ዓይነት ስሜት እኛም በጥቂቱ ማየትና መስማት ችለናል። እነዚህ ሁሉ ድንጋዮች ታላላቅ መዝገቦችና የያዟቸው መገለጦችም በሙሉ እጅግ ውድ እንደሆኑ እናውቃለን። ጌታ ከመሰቀሉ በፊት ለጥቂት ጊዜ ያህል ያሰማው የነበረውን የጭንቀት ሲቃ ተመለከትንና በዚያች አስጨናቂ ምሽት ተሰምቶት የነበረውን የመከራ ስሜት በደንብ ተሰማን። ለእኛ አምላካችን እንዴት እንደዚያ ሊሰቃይ እንደ ቻለ መረዳቱ ከባድ ነው የሆነብን። ለእኛ ይህን የመሰለውን አስጨናቂ ዋጋ የከፈለላቸውን ሰዎች ማገልገሉ ምን ያክል ክብር እንደሆነ፣ እርሱንም ይበልጥ እንድናመሰግነውና እንድናደንቀው ነው ያደረገን" አለኝ።

የመላዕክቱ ንግግር በቀጥታ ወደ ነፍሴ እየተወረወረ እንደሚገባ የመብረቅ ዱላ ያህል ተሰማኝ። በታላቁ ጦርነት ላይ ተዋግቻለሁ፣ ተራራው

ጫፍ ድረስም ወጥቻለሁ፣ መላዕክት እንደነበሩ እምብዛም ከማላውቃቸው የመንፈሳዊው ዓለም ፍጥረታት ጋር ተገናኝቻለሁ፣ ትላልቆቹ መላዕክት ይናገሩት በነበረው ቋንቋም እኩል ከእነርሱ ጋር መነጋገር ችያለሁ:: ይሁንና ወደሚበልጥ አስደሳች ልምምድ ውስጥ ለመሸሽ ሳልፈልግ የጌታን የጭንቀት ሰዓት ለሌሎች ማካፈል ባለመቻሌ "ከማንም ይበልጥ የከፋው ምርኮኛ የሆንኩና እዚህ ቦታ መገኘት የማይገባኝ ሰው ነኝ" ብዬ ጮኽኩ::

መልዓኩም መጪውን ሁኔታ በመፍራት "ጌታው! በዚህ ስፍራ መገኘት የተገባው ማንም ሰው እንደሌለ ነው እኛ የምንረዳው:: አንተም ብትሆን እዚህ የተገኘኸው ዓለም ሳይፈጠር በፊት ለአንድ ዓላማ ስለ ተመረጥክ ነው:: ይህ የተመረጥክበት ዓላማ ምን እንደሆነ ባናውቀውም በዚህ ተራራ ላይ ለተገኘ ለእያንዳንዱ ሰው ግን እጅግ ታላቅ ዓላማ እንደሆነ ነው የምንረዳው" አለኝ::

እኔም "አመሰግናለሁ:: አንተ ጠቃሚ ነህ:: ስሜቶቼ በዚህ ስፍራ እጅግ የተለቀቁና መረዳቴንም ለማሸነፍ በታላቅ ሁኔታ እየሰሩ ናቸው:: እዚህ ስፍራ በራሱ መገኘት የተገባው ማንም ሰው እንደሌለ የተናገርከው ቃልም በእርግጥ ልክ ነው:: በእውነቱ ወደዚህ ተራራ ጫፍ ላይ በወጣን መጠን እዚህ ቦታ ለመገኘት የማይገባንና ለመቆየትም ብዙ ጸጋ ማግኘት የሚያስፈልገን ሰዎች ነን:: ለመሆኑ ተራራው ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዴት ነበር መውጣት የቻልኩት?" ስል ጠየቅሁት::

አጠገቤ የነበረው መልዓክም "በጸጋው!" ሲል መለሰልኝ::

እኔም "ይህንን ቃል ከሌላ ከየትኛውም ሰው በተሻለ ወደ መረዳት መጥቻለሁና ግራ ተጋብቼ ወይም ተስፋ ቆርጬ ባየኸኝ ጊዜ ሁሉ ልትረዳኛ ከፈለግህ ይህን ቃል ደጋግመህ ንገረኝ" አልኩት::

አሁን ወደ ቀዩ ድንጋይ ተመልሼ መሄድ አለብኝ:: በዚህ ክፍል ውስጥ እጅግ የላቀው መዝገብ እርሱ መሆኑን አሁን ስላወቅሁኝ ያንን መዝገብ በልቤ ውስጥ እስካልተሸከምኩት ድረስ ይህንን ስፍራ ለቅቄ መሄድ የለብኝም::

## የጸጋው እውነት

ቀዩ ድንጋይ ባለበት ቦታ ላይ ያሳለፍኩት ጊዜ፤ ከዚህ በፊት ተለማምጄው የማላውቀው እጅግ አስጨናቂ ጊዜ ነበር:: ከዚያ በላይ ብዙ ማቆየት ስላልቻልኩም እጄን ከድንጋዩ ላይ ማንሳት ነበረብኝ:: ተመልሼ ከመሄዴ በፊትም ነፍሴን ለማደስ ስል ለበርካታ ጊዜያት ያህል ወደ ሰማያዊዎቹ ወይም አረንጓዴዎቹ ድንጋዮች ተመልሼ ሄድኩ:: ሆኖም



በየጊዜው ወደ ቀዩ ድንጋይ መመላለሱ ግን ከባድ ነበር:: ነገር ግን ለጌታ ያለኝ ፍቅርና አድናቆት ግን ከተማርኩትም ሆነ ከተለማመድኩት ከሌላ ነገር ይልቅ በዚህ አማካይነት የበለጠ ያድግ ነበር::

በመጨረሻም ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሆኖ የአብ አብሮነት ሲለየው ስመለከት ግን ያንን መቋቋም ተሳነኝ:: እኔ እመለከት የነበረውን ይመለከቱ የነበሩ መላዕክቱም ሙሉ በሙሉ የእኔ ዓይነት ተመሳሳይ ስሜት ተሰምቷቸው እንደነበር መናገር እችላለሁ:: ድንጋዩን እንደገና ለመንካት በውስጤ የነበረው የፈቃዴ ኃይል አሁን ስለሌለ ወደ ሰማያዊው ድንጋይ የመመለስ ፍላጎት እንኳን አልተሰማኝም:: ስለዚህ ዝም ብዬ ወለሉ ላይ ተዘርግቼ ወደቅሁ:: ጌታ ያለፈበትን መከራና ጭንቀት እያሰብኩም አለቀስሁ:: እኔም ራሴ በመከራው ሰዓት ላይ ጥለውት እንደ ሸሹት ደቀ መዛሙርቱ እጅግ በሚፈልገኝ ሰዓት ላይ ብቻውን ጥዬው መሄዴ ስለተሰማኝና ይህንንም ስላወቅሁ ምርር ያለ ልቅሶ አለቀስሁ::

ከበርካታ ቀናት በኋላ ይመስለኛል ዓይኖቼን ገለጥኩ:: ከዚያም አንድ ሌላ መልዓክ አጠገቤ ቆሞ አየሁ:: ከእርሱ ፊት ለፊት ደግሞ ቀለማቸው አረንጓዴ፣ ሰማያዊና ቀይ የሆኑ ሦስት ድንጋዮች ነበሩ:: መልዓኩም እነዚህን ድንጋዮች "ብላ" አለኝ:: ስበላቸውም መላው እኔነቴ ታደሰ፣ ነፍሴንም ታላቅ ደስታ እና ልቅሶ ሁለቱም እንደ ጎርፍ አጥለቀለቃት::

ተነስቼ በእግሮቼ ስቆምም በሰይፌ እጀታ እና በሁለቱ ትከሻዎቼ ላይ ከእነዚህ ድንጋዮች ጋር ተመሳሳይ ቀለም ያሏቸው ሦስት ድንጋዮች ተቀምጠው አየሁ:: በዚህን ጊዜ ንስሩ "እነዚህ ድንጋዮች ከአሁን በኋላ ለዘለዓለም የአንተ ናቸው:: ከአንተ ሊወሰዱብህም ሆነ አንተም ልትጥላቸው አትችልም" አለኝ::

"ግን እኮ ይህን የመጨረሻውን በልቼ አልጨረስኩትም" ስል ተሟገትኩት::

"ያንን ጣዕም አጣጥሞ የጨረሰው ክርስቶስ ብቻ ነው:: አንተ የቻልከውን ያህል ስለበላህ አሁን ጉዞህን መቀጠል አለብህ" ሲል መለሰልኝ::

እኔም "ወዴት ነው የምቀጥለው?" ስል ጠየቅሁት::

ንስሩም "መወሰን ያለብህ አንተ ነህ:: ይሁንና ጊዜው አጭር በመሆኑ አሁኑኑ ፊጥነህ ወደ ተራራው ጫፍ ለመውጣት ጥረት ማድረግ ይኖርብሃል" ብሎኝ ፍጹም እየተቻኮለ ጥሎኝ ሄደ::

ከዚያም በሮቹን አስታወስኳቸውና በጣም አስደሳች ወደሆኑት መሄድ ጀመርኩ:: የመጀመሪያው በር ላይ ስደርስም እንደ መጀመሪያው ደስ የሚያሰኝ አልነበረም:: ከዚያም ወደ ሌላው ብሄድ ተመሳሳይ ስሜት ስለተሰማኝ "የሆነ የተሰወጠ ነገር ያለ ይመስላል" ስል ድምጼን አውጥቼ ተናገርኩ::

ንስሮቹም በአንድ ድምጽ "የተለወጥከው አንተ ነህ" አሉኝ:: ፊቴን ወደ እነርሱ በማዞር ሳያቸው እነርሱም ራሳቸው በመለወጣቸው ተደነቅሁ:: የገራገርነት ባይሆንም አሁን ግን የሚበልጥ ክብርና ደስ የሚል መልክ ነበራቸው:: እነርሱም በእኔ ውስጥ የተከናወነውን ዓይነት ለውጥ እያንጸባረቁ እንዳሉ አወቅሁ:: ይሁንና ግን አሁን ስለ ራሴ ማሰቡ ምቾት አልተሰማኝም::

የዚህን ጊዜ መሪውን "ምክርህ ያስፈልገኛል" አልኩት::

እርሱም "በአሁኑ ሰዓት እነዚህ ታላላቅ እውነቶች የሚገኙት በልብህ ውስጥ ስለሆነ ልብህን አድምጠው" አለኝ::

እኔም "ራሴ ለከንቱ ስሜት መነሳሳት፣ ለመሳት እና ለራስ ወዳድነት ምኞት እንደዚሁም ልቤም በጣም ለብዙ የሃሳብ ግጭቶች ተገዢ በመሆኑ በፍፁም የገዛ ልቤን ማመን አልችልም:: ልቤ ከሚሰማቸው ጩኸቶች የተነሳ ጌታ ሲናገረኝ ለመስማት እንኳን ከብዶኛል" ስል መለስኩለት::

መሪውም "ጌታዬ አሁን ቀዩ ድንጋይ በልብህ ውስጥ ከመኖሩ የተነሳ ነገሮች እንደ ቀድሟቸው ይቀጥላሉ ብዬ አላምንም" ሲል በተለመደ የራስ መተማመን ተናገረ::

ያ ንስር እጅግ በጣም በሚያስፈልገኝ በዚህ ሰዓት፣ በዚህ ቦታ አለመገኘቱን እያሰብኩ ግድግዳውን ደገፍ ብዬ ቆምኩ:: እርሱ ከዚህ በፊት በዚህ መንገድ ውስጥ ያለፈ በመሆኑ የትኛውን በር መምረጥ እንዳለብኝ ያውቅ ነበር:: ሆኖም ተመልሶ እንደማይመጣና ምርጫዬም ትክክል መሆኑን ግን አወቅሁ:: ነገሩን በሃሳቤ ሳወጣና ሳወርድ ማሰብ የቻልኩት ስለ "አስፈሪው በር" ብቻ ነበር:: ይህንን በር ለማየት ከመጓጓቴ የተነሳ ወደ ኋላ ተመልሼ ሄጄ በሩን ለማየት ወሰንኩ:: መጀመሪያ ላይ ከዚያ ቦታ ተለይቼ ስሄድ በሩ ላይ የተጻፈው የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ምን የሚል እንደሆነ እንኳን ሳላይ ነበር::

አሁን ወደ በሩ እየተጠጋሁ መሄድ ስጀምር ፍርሃት በውስጤ ይፈስ ጀመር:: ይሁንና እንደ መጀመሪያዬ ያህል የበረታ ግን አልነበረም:: ይህ በር ከሌሎቹ በሮች ሁሉ ይልቅ በጣም ጨለማ የዋጠው ስለነበር በበሩ ላይ የተጻፈውን የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ለማንበብ በጣም ወደ በሩ መጠጋት



ነበረብኝ:: ቀርቤ ስመለከትም "የክርስቶስ የፍርድ ወንበር" የሚል ቃል በማንበቤ ደነገጥኩ:: በዙሪያዬ ከበውኝ የነበሩት መላዕክት እንደማይሰሙኝ በማወቅ "ለምንድን ነው ይህ እውነት እንዲህ በጣም የሚያስፈራው?" ስል ድምጼን አውጥቼ ጠየቅሁ:: በሩን ያለማቋረጥ ማየቴን እንደ ቀጠልኩም አልፌ ልገባበት የሚገባ በር እንደሆነ ተረዳሁ::

ንስሩም በተለመደ ድምጹ "በሩ እንዲህ የሚያስፈራበት በርካታ ምክንያቶች አሉት" አለኝ::

እኔም "ተመልሰህ በመምጣትህ በጣም ደስ ብሎኛል:: ነገር ግን የተሳሳተ ምርጫ መርጬ ይሆን ወይ?" ስል ጠየቅኩት::

"የለም! ምርጫህ ትክክል ነው:: ይህ በር ከሌሎቹ በሮች ሁሉ ይልቅ በፍጥነት ወደ ተራራው ጫፍ መልሶ የሚወስድህ በር ነው:: ይህ በር ከሌሎቹ በሮች ይልቅ አስፈሪ የሆነበት ምክንያትም በፍጥረት ውስጥ ያለው ትልቁ ፍርሃት ምንጩ በዚህ በር ውስጥ ያለ መሆኑ ነው:: ሰዎች በዚህ ምድር ወይም በሚመጣው ዓለም ሕይወት ውስጥ ሊያውቁት የሚችሉት እጅግ የላቀው ጥበብ የሚገኘው በዚህ በር ውስጥ ቢሆንም ይህንን በር አልፈው የሚገቡት ግን በጣም ጥቂቶች ናቸው" አለኝ::

"ታዲያ ለምንድነው ይህ በር እንዲህ በጨለማ የተዋጠው?" ብዬ ጠየቅሁት::

ንስሩም "የእነዚህ በሮች መብራት ቤተ ክርስቲያን ስትሆን ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ሰዓት በሮቹ ላይ ለተጻፉት የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች እየሰጠች ያለችውን ትኩረት የሚያጸባርቅ ነው:: በዚህ በር ላይ የተጻፈው እውነት በዚህ ዘመን እጅግ ችላ ከተባሉት እውነቶች አንዱ ነው:: ይህንን እውነት የምትገነዘበው በሩን አልፈህ ስትገባ ነው:: ሊያገኙ የሚችሉትን እጅግ ትልቁን ሥልጣን በአደራ የሚቀበሉትም በዚህ በር ውስጥ አልፈው የሚገቡ ሰዎች ብቻ ናቸው:: ክርስቶስ ኢየሱስን በዚህ ዙፋን ላይ ተቀምጦ ስታየው፣ አንተም አብረህ በዚያ ዙፋን ላይ ለመቀመጥ ትዘጋጃለህ" አለኝ::

ከዚያም "ለዚህ እውነት ይበልጥ ትኩረት ሰጥተነው ቢሆን ኖሮ ይህ በር እንዲህ በጣም ጨለማና ገና ያልታየ አደጋ አይሆንም ነበርን?" ስል ጠየቅሁት::

ንስሩም አዝኖ "እውነት ነው:: ሰዎች ከዚህ በር በስተጀርባ የተገለጠውን ክብር ቢያውቁ እጅግ አስደናቂ በሆነ ነበር:: ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን አልፎ

ለመግባት አስቸጋሪ በር ነው። በቅርቡም ስለምትፈልገው ቶሎ ተመልሼ እንድመጣና እንዳበረታታህ ተነግሮኛል። ከዚህ በኋላ የሚበልጥ ታላቅ ክብርና እንደዚሁም ከዚህ በፊት አይተኸው የማታውቀውን ታላቅ ሰቆቃም ታያለህ። ይሁንና አሁን ግን አስጨናቂውን መንገድ መምረጥህ በኋላ ላይ የበለጠ ቀላል እንደሚሆንልህ ተረዳ። አሁን ከከባዱ እውነት ጋር ፊት ለፊት ለመፋጠጥ ፈቃደኛ በመሆንህ በኋላ ላይ ውድቀት አይገጥምህም። የእግዚአብሔርን ደግነት ለማወቅ የሚወዱ ብዙዎች ቢሆኑም፤ ጨካኝ ፈራጅነቱን ለማወቅ ፈቃደኛ የሚሆኑት ግን ጥቂቶች ናቸው። እነዚህን ሁለቱንም ልብ ካላልካቸው ሁልጊዜ በመሳትና ከታላቁ ጸጋው የመውደቅ አደጋ ውስጥ ትገባለህ" አለኝ።

"ቀዩ ድንጋይ ባለበት ቦታ ላይ ጊዜ ወስጄ ባላሳልፍ ኖሮ በፍጹም እዚህ ቦታ ላይ እንደማልመጣ ተረዳሁ። ያ ነገር ከጌታ ባህርይ ጋር በጣም ተጻራሪ በሆነ ጊዜ እንዴት ነው ቀላሉን መንገድ ለመምረጥ ጥረት ማድረጌን መቀጠል የምችለው?" ስል ንስሩን ጠየቅሁት።

ንስሩም "አሁን መርጠሃል። ስለዚህ ፈጥነህ ሂድ። ሌላ ታላቅ ጦርነት ሊጀመር ስለሆነ ጦርነቱ ግንባር ላይ ትፈለጋለህ" አለኝ።

እኔም ንስሩንና በዓይኖቹ ውስጥ ያለውን ቁርጠኛ ውሳኔ ስመለከት በራስ መተማመኔ አደገ። በመጨረሻም ፊቴን ወደ በሩ አዞርኩ።



# ክፍል አራት

# ነጩ ዙፋን



# ክፍል አራት

## ነጩ ዙፋን

ተራራው ውስጥ ያለውን ሰፊ ክፍል ዙሪያውን ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ አትኩሬ ተመለከትኩት:: በዚያ የነበሩትና የመዳንን እውነት የሚወክሉት በጣም ውድ የሆኑ መዝገቦችና የከበሩ ድንጋዮች ክብር ልብን የሚያማልል ነበር:: የክፍሎቹ ስፋት መጨረሻ የሌለውና ውበታቸውንም ሙሉ ለሙሉ መረዳት የማይቻል ነበር:: የእምነት ታላላቅ እውነቶችን የያዙ ሌሎቹ ክፍሎች እንዲህ የከበሩ ሊሆኑ ይችላሉ ብዬ መገመት አልቻልኩም:: ይሄ ብዙ ክርስቲያኖች በእምነት መሠረታዊ አስተምህሮዎች ላይ በመወሰንና በዚያም ብቻ በመደነቅ ይህን ደረጃ ለምን ፈጽሞ መልቀቅ እንደማይፈልጉ እንድረዳ ረድቶኛል:: በዚያ ለዘላለም መኖር እንደምችልና ፈጽሞ እንደማይሰለቸኝ አውቂያለሁ::

ከዚያም አጠገቤ የነበረው ንስር በሁኔታዬ ተደንቆ "አሁን ጉዞህን መቀጠል አለብህ" ብሎ አደፋፈረኝ:: እርሱን ለማየት ዘወር እንዳልኩ ድምጹን ዝቅ በማድረግ እንዲህ ሲል ንግግሩን ቀጠለ:: "በጌታ ማዳን ውስጥ ከመኖር የሚበልጥ ታላቅ ሰላምና እረፍት እኮ የለም:: ይህ እምነት አሁን በምትሄድበት ቦታ ስለሚያስፈልግህ እዚህ እንድትመጣ የተደረገው ይህንን ታውቅ ዘንድ ነው:: ይሁንና ከዚህ በኋላ ግን እዚህ መቆየት የለብህም"::

ንስሩ ስለ ሰላምና እረፍት የተናገረው ቃል ጦርነቱን በተራራው የመጀመሪያ መወጣጫ ደረጃ ላይ ሆነው በጀግንነት ይዋጉ ስለነበሩት ስለ ብርቱዎቹ ተዋጊዎች እንዳስብ አደረገኝ:: እነዚህ የእምነት አርበኞች በጽናት ተዋግተውና ብዙዎችን ከጠላት ቁጥጥር ስር ነጻ ያወጡ ቢሆኑም ሁሉም ግን በጠላት ፍላጻ ክፉኛ ቆስለው ነበር:: በዚህ ደረጃ ላይ ሰላምና ድነትን ያገኙም አይመስሉም ነበር:: ከዚያም ንስሩ የልቤን ሃሳብ አውቆ ንግሬን አቋረጠኝና እንዲህ አለኝ::

"እግዚአብሔር ስለ ሰላምና ድነት ያለው ትርጉም እኛ ካለን ትርጉም የተለየ በመሆኑ በጦርነቱ መካከል መቁሰል ትልቅ ክብር ነው:: የተፈወስነው በጌታ ቁስል እንደሆነ ሁሉ እኛም ሌሎችን የመፈወስ ሥልጣኑ የተሰጠን በመገረፋችን ቁስል ነው:: ጠላት ያቆሰለንን ቁስል አንዴ ስለተፈወስን ሌሎችን የምንፈውስበት ሥልጣን ተሰጥቶናል:: ፈውስ የጌታ የምድር አገልግሎት



መሠረታዊ አካል እንደነበረ ሁሉ የእኛም አገልግሎት መሠረታዊ አካል ነው:: ጌታ በህዝቡ ላይ ክፉ ነገሮች እንዲደርሱ የሚፈቅድበት አንዱ ምክንያት የፈውስ ኃይል የሚሰራበትንና ለሌሎች ማሳየት የሚገባቸውን ርህራሄ መቀበል ይችሉ ዘንድ ነው:: ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ሐዋርያዊ ሥልጣኑ ጥያቄ ውስጥ በገባ ጊዜ ስለ ግርፋቱና ስለደረሰበት ስደት የተናገረው:: ታላቁ ሐዋርያ የደረሰበት እያንዳንዱ ድብደባ ለሌሎች መዳን ምክንያት ሆኗል:: እያንዳንዱ አርበኛ የሚደርስበት ቁስል፣ የሳቱት እንዲመለሱ፣ ድነትን እንዲያገኙና እንዲፈወሱ ምክንያት የሚሆኑ ናቸው" አለ::

ንስሩ ንግግሩን በመቀጠል "ጌታ እንድንቆስል የሚፈልግበት ሌላም ምክንያት አለው:: እውነተኛ አደጋ ከሌለ ጉብዝና አይኖርም:: ኢያሱ የተስፋይቱን ምድር ይወርስ ዘንድ ጌታ ከእርሱ ጋር እንደሚወጣና እንደሚዋጋ፣ እርሱ ግን እንዲበረታና እንዲጸና ደጋግሞ ነግሮት ነበር:: ይሄም በጣም እውነተኛ የሆነ አደጋ ስላለውና መዋጋት ስላለበት ነው:: ጌታ የተስፋ ቃል የተገባቸውን ሰዎች የሚያረጋግጠው በዚህ መንገድ ነው::

ዕድሜው የገፋውን ንስር ባየሁት ጊዜም ለመጀመሪያ ጊዜ በተሰባበሩትና በተነጫጩት ላባዎቹ መካከል የሚታየውን የቁስል ጠባሳዎቹን አየሁ:: ይሁንና ጠባሳዎቹ የሚያስጠሉ ሳይሆኑ በማይታወቅ ሁኔታ ወርቅ በለበሱ ሥጋና ላባ የተለበጡ ነበሩ:: ከዚያም የንስሩን መገኘት በጣም አስደናቂ ያደረገውና ከውስጡ የሚፈነጥቅ ብርሃንን የሰጠው ይህ ወርቅ እንደሆነ ማየት ቻልኩ::

"ለምንድነው ከዚህ በፊት ይህንን ወርቅ የለበሰ ሥጋና ላባህን ማየት ያልቻልኩት?" ስልም ጠየቅሁት::

"የመዳን መዝገቦችን ጥልቀት አይተህ እስክምትደነቅ ድረስ ስለ ወንጌል ከሚደርሰው መከራ ውስጥ የሚወጣውን ክብር ማየት አትችልም:: ይህንን ክብር አንዴ ካየህ ግን የመንፈሳዊ ሥልጣን ከፍተኛ ደረጃዎች ወደ ሕይወትህ የሚያመጧቸውን ፈተናዎችን ለመቀበል ዝግጁ ትሆናለህ:: እነዚህ ጠባሳዎች ለዘላለም የምንሸከማቸው ክብሮቻችን በመሆናቸው ለዚህ ነው ጌታ የቆሰለው ቁስሉ ከእርሱ ጋር በመንግስተ ሰማይ እንኳን የሚኖረው:: ቁስሎቹን በዚያ አሁንም ድረስ ማየት ትችላላችሁ:: የእርሱ የሆኑትና የተመረጡት በሙሉ ቁስሎቻቸው ስለ ስሙ የተቀበሏቸውና በመንግስተ ሰማያት በደረታቸው ላይ የሚያንጠለጥሏቸው የክብር ሜዳልያዎቻቸው ናቸው:: እነዚህን ሜዳልያዎች ያንጠለጠሉ በሙሉ ከገዛ ሕይወታቸው ይልቅ እግዚአብሔርንና የእርሱን እውነት የሚወዱ፣ በጉንም በመንገዳቸው ሁሉ የተከተሉና ስለ እውነት፣ ስለ ጽድቅና ስለ ሰዎች መዳን መከራን ለመቀበል ፈቃደኛ የሆኑ ናቸው:: እውነተኛ

የህዝብ መሪዎች እውነተኛውን መንፈሳዊ ሥልጣን የተላበሱና በቅድሚያም ለጌታ የተሰጡ መሆናቸው በዚህ መንገድ መረጋገጥ አለበት" አለኝ::

ይከተለኝ የነበረውን የመላዕክቱን ሠራዊት መሪ ተመለከትኩት:: ከዚህ በፊት እንዲህ ጥልቅ በሆነ ስሜት ፈጽሞ ለአንድም መልዓክ መስክሬ አላውቅም:: ይሁንና እነዚህ ታላቶች ግን እርሱንና የተቀሩትን በሙሉ ያለ ጥርጥር እጅግ ያንቀሳቅሱ እንደነበሩ አሰብኩ:: ከዚያም መሪው እንዲህ አለኝ::

"ፍጥረት ከተፈጠረበት ዘመን አንስቶ ስለተከናወኑት በርካታ ተዓምራቶች ስንመሰክር ኖረናል:: ይሁንና እጅግ ከሁሉ የላቀው ተዓምር ግን ሰዎች ስለ ጌታና ስለ ባልንጀሮቻቸው በፈቃዳቸው የሚቀበሉት መከራ ነው:: አንዳንድ ጊዜ እኛም መዋጋትና መከራን መቀበል አለብን:: ነገር ግን የምንኖረው ይህን የመሰለው ብርሃንና ክብር ባለበት በመሆኑ ይህንን ማድረግ በጣም ቀላል ነው:: በጣም ጥቂት መጽናናት በሚገኝበት የጨለማና የክፋት ስፍራ የሚኖሩ ወንዶችና ሴቶች በዚያ ውስጥ ያለውን ተስፋ እንኳ ክብሩን ማየት በተሳናቸው ጊዜ በልባቸው ውስጥ በጣም በድንግዝግዝ ማየት ለሚችሉት ለዚያ ተስፋ ብቻ መከራ መቀበልን መረጡ:: ይሄ እጅግ ታላላቆቹ መላዕክት እንኳን ጉልበታቸውን እንዲያንበረክኩና እነዚህን መዳንን የሚወርሱትን ደስ እያላቸው እንዲያገለግሉም አድርጓቸዋል:: አብ መጀመሪያ ላይ ሰዎች የሰማያዊውን ዓለም እውነትና ብርሃን በማየት ሳይሆን በእምነት መመላለስና ይህን የመሰለውን ተቃውሞ መቀበል እንዳለባቸው ለምን እንደተናገረ አልገባንም ነበር:: አሁን ግን በእነዚህ መከራዎች አማካይነት የገዛ ራሱ ቤተሰብ አባልነታቸው ይህን ታላቅ ሥልጣን ይቀበሉ ዘንድ ተገቢ መሆኑን ተረድተናል:: ይህ በእምነት መመላለስ በሰማይ እጅግ ታላቅ ተዓምር ነው:: ይህንን ፈተና ያለፉ ሰዎች ከበጉ ጋር በዙፋኑ ላይ አብረው ለመቀመጥ የተገባቸው ናቸው:: የተገባቸው እንዲሆኑ ያደረጋቸው እርሱ ሲሆን፤ እነርሱ ደግሞ ፍቅራቸውን በመግለጽ አረጋግጠዋል" አለኝ::

በመቀጠልም ንስሩ "እምነት የሚገለጥበት አንዱ መንገድ እኮ ድፍረት ነው" ሲል ሃሳቡን ሰነዘረ:: ጌታ ልንሄድበት የተገባን መንገድ ይህ እንደሆነ አረጋግጦልን እንጂ ቀላል ነው ብሎ በፍጹም ተስፋ ቃልን አልሰጠንም:: ይሁንና በመዳን መወጣጫ ደረጃ ላይ ሆነው በድፍረት ይዋጉ የነበሩት ሰዎች ድፍረታቸው የሰማይ መላዕክቱ እግዚአብሔር በወደቀው ሰው ውስጥ የሰራውን ሥራ እንዲያደንቁ አንቀሳቅሷቸው ወይም ስሜታቸውን ነክቶት ነበር:: ልክ ጌታችን በመስቀል ላይ እንዳደረገው፤ ጨለማውን ብቻ እያዩ እውነት የሚሸነፍ እየመሰላቸው በእልቂቱ ውስጥ የተጎዱ ቁስለኞቻቸውን



ቢወስዷቸውም እነርሱ ግን ሥራቸውን አላቆሙም፣ ወደ ኋላም አላፈገፈጉም::

በመዳን መወጣጫ ደረጃው ላይ ለምን ጸንቼ አልቆምኩም፤ ለምንስ ከእነዚያ ጀግኖች ነፍሳት ጋር አብሬ ተሰልፌ አልተዋጋሁም እያልኩ እንደገና መጸጸት ጀመርኩ:: ንስሩ ግን የልቤን ሃሳብ አውቆብኝ ጣልቃ በመግባት እንዲህ አለኝ::

"ተራራውን ስትወጣ ሥልጣንን የሚለቁትን እምነትና ጥበብን ገልጠህ ታሳይ ነበር:: ሰዎች ለመዳን ወደ ተራራው መምጣት ይችሉ ዘንድ እምነትህ ብዙ ነፍሳትን ነጻ አውጥቷቸዋል:: አንተም በጥቂቱ ቆስለሃል:: ይሁንና በመንግስቱ ውስጥ ያለህ ሥልጣን የመጣው ግን መከራን ከመቀበል ይልቅ በእምነት ሥራህ ነው:: በጥቂቱ ታማኝ ሆነህ በመገኘትህ ምክንያት ገና በብዙ ላይ ትሾም ዘንድ መከራ ለመቀበል ተመልሰህ የመሄድ ትልቅ ክብር ይሰጥሃል:: ይሁንና ሁላችንም እያነጽንም ይሁን መከራን እየተቀበልን ለተመሳሳይ ዓላማዎች አብረን እንደምንሰራ ግን አትርሳ:: ለመንግስተ ሰማይ ታላቅ ደስታ ወደ ከፍታ የምትወጣ ከሆነ እነዚህን ክፍሎች ገና ብዙ ነፍሳት ይሞሏቸዋል:: አሁን የተጠራኸው ወደ ከፍታ ለመውጣትና ለማነጽ ሲሆን ለዚህ ጥሪ ታማኝ ከሆንክ ግን በኋላ ላይ መከራን የመቀበል ክብር ይሰጥሃል"::

ከዚያም ፊቴን ዘወር ሳደርግ *"የክርስቶስ የፍርድ ወንበር"* የሚል ቃል የተጻፈበትን ጨለማውንና ገና ያልተከፈተውን አስፈሪ በር አየሁ:: በየጊዜው ወደ መዳን ታላላቅ መዝገቦች ስመለከት ነፍሴን ሰላምና የጋለ ስሜት የሚያጥለቀልቋትን ያህል ይህን በር በተመለከትኩበት ጊዜ ግን ፍርሃትና ጥርጣሬ አንቀው ያዙኝ:: አሁን ውስጤ ያለው ነገር በሙሉ በዚህ ክፍል ውስጥ መቆየት እንጂ ያንን በር አልፎ ለመግባት የሚፈልግ አንዳችም ፍላጎት የለውም:: ንስሩም ይህንን ሃሳቤን ተረድቶ እንዲህ አለኝ::

"በሩን አልፈህ ወደ የትኛውም ታላቅ እውነት ከመግባትህ በፊት እነዚሁ ተመሳሳይ ስሜቶች ይሰሙሃል:: እነዚህ ስሜቶች በመዳን መዝገቦች ወደ ተሞላው ወደዚህ ክፍል ስትገባም ተሰምተውህ ይሆናል:: እነዚህ የፍርሃት ስሜቶች የውድቀት ውጤቶች ናቸው:: መልካሙንና ክፉውን የምታስታውቀው ዛፍ፣ እውነተኛው የእግዚአብሔር ዕውቀት አስፈሪ እንደሆነ አስመስላ ነው የምታሳየው:: እርግጥ ነው የእግዚአብሔር መንገዶች ሁሉ ፍጹም በመሆናቸው ማንኛውም የእግዚአብሔር እውነት የሚመራን ወደ ላቀ ሰላምና ደህንነት ነው:: ፍርዶቹ እንኳን መፈለግ ያለባቸው ናቸው"::

በአሁኑ ሰዓት ትክክል የሚመስለውን ነገር ማወቅ ብዙጊዜ የመጨረሻ

የዝቅተኛ ፍሬያማነት ጉዞና ወደ ውድቀት የሚያደርስ መንገድ እንደሆነ በቂ ተሞክሮን አግኝቻለሁ። ምንም እንኳን አብላጫ ውጤቱ ኪሳራ ቢመስልም በጉዞዬ ሁሉ ወደ ታላቅ ሽልማት የሚያደርሰው መንገድ ትልቅ አደጋ የተጋረጠበት መንገድ ነበር። ስለሆነም በየጊዜው ወደ ተራራው ከፍ ብሎ የመውጣቱ ምርጫ የበለጠ አስቸጋሪ ሆነ። ምንም እንኳን ይሄ ስህተት መሆኑን ከመቼውም ጊዜ ይልቅ አሁን ብረዳውም ጉዟቸውን አንድ ነጥብ ላይ ሟቆም ከሚፈልጉና ለመቀጠልም ፈቃደኛ ካልሆኑ ጋር መስማማት ጀመርኩ። እውነተኛና ብቸኛ የደህንነት ዋስትና የሚመጣው የበለጠ እምነት ወደሚጠይቀው ዓለም ውስጥ ያለማቋረጥ በጌታ ወደፊት ከመጓዝ ነው።

ንስሩም "አዎን፣ በመንፈስ ዓለም ከፍታ ላይ መመላለስ ከዚህ የሚበልጥ እምነትን ይጠይቃል። ጌታ 'ነፍሱን ሊያድን የሚፈልግ ሁሉ ያጠፋታል፣ ነፍሱንም የሚያጠፋ ሁሉ በሕይወት ይጠብቃታል' ሲል ወደ መንግስቱ የምንገባበትን ካርታ ሰጥቶናል። እነዚህ ቃሎች ብቻቸውን ወደ ተራራው ጫፍ የሚያስኬደውን መንገድ ሊያስቀጥሏችሁ የሚችሉ፣ ወደፊት በምትዋጉት ታላቅ ጦርነትም ላይ ወደ ድል አድራጊነት የሚመሯችሁና በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እንድትቆሙ የሚረዷችሁም ናቸው" አለኝ።

አሁን መሄጃ ጊዜዬ እንደሆነ ስላወቅሁ የመዳን መዝገቦች ስለሚገኙበት ስለዚህ የእንግዳ መቀበያ ክፍል ለማሰብ ወሰንኩ። ይሁንና ጉዞዬን መቀጠል ነበረብኝና አልፌ መጓዝ እንዳለብኝ ተረዳሁ። ዘወር ብዬ መሰብሰብ የቻልኩትን ያህል ልበ-ሙሉነትን በመሰብሰብ ወደ የክርስቶስ የፍርድ ወንበር የሚያስገባውን በር ከፍቼ አልፌ ገባሁ። ይህን ጊዜ ለእኔ ተመድበው የነበሩት የመላዕክቱ ሠራዊት በበሩ ዙሪያ በታ፣ በታቸውን ይዘው ቆሙ። ይሁንና ወደ ውስጥ ግን አልገቡም። እኔም፡-

"ምንድነው ነገሩ ለምን አትገቡም?" ስል ጠየቅኋቸው። ከመካከላቸውም አንዱ መልዓክ፡-

"አሁን ወደምትሄድበት ስፍራ መሄድ ያለብህ ብቻህን ስለሆነ እኛ በወዲያኛው በር በኩል እንጠብቅሃለን" አለኝ።

እኔም ለመልዓኩ ምንም መልስ ሳልሰጠው ፊቴን አዙሬ መጓዝ ጀመርኩ። ድነቴን በመላዕክቱ ሠራዊት ላይ አለማድረጌ ትክክል እንደሆንኩ ተረድቻለሁ። በጨለማው ውስጥ እየተራመድኩ እያለሁም "ከዚህ በኋላ በጌታ ብቻ ካልሆነ በቀር በሌላ በማንም፣ በራስህም ላይ እንኳን ቢሆን አትደገፍ" የሚል የመልዓኩን ቃል ሰማሁ።



የገባሁት በፍጹም አይቼው ወደማላውቀው እጅግ አስፈሪ ጨለማ ውስጥ ነበር። እያንዳንዱን ርምጃዬን በፍርሃት መራመድ እጅግ አስጨናቂ ጦርነት ሆኖ ስለታየኝ ወደ ራሱ ወደ ገሃነም እየገባሁ እንደሆነ አሰብ ጀመር። በመጨረሻም ወደ ኋላዬ ለመመለስ ወስኜ ተመልሼ ፊቴን ባዞር በሩ በመዘጋቱ ምንም ነገር ማየት አልቻልኩም። በዚህ ጊዜ በንስሮቹ የተነገረኝና ይህ የደረሰብኝ ማንኛውም ነገር መላዕክቱ እኔን በዚህ ገሃነም ውስጥ ለማጥመድ የዘየዱት ዘዴ እንደሆነና እንዳታለሉኝም ሆኖ ይሰማኝ ጀመር።

በዚህ ጊዜ ጌታ ምህረት እንዲያደርግልኝና እንዲረዳኝም ወደ እርሱ አለቀስኩ። ወዲያውኑም እጄን እንግዳ መቀበያው ክፍል ውስጥ ባለውና ትቼው በወጣሁት ቀዩ ድንጋይ ላይ ስጭን ጌታን መስቀል ላይ እንደ ተሰቀለ ሆኖ አየው ጀመር። እንደገናም ብቻውን የዓለምን ሁሉ ሃጢአት ተሸክሞ ቆሞ እያለም በነፍሱ ውስጥ የነበረውን ጨለማ ተመለከትኩ። በዚያ እንግዳ መቀበያ ክፍል ውስጥ ይህንን ጨለማ መመልከት አስፈሪ ቢሆንም አሁን ግን ብርሃን ሆነ። ሃሳቤን በእርሱ ላይ ጥዬ ጉዞዬን መቀጠል እንዳለብኝ ወሰንኩ። ይህን ሳደርግም በእያንዳንዱ ርምጃዬ በልቤ ውስጥ ሰላም መፍሰስ ጀመረና ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ከነበረው ሁኔታ ይልቅ ቀለል አለልኝ።

ወዲያው ጨለማውን መኖሩን እንኳን ረሳሁት። ከዚያም ደብዘዝ ያለ ብርሃን ማየት ጀመርኩና ብርሃኑ ቀስ በቀስ እየጨመረ ሄዶ በጣም አስደናቂ ብርሃን ሆነ። በቀጥታ ወደ መንግስተ ሰማይ የገባሁኝ ያህል ተሰማኝ። በእያንዳንዱ ሂደት ክብር እየጨመረ ይሄድ ስለነበር ይሄ ሁሉ አስደናቂ ነገር እያለ በጣም ጨለማና ገና ያልታየ አስፈሪ በር እንዴት ሊኖረው እንደቻለ ደነቀኝ። አሁን በእያንዳንዱ ርምጃዬ መደሰት ጀመርኩ።

ከዚያም ምድር ራሷ ልትይዘው ትችላለች ብዬ ወደማላስበው ወደ አንድ በጣም ትልቅ አዳራሽ የሚወስድ መንገድ ተከፈተ። አዳራሹ ውበቱ በየትኛ ውም ዓይነት የሰው የሥነ ህንጻ ጥበብ መግለጫ እንዲህ ነው ተብሎ እንኳን ሊታሰብ የማይችል ነበር። ይሄ ገና ያላየሁትን የኤደን ገነትን ጨምሮ ወይም አስደናቂ ከተባለውና በውስጡ የመዳን መዝገቦችን ከያዘው ከእንግዳ መቀበያው ክፍል የሚበልጥ ነበር። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ውስጤ በጨለማው ፍርሃት መሰበሩን እንደ ገለጽኩት አሁን ደግሞ በአዳራሹ ውበት በደስታ ተሰበርኩ። ከዚያም ታላቅ ችግር ወይም የነፍስ ጨለማ ባጋጠመኝ ከማንኛውም ጊዜ ቀጥሎ ከዚያ በብዙ የሚበልጥ የክብርና የሰላም መገለጥ ተከትሎ እንደሚመጣ ገባኝ።

በክፍሉ የወዲያኛው ጥግ ላይ በማንኛውም ነገር ላይ የሚፈነጠቅ የክብር ምንጭ ነበረ። ይሄ ራሱ ጌታ እንደሆነ አውቄያለሁ። ጌታን ብዙጊዜ ያየሁት ቢሆንም እንኳን አሁን ግን ወደ እርሱ እየተራመድኩ ስሄድ በትንሹ መፍራት ጀመርኩ። ይሁን እንጂ ይህ ፍርሃት ግን የተሰማኝን ክብርና ደስታ አጉልቶ የሚያሳይ የተቀደሰ ፍርሃት ብቻ ነበር። የክርስቶስ የፍርድ ወንበር እስከ ዛሬ ከማውቀው በበለጠ የድነት ምንጭ እንደነበር ብረዳም አሁን ግን በተመሳሳይ የታላቅና የንጹህ ፍርሃት ምንጭም ነበር።

ወደ ጌታ ዙፋን የሚወስደው ርቀት ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ልብ ባልለውም በዚህ ቦታ ላይ በእግር መራመዱ በጣም ድንቅ ነገር ስለነበር ወደ ዙፋኑ ለመድረስ ሺህ ዓመት ቢወስድብኝም እንኳን ግድ አልነበረኝም። በምድራዊው ቋንቋ በጣም ረዥም ጊዜ የሚወስድብኝ ሲሆን በአንዳንድ ሁኔታ ቀናት በሌላ በኩል ደግሞ ዓመታት እንደሆኑ ይሰማኝ ነበር። ይሁንና እዚህ ቦታ ላይ ግን የምድራዊው የጊዜ አቆጣጠር እምብዛም አግባብነት የለውም።

ከእኔ በስተግራ እንደ ማዕረጋቸው ቀደም ተከተል ተሰልፈው ቆመው በነበሩበት በብዙ ህዝብ መካከል እያለፍኩ እንደሆነ ከመረዳቴ በፊት ዓይኖቼ ለረዥም ጊዜ ያህል በተመላለስኩበት በጌታ ክብር ላይ በጣም ተተክለው ነበር። (በቀኜም በኩል እንዲሁ ቁጥራቸው በስተግራዬ የቆሙትን ህዝብ ያህል ቆመው ነበር። ይሁንና እነዚህኞቹ ግን ወደ ዙፋኑ ለመቅረብ ማየት እስከማልችል ድረስ እጅግ ብዙ ነበሩ) እነዚህ መልካቸው እስከ ዛሬ ካየኋቸው ከማንም በበለጠ የሚማርክ እጹብ ድንቅ ስለነበር ሳያቸው መቆም ነበረብኝና ቆምኩ። የሰው ልጅ ፊት እንዲህ ይህን በመሰለ ሰላምና በራስ የመተማመን ጸጋ ተሞልቶ በፍጹም አይቼ አላውቅም። እያንዳንዳቸው ከየትኛውም ምድራዊ የውበት መለኪያ ባለፈ ውብ ነበሩ። ፊቴን ለእኔ ቅርብ ወደነበሩት ሳዞር ልክ እንደሚያውቁኝ ሆነው ዝቅ እያሉ የአክብሮት ሠላምታቸውን አቀረቡልኝ።

“እንዴት አወቃችሁኝ?” ብዬ ጠየቅኋቸው። በኋላ ግን ይህን ጥያቄ በድፍረት በመጠየቄም በራሴ ተገረምኩ።

አጠገቤ የነበረው ሰውዬም “በመጨረሻው ጦርነት ላይ ከሚዋጉት ቅዱሳን አንዱ በመሆንህ በዚህ ያለው እያንዳንዱ ሰውና በአሁኑ ሰዓት በምድር ላይ እየተዋጉ ያሉትም ሁሉ ያውቁሃል። እኛ ከአንተ በፊት በነበሩት ትውልዶች መካከል ጌታን አገልግለን ያለፍን ቅዱሳንና የመጨረሻውን ፍልሚያ ለማየት መብቱ የተሰጠን፣ በዙሪያችሁ እንደ ደመና የከበብናችሁ ምስክሮች ነን። ሁላችሁንም እናውቃችኋለን፣ ያደረጋችሁትንም ሁሉ አይተናል” ሲል መለሰልኝ።



የገረመኝ ነገር ከእነዚህ ሰዎች መካከል በምድር ላይ አውቀው የነበረን አንድ ሰው ማግኘቴ ነበር። ይህ ሰው ታማኝ ክርስቲያን ቢሆንም ያን ያህል ቁም ነገር ያለው ሥራ የሰራ ሰው ነው ብዬ ግን በፍፁም አስቤው የማላውቀው ሰው ነበር። በምድር እያለ ሰውነቱ ደካማና ዓይን የሚገባ ስላልነበረ ዓይን አፋር አድርጎት ነበር። የሰውነቱ ገጽታ አሁንም እንደዚያው ቢሆንም በምድር ላይ አውቃቸው ከነበሩ ከየትኞቹም መልክ መልካም ሰዎች ሁሉ ግን የበለጠ ውብ ሰው ሆኖ ነበር የታየኝ። ይህ ሰው ፈጥኖ ወደ እኔ በመምጣት ከዚህ በፊት ይህን የመሰለ ውበትን በእርሱ ወይም በሌላ በማንኛውም ሰው ላይ ፈጽሞ እንዳላየሁ በአክብሮት አረጋገጠልኝ።

የለበስኩትን ልብስ እያየም እንዲህ ሲል ንግግሩን ጀመረ። “መንግስተ ሰማይ እኛ በምድር ሳለን ማለም ከምንችለው በላይ እጅግ ትልቅ ነው። ይህ ክፍል ከእኛ የማስተዋል ችሎታ በብዙ ያለፈ የክብር ግዛት ጅማሬ ወይም መግቢያ ነው። አስፈሪው እውነትም እኛ ከምንረዳው በላይ ከሁሉ የሚበልጠው ሁለተኛው ሞት ነው። መንግስተ ሰማይም ሆነ ገሃነም እኛ እንደምናስባቸው አይደሉም። አሁን እዚህ እያለሁ ያወቅሁትን ነገር በምድር ላይ ስኖር አውቄው ቢሆን ኖሮ ያንጊዜ የኖርኩትን ዓይነት ሕይወት ባልኖርኩ ነበር። አንተ ግን የሥጋን ሞት ከመቅመስህ በፊት ወደዚህ መምጣትህና ይህን ማወቅህ እጅግ የተባረክህ ሰው ነህ” አለኝ።

ከዚያም እኔም ወደ ራሴ ስመለከት አሁንም ያንኑ አሮጌ የትህትና መጎናጸፊያ እንደለበስኩ ነኝ። የጦር ዕቃዬም በለበስኩት በዚህ መጎናጸፊያ ስር ተሸፍኖ ነበር። እጅግ በክበሩ በእነዚህ ሰዎች ፊት በመቆሜም ስህተተኛነትና ጥፋተኛነት ሁለቱም ተሰማኝ። በጌታ ፊት በዚህ ዓይነት ሁኔታዬ ለመታየት የማቅድ ከሆነ ከባድ ችግር ይገጥመኛል ብዬ መስጋትም ጀመርኩ። ይኼው ሰውዬ ልክ ከዚህ በፊት እንደማውቃቸው ንስሮች የልቤን ሃሳብ መረዳት ስለቻለ እንዲህ አለኝ።

“ይህንን መጎናጸፊያ ለብሰው ወደዚህ ስፍራ የሚመጡ ሰዎች ምንም የሚያስፈራቸው ነገር የለም። ይህ መጎናጸፊያ እጅግ ከፍተኛው የክብር ማዕረግ ስለሆነ ከእርሱ የተነሳ ነው ሁሉም ሰው በዚህ ሲያልፍ ለጥ ብሎ እጅ እየነሳ ሠላምታ የሰጠህ”።

ጥቂት ግራ እንደ መጋባት ብዬ “በእውነቱ እስካሁን ድረስ አንድም ሰው ሲሰግድልኝ ልብ አላልኩም” ብዬ መለስኩለት።

እርሱም ንግግሩን እንዲህ ሲል ቀጠለ:: "ያንን ማድረጋቸው ተገቢም ትክክልም ነው:: እዚህ እርስ በርሳችን ተገቢውን አክብሮት እንሰጣጣለን:: በዚህ ስፍራ ላይ መላዕክት ቢያገለግሉንም የሚመለኩት ግን አምላካችንና የእርሱ ክርስቶስ ብቻ ናቸው:: እርስ በርሳችን በፍቅር በመከባበርና እነርሱን በማምለክ መካከል ግልጽ ልዩነት አለ:: ይህንን እውነት በምድር ላይ ሳለን ተረድተነው ቢሆን ኖሮ ሌሎች ሰዎችን በጣም በተለየ መንገድ በተቀበልናቸው ነበር:: አንዳችን ሌላውን ሙሉ በሙሉ መረዳት፣ ማወቅና በተገቢው መንገድ መቅረብ የቻልነው በዚህ በክብሩ ብርሃን ውስጥ ነው"::

ለመላዕክቱ ከመስገድ ራሴን ባለማቀቤና ባለመግዛቴ አሁንም ድረስ በጣም የሃፍረትና የውርደት ስሜት ስለተሰማኝ ራሴን መሸሸግ ነበረብኝ:: ከዚያም ይህ ሃሳቤ በምድር ሳለሁ አስበው እንደ ነበረው የሞኝ ሰው ሃሳብ በመሆኑና በዚያ ያለው ሰው ሁሉ ስላወቀብኝ የሃዘን እንጉርጉሮ ማንጎራጎር ጀመርኩ:: በእነዚህ እጅግ አስገራሚና ንጹሃን ሰዎች ፊት በመቆሜም የማልረባና የከንቱነት፤ ሁለቱንም ዓይነት ስሜት ተሰማኝ:: ይህ ድሮ በምድር ሳለ የማውቀው ሰውም ለዚህ ሃሳቤ እንዲህ ሲል ምላሹን ሰጠኝ::

"አሁን እኛ የለበስነው ሥጋ የማይበሰብሰውን ሲሆን አንተ ግን ይህን ሥጋ ገና አልለበስክም:: እኛ ከእንግዲህ በኋላ ሃሳባችን በሃጢአት ስለማይበከል ብዙጊዜ ምድራዊው ሃሳብ መረዳት ከሚችለው እጅግ በላቀ ሁኔታም እንኳን ማወቅ መጀመር ችለናል:: እኛም እዚህ ካሉት ሁሉ ታናናሾች ነን" አለኝ::

እኔም በመጠራጠር "እንዴት ከታናናሾች አንዱ ልትሆን ቻልክ?" ስል ጠየቅሁት::

እርሱም መልሶ እንዲህ አለኝ:: "በዚህ ቦታ ላይ የክብር ደረጃ ልዩነት አለ:: በምድር ስለኖርነው ሕይወት የምንቀበላቸው ሽልማቶቻችን ለዘላለም የእኛ የሆኑ ዘላለማዊ ሃብቶቻችን ናቸው:: ይህ ታላቅ ህዝብ ጌታ 'ሞኝ ደናግል' ብሎ የጠራው ህዝብ ነው:: ጌታን እናውቀዋለን፣ በመስቀሉ ሥራ ስለ መዳናችንም እናምናለን:: ይሁንና በምድር የኖርነው ግን ለእርሱ ሳይሆን ለራሳችን ነው:: ማድጋችንንም በመንፈስ ቅዱስ ዘይት ሞልተን አልጠበቅነውም:: የዘላለም ሕይወት አለን፤ ነገር ግን በምድር ላይ ስንኖር ሕይወታችንን በከንቱ ነገር አባክነን የኖርን ሰዎች ነን" አለኝ::

በእውነቱ እዚህ ስፍራ ስለ ሰማሁት ነገር ድንጋጤ ቢሰማኝም ማንም በዚያ ቦታ ላይ ግን ውሸት መናገር እንደማይችል ተረዳሁ::



"ሞኞቹ ደናግልማ በውጪኛው ጨለማ ውስጥ ጥርሳቸውን እያፋጩ ናቸው" ስል በግልጽ ተቃወምኩት::

"የምድር ሕይወታችንን እንዴት ለከንቱ ነገር አባክነነው እንደነበር በተረዳን ጊዜ የደረሰብን ሃዘን በምድር ላይ ሊደርስ ከሚችለው ሃዘን ሁሉ የከፋ ነበር:: የዚህን ሃዘን ጨለማነት መረዳት የሚችሉት ደግሞ ሃዘኑ የደረሰባቸው ሰዎች ብቻ ናቸው:: ይህን የመሰለው ጨለማ ጎልቶ የሚታየው ደግሞ በፊቱ ከማደግ የጎደልነበት ጌታ ክብር ቀጥሎ ሲገለጥ ነው:: እናንተ አሁን የቆማችሁት መንግስተ ሰማይ በሚገኙ በታናናሾች ማዕረግ ተርታ ነው:: ታላቁን የእግዚአብሔርን ማዳን ተረድቶ ለራስ ከመኖር የሚበልጥ ጅልነት የለም:: እዚህ መጥቶ ይህን እውነታ መማር አንዲት ምድራዊት ነፍስ መለማመድ ከምትችለው ሃዘን ሁሉ ያለፈ ነው:: እኛም ከዚህ ከሁሉ ከላቀው ጅልነት የተነሳ፤ ይህ የውጪኛው ጨለማ መከራ ከደረሰባቸው ሰዎች አንዱ ነን" አለኝ::

አሁን ጥርጣሬ ገባኝና "እናንተ እኔ ከማስበው በላይ በመንግስተ ሰማይ ካሉት እንኳን የበለጠ ታላቅና ብዙ ደስታና ሰላም የበዛላችሁ ናችሁ:: በእናንተ ምንም አልጸጸትም:: የሆኖ ሆኖ እዚህ ሆናችሁ መዋሸት እንደማይቻላችሁ ባውቅም ይህ የነገርከኝ ነገር ግን አልገባኝም" አልኩት::

ይህን ጊዜ ትኩር ብሎ ዓይን፣ ዓይኔን ተመለከተና እንዲህ ሲል ንግግሩን ቀጠለ: "በፍርድ ዙፋኑ ፊት እጅግ የከፋ ነው የተባለውን የነፍስ ጨለማን ቀምሼዋለሁ፣ ምህረትንም አግኝቻለሁ:: ጌታም አንተ ገና ልትረዳው በማትችለው በሚበልጥ ፍቅር ነው የሚወደን:: እዚህ ቦታ ላይ እናንተ በምድር ላይ ጊዜን እንደምትቆጥሩት ባንቆጥርም ሕይወቴ በምድር ላይ የቆየውን ያህል የሚቆይ ይመስለኛል:: ንስሃ ያልገባሁባቸው ሃጢአቶቼና በደሎቼ ሁሉ በእኔና እዚህ ባሉት ሁሉ ፊት አልፈዋል:: ይህ ዓይነቱ ሃዘን እስካልደረሰብህ ድረስ ልትረዳው አትችልም:: በጌታ ክብር ፊት በቆምኩኝ ጊዜ እንኳን እጅግ ጥልቅ በሆነ ጨለማ ውስጥ እንደ ወደቅሁ ነበር የተሰማኝ:: እርሱ ሕይወቴን ሙሉ በሙሉ ፈትሿል፣ መርምሮታልም:: በደለኛ ነኝና ይቅር በለኝ ብዬ ምህረትን በጠየቅሁት ጊዜ እምባዬን ከዓይኖቼ አብሶልኛል፣ ጨለማውንም ገፎልኛል:: ከእንግዲህ በፊቱ ስቆም ከዚህ በፊት ይሰማኝ የነበረው ዓይነት የመራርነት ስሜት ባይሰማኝም ይህን ስሜት ግን አልረሳውም:: እንዲህ ያሉ ነገሮችን ስቃዩ ሳይሰማችሁ ማስታወስ የምትችሉት እዚህ ቦታ ላይ ብቻ ነው:: መንግስተ ሰማይ ባለው ዝቅተኛ ክፍል ውስጥ ያለችው የጥቂት ሰዓት ቆይታ በምድር ካለው የሺህ ዓመታት ታላቅ ሕይወት

በብዙ ትበልጣለች:: አሁን በራሴ ስህተት የደረሰብኝ ሃዘን ወደ ደስታ ተለውጧል:: ምንም እንኳን አሁን ያለሁት በመንግስተ ሰማይ ዝቅተኛው ቦታ ቢሆንም የዘላለም ደስታን እንደማገኝ ግን አውቃለሁ" አለኝ፡

እኔም ይህ ሰው የነገረኝ ነገር በሙሉ በመዳን መዝገቦች ተገልጦ እንደነበር ስላወቅሁ እንደገና ስለ እነዚያ መዝገቦች ማሰብ ጀመርኩ:: በተራራው ላይ ወይም ውስጥ ወስጻቸው የነበሩት እያንዳንዱ ርምጃዎች፤ የእርሱ መንገዶች ፈጽሞ ከዚህ በፊት መረዳት ከቻልኳቸው ይልቅ የበለጠ አስፈሪና አስደናቂ ሁለቱም መሆናቸውን የገለጡ ነበሩ::

ይህ የቀድሞ ወዳጄ ትኩር ብሎ ተመለከተኝና ንግግሩን እንዲህ ሲል ቀጠለ:: "እዚህ ያለኸው ማስተዋልን ለማግኘት ሳይሆን በእርሱ ትለወጥና ትለማመደው ዘንድ ነው:: በእዚህ ያለው ቀጣዩ የማዕረግ ደረጃ እኛ ካለን ይልቅ በብዙ እጥፍ የሚበልጥ ነው:: ቀጥሎ ያለውም እያንዳንዱ ደረጃ ከእርሱ ቀደም ብሎ ከነበረው ደረጃ በብዙ እጥፍ የሚልቅ ቢሆንም ከሌላው የሚበልጥ መንፈሳዊ አካል ግን የለውም:: ሆኖም የክብሩ ምንጭ ለሆነው ለዙፋኑ ግን ቅርብ ነው:: ከእንግዲህ በውድቀቴ ሃዘን አይሰማኝም:: በእውነቱ እኔ ይህ ሁሉ ነገር የሚገባኝም ሰው አልነበርኩም:: እዚህ የተገኘሁት በጸጋው ብቻ ነው:: ስለተቀበልኩት ነገር ሁሉ ጌታን በጣም አመሰግነዋለሁ:: እርሱ ሊወደድ የተገባው ነው:: አሁን በመንግስተ ሰማይ በሚገኙ የተለያዩ ዓለማት ውስጥ ብዙ ድንቅ ነገሮችን ማድረግ እችላለሁ፤ ይሁንና ከዚያ ይልቅ ግን ምንም እንኳን በውጪ ያለሁ ብሆንም እዚህ ቆይቼ ክብሩን ባይ ይሻለኛል" አለኝ::

ከዚያም በርቀት እየተመለከተ እንዲህ አለኝ:: "አሁን በመንግስተ ሰማይ ያለ ማንኛውም ሰው የመጨረሻውን ጦርነት የምትዋጉትን እናንተንና የተገለጠውን የእርሱን ታላቅ ምስጢር ለማየት በዚህ ክፍል ውስጥ ነው ያለው"::

እኔም "ክብሩን ከርቀት ባየውም እርሱን ግን ማየት አልቻልኩም:: እናንተስ እርሱን ከዚህ ሆናችሁ ማየት ትችላላችሁን?" ስል ጠየቅሁ::

"አዎን! አንተ ማየት ከምትችለው በብዙ እጥፍ ማየት እችላለሁ:: ከዚህ እንኳን ሆኜ እርሱንና የሚያደርገውን ሁሉ፤ ምድርንም ማየት እችላለሁ:: ያንን ሁሉ ለማድረግ ኃይል ሰጥቶናል:: እኛ እናንተን የምንመለከት የምስክሮቹ ታላቅ ደመናዎች ነን" ሲል መለሰልኝ::



ከዚያም እጅ ነስቶኝ ወደ ባለ ማዕረጎቹ ተመልሶ ሲሄድ እኔም የተናገረኝን በሙሉ እያሰላሰልኩ መራመዴን ጀመርኩ:: "ሞኝ ደናግል" እንደሆኑ የገለጻቸውንና በምድር የነበረውን መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ተኝተውበት የነበሩትን ታላቅ ሠራዊትን በጥንቃቄ ተመለከትሁ:: አሁን ከእነዚህ አንዱ በምድር ላይ ተመልሶ ቢገለጥ እንደ ጣዖት ይመለክ እንደነበር፤ ይሁንና በዚህ ካሉት ሁሉ ግን በጣም ታናሽ እንደሆነ አወቅሁ::

ከዚያም በከንቱ ስላባከንኩት የገዛ ራሴ የምድር ሕይወት ሁሉ ማሰብ ጀመርኩና ስለበዛብኝ አቆምኩት:: ከዚያም በምድር ያሳለፍኩት ሕይወቴ በፊቴ ማለፍ ሲጀምር በአንድ ሃጢአቴ ላይ አስጨናቂ ሃዘን ይሰማኝ ጀመር:: መቅረዜ ውስጥ ከሌሎች ሰዎች ይልቅ ብዙ ዘይት ይገኝ ነበር:: ይሁንና አሁን ግን ሌሎች ያደርጉት ከነበረው ነገር፤ ከእኔ ምን ይጠበቅ እንደ ነበር ስመዝነው ግን ምን ያህል ሞኝ እንደ ነበርኩ አወቅሁ:: ለካስ እኔም ከሞኞቹ ደናግል አንዱ ነበርኩና!

በዚህ አዲስ አስጨናቂ ሃሳብ ተጽዕኖ ስር እወድቃለሁ እያልኩ እያሰብሁ ሳለሁ በምድር ሕይወቱ አውቀውና ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው ነው ብዬም አከብረው የነበረ አንድ ሰው ሊያጽናናኝ ወደ እኔ መጣ:: ከዚያም እጄን ጨብጦ ሞቅ ያለ ሰላምታ ሲሰጠኝ ተነቃቃሁ::

ይህ ሰው በምድር ሳለ ደቀ መዝሙሩ ሆኜ እግሩ ስር ቁጭ ብዬ ለመማር እፈልግ የነበረ ሰው ነበር:: ይሁን እንጂ አብረን ተግባብተን መቀጠል ግን አልቻልንም:: ብዙዎች ይመኙት እንደነበረው እኔም ከእርሱ ለመማር በመፈለግ ልቀርበው ሞክሬ ነበር:: ሆኖም በወቅቱ ከነበረኝ የሥነ ምግባር ጉድለት የተነሳ ግን በነገር ሁሉ አሳዝነው ስለነበር፤ መጨረሻ ላይ ትምህርቱን እንዳቆም አደረገኝ:: እኔም ያገኘሁትን ይህን ትልቅ ዕድል በማበላሸቴ ለዓመታት ይህል የበደለኝነት ስሜት ሲሰማኝ ኖረ:: ምንም እንኳን ጊዜው እየገፋ ሲሄድ ነገሩን ከአዕምሮዬ ባወጣውም የዚህን ውድቀቴን ሸክም ግን አሁንም ድረስ እንደ ተሸከምኩት አለሁ:: አሁን ይህን ሰው ፊት ለፊት ባየሁት ጊዜ የተሰማኝ የህመም ስሜት ይህ ነበር:: ይሄ ሰው አሁን በጣም በክብር ውስጥ ያለ በመሆኑ ደካማው ባህርዬ ከፊት ይልቅ አስጠላኝ፣ አስፈራኝም:: ለመደበቅ ሁሉ ፈለግሁ፤ ነገር ግን ከፊቱ ዘወር ማለት የምችልበት፣ ምንም መንገድ አልነበረኝም:: የገረመኝ ግን ለእኔ ያለው ስሜት እውነተኛና ከልብ

የመነጨ ስለነበር ወዲያውኑ ምኞት እንዲሰማኝ አደረገኝ:: አሁን በመካከላችን ምንም ዓይነት ቅሬታ ያለ አይመስልም:: በእርግጥም እርሱ በመምጣቱ የተሰማኝ ፍቅር ሙሉ በሙሉ ሃፍረቴን አስወግዶልኛል::

ከዚያም “ይህን መገናኘታችንን በጉጉት ስጠብቀው ነበር” አለኝ::

እኔም “ትጠብቀኝ ነበር? ለምን?” ስል ጠየቅሁት::

“እዚህ ቦታ መጥተው ላገኛቸው ከምናፍቃቸው ብዙ ሰዎች መካከል አንዱ አንተ ነህ:: እንድረዳቸው፤ ያውም ደቀ መዝሙር እንዳደርጋቸው ከተጠራሁባቸው፤ ነገር ግን ከገፉኚቸው ሰዎች አንዱ አንተ መሆንህ እስከ ፍርድ ቀኔ ድረስ አልገባኝም ነበር” አለኝ::

“ጌታው! የአንተ ደቀ መዝሙር ሆኖ መሰልጠን እኮ ለእኔ ታላቅ ክብር ነበር:: ጥቂትም ቢሆን ከአንተ ጋር ስላሳለፍኩት ጊዜ በጣም አመሰግናለሁ:: ይሁንና እኔ በጣም ትዕቢተኛና መገፋት የሚገባኝ ሰው ነበርኩ:: ትዕቢተኛነቴና አመጸኛነቴ እውነተኛ መንፈሳዊ አባት እንዳይኖረኝ እንዳደረገኝ አውቃያለሁ:: ይሄ ደግሞ የእኔ እንጂ በፍጹም የአንተ ስህተት አልነበረም” አልኩት::

“ትዕቢተኛ እንደ ነበርክ እውነት ነው:: ይሁን እንጂ ስሜቴ በአንተ የተጎዳበት ምክንያቱ ግን ያ አይደለም:: የተጎዳሁት በዙሪያዬ ያሉትን እያንዳንዱን ሰው በቁጥጥሬ ስር ለማዋል እንድፈልግ ባደረገኝ በራስ መተማመን ከማጣት የመነጨው ፍራቻዬ ነበር:: የማዝህን እያንዳንዱን ትዕዛዝ ያለ ማንገራገር አትቀበለኝም በሚል ስጋት ነበር የተረዳሁህ:: ከዚያ አንተን ከትምህርት ገበታው ላይ ማባረሬ ትክክል እንደሆንኩ ራሴን ለማሳመን ስል አንተን ጥፋት ስትሰራ ለማጥመድ ማንኛውንም እንቅስቃሴህን እያነፈነፍኩ መከታተል ጀመርኩ:: አንተን በቁጥጥሬ ስር ማዋል ካልቻልኩ አንድ ቀን ለእኔም ሆነ ለአገልግሎቴ እንቅፋት እንደምትሆንብኝ ተሰማኝ:: እንዳገለግላቸው ከእግዚአብሔር ከተሰጡኝ ሰዎች ይልቅ ለአገልግሎቴ ከፍተኛ ትኩረትና ክብርን በመስጠቴ አንተንና ሌሎች አንተን የመሰሉትን ብዙዎችን ከትምህርት ገበታው አባረርኳችሁ” አለኝ::

“አንተ ወደ. . .እንደ ተቀየርክ እምኜ መቀበል እንዳለብኝ ነበር የማስበው” ብዬ ልናገር በነበረው ቃሌ ሃፍረት ተሰማኝና ራሴን ገታሁት::



እርሱም መልሶ ምድር ላይ አይቼ በማላውቀው የልብ-ቅንነት እንዲህ አለኝ:: “ልክ ነህ:: መንፈሳዊ አባት እንድሆንህ ጸጋው ተሰጥቶኝ ነበር:: ይሁንና እኔ ግን በጣም ክፉ ሰው ነበርኩ:: ልጆች ሁሉ ዓመጸኞች፣ ራሳቸውን የሚወዱ፤ ዓለም በእነርሱ ዙሪያ እንደምትሽከረከር የሚያስቡ ስለሆኑ አሳዳጊ ወላጆች የሚያስፈልጋቸው ለዚህ ነው:: አንዳንድ ጊዜ አብዛኛው ልጅ የቤተሰቡን ስም ያስነቅፋል:: ቢሆንም የቤተሰብ አካልነቱ ግን አይወሰድበትም:: ጌታ ተጠንቅቄ ወደ መንፈሳዊ ጉልምስና እንዳደርሳቸው አምኖ የሰጠኝን ብዙ ልጆቼን ከትክክለኛው መንገድ ፈቀቅ እንዲሉ፣ እንዲያፈነግጡም አደረግኋቸው:: አብረውኝ የነበሩትን ብዙዎቹንም ወደዚህ ደረጃ ሳላደርሳቸው ቀረሁ:: አብዛኞቹ ያስወግዱት ዘንድ ልረዳቸው በምችላቸው፣ ነገር ግን አላስፈላጊ በሆኑ ቁስሎችና ውድቀቶች በመሰቃየት አሁንም ድረስ የጠላት ምርኮኛ እንደሆኑ ናቸው:: ግዙፍ የቤተ እምነት ተቋም ገንብቼ፣ በቤተ ክርስቲያንም ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖን ማሳደር ችዬ ነበር:: ይሁንና ደቀ መዝሙር እንዳደርጋቸው ወደ እኔ መጥተው የነበሩትንና ጌታ የሰጠኝን ከሁሉም የላቁትን ስጦታዎቼን ግን ገፍቼ አበረርኳቸው:: ለስሜና ለዝናዬ የማልጨነቅ በጣም ራስ ወዳድ ሰው ባልሆን ኖሮ በዚህ ስፍራ በሚገኙት ከፍተኛ ዙፋኖች በአንዱ ላይ ለመቀመጥ የተጠራሁ ንጉሥ ነበርኩ:: አንተም አሁን እያከናወንክ ያለኸው የአገልግሎት ፍሬ ሁሉ በእኔ ሰማያዊ መዝገብ ውስጥ ይከማችልኝ ነበር:: እኔ ግን በዚያ ፈንታ ለዘላለማዊ ነገር በጣም አናሳ ትኩረት ሰጠሁ::

“ቢሆንም በምድር ላይ ሳለህ ያከናወንከው ሥራ ግን አስገራሚ ነበር” ስል ንግግሩን አቋረጥኩት::

“በምድር ላይ መልካም መስሎ የሚታየው ነገር እዚህ ግን የተለየ ነው የሚሆነው:: ብዙጊዜ በምድር ላይ ንጉሥ እንድትሆን የሚያደርግህ ነገር፤ እዚህ ግን ንጉሥ ከመሆን የሚያጎድልህ ነው:: እዚህ ንጉሥ የሚያደርግህ ደግሞ፤ ምድር ላይ ተራና ክብር የሌለው ነው የሚሆነው:: በምድር ላይ ተሰጥተውኝ ከነበሩት አንዳንድ እጅግ የላቁ የፈተና ዕድሎች አንዱ በነበርከው በአንተ ተፈትኜ በመውደቄ ይቅር በለኝ” አለኝ::

እኔም ሃፍረት እየተሰማኝ “በእርግጥ ይቅር ብዬሃለሁ! ይሁንና እኔም ራሴ የአንተ ይቅርታ የሚያስፈልገኝ ሰው ነኝ:: እሁንም ድረስ በዓመጸኝነት ያስቸገርኩህ እኔ እንደሆንኩ ነው የማስበው:: በእርግጥ አጠገብህ እንድደርስ በማትፈልግበት ተመሳሳይ ምክንያት እኔም ራሴ ወደ እኔ መቅረብ የሚፈልጉ አንዳንድ ሰዎችን እንዳይቀርቡኝ አድርጌያለሁ” አልኩት::

“ፍጹም አለመሆንህ እውነት ነው። እኔም አንዳንድ ችግሮችህን በሚገባ አውቃቸዋለሁ። ይሁንና ያ ግን አንድን ሰው ለመግፋት በፍጹም ምክንያት አይሆንም። ጌታ የዓለምን ውድቀት እንደ ተመለከተ ነፍሱን ስለ ዓለም ሁሉ አሳልፎ ሰጠ እንጂ አልገፋትም። ምንጊዜም ነፍሱን ስለ ታናሹ አሳልፎ መስጠት ያለበት ትልቁ ነውና፤ የእኔንም ሃጢአት ባየ ጊዜ አልገፋኝም። ከአንተ በብዙ አድጌ ስለነበር ከአንተ የሚበልጥ ሥልጣን ነበረኝ። እኔ ግን ጌታ አንተንና ሌሎችን ወደ እኔ የላካቸውን ሰዎች በመግፋት እርሱንም ገፋሁት” አለኝ።

እኔም ብሆን እርሱ በጠቀሳቸው በእነዚህ ችግሮች ሁሉ በደለኛ ስለነበርኩ የሚናገረው ቃል ውስጤን ነካው። በዚህን ጊዜ አያስፈልጉም ብዬ በግልጽ የገፋኋቸው ብዙ ወጣት ወንዶችና ሴቶች ወደ አዕምሮዬ መጡ። ወደ ምድር ለመመለስና እነርሱንም አንድ ላይ ሰብስቤ ለማነጋገር ፈለግሁ! በዚህ ወቅት ይሰማኝ የጀመረው ሃዘን ግን የምድር ዘመኔን በከንቱ እንዳባከንኩ ተሰምቶኝ ከነበረው ሃዘን እንኳን የከፋ ነበር። ሰዎችን ገፍቼ ነበር። ከእነዚህም ሰዎች አብዛኞቹ ተራራው ላይ በተካሄደው ጦርነት የቆሰሉና በጠላት የተማረኩ ምርኮኞች ናቸው። ይህ ጦርነት ሙሉ በሙሉ ለህዝቡ የተደረገ ጦርነት ቢሆንም፤ ብዙጊዜ ግን በህዝቡ ዘንድ አላስፈላጊ እንደሆነ ተደርጎ ይታይ የነበረ ነው። እኛ ግን ስንጋደል የኖርነው ስለተሰጠን ህዝብና ስለሚያገለግሉ ሰዎች ሳይሆን ስለ ግል አገልግሎታችን (ሚኒስትሪያችን) ነው።

“እናም ብዙ ሰዎች ስለ እኔ ያስቡ የነበረው፤ መንፈሳዊ መሪ እንደሆንኩ ነበር። እውነቱ ግን እኔ ከቅዱሳን ሁሉ የማንስ ሰው መሆኔን ነው የማስበው”።

በዘመኑ ከነበሩና እጅግ ታላላቅ ከተባሉ ክርስቲያን መሪዎች አንዱ እንደነበር የማውቀው ሌላ ሰው ደግሞ “የሚሰማህን ስሜት እረዳልሃለሁ። ሐዋርያው ጳውሎስ በምድር ሕይወቱ ፍጻሜ አካባቢ ላይ ‘ከቅዱሳን ሁሉ እንደሚያንስ’ ተናግሯል። ከዚያም ከምድር ከመወሰዱ ጥቂት ጊዜ አስቀድሞ ራሱን ‘ከሃጢአተኞች ዋና የሆንኩ’ ሲልም ጠርቷል። ይህን ሲል በምድር ሕይወቱ በመንግስተ ሰማይ ከታናናሾቹ አንዱ የመሆን አስጊ ነገር እንደሚገጥመው አላወቀም ነበር። ይሁንና ይህንን በምድር ሳለ ስለተማረው ግን አሁን ለጌታ ቅርብ ከሆኑት ሰዎች አንዱ ሆኗል። ለዘላለምም ከፍተኛ ማዕረግ ያለው ሰው ሆኖም ይኖራል” ሲል አስተያየቱን ሰነዘረ።



ለእኔ ይህንን ሰው “በሞኞቹ ደናግል” ሠራዊት መካከል ማየቴ እጅግ ስላስገረመኝ “የምድር ሕይወታቸውን በከንቱ ካሳለፉ ሞኞች አንዱ አንተ መሆንህን በፍጹም ማመን አልችልም። እንዴት ነው እዚህ ልትገኝ የቻልከው?” ስል ጠየቅሁት።

እርሱም “እዚህ የተገኘሁት አዳኛችን የከበረን ወንጌል አደራ የሰጣችሁ እናንተ ልትሰሯቸው ከምትችሏቸው እጅግ የከፉ ስህተቶች መካከል አንዱን በመስራቴ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ራሱን ከታላላቆቹ ሐዋርያት ያነሰ አድርጎ ከመቁጠር፤ የሃጢአተኞች ዋና ወደ መሆን ዝቅ እንዳደረገ እኔ ግን የዚህ ተቃራኒውን ርምጃ ወሰድኩ። ዳግም መወለዴን ከሃጢአተኞች ዋና መሆኔን በማወቅ በጸጋ ብጀምርም፤ ከታላላቆቹ ሐዋርያት አንዱ እንደሆንኩ በማሰብ ደመደምኩት። እዚህ እንዳለው ጓደኛችን በራስ መተማመንን ከማጣት ሳይሆን፤ ከታላቅ ትዕቢቴ የተነሳ ነገሮችን እኔ በማይበት ዓይን በማያዩ ሰዎች ላይ ማንኛውንም ጥቃት መሰንዘር ጀመርኩ። እኔን ይከተሉ የነበሩ ሰዎችን ከገዛ ጥሪያቸው ባለፈ ሁሉም ልክ እንደ እኔ እንዲያስቡ፣ እንዲናገሩና እንዲሰሩ ተጽዕኖዬን በማሳደር ስብዕናቸውን ሳይቀር ገፈፍኳቸው። ከዚህ የተነሳም በዙሪያዬ ያለ ማንም ሰው ራሱን መሆን እንዳይችል አደረኩት። ለምን እንዲህ ይሆናል ብሎ? የተቃውሞ ጥያቄ ይዞ ቢመጣ እንደ ዱቄት እንደማደቀው ስለሚያውቅ ማንም ሊጠይቀኝ የሚደፍር አልነበረም። ሌሎችን በማንኳሰስ ራሴን ትልቅ አደረኩት። ለሁሉም እንደ መንፈስ ቅዱስ እንደሆንኩም አሰብኩ።

ሚኒስትሪዬ ከውጪ ሲታይ እያንዳንዱ ሰው በኅብረት የሚሰራበትና ፍጹም ሥርዓትን የተከተለ፣ የተረጋጋና የተዋጣለት ነበር የሚመስለው። እውነቱ ግን የእስር ቤት ሥርዓት ነው የነበረው። የራሱን የጌታን ልጆች ወስጄ የእርሱን መልክ እንዲይዙ ከማድረግ ይልቅ የራሴን መልክ እንዲመስሉ እንደ ሮቦት አደረግኳቸው። በመጨረሻም ለራሴ የሰራሁትን ጣዖት እንጂ ጌታን የማገለግል ሰው ሳልሆን ቀረሁ። በእውነቱ በሕይወቴ ፍጻሜ ላይ የማስተምራቸው ትምህርቶች፣ የምጽፋቸው ጽሁፎችና ተግባሮቼ እንከን የሌለባቸው ‘መጽሐፍ ቅዱሳዊ’ ቢመስሉም እኔ ግን የእውነተኛው ወንጌል ጠላት ሆንኩ” ሲል መለሰልኝ።

ይህ ሰው የተናገረው በጣም አስደንጋጭ ነገር ነበር። በዚህ ስፍራ አድርጌው የነበረው ስብሰባ ከበፊቱ የባሰ ትልቅ ፍርሃትና ድንጋጤ ይፈጥርብኝ ይሆን ወይ? ብዬም መፍራት ጀመርኩ።

“የወንጌል ጠላት እየሆንክ መምጣትህ እውነት ከሆነ ታዲያ አሁን እዚህ እንዴት ተገኘህ?” ስል ጠየቅሁት።

“በእውነቱ ምንም እንኳን ሰዎችን ወደ ጌታ ከመምራት ይልቅ ወደ ራሴ በመምራት ከእርሱ ባርቃቸውም፤ መዳኔ ግን በግል በመስቀሉ በመታመኔ የተቀበልኩት የእግዚአብሔር ጸጋ ነበር። የተባረከው አዳኝ እኛ ለእርሱ ታማኞች ባልሆንበት ጊዜ እንኳን እርሱ ግን ታማኝነቱን ይጠብቃል። ጌታ ያለጊዜዬ ፈጥኖ ከምድር የወሰደኝ በስሬ የነበሩ ሰዎች እርሱን ማግኘትና ማወቅ ይችሉ ዘንድ በጸጋው ነበር” አለኝ።

የዚህ ሰው ታሪክ በጣም የተለየ ዕይታን ሰጥቶን ስለነበር ይህ ሰው ስለ ራሱ የተነገረው ነገር እውነት ለመሆኑ ከዚህ የበለጠ ማሰብ አልቻልኩም። በመቀጠልም በልቤ አስበው የነበረውን ሃሳብ ካነበበ በኋላ እንዲህ ሲል ንግግሩን ቀጠለ።

“እግዚአብሔር በምድር ላይ ካሉት የታሪክ መጻህፍት ሁሉ የተለዩና ሙሉ የሆኑ የታሪክ መጻህፍት አሉት። ስለ እነዚህ ፍንጩ ቢኖርህም ምን ያህል ልዩ እንደሆኑ ግን ገና አላወቅካቸውም። ምድራዊ ታሪኮች ሲያልፉና ሲጠፉ እነዚህ ቅዱሳት መጻህፍት ግን ለዘላለም ይኖራሉ። መንግስተ ሰማይ ስለ ሕይወታችሁ በሚናገረው ደስ መሰኘት ከቻላችሁ እናንተ በእርግጥ ብፁዓን ናችሁ። ሰዎች ሁልጊዜ ታሪካቸው እንዲድበሰበስ፤ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሙሉ በሙሉ የተሳሳተ እንዲሆን በጨለመ መስተዋት ነው የሚያዩት”።

ይህን የሚናገረኝን ቃል አምኜ ለመቀበል ስለተቸገርኩ “ታዲያ ሌሎች ብዙ መሪዎች እንደዚያ የተለየ አክብሮታቸውን የቸሩህ እንዴት ነው?” ስል ጠየቅሁት።

“መንፈስን የመለየት ስጦታ ከሌለ ያለፈውንም ሆነ አሁን ያለውን እውነት በትክክል መለየት አይቻልም። እውነተኛው የመለየት ስጦታ ያላቸው ደግሞ በጣም ጥቂት ክርስቲያኖች ናቸው። አንዳንድ ጊዜ ይህ ስጦታ እያለ እንኳን መለየቱ ይቸግራል። በምድር እስካለህ ድረስ ገንቢም ወይም አፍራሽ ከሆኑ የተሳሳቱ ጥላቻዎች የተነሳ በሌሎች ላይ ትፈርዳለህ። ጊዜው ከመድረሱ በፊት አስቀድመን እንዳንፈርድ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶን የነበረው ለዚያ ነው። እዚህ እስከምንመጣ ድረስ በሌሎች ሰዎች ልብ ውስጥ ያለውን ሃሳብም ሆነ የሰሩትን መልካምም ይሁን ክፉ ሥራ በትክክል ማወቅ አንችልም ነበር። እጅግ ክፉ በሆኑ ሰዎች ውስጥ መልካም፣ እንዲሁም መልካም በሆኑ ሰዎች ውስጥ ደግሞ እጅግ ክፉ ሃሳቦች ይኖራሉና ሰዎች በልባቸው ሃሳብና በሥራቸው



ሊፈረድባቸው የሚችለው እዚህ ቦታ ብቻ ነው” አለኝ።

“እዚህ ተገኝቼ ይህንን በማወቄ ወደ ምድር ስመለስ ነገሮችን በትክክል መረዳት ይቻለኛ ይሆንን?” ስል ጠየቅሁት።

“እዚህ የተገኘኸው እርሱን ይበልጥ በፍጹምነት ማገልገል ትችል ዘንድ ጌታ ምህረት በሌለው ተግሳጽ ይገስጽህ ዘንድ ወደ እርሱ በመጸለይህ ነው። ይሄ ጠይቀኸው የማታውቀው እጅግ የላቀ ማስተዋልን የተሞላ ጥያቄ ነበር። አስተዋይ ፈራጆች ሌላው ሰው እንዳይፈርድባቸው በራሳቸው ላይ የሚፈርዱ ናቸው። ከዚያ የበለጠ አስተዋይ የሆኑት ደግሞ በራሳቸው ላይ እንኳን መፍረድ እንደማይችሉ የተገነዘቡና የጌታን ፍርድ የሚጠይቁ ናቸው። እዚህ በመምጣትህ የሚበልጥ ጥበብና መንፈስን መለየት ስትቀበል፤ በምድር ላይ ግን ሁልጊዜ ቢያንስ በተወሰነ ደረጃ በድንግዝግዝ ነው የምታየው። እዚህ ያገኘኸው ተሞክሮ ሰዎችን በተሻለ ለማወቅ ይረዳህ ይሆናል። ይሁንና ሰዎችን ሙሉ በሙሉ ልታውቃቸው የምትችለው ግን እዚህ ስትሆን ነው። ይህን ስፍራ ለቀህ ስትሄድ ግን ሰዎችን እንዴት በደንብ እንደምታውቃቸው ሳይሆን ስለ ሰዎች ያለህ ዕውቀት ምን ያህል አናሳ እንደሆነ ስታውቅ የበለጠ ትደነቃለህ። ይህ እውነት ከሰው ልጅ ታሪክ ጋር የተያያዘ ነው። በጻፍኳቸው ጽሁፎች ደቀ መዝሙር አድርጌህ ነበር። አሁን ከአንተ ጋር እንድነጋገር ተፈቅዶልኛልና ስለ እኔ እውነቱን ማወቁ ይረዳሃል” ሲል ይህ ቀድሞ የተሃድሶ አራማጅ የነበረ ሰው ንግግሩን አጠናቀቀ።

በመቀጠልም አንዲት የማላውቃት ሴት ወደፊት መጣች። ይህች ሴት ቁንጅናዋ ልብን የሚያማልል ነበር። ይሁን እንጂ በየትኛውም መንገድ ቢሆን የወንድነት ስሜትን የሚቀሰቅስ ዓይነት ግን አልነበረም።

ሴቲቱም እንዲህ ስትል ንግግሯን ጀመረች። “በምድር እያለን የዚህ ሰው ሚስት ነበርኩ። በዚያም ሳለን ስለ እርሱ የምታውቀውና በእርሱ ሲገለጥ ያየኸው አብዛኛው ነገር የሚወጣው ከእኔ ነበር። ስለዚህ አሁን መናገር የምፈልገው ስለ እርሱ ሳይሆን ስለ እኛ ነው። የገዛ ራስህን ነፍስ ሳታድስ ተሃድሶን በቤተ ክርስቲያን ማካሄድ ትችላለህ። የታሪክ ትምህርትን ልታስተምር፤ ሆኖም የአብን ፈቃድ ሳታደርግ ወይም ልጁን ሳታከብረው ትችላለህ። ሰዋዊ ታሪክ ለመስራት ራስህን ከሰጠህም ይህንን ታደርገው ይሆናል። ይሁንና የሥራ ውጤትህ ግን ተንኖ እንደሚጠፋ እንፋሎት ነው የሚሆነው”።

እኔም "ቢሆንም የባለቤትሽ ወይም የአንቺ ሥራ ከእርሱ በኋላ በመጣው ትውልድ ሁሉ ላይ እኮ ትልቅና በጎ ተጽዕኖን አሳድሯል። ያለ እርሱ ዓለም እንዴት በጨለማ ትዋጥ እንደነበር ስናስብ ከባድ ነው" ስል ተቃወምኳት።

"እውነት ነው። ዓለምን በሙሉ ማትረፍ፣ ነፍስህን ግን ማጣት ትችላለህ። በዓለም ላይ ተጽዕኖ ማሳደር የምትችለው፤ ለእውነተኛው ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ዓላማ የገዛ ነፍስህን በንጽህና ከጠበካት ብቻ ነው። ባለቤቴ ነፍሱን ለእኔ ሲል አጥቷል። መዳን የቻለውም እኔ ነፍሴ ከምድር በመወሰዱ ምክንያት በሕይወቱ ፍጻሜ አካባቢ ነው። በምድር አገልግሎቱ ወቅት ያከናወናቸው አብዛኞቹ ተግባራት ከጌታ ይልቅ ይበልጥ ለእኔ ሲል ያደረጋቸው ነበሩ። እንዲያውም ተጽዕኖ አሳድርበት፣ ያስተምራቸው የነበሩ ብዙ ትምህርቶችንና ዕውቀትን የምሰጠው እኔ ነበርኩ። ሴት እንደ መሆኔ መጠን ወቅቱ ሴቶች በመንፈሳዊ መሪነት ማገልገል የማይችሉበት ዘመን ስለነበር እርሱን የገዛ ራሴን አስተምህሮና አመላካከት ማስተላለፊያ ቧንቧ አድርጌ ተጠቀምኩበት። የእኔን ሕይወት በእርሱ አማካይነት መኖር እችል ዘንድም የእርሱን ሕይወት ነጠቅሁት። ከዚያም ራሱን ለእኔ መስጠቱን እርግጠኛ ለመሆን ስል ማንኛውንም ነገር እንዲያደርግ አደረግሁት" አለችኝ።

ባሏን ዓይን፣ ዓይኑን እያየሁት "በጣም ትወዳት ነበር ወይ" አልኩት።

"የለም፣ በፍጹም አልወዳትም፤ እርሷም አትወደኝም ነበር። እርግጥ ነው ከተጋባን ከጥቂት ዓመታት በኋላ እንኳን መፋታት ደረጃ ሁሉ ደርሰን ነበር። ነገር ግን አንዳችን ለሌላችን እናስፈልግ ስለነበር አብረን የምንሰራበትን መንገድ ፈለግን። ትዳራችን ያቆራኘን በባርነት እንጂ በፍቅር ቀንበር አልነበረም። ስኬታማ እየሆንን በመጣን ቁጥር ደስታ የበለጠ ከእኛ እየራቀ መሄድ በመጀመሩ ይከተሉን የነበሩትን ሰዎች የበለጠ ማሳት ጀመርን። በመሆኑም በምድር ሕይወታችን ፍጻሜ አካባቢ ላይ ሁለታችንም ባዶ ምስኪኖች ሆንን። በገዛ ራስህ ስኬት ይበልጥ ተጽዕኖ የማሳደር ዕድሉን ስታገኝ የምታደርገው ጥረት ሥልጣንህን ማስጠበቅ በመሆኑ ሕይወትህ የበለጠ በጭካኔና በጨለማ የተዋጠ ይሆናል። ነገሥታቱ እኛን ሲፈሩን እኛ ደግሞ ከነገሥታቱ ጀምሮ እስከ ታች አንድ ድሃ ድረስ ያለውን ተራ ሰው ሁሉ እንፈራው ነበር። ራሳችንን ይህን በመሰለው የማሳት ሕይወት የምንኖርና እርስ በርሳችንም የማንተማመን ስለነበርን ማንንም ማመን እንኳን የማንችል ነበርን። ከዚህ የተነሳ እያንዳንዱን ሰው እንፈራው፣ በድብቅም እንንቀው ነበር። እጅግ ታላላቅ የእውነት ስብከቶችን እየሰበክህ የሰበክውን እውነት የማትኖረው ከሆነ አንተ ትልቅ ግብዝና ነፍስህ የተጨነቀች ሰው ነህ" አለኝ።



እነዚህ ባልና ሚስት ንግግራቸው እንደ መዶሻ ይቀጠቅጠኝ ጀመር። የእኔም ሕይወት እነርሱ በሚሉት ተመሳሳይ ጎዳና ላይ እያመራ እንደሆነ ማየት ቻልኩ። ከክርስቶስ ይልቅ ራሴን ለማስተዋወቅ ምን ያህል ነበር እተጋ የነበረው? ማንነቴን ለሌሎች ሰዎች በተለይ ደግሞ ለማይወዱኝና ለማይቀበሉኝ ወይም ተቀናቃኞቼ ናቸው ብዬ ለማስባቸው ሰዎች ለማሳየት ምን ያህል ስለፋ እንደነበርኩም ማየት ጀመርኩ። እነዚህ ሁሉ ታላላቅ የምስክር ደመናዎች ከተደበቅሁበት መጋረጃ በስተጀርባ ያለውን ማንነቴንና የልቤን ሃሳብ ስለሚያውቁ ሕይወቴ በእውነተኛ ማንነቴ ላይ በተጣበቁ ሃሰተኛ ገጽታዎች ላይ መገንባቱን እዚህ ላይ መደበቅ አልቻልኩም።

እነዚህን ጥንዶች እንደገና ተመለከትኳቸው። አሁን ያላቸው የልባቸው ምኞት ጥያቄ ውስጥ መክተት የማይቻል፣ ተንኮል የሌለበትና በጣም ቅን እንደሆነ ተረዳሁ። ይህንን እጅግ የከፋ ሃጢአታቸውን ለእኔ ገልጠው መንገር በመቻላቸውም ከልባቸው ደስተኞች ነበሩ።

ከጻፍከው ጽሁፍና በታሪክ ስለ አንተ ከሰማሁት ነገር የተነሳ ለአንተ የተሳሳተ ሃሳብ ኖሮኝ ይሆናል። አሁን ግን የላቀ አክብሮት ነው ያለኝ። ከዚህ በኋ ስሄድ ይህን ቅንነትህንና ግልጽነትህን ይዤው መሄድ እችል ዘንድ ጸሎቴ ነው። እኔም የአስመሳይነት ሕይወት መኖር ሰልችቶኛል። የዚህን አጋጣሚ እያንዳንዱን ዝርዝር ሁኔታ በልቤ እያወጣሁና እያወረድኩ በማሰብ ይህን ዓይነቱን ግልጽነት አገኛለሁ ብዬ እንዴት እጠብቃለሁ! ብዬም አለቀስኩ። ከዚያም ይህ ታዋቂ የተሃድሶ አራማጅ የነበረ ሰው እንዲህ ሲል የመጨረሻ ልባዊ ምክሩን ለገሰኝ።

"አንተ ራስህ የማታደርገውን ነገር ሌሎች እንዲያደርጉት ለማስተማር አትሞክር። ተሃድሶ በቃል ብቻ የሚነገር አስተምህሮ አይደለም። እውነተኛ ተሃድሶ የሚመጣው ከአዳኙ ጋር ኅብረት ሲኖርህ ብቻ ነው። ክርስቶስ የሰጠህን ሸክሞች በመሸከም ከእርሱ ጋር ስትተሳሰር ያሸከመህን ሸክሞች እርሱ ራሱ ይሸከምልሃል፤ ከአንተም ጋር ይሆናል። የእርሱን ሥራ መስራት የምትችለው ለእርሱ ስትሰራ ሳይሆን ከእርሱ ጋር ስትሰራ ብቻ ነው። መንፈስ መውሰድ የሚችለው መንፈስን ብቻ ነው። ከእርሱ ጋር ከተሳሰርህ ስለ ፖለቲካ ወይም ታሪክ ብለህ አንዳች ነገር አትስራ። ለፖለቲካዊ ተጽዕኖ ወይም ሁኔታ ብለህ የምትሰራው ማንኛውም ሥራ የአገልግሎትህን ፍጻሜ ነው የሚያፋጥነው። ታሪክ ለመስራት የምታደርገው ጥረት፤ በሥራህ ያገኘኸውን ስኬትህን በሙሉ ታሪክ አድርጎት ነው የሚደመድመው። ከዚህ የተነሳ አንተም በዘላለማዊነት ላይ ተጽዕኖ ሳታደርስ ትቀራለህ። ለሌሎች የምትሰብከውን

በሕይወትህ የማትኖረው ከሆነ ልክ እኛ እንደ ሰራነው ዓይነት ስህተት ራስህን ከእግዚአብሔር ሉዓላዊ ጥሪ ውጪ ነው የምታደርገው"።

በዚህ ንግግሩ መሃል ጣልቃ ገባሁና "እኔ በመንግስተ ሰማይ ውስጥ ከሁሉ ያነሰ ነው በምትለው በዚህ ቦታ ላይ መቀመጥ የሚገባኝም ሰው ስላይደለሁ ከፍተኛ ጥሪን መፈለግ እንዳለብኝ እንኳን አላስብም። ይሁንና ከፍተኛ ጥሪን እንዴት ነው መፈለግ የምችለው?" አልኩት።

"ከፍተኛ ጥሪ እግዚአብሔር የጠራቸው ሰዎች የሚደርሱበት ጥሪ ነው። የምመክርህ ነገር ቢኖር በሕይወት መንገድ ጉዞህ ላይ መንገድህን እንዳትስት የሚጠብቅህን አዳኙን ውደደው፣ ክብሩንም ብቻ ፈልግ የሚል ነው። ከሌሎች ላቅ ብለህ ለመታየት የምትሰራው ማንኛውም ነገር አንድ ቀን እጅግ የከፋ ውርደትን ነው የሚያመጣብህ። ይሁንና የአዳኙን ስም ለማክበር ካለህ እውነተኛ ፍቅር የተነሳ የምታደርገው ማንኛውም ነገር ግን የመጨረሻ ውጤቱ የዘላለማዊ መንግስቱን ግዛት ያስፋፋል፣ ለአንተም ወደ ከፍታ ቦታ መውጣት ይሆንልሃል። እዚህ ላለው መዝገብ ኑር እንጂ፤ በምድር ላለው መዝገብ አትጨነቅ" አለኝ።

ከዚያም ጥንዶቹ ልባዊ ሰላምታቸውን በመስጠት ተሰናብተውኝ ሲሄዱ ደስታ ሳይሆን ተቃራኒው ስሜት ተሰማኝ። እነርሱ ሲሄዱ እንደገና በገዛ ራሴ ሃጢአት ሸክም ስር ወደቅሁ። ከዚያም የገዛ ራሴን ዓላማ ለመፈጸም የተጠቀምኩባቸው ሰዎች ወይም የልቤን ሃሳብ ለመፈጸም ወይም ራሴን ከሌሎች የተሻልኩ ሰው መሆኔን ለማሳየት ስል የኢየሱስን ስም የተጠቀምኩባቸው ጊዜያት እንደ ጎርፍ ይውጡኝ ጀመር። በዚህ በአንድ ወቅት በጣም ተጠቅሜበት የነበረውን ኃይሉንና ክብሩን ማየት በምችልበት ቦታ ላይ ነፍሴ ልቋቋመው ከምችለው በላይ አስጸያፊ ሆነችብኝ። ከዚህ የተነሳም ከዚህ በፊት አጋጥሞኝ በማላውቀው እጅግ የከፋ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ወድቄ በግንባሬ ተደፋሁ። እነዚህ ሰዎችና ክስተቶች በፊቴ ካለፉ በኋላም፤ የተሃድሶ አራማጁ ሰው ሚስት ተመልሳ መጥታ ከወደቅሁበት እንስታ በእግሮቼ አቆመችኝ። በተለይ በዚህ ሰዓት ላይ በንጽህናዋ ተሸንፌ ስለነበር እጅግ ብልሹ ሰው እንደ ሆንኩ ተሰማኝ። እጅግ ንጽህት ከመሆኗ የተነሳም እርሷን የማምለክ ያህል ጠንካራ ፍላጎትም ሁሉ አደረብኝ።

በዚህን ጊዜ "ፊትህን ወደ ልጁ (ወደ ኢየሱስ) አዙር! እኔን ወይም ማንኛ ውንም ሰው ለማምለክ የሚያድርብህ ፍላጎት፤ ትኩረትህን ከራስህ ላይ ለማንሳትና ያልኖርከውን እውነት በማገልገል፤ ራስህን ለማጽደቅ ብቻ የምታደርገው ከንቱ ሙከራ ነው የሚሆነው። እኔ ፊቴን ወደ እርሱ ስላዞርኩ



አሁን ንጹህ ነኝ። በገዛ ራስህ ነፍስ ውስጥ ያለውን እምነት ማጉደልን ማየት ያስፈልግሃል። ከዚያም ፊትህን ወደ እርሱ መመለስ እንጂ በራስህ ውስጥ መኖር ወይም ራስህን በሞቱ ሥራዎችህ ለማጽደቅ መፈለግ አይገባህም" ስትል አስጠንቅቃ ነገረችኝ።

ይህን በመሰለ እውነተኛ ፍቅር ውስጥ የጉዳት ወይም የጥቃት ሰለባ መሆን የማይቻል ነው ይባል ነበር። ንግግሯን እንደተረዳሁላት ስታውቅም እንዲህ ስትል ቀጠለች።

"ይህ አሁን በእኔ ውስጥ የምታየው ንጽህና መጀመሪያ ላይ ወጣት ሳለሁ ባሌ በእኔ ውስጥ ያየው ንጽህና ነበር። ያኔ የነበረኝ የልብ ሃሳቤ ከአሁኑ ጋር ሲነጻጸር የያኔው ንጹህ ነበር። ይሁንና እኔ ግን እንዲያመልከኝ በማድረግ የእርሱን ልባዊ ፍቅርና የእኔንም ንጽህና በተሳሳተ መንገድ አበላሸሁት። ንጹህ የሆኑ ሰዎችን ከራስህ በበለጠ በማምለክ በፍጹም ንጹህ መሆን አትችልም። ከእነርሱ አልፈህ እነርሱን ንጹሃን አድርጎ የፈጠራቸውንና ሃጢአት የሌለበትን እርሱን ብቻ ለማግኘት አልፈህ መሄድ አለብህ። ሰዎች አብዝተው ሲያወድሱንና እኛም ይህን ውዳሴያቸውን በተቀበልናቸው ቁጥር የበለጠ ከሕይወት መንገድ እየወጣን ነው የምንሄደው። ከዚያም ከሰዎች ውዳሴን ለማግኘትና በማያወድሱን ላይ ደግሞ የበላይነታችንን እያሳየን መኖር እንጀምራለን። ለሌሎች ያስተላለፍነው ውርስ ይሄ ሲሆን በዚህ ቦታ ላይ ያሉትና ከሁሉ የሚያንሱት የብዙዎቹም ችግር የዚሁ ተመሳሳይ ነው" አለችኝ።

ጨዋታችንን ለማስረዘም በመፈለግም ዝም ብዬ ወደ አዕምሮዬ የመጣውን ቀጣይ ጥያቄዬን እንዲህ ስል ጠየቅኋት። "አንቺና ባለቤትሽ በዚህ ቦታ አንድ ላይ መሆናችሁ ችግር አልፈጠረብሽምን?"

"እንዲያውም! አልፈጠረብኝም። በምድር ላይ የነበሩህ ግንኙነቶች በሙሉ እዚህ ሲቀጥሉ፤ ልክ አሁን እኛ መንፈስ እንደሆንነው መንፈሳዊ የመሆናቸው እውነትም በፍርድ ይነጻል። ሰዎች ይቅር ባሏችሁ ቁጥር የበለጠ ትወዷቸዋላችሁ። እርስ በርሳችን ይቅር ከተባባልን በኋላ የበለጠ እንዋደዳለን። ይህንን መዳን አብረን ወራሾች በመሆናችን አሁን ግንኙነታችን በሚበልጥ በብዙ ጥልቀትና መልካምነት ይቀጥላል። እርስ በርስ ክፉኛ ብንቆሳሰልም ስንፈዋወስ ደግሞ ፍቅር የበለጠ መከተል ይችላል"።

ይህንን በምድር ሳለን መለማመድ እንችል ነበር። ይሁንና በጊዜው ይቅር መባባልን አልተማርንም። ይቅር ማለትን ተምረን ቢሆን ኖሮ በኅብረታችን

መካከል ዘልቆ የገባውና ሕይወታችንን ያዘመመው ፉክክር በውስጣችን ስር መስደድ ባልቻለ ነበር። በእውነቱ ፍቅር ካላችሁ በእውነት ይቅር ትላላችሁ። ይቅር ማለት በከበዳችሁ መጠን ግን ከእውነተኛ ፍቅር እየራቃችሁ ነው የምትሄዱት። ይቅር ማለት አስፈላጊ ነው። አለበለዚያ ተሰናክላችሁ ከተመረጠላችሁ የሕይወት መንገድ ትምህርት በብዙ ስታችሁ ትጠፋላችሁ።

በተመሳሳይም በገዛ ራሴ ሕጉ-ወጥነት እንዲህ ያለ ስቃይ ባለበት ፍጻሜ ውስጥ የከተተችኝ ይህች ሴት፣ ከዚህ ቀደም አግኝቻቸው ከነበሩና ማስታወስ ከምችላቸው ሰዎች ሁሉ እጅግ ውብ እንደሆነች ተገነዘብኩ። ይህ ውበቷ የሥጋዊ ፍቅር ሳይሆን ጥያት ለመሄድ አለመፈለግ ነው። ሃሳቤ ገብቷት ልትሄድ እንደሆነ በሚናገር ሁኔታ አንድ ርምጃ ወደ ፊት በመራመድ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አየችኝ።

"መቼም ቢሆን በንጹህ ፍቅር የተነገረ ንጹህ እውነት ይማርካል። እዚህ ቦታ ላይ የተሰማችሁን ስቃይ ማሰቡ በቀረው የሕይወት ዘመናችሁ ሁሉ ይጠቅማችኋል። ስቃይ ችግር ያለበትን የህይወታችሁን ክፍል ስለሚጠቁማችሁ መልካም ነውና ችግሩን እስክምታገኙት ድረስ ስቃዩን ለመቀነስ አትሞክሩ። አብዛኛውን ጊዜ የእግዚአብሔር እውነት ያለብንን ችግር አጉልቶ ሊያሳየን ሲፈልግ ስቃይን ነው የሚያመጣብን። የእርሱ እውነት ሁልጊዜ የነጻነትን መንገድ ነው የሚያሳየን። ይህንን ስታውቅ በሕይወት መንገድህ ላይ በጽናት እንድትሄድ እንዲረዳህ በተላኩልህ መከራዎች ሁሉ ደስ መሰኘት ትጀምራለህ።

"እንደዚሁም አንተ ለእኔ ያለህ ማራኪነት ከሥርዓት የወጣም አይደለም። ከመጀመሪያም ለወንድና ለሴት ተሰጥቶ የነበረው እውነተኛ ገጽታው ምንጊዜም ንጹህ የሆነ ማራኪነት ነው። ንጹህ እውነት ከንጹህ ፍቅር ጋር ሲገናኝ ደግሞ ሰዎች ያለ ምንም ጥርጣሬ ለተፈጠሩለት ዓላማ ለዚያ መሆን ይችላሉ። ይሄ ሌላ ሳይሆን ፍቅር በሃጢአታችን ምክንያት የወደቀበት የመጨረሻው ጥልቅ ርኩሰት ነው። ወንዶች በእውነተኛ ፍቅር እውነተኛ ወንዶች ሲሆኑ፤ ሴቶችም ፍቅር ፍርሃታቸውን ስለተካው ይሆኑ ዘንድ የተፈጠሩለትን ሴትነት መሆን ይችላሉ። ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ስለሚጥል በፍጹም ማንንም ግራ አያጋባም። ወይም ማንንም በቁጥጥሩ ስር ለማዋል አይሞክርም። ሰዎች መቤገርት ሥራውን በውስጣቸው ከሰራ በኋላ ግንኙነቶች እጅግ ሊበላሹ የሚችሉበት ስፍራ ቢኖር ስኬት ማግኘት የሚችሉበት ቦታ ነው። እውነተኛ ፍቅር የመንግስተ ሰማይ ጣዕም ሲሆን፤ ርኩሰት ግን የጠላት የመጨረሻው የመንግስተ ሰማይን ክብር ማበላሻ ነው። በምድር ላይ ካለው ርኩሰት ነጻ በሆንክው መጠን በዚያው ልክ መንግስተ ሰማይን መለማመድ ትጀምራለህ"።



"ይሁንና እዚህ ግን ምንም ዓይነት ርኩሰት እንደተሰማኝ አላስብም ወይም አንቺም. . ." ብዬ ሃሳቧን በጨዋነት ተቃወምኩና ንግግሬን እንዲህ ስል ቀጠልኩ። "በተቃራኒው ውብ የሆነውን ማራኪ ውበትሽን ማየት ብችልም ርኩሰት ስላልተሰማኝ ግን ገርሞኛል" አልኳት።

"ይህ የሆነው እኮ እዚህ ስላለህ ነው። እዚህ ያለው የክብሩ ብርሃን የትኛውንም ዓይነት ጨለማ የሚያስወግድ ነው። ይሁንና እዚህ ባትኖር ኖሮ ግን ርኩሰት ወዲያውኑ ነበር አንቆ የሚይዝህ" አለችኝ።

"ትክክል ለመሆንሽ እርግጠኛ ነኝ። በምድር ላይ ከሚገኝ ከዚህ አስጨናቂ ምግባረ ብልሹነት ነጻ መሆንስ እንችል ይሆን ወይ?" ስል ለመንኳት።

"አዎን አዕምሮህ በእውነት መንፈስ በታደሰ ጊዜ ያገኘሃቸውን የግንኙነት ፅድሎች ሌሎችን ለመጥቀሚያ እንጂ ከሌሎች ጥቅም ማግኛ አጋጣሚ አድርገህ አትወስዳቸውም። መስጠት ከዚህ በፊት በፍጹም አይተነው የማናውቀውን እጅግ የተዋጣላትን ስኬትን ይሰጣል። እጅግ የላቁት የሰው ልጅ ግንኙነቶች፤ ራሳችንን በንጹህ አምልኮ ለጌታ ስንሰጥ የሚመጡ የፍንደቃ ብልጭታዎች ናቸው። እዚህ በአምልኮ ውስጥ የተለማመድናቸው ልምምዶች ገና ያልከበረው ደካማው ሥጋችሁ ሊሸከመው የሚችላቸው አይደሉም። እውነተኛው አምልኮተ እግዚአብሔር ነፍስን ለእውነተኛ ግንኙነት ክብር የሚያነጻ ስለሆነ ግንኙነቶችን ሳይሆን እውነተኛ አምልኮን መፈለግ አለብህ። ያንጊዜ ብቻ ነው ግንኙነቶች መሆን የሚፈለጉትን መሆን መጀመር የሚችሉት። እውነተኛ ፍቅር ዝቅ ብሎ የሁሉ አገልጋይ መሆንን እንጂ በፍጹም የበላይ መሆንን አይሻም። እኔና ባለቤቴ በትዳራችን ዘመን ይህንን እውነት አክብረን ጠብቀነው ቢሆን ኖሮ አሁን ከነገሥታቱ ንጉሥ ዙፋን አጠገብ በተቀመጥን ነበር። ይህም ታላቅ አዳራሽ ቁጥራቸው ከዚህ በሚበልጡ በርካታ ነፍሳት በተሞላ ነበር" አለችኝ።

ይህንን ብላኝ ወደ ከበሩት ቅዱሳን ተመልሳ ሄደች። ከዚያም ቀና ብዬ ወደ ዙፋኑ ስመለከት፤ ዙፋኑ ከዚህ በፊት ከነበረው ክብር በብዙ በሚበልጥ ተውቦ በማየቴ ተደነቅሁ። በዚህ ጊዜ አጠገቤ ቆሞ የነበረ አንድ ሌላ ሰው እንዲህ አለኝ።

"እርሱን የበለጠ ማየት ትችል ዘንድ፤ መጋረጃው በእያንዳንዱ አጋጣሚ ከፊትህ ይወገድ ነበር። አንተ ያልተለወጥከው የእርሱን ክብር በማየትህ ሳይሆን ባልተሸፈነ ፊት በማየትህ ነው። ወደ እውነተኛው የእግዚአብሔር

ፍርድ የሚመጣ የትኛውም ሰው፤ ለእርሱ ያላቸውን ዕይታ የሚያበላሽባቸውን የለበሱትን ምንም ዓይነት መጋረጃ ለማስወገድ ሊረዷቸው የሚችሉትን ሰዎች ለመገናኘት ይህን ወደ መሰለው መተላለፊያ ተራምደው ይመጣሉ"።

ይህ የሰማሁት ቃል በምድር ላይ የነበሩኝ በርካታ የአገልግሎት ዘመናት ሰጥተውኝ ከነበረው መረዳት የሚበልጥ መረዳትን ሰጠኝ። ከዚያም በምድር ላይ የነበረኝ መሻቴና የግል ጥናቶቼ ሁሉ ወደፊት ያራመዱኝ የቀንድ አውጣ ርምጃ ያህል ብቻ ሆኖ ይሰማኝ ጀመር። እዚህ ቦታ ካገኘኋቸው ሰዎች ሁሉ ይልቅ ከጉዞዬ ወደ ኋላ ያስቀረኝ ሕይወቴ በመሆኑ፤ ታዲያ እንዴት ነው ብዙ የሕይወት ዘመናት ለፍርድ ቀን ሊያዘጋጁኝ የሚችሉት? "የዚህ ጸጋ ልምምድ ያልተሰጣቸው ሰዎችስ ሁሉ እንዴት ነው ተስፋ ሊኖራቸው የሚችለው?" ስል ጠየቅሁ።

"እዚህ እየተለማመድህ ያለኸው በምድር ላይ ተሰጥቶህ የነበረ ነገርን ነው። ያንን የትህትና ካባ ከደረብህና ሁልጊዜም የመማር ትኩረትህን ከክብሩ ላይ የማታነሳ ከሆንክ፤ ከሌላ ሰው ጋር ያለህ ማንኛውም ግንኙነትና አጋጣሚ እዚህ የምትማረውን ትምህርት ሊያስተምርህ ይችላል። አሁን ራዕዩን ስለምትጽፈውና የሚያነቡትም ስለሚገባቸው ይህ ልምምድ ተሰጥቶሃል። ያንጊዜ ብዙዎች በመጨረሻው ጦርነት ትንቅንቅ ውስጥ መሸከም ያለባቸውን ክብሩንና ኃይሉን መሸከም ይችላሉ" የሚል አዲስ ድምጽ ሰማሁ።

ይህንን የተናገረኝ ሰው እኔ በምድር ላይ እኖር በነበርኩበት ጊዜ ላይ የኖረ ሰው መሆኑን ሳውቅ ተደነቅሁ። ይሁንና ይህ ሰው በሞት መለየቱን ግን አላውቅም ነበር። በምድር ይኖር በነበረበት ዘመን ፊት ለፊት አግኝቼው ባላውቅም፤ በጣም የማከብርለትን ታላቅ አገልግሎት ያገለግል የነበረ ሰው ነበር። እርሱ ደቀ መዝሙር አድርጎ ባሰለጠናቸው ሰዎች አማካይነት በብዙ ሺህዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ዳግም ልደትን እንዲያገኙ ምክንያት ሆኖ ነበር። እነኚህ ያሰለጠናቸው ሰዎችም በሙሉ ማለት ይቻላል ለወንጌል ስርጭት ሥራ የተሰጡና ብዙ ትላልቅ አብያተ ክርስቲያናትን የተከሉ ታማኞች ነበሩ።

ይህ ሰው ለአንዲት ደቂቃ እንኳን ቢሆን አቅፎ ለመሳም እፈቅድለት እንደሆነ ሲጠይቀኝ፤ ሃፍረት እየተሰማኝ ጥያቄውን ተቀበልኩ። ስንተቃቀፍም ከእርሱ አንዳች ኃይል እየወጣ ወደ ውስጤ ዘልቆ ሲገባና የነበረብኝ ታላቅ ስቃይ ሲቆም ተሰማኝ። ስቃዩ ከእኔ ጋር ለብዙጊዜ የቆየ በመሆኑ እስከቆመበት ጊዜ ድረስ መኖሩን እንኳን አላስበውም ነበር። በኋላም አቅፎ በሳመኝ ጊዜ ከሆነ ህመም እንደ ተፈወስኩና በዚህም በጣም ጥልቅ ደስታ እንደ ተሰማኝ ነገርኩት። ከዚያም በምድር ሕይወቱ ያንን የመሰለ አገልግሎት አበርክቶ



ያለፈው ይህ ሰው፤ አሁን በመንግስተ ሰማይ ውስጥ ለምን በዚህ ዝቅተኛ የማዕረግ ስፍራ እንደ ተቀመጠ እንዲህ ሲል ይነግረኝ ጀመር።

"በምድር ሕይወቴ ፍጻሜ አካባቢ ላይ ጌታ በእኔ ካልሆነ በቀር በሌላ በማንም ሰው ምንም ነገር እንደማይሰራ እስከማሰብ ድረስ በጣም እየታበይኩ መጣሁ። ከዚህ የተነሳ ጌታ የቀባቸውን ሰዎችና ነቢያቱን በክፉ መፈለግና ማጥቃት ጀመርኩ። ጌታ እኔ ራሴ ባሳደኳቸው ደቀ መዛሙርት ሲጠቀምባቸው ስመለከት እንኳን በራስ ወዳድነት እታበይ ነበር። ከእኔ የወንጌል አገልግሎት ውጪ ያሉ ማናቸውንም ሰዎች ሲጠቀምባቸው ሳይም በቅናት እቃጠል ነበር። እነርሱን ተሰሚነት ለማሳጣት ስልም ስህተታቸውን ለማግኘት አነፍንፌ እከታተላቸው ነበር። ይህን በማናቸውም ሰዓት ሳደርግ ራሴን ለውርደት አሳልፌ እየሰጠሁኝ እንደነበር ግን አልተረዳሁትም ነበር"።

በዚህ በሰማሁት ነገር ደንግጬ "እንዲህ ያለ ነገር ታደርግ ነበር? እኔ ግን ይህን ታደርግ እንደነበር በፍጹም አላውቅም" አልኩት።

"ይህን አደርግ የነበረው እኔው ራሴ አልነበርኩም። ነገር ግን ይህንን ቆሻሻ ሥራዬን በስሬ ያሉት ሰዎች እንዲሰሩልኝ አነሳሳቸውና አደፋፍራቸው ነበር። ሌሎች በሰዎች ዘንድ ተሰሚነትን እንዲያጡና እንዲወድቁ ለማድረግ፤ በሕይወታቸው ማናቸውንም ዓይነት ስህተት ወይም ሃጢአት ለማግኘት ምድርን ሁሉ እንዲያስሱ እልካቸው ነበር። ከዚህ የተነሳ ሰው በምድር ላይ ሲኖር ሊሆን የሚችለውን የመጨረሻውን ክፉ ሰው ሆንኩ። የመሰናከያ አለቶችን የሚያፈራ የመሰናከያ አለትም ሆንኩ። ስለ እውነት መጋደል በሚል ሽፋንም በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት መካከል የአለመተማመንና የመለያየትን ክፉ ዘር ዘራሁ። ራሴን ጻድቅ አድርጌ በመመጻደቅም ወደ ጥፋት አመራሁ። በመጨረሻም ጌታ በታላቅ ምህረቱ ቀስ በቀስ እያደከመ በሚገድል በሽታ እንድያዝ ፈቀደና ልክ ከመሞቴ በፊት ወደ አዕምሮዬ ተመልሼ ከዚህ ክፉ ሥራዬ ንስሃ ገባሁ። አሁን እዚህ ቦታ ላይ እንድገኝ ዕድሉን ስለ ሰጠኝም አመሰግነዋለሁ። እዚህ ቦታ ላይ የእርሱ ከሆኑት ከታናናሾቹ አንዱ እሆን ይሆናል። ይሁንና መሆን ይገባኝ ከነበረው አንጻር ሲታይ ግን እንዲያውም አሁን ያለሁበት ይበዛብኛል። የበደልኳችሁን ሰዎች ሁሉ አግኝቼ ይቅርታ ለመጠየቅ ዕድሉን እስከማገኝ ድረስም ይህንን ክፍል ለቅቄ መውጣት አልችልም" አለኝ።

"ይሁን እንጂ እኔን ግን በፍጹም አልበደልከኝም" አልኩት።

“አይ እርግጠኛ ነኝ በድዬሃለሁ። በአንተ ላይ የተሰነዘሩብህን አብዛኞቹን ጥቃቶች እኔ በግሌ ባልሰነዘራቸውም አንተን እንዲያጠቁልኝ ባነሳሳኋቸውና ባበረታታኋቸው ሌሎች ሰዎች የተሰነዘሩብህ ነበሩ። ጌታ ግን እኔንም ጥቃቱን ከሰነዘሩት ሰዎች እኩል ይጠይቀኛል” ሲል መለሰልኝ።

“አሃ! ነው እንዴ። እንግዲያው እኔ በበኩሌ ይቅር ብዬሃለሁ” አልኩት።

ምንም እንኳን መጠኑ ቢያንስም እኔም ራሴ ይህንኑ ዓይነት ተመሳሳይ ስህተት እፈጽም እንደነበር ማስታወስ ጀመርኩ። አኩራፊ የሆኑ የአንዲት ቤተ ክርስቲያን የቀዩ አባላት ያሉ ማቋረጥ ስለዚያች ቤተ ክርስቲያናቸው ክፉ መርዛቸውን እንዲረጩ እንዴት ፊቅጄላቸው እንደ ነበር አስታወስኩ። ይህን ስህተታቸውን እንዲያርሙና እንዲያስተካክሉ ከመምከርና ከመርዳት ይልቅ ይህን ክፉ ሥራ እንዲሰሩ፤ በዚያ እንዲቀጥሉበትም እንዴት አበረታታቸው እንደነበርና ለዚህ ጥፋቱም የዚያችን ቤተ ክርስቲያን ስህተቶች ምክንያት አድርጌ አቀርብ እንደ ነበር አስታወስኩ። ከዚያም ስለ እነርሱ እጸልይ የነበረውን የግብዝነት ጸሎትና ብዙዎቹን ታሪኮች ደጋግሜ ማስታወስ ጀመርኩ። ወዲያውኑ ይህን የመሰሉ ሌሎች ክስተቶችም እንደ ታላቅ ጎርፍ ወደ ልቤ መጉረፍ ጀመሩ። ይህን ጊዜ በገዛ ነፍሴ ክፋትና ጨለማነት መገረም ጀመርኩ።

እናም “እኔም ለሌሎች የማሰናከያ አለት ሆኜ ነበር!” ስል አለቀስሁ። ይህን ዓይነት ክፋትና ጭካኔ በገዛ ራሴ ልብ ውስጥ በፍጹም አይቼ ባለማወቄ፤ ሞትና እጅግ የከፋው የገሃነም ፍርድ የሚገባኝ ሰው እንደሆንኩም ተረዳሁ።

ከዚያም እንዲህ የሚል የዚህ ሰው ድምጽ ተሰማ። “እናም ሁላችንም የገዛ ልጆቹን እያሳደድን ለእግዚአብሔር ውለታ እየሰራን እንዳለን አድርገን በማሰብ ራሳችንን አጽናናን። አንተ ወደ ምድር ተመልሰህ መሄድ ስለምትችል፤ ለአንተ ይህንን እዚህ ማየትህ መልካም ነው። እባክህ ተመልሰህ ስትሄድ በዚያ ያሉትን ደቀ መዛሙርቴን ንስሃ የማይገቡ ከሆነ የሚጠብቃቸው ክፉ ቀን መኖሩን አስጠንቅቀህ ንገርልኝ። አብዛኞቹ እዚህ በነገሥታት ዙፋን ላይ እንዲቀመጡ የተጠሩ ቢሆኑም ንስሃ ካልገቡ ግን፤ በማሰናከያ አለቶች ላይ የሚደርሰውና እጅግ ከሁሉ የከፋው ፍርድ ያገኛቸዋል። እኔን ቀስ በቀስ እያዋረደ ለሞት ያበቃኝ በሽታ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላከልኝ የእርሱ ጸጋ ነበር። በዙፋኑ ፊት በቆምሁ ጊዜ፤ ወደ እነርሱ ተመልሼ መሄድ እንደማልችል ስረዳ ጌታ ይህንን ጸጋውን ለደቀ መዛሙርቴ እንዲልክላቸው ጠየቅሁት። ይሁንና ይህችን ጊዜ ከአንተ ጋር አብሬ እንዳሳልፍ ፈቀደልኝ። እባክህ ጥቃት ያደረሱብህን ሰዎች ይቅር በላቸው፣ ከእስርካቸውም እስራት ፍታቸው። እንደ



እውነቱ ከሆነ እነዚህ ሰዎች የከሳሻችንን ሥራ እየሰሩ መሆናቸውን አልተገነዘቡትም። እኔን ይቅር ስላልከኝም አመሰግንሃለሁ። ሆኖም እነርሱንም ይቅር በላቸው እባክህ። ሃጢአታቸውን መያዙ ወይም በፍቅር መሸፈኑ የአንተ ምርጫ ቢሆንም አሁን ግን ጠላቶችህን እንድትወዳቸው ነው የምለምንህ”።

የገዛ ራሴን ሃጢአት ማሸነፍ በጣም ስለከበደኝ፤ ይህንን ሰው መስማት አልቻልኩም ነበር። እርሱ በጣም የከበረ፣ ንጹህና በእርግጥ በምድር ላይ ፍጹም የነበሩ ሥልጣኖች የነበሩት ሰው ቢሆንም፤ አሁን ግን በታላቅ ትህትና እየለመነኝ ነው። ከእርሱ ይህን የመሰለ ፍቅር ሲወጣና ሲሰማኝ እምቢ ልለው አልቻልኩም። ይሁንና የእርሱ ፍቅር ተጽዕኖ ሳያሳድርብኝ እንኳን ያሳድዱኝ ከነበሩት ከማናቸውም ሰዎች ይልቅ እኔን የበደለኝነት ስሜት ተሰማኝ።

“በእርግጥ እኔ፤ በእኔ ላይ ያደረጉት ማንኛውም ነገርም ሆነ ወይም ከዚያም በላይ ሊደርስብኝ የሚገባኝ ሰው ነኝ” ስል መለስኩለት።

“ያ እውነት ነው። ይሁንና እየተነጋገርን ያለነው ነጥብ ግን ሌላ ነው። በምድር ላይ የሚኖር ማንኛውም ሰው ሁለተኛው ሞት የተገባው ነበር። ይሁዓና አዳኛችን ጸጋና እውነትን ስላመጣልን ግን፤ የእርሱን ሥራ እንሰራለን የምንል ከሆነ ሁሉንም ነገር በጸጋና በእውነት መስራት አለብን። ጠላት ‘የብርሃን መልዓክ’ ሆኖ ሲገለጥ ይዞት የሚመጣው ነገር እውነትን ያለ ጸጋ ነው” ሲል ልመናውን አቀረበ።

“ምናልባትም ከዚህ ነገር ነጻ መውጣት ከቻልኩ ልሰራው እችል ይሆናል። ይሁንና እነርሱ ከሆኑት በላይ ክፉው ሰው እኔ መሆኔን መገንዘብ አትችሉምን?” ስል መለስኩለት።

ፍጹም ጥልቅ በሆነ ፍቅርና ጸጋ “አልፈህ የመጣሃቸው ትዝታዎችህ መጥፎ እንደሆኑ እረዳልሃለሁ” ሲል መለሰልኝ። ይህ ሰው ለገዛ ራሱ ደቀ መዛሙርት እንደሚያስብላቸው ሁሉ አሁን ደግሞ ስለ እኔና ስላለሁበት ሁኔታዬ እያሰበልኝ እንደሆነ ተረዳሁ።

“በእርግጥ ይህ ቦታ መንግስተ ሰማይ ነው፤ ብርሃንና እውነትም ነው” ስል በሆዴ የያዝኩትን ምስጢር አውጥቼ ተናገርኩ። ይህንን በመሰለ የጨለማ ህይወት ውስጥ የምንኖር ሰዎች እንዴት ነው ስለ እግዚአብሔር ብዙ እንደምናውቅ በማሰብ በጣም ትዕቢተኞች መሆን የቻልነው? ጌታ ሆይ! እባክህ ስመለስ ይህንን ብርሃን ወደ ምድር ተሸክሜ ልሂድ!” ስል ዙፋኑ ወዳለበት አቅጣጫ ጩኸቴን አሰማሁ።

ወዲያውኑም መላው የሰማይ ሠራዊት በትኩረት ሲቆሙና የትኩረታቸው ማዕከሉም እኔ መሆኔን አየሁ:: በእነዚህ በጣም በከበሩ ሠራዊት በአንዳቸውም ፊት የማልጠቅም ሰው እንደሆንኩ ቢሰማኝም ሁሉም ወደ እኔ ይመለከቱ እንደነበር በተረዳሁ ጊዜ ግን የፍርሃት ማዕበል ዋጠኝ:: አሁን ሊገጥመኝ ያለው ክፉ ቀንም ወደፊት ሊገጥመኝ እንደማይችል ተሰማኝ:: ያንን ስፍራ የሞላው እጅግ ታላቁ የክብርና የእውነት ጠላት እኔ እንደሆንኩም ተሰማኝ::

ከዚያም ወደ ምድር ስመለስ ይገፍው ለመሄድ ስላቀረብኩት ጥያቄዬ አሰብኩ:: እምነቴን በጣም በማጉደሌም ይህን የመሰለውን ክብርና እውነት በፍጹም በበቂ ሁኔታ መወከል የምችል ሰው አልነበርኩም:: በእኔ እምነት አጉዳይነት ያንን በመገኘቱ ኀልዎት የከበረውን ስፍራ እውነታ ማየት የምችልበት መንገድም አልነበረም:: እኔ የወደቅሁትን ውድቀት ያህል ሰይጣን እንኳን እንዳልወደቀ ሆኖ ነበር  የተሰማኝ:: ስለዚህም "ይሄ ገሃነም ነው" ብዬ አሰብኩ:: እንዲህ ያለ ክብር እንዳለ ከማወቅና እንደ እኔ ክፉ ሰው ከመሆን ከዚህ የከፋ ስቃይ ሊኖር አይችልም:: ወደዚህ ቦታ ለመግባት ስለ መከልከል ሳስብ ከዚህ በፊት ፈርቼ የማላውቀው ዓይነት የከፋ የስቃይ ቅጣት ሆነብኝ:: ድምጼን ዝቅ አድርጌም "እንዲህ ከሆነ አጋንንት በጣም ቢቆጡና ቢያብዱ ምንም ያስደንቃል" ስል ለራሴ ነገርኩት::

ልክ ወደ ገሃነም፣ ወደ ጥልቁ ልላክ እንደሆን በተሰማኝ ጊዜ "ኢየሱስ!" ብዬ ጩኸቴን ለቀኩት:: በዚህ ጊዜ ሰላም ወዲያውኑ በላዬ ፈሰሰ:: እንደገና ወደ ክብር ተመልሼ መጓዝ እንዳለብኝ አወቅሁ:: ይህንን ለማድረግ በራስ መተማመኑ ስለነበረኝ በዘመናቸው ሁሉ ታላላቅ ከተባሉ ጸሐፊያን አንዱ እንደነበር ከምቆጥረው ግለሰብ ጋር እስከ ተገናኘሁበት ቦታ ድረስ ጉዞዬን እንደ ምንም ቀጠልኩ:: የዚህ ሰው እውነትን በጥልቀት አርቆ ማስተዋል ምናልባትም በጥናቶቼ ካገኘኋቸው ሁሉ እጅግ የላቀ ሊሆን እንደሚችል መዝኜው ነበር::

"ክቡር ሆይ! ይህችን ቀን ዘወትር በጉጉት ስጠብቃት ነው የኖርኩት" ስል በልቤ ምስጢር አድርጌ የያዝኩትን አውጥቼ ነገርኩት::

እርሱም "እኔም እንደ አንተ ስጠብቃት ነበር" ሲል ከልብ በሆነ ትህትና መለሰልኝ::

በዚህ አነጋገሩም ደነገጥኩ:: ሆኖም ከእርሱ ጋር በመገናኘቴ በጣም ደስ ተሰኝቼ ስለነበር ግን "እንደማውቅህ ይሰማኛል:: አንተም በጻፍካቸው



መጽሐፎችህ እንደምታውቀኝ ነው የሚሰማኝ:: ቅዱሳት መጻህፍትን ከጻፉልን ጸሐፊያን ውጪ ከማንም በበለጠ የአንተ ትልቅ ውለታ እንዳለብኝ ነው የማስበው" ስል ንግግሬን አቆምኩ::

"አንተ በጣም ትሁት ሰው ነህ:: ይሁንና አንተን ከዚህ በተሻለ ሁኔታ ባለማገልገሌ ግን አዝኛለሁ:: እኔ በጣም የማልረባ ሰው ነበርኩ:: ጽሁፎቼም ከመለኮታዊ እውነት ይልቅ ዓለማዊ ጥበብን የተሞሉ ነበሩ" አለኝ::

እኔም "በዚህ መሆንና፣ የተማርኩትን ሁሉ መማር ከጀመርኩበት ጊዜ አንስቶ እዚህ ቦታ ላይ መናገር የምችለው እውነትን ብቻ ስለሆነ ይሄ እውነት መሆን እንዳለበት እረዳለሁ:: ይሁንና ለእኔ ግን አሁን ይህን የምትለኝን መቀበሉ ይከብደኛል:: መጽሐፎችህ በምድር ላይ ከሚገኙ ጥቂት ምርጥ ከሚባሉ መጽሐፎች እንደሆኑ ነው የማስበው" ስል መለስኩለት::

ይህ ዝነኛ ጸሐፊም "እውነትህን ነው" ሲል ሃሳቤን በትህትና ከተቀበለኝ በኋላ "በጣም አሳዛኝ ነገር ነው:: እዚህ ስፍራ ያለ እያንዳንዱ ሰው እንዲያውም በንጉሡ አጠገብ እንኳን የተቀመጡት ሳይቀሩ ሕይወታቸውን በተለየ ሁኔታ መኖር ስለነበረባቸው ኖረውታል:: ይሁንና እኔ ግን ሕይወቴን ከማንም በተለየ ሁኔታ ኖሬዋለሁ ብዬ ነው የማስበው:: በምድር ነገሥታት ዘንድ ታላቅ ክብር ተሰጥቶኝ ነበር፣ ይሁንና በነገሥታቱ ንጉሥ ዘንድ ግን ክብርን አላገኘሁም:: በተሰጡኝ ታላላቅ ስጦታዎችና ማስተዋሎች ሰዎችን ወደ እርሱ ከመምራት ይልቅ ይበልጥ ወደ ራሴና ጥበብ ነው ወደምለው ለመሳብ ተጠቅሜባቸዋለሁ:: በተጨማሪም እኔ እርሱን የማውቀውና ሌሎችም እርሱን ያውቁት ዘንድ ግድ የምላቸው በጆሮ በመስማት ብቻ ስለነበር የእኔ ጥገኛ አደረኳቸው:: ሌሎች ፊታቸውን እኔ ራሴ እምብዛም ኅብረት ወደሌለኝ ወደ መንፈስ ቅዱስ እንዲመልሱ ከማድረግ ይልቅ፤ ይበልጥ ወደ መንፈሳዊ አመንክዮ (ምክንያታዊነት) እንዲያዞሩ አደረኳቸው:: ሰዎችን ወደ ኢየሱስ ሳይሆን ወደ እኔና እርሱን እንደሚያውቁት ወደሚናገሩ፤ እኔን ወደ መሳሰሉ ሰዎች እንዲመጡ መራኋቸው:: እርሱን እዚህ ባየሁት ጊዜ ልክ ሙሴ የወርቁን ጥጃ ወርውሮ እንደሰበረው እኔም ጽፌያቸው የነበሩትን መጽሐፎቼን በእሳት አቃጥዬ ወደ አመድነት ለመለወጥ ፈለግሁ:: አዕምሮዬ ጣዖት ሆኖብኝ ስለነበር ሰዎች ሁሉ ከእኔ ጋር ሆነው አዕምሮዬን እንዲያመልኩ ፈለግሁ:: አንተ ለእኔ ያለህ አክብሮት ደስ  አላሰኘኝም:: በነበረኝ ዕውቀት የሌሎችን አድናቆት ለማግኘት ስል ያጠፋሁትን ጊዜ፤ እርሱን በማወቅ ላይ አጥፍቼው ቢሆን ኖሮ ሌሎች ብዙ ህዝቦች የዘላለም ሕይወትን አግኝተው በዚህ በተገኙ፤ በዚህ ክፍል ውስጥ በዝቅተኛ ማዕረግ ላይ የተቀመጥነው ብዙዎቻችንም

በተዘጋጀልን ዙፋን ላይ በተቀመጥን ነበር” አለኝ።

እኔም ቀጠል በማድረግ “የጻፍካቸው ጽሁፎች ለብዙ ዓመታት ያህል መንፈሳዊ ምግብን ሲመግቡኝ የኖሩ ናቸው። እኔ እስከማውቀው ድረስ እኔን ብቻም ሳይሆን ሌሎች ብዙዎችንም መግበዋል። የተናገርከው ቃል እውነት መሆን እንዳለበት አውቃለሁ። ይሁንና ስለ ሥራዎችህ ግን በራስህ ላይ እንዲህ ለመፍረድ ትንሽ አልከበድክምን? ” ስል ጠየቅሁት።

“በራሴ ላይ ለመፍረድ አልከበድኩም። አሁን የነገርኩህ በሙሉ በዙፋኑ ፊት በቆምኩኝ ጊዜ እውንነቱ ተረጋግጧል። ብዙ ፍሬ ባፈራም፤ ያፈራሁት በዚህ ቦታ ከሚገኙት ከማናቸውም ሰዎች ይልቅ ብዙ ክህሎቶች ተሰጥተውኝ ነው። ይሁንና አዳም በመታዘዝ የሰው ልጅን በሙሉ እጅግ ወደ ከበረው ተስፋ ማድረስ ሲችል፤ ነገር ግን በዚያ ውድቀት በቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ነፍሳትን ወደ አስፈሪው ክፉ ቀን እንደ መራቸው፤ እኔም የተሰጡኝን እነዚህን ክህሎቶች በገዛ ራሴ መንፈሳዊ ትዕቢትና ምኞት ስር ቀበርኳቸው። ኃላፊነት ሥልጣንን ተከትሎ የሚመጣ ነገር ነው። ይበልጥ ሥልጣን በተሰጣችሁ መጠን፤ መልካምም ሆነ ክፉ ነገር የሚያደርስባችሁ የሚበልጥ ኃይል ይኖራችኋል። በዘመናት ሁሉ ከእርሱ ጋር የሚጓዙ ሰዎች እጅግ ከባዱ ኃላፊነት ምን እንደሆነ ያውቁታል። ማንም ብቻውን የሚቆም ሰው የለም። እያንዳንዱ የሰው ልጅ ውድቀት ይሁን ስኬት እኛ ከምናስበውና ከምንገምተው በላይ ለሚመጣው ትውልድ እንኳን ድምጹን ያስተጋባል።

ቃልን ወደ ተግባራዊ የሥነ ጥበብ ሥራዎች የሚለውጥና “የቃል አንጥረኛ” የሚል ስያሜ የተሰጠው ይህ ሰው መጽሐፎቹን እጅግ በተዋበና ግልጽ በሆነ ቃል እንዴት ይጽፋቸው እንደነበር አሰብኩ። እዚህ ስፍራ የሚናገረው ግን እነዚህን ታዋቂ ጽሁፎቹን ያለ ተሰጥዖ እንደ ጻፈ ተራ ሰው ነበር። እዚህ ቦታ የተገኙ ማናቸውም ሰዎች የልቤን ሃሳብ እንዳወቁብኝ እርሱም እንዳወቀብኝ አውቄያለሁ። ሆኖም ይበልጥ አስፈላጊ እንደሆነ የሚያስበውን ሃሳብ ግን እንዲህ ሲል በግልጽ መናገሩን ቀጠለ።

“ስለ ጌታ ያለን ዕውቀት ከመፈለጌ ይልቅ እርሱን ራሱን ጌታን ፈልጌው ቢሆን ኖሮ፤ አሁን በዚህ ስፍራ በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ህዝቦች መገኘት ይችሉ ዘንድ ማድረግ የሚችሉ ብዙ ሺህ ደቀ መዛሙርትን ማፍራት እችል ነበር። የሥልጣንን እውነተኛ ባህርይ የተረዳ ማንም ሰው፤ ሥልጣንን ያለ ምንም መሰናከል መሸከም የቻለው ብቸኛ ጌታ ቀንበር የተጠመደበት መሆኑን ያወቀ ነው። ይህንን ሥልጣን ደግሞ ሲሰጠው የሚቀበለው እንጂ፤ በፍጹም ጓጉቶ የሚፈልገው አይደለም። ስለዚህ ጌታንና የእርሱን ቀንበር ብቻ ለመሸከም



ፈልግ እንጂ ፈጽሞ የራስህን የበላይነት አትሻ። የእኔ ተጽዕኖ የመገበሁ ልብህን ሳይሆን በዕውቀት መታበይን ነው” አለኝ።

ስለ ራሴ ጽሁፎች ማሰብ ጀመርኩና “እኔስ ተመሳሳዩን ስህተት አለመፈጸሜን እንዴት ነው ማወቅ የምችለው?” ስል ጠየቅሁት።

እርሱም በክብር ስፍራ ወደ ተቀመጡት ወደ ባለ ማዕረጎቹ ተመልሶ እየሄደ “ራስህን ለሰዎች ሳይሆን ለእግዚአብሔር ለማቅረብ ትጋ” ሲል መለሰልኝ። ከዓይኔ ከመሰወሩ በፊትም ዘወር ብሎ በፈገግታ “እኔን ግን እንዳትመስል” ሲል የመጨረሻ ምክሩን ለገሰኝ።

በእነዚህ በርካታ ህዝብ መካከል በታሪክ ከማውቃቸው ከመጀመሪያዎቹና እኔ ከነበርኩበት ዘመን ትውልዶች ከሁለቱም የመጡ ሌሎች በርካታ የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ተመለከትኩ። ብዙዎቹንም ቆሜ አነጋገርኳቸው። በመንግስቱ ውስጥ በከፍተኛ ማዕረግ ላይ እንደሚቀመጡ ጠብቄያቸው የነበሩ በጣም ብዙ ሰዎች በመጨረሻው ዝቅተኛ ማዕረግ ላይ ባገኘኋቸው ጊዜ እጅግ ደነገጥሁ። ሁሉም ከትላልቅ ስኬቶቻቸው በኋላ ገዳይ በሆነው ሃጢአት በትዕቢት ወይም የእነርሱን ያህል የተቀቡ ሌሎች ሰዎችን በመመቅኘት ወድቀው ስለነበር ብዙዎቹ ይህን ክፉ ታሪካቸውን ነበር የሚናዘዙት። ሌሎች በምድር ህይወታቸው ፍጻሜ አካባቢ ላይ የጥፋትን ድንበር አልፈው ከመሄዳቸውና በሞት ወደ መንግስተ ሰማይ ከመወሰዳቸው በፊት ርኩሰትን በመፈጸም፣ በተስፋ መቁረጥ ወይም በመራርነት የወደቁ ነበሩ። ሁሉም የሰጡኝ ተመሳሳይ ማስጠንቀቂያ ግን “ወደ ላቀ ከፍተኛ መንፈሳዊ ሥልጣን ስትሸጋገር ፍቅርና ትህትና ከሌለህ ልትወድቅ ትችላለህ” የሚል ነበር።

ወደ ጌታ የፍርድ ወንበር እየተጓዝኩ እያለሁ በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ በከፍተኛ ማዕረግ ላይ በተቀመጡ ሰዎች ፊት እያለፍኩ መሄድ ጀመርኩ። እኔ ተሰናክዬ ወድቄባቸው በነበሩ ተመሳሳይ ስህተቶች ተሰናክለው ወድቀው ከነበሩት ጋር በመገናኘቴ በጣም ብዙ መጋረጃዎች ተወገዱልኝ። ከዚያም በኋላ ችግሮችን ሁሉ አሸንፈው ካለፉ ጥቂት ሰዎች ጋር ደግሞ መገናኘት ጀመርኩ። በመጀመሪያም ጌታንና እርስ በርሳቸውም በታማኝነት እስከ መጨረሻ አገልግለው ከነበሩ ባልና ሚስት ጋር ተገናኘሁ። እነዚህ ሰዎች በዚህ ቦታ ያላቸው ክብር በቃላት ሊገለጽ የማይችል ሲሆን ያገኙት ድልም በሕይወት መንገድ መጽናትና ጌታን በታማኝነት ማገልገል እንደሚቻል አበረታታኝ። ተሰናክለው የወደቁት በብዙ የተለያዩ መንገዶች ተሰናክለው

ሲወድቁ፣ ስኬታማ የሆኑትም እንዲሁ በተመሳሳይ መንገድ የመጀመሪያና ትልቁ ትዕዛዝ የሆነውን ጌታን ስለ መውደድ ከመስጠት ፈቀቅ ያላሉ ነበሩ። በዚህም ሰዎችን በተለይም መንፈሳዊ ሰዎችን ሳይሆን እርሱን በማገልገላቸው ፍጻሜያቸው ያማረ ሆነ። እነዚህ ሰዎች በጉን ያመለኩና እርሱ በሄደበት ሁሉ ፍለጋውን የተከተሉ ነበሩ።

ገና ግማሽ ያህል ርቀት ወደ ዙፋኑ ሳልጓዝ በቃላት ሊገለጽ የማይችል ክብር የነበረው የመጀመሪያው ማዕረግ፤ አሁን እያለፍኩት ካለሁት ክብር ጋር ሲነጻጸር የውጪኛውን ጨለማ ነበር የሚመስለው። በምድር ላይ አለ የተባለለት እጅግ የላቀ ውበት በዚህ በመንግስተ ሰማይ ውስጥ ለመገኘት ብቃት የለውም። እናም ይህ ክፍል በቃላት ሊገለጹ የማይቻሉ እውነቶች መግቢያ በር መሆኑ ተነገረኝ።

እዚህ ስፍራ ላይ ጊዜን የምንለካበት መለኪያ ስለሌለ ወደ ዙፋኑ የማደርገው ጉዞ ቀናትን፣ ወራትን ወይም ዓመታትን እንኳን ይወስድብኝ ይሆናል። እናም በዚህ የተገኘው ሰው ሁሉ በማንነቴ ወይም በሰራሁት ሥራ ሳይሆን ነገር ግን በፍጻሜው ዘመን ላይ የተጋደልኩ የእምነት አርበኛ በመሆኔ አክብሮትን ሰጠኝ። ይህም የእግዚአብሔር ክብር፤ በዚህ በመጨረሻው ጦርነት በኩል ከዘላለም ለተፈጠረው ወይም ገና ለሚፈጠረው ለየትኛውም ኃይልና ሥልጣን ሁሉ ምስክር ይሆን ዘንድ በዚህ መንገድ እንዲገለጥ ነበር። ይህ ጦርነት በሚካሄድበት ወቅት የመስቀሉ ክብር ይገለጣል፣ የእግዚአብሔርም ጥበብ በልዩ መንገድ ይታወቃል። በዚህ ጦርነት ውስጥ ተካፋይ መሆንም እጅግ ታላቅ ከሆኑ ክብሮች አንዱን ማግኘት ነው የሚሆነው።

በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት በደረስኩ ጊዜም በከፍተኛ ማዕረግ ላይ ተቀምጠው የነበሩት በሙሉ፤ የጌታ ዙፋን አካል በሆኑ ዙፋናት ላይ ተቀምጠው ነበር። ከእነዚህ ታናናሽ ዙፋናት አንዱ በምድር ላይ ለብዙ ዘመናት ከኖሩ ከየትኞቹም ምድራዊ ዙፋናት የሚበልጥ ክብር ያለው ነበር። በእነዚህ ዙፋናት ላይ ከተቀመጡት ሰዎች አንዳንዶቹ በምድር ህይወታቸው የከተማ አስተዳዳሪዎች ሌሎቹ በመንግስተ ሰማያት ጉዳዮች፣ ሌሎች ደግሞ ክዋክብትን በመሳሰሉ ፍጥረታዊ አካላት ጉዳዮች ላይ ገዢዎች ነበሩ። ይሁን እንጂ በከተሞች ላይ ሥልጣን ተሰጥቷቸው የነበሩት ሰዎች በከዋክብቱ ላይ ሥልጣን ተሰጥቷቸው ከነበሩት በላይ ከፍተኛ ክብር የተሰጣቸው እንደነበሩ ግልጽ ነው። ይህም ሰዎች የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ በመሆናቸውና ጌታም ሰዎችን ዘላለማዊ ማደሪያው አድርጎ ስለ መረጣቸው የአንድ ልጅ ዕሴት ወይም ዋጋ ከከዋክብት ክምችት ዋጋ የሚበልጥ ስለሆነ ነው። ምድርና መላዋ በእርሱ ክብር መገኘት ፊት እንደ ምድር ትቢያ ምንም የማትረባ ስትመስል፤



የፍጥረት ሁሉ ትኩረትም አለቅጥ በእርሷ ከፍተኛ ክብር ላይ ያረፈ ነበር የሚመስለው።

አሁን በዙፋኑ ፊት ስቆም ከምድር ትቢያ ያነስሁ ያህል ቢሰማኝም መንፈስ ቅዱስ ግን ከዚህ በፊት በፍጹም ተለማምጄው በማላውቀው ታላቅ ሁኔታ በላዬ ነበረ። መቆም የቻልኩት በእርሱ ኃይል ብቻ ሲሆን የአጽናኝነት አገልግሎቱን እያከናወነ መሆኑን ከልብ ወደ መረዳት የመጣሁትም በዚህ ስፍራ ላይ ነበር። በአብዛኛው ጉዞዬ አብሮኝ ስለ መሆኑ ባላስተውልም እንኳን አሁን ግን እየመራኝ ያለው እርሱ ነው።

ጌታም እስቤ ከማውቀው በላይ ቸር፤ ይበልጥ ደግሞ አስፈሪ ሁለቱንም ነበር። ተራራው ላይ ሳለሁ በእርሱ ውስጥ የረዳኝን ጥበብን አየሁት። ብዙጊዜ በእርሱ አማካይነት ያናግረኝ ስለነበር እርሱን በምድር ላይ የነበሩ ጓደኞቼን የማውቃቸውን ያህል እንደማውቀው ሆኖ ተሰማኝ። ብዙጊዜ ግን ችላ ብዬው እንደ ነበር ተገነዘብኩ። አንበሳና የበግ ጠቦት፣ ሙሽራና እረኛ ሁለቱንም ሆኖ ቢታየኝም ከሁሉም በላይ ይታየኝ የነበረው ግን ቅን ፈራጅነቱ ነበር።

አጽናኙ በአስደናቂ መገኘቱ ከእኔ ጋር ስለነበር በጣም ተጽናናሁ። ጌታ ከእኔ የሚፈልግብኝ እውነትን እንዳውቅ ብቻ ስለነበር በምንም ዓይነት መንገድ ምቾቴ እንዲጓደል እንደማይፈልግ ግልጽ ነበር። በእርሱ ፊት መቆም ምን ያህል አስደሳች፣ አስፈሪም መሆኑን የሰው ቋንቋ ሊገልጸው አይችልም። ፍርዱ መልካምም ይሁን ክፉ ትክክል እንደሆነና ፈራጁ ዳኛዬንም ሳምነው እንደምችል ስለተረዳሁ ነጥቡን ማለፍ በሚገባኝ ስፍራ ላይ አለፍኩ።

አንድ ነጥብ ላይ ስደርስ ግን ጌታ በዙሪያው ወደነበሩት የከዋክብቱ ክምችት ዙፋናት ተመለከተ። ብዙዎቹ ዙፋናት ሰው የተቀመጠባቸው ቢሆኑም አብዛኞቹ ግን ባዷቸውን ነበሩ። ከዚያም *"እነዚህ ዙፋናት አባቴና እኔ ዓለም ሳይፈጠር በፊት ለእነርሱ ያዘጋጀናቸው፤ በየትኛውም ትውልድ መካከል በታማኝነት ላገለገሉኝ ድል ነሺዎች የሚሰጡ ናቸው። አንተስ በዚህ ዙፋን ለመቀመጥ የተገባህ ነህን?"* አለኝ።

በዚህን ጊዜ አንድ ወቅት ላይ አንድ ጓደኛዬ "ሁሉን አዋቂው አምላክ ጥያቄ የሚጠይቅህ እኮ እርሱ የማያውቀው ነገር ኖሮ ከአንተ ለማወቅ ፈልጎ አይደለም" ሲል የተናገረው ቃል ትዝ አለኝ። ወደ ዙፋናቱ ስመለከት በዙፋናቱ ላይ የተቀመጡባቸውን ሰዎች አየሁ። አንዳንዶቹም ታላላቅ የእምነት ጀግኖች እንደሆኑ መገንዘብ ቻልኩ። ይሁንና ከተቀመጡት መካከል አብዛኞቹ ግን በምድር ላይ በደንብ የሚታወቁ ሰዎች እንኳን እንዳልነበሩ ተረዳሁ።

እነዚህ ሰዎች የምድር ሕይወታቸውን ከጨለማው ኃይላት ጋር ተናንቀው ያጠናቀቁ እንደነበሩ የማውቃቸው የወንጌል መልዕክተኞች (ሚሲዮናውያን) ነበሩ። በምድር ላይ መታሰቢያ ሃውልት እንዲቆምላቸው ፈጽሞ ግድ ያልነበራቸው፤ ነገር ግን በእርሱ ብቻ መታሰብን የፈለጉ ነበሩ። አንዳንዶቹ ደግሞ ባለጠጎች ወይም ለተሰጣቸው ኃላፊነት ታማኝ የነበሩ ገዢዎች የነበሩ ሲሆኑ እነርሱን በዚያ ማየቴም ትንሽ አስደነገጠኝ። ይሁን እንጂ ከሌላ ከየትኛውም የህዝብ ወገን ይልቅ አብዛኞቹን ዙፋናት የያዙት ግን ታማኝ የነበሩ እናቶችና ሴት የጸሎት አርበኞች ይመስላሉ።

እኔ ከእነዚህ ጋር አብሬ መቀመጥ የተገባኝ ሰው አልነበርኩም። ጌታ በዚህ ቦታ ላይ ለመቀመጥ የተገባኝ ሰው መሆኔን ለጠየቀኝ ጥያቄ ራሴን የተገባው ሰው አድርጌ ከቆጠርኩ "አዎን" ብዬ መልስ መስጠት የምችልበት መንገድ አልነበረኝም። በሰማይም ሆነ በምድር እጅግ ለላቀው ሽልማት እንድሮጥ ዕድሉ ተሰጥቶኝ እንደነበር፤ ሆኖም ግን እንዳልተሳካልኝ አውቄዋለሁ። ተስፋ ብቆርጥም አሁንም ግን አንድ ተስፋ አለኝ። ምንም እንኳን አብዛኛው የምድር ሕይወቴ በውድቀት የተሞላ ቢሆንም በዚህ ስፍራ የተገኘሁት በምድር ላይ የነበረኝን ሕይወት ከማጠናቀቄ በፊት እንደሆነ ግን አውቄያለሁ። ጌታም የተገባኝ ሰው እንዳልሆንኩ ስናገር ስለሰማኝ እንዲህ ሲል ጠየቀኝ።

*"ይሁንና ይህንን መቀመጫ ግን ትፈልገዋለህ?"*

እኔም "አዎን! በሙሉ ልቤ ነው የምፈልገው" ስል መለስኩለት።

ከዚያም ወደ ክዋክብቱ ክምችት ተመለከተና እንዲህ አለኝ። *"እነዚያ ባዶ መቀመጫዎች በየትኛውም ትውልድ ሊሞሉ የሚችሉ ናቸው። ለሚፈልጉ ሁሉ በዚህ እንዲቀመጡ የጥሪ ግብዣዬን አቅርቤአለሁ። አሁን ግን ስላልተያዙ ባዶ ናቸው። አሁን የፍጻሜው ጦርነት ተቃርቧል። ፊተኛ የሆኑ ብዙዎች ኋለኞች ይሆናሉ። እነዚህ መቀመጫዎች ጦርነቱ ከመጠናቀቁ በፊት የሚያዙ ሲሆኑ የሚቀመጡባቸውም ሰዎች በሁለት ነገሮች ተለይተው ይታወቃሉ። አንደኛው የትህትናን መጎናጸፊያ በመደረባቸው፤ ሁለተኛው ደግሞ የእኔን መልክ በመያዛቸው። አሁን አንተ መጎናጸፊያው አለህ። በጦርነቱ ውስጥ መጎናጸፊያውን ጠብቀህ መያዝ ከቻልክና ካልጣልከው ከዚያ ስትመለስ የእኔ መልክ ይኖርሃል። ከዚያም ከእነዚህ ጋር ለመቀመጥ የተገባህ ስለማደርግህ፤ የተገባህ ሰው ትሆናለህ። ኃይልና ሥልጣን ሁሉ ስለተሰጠኝ በሙሉ ኃይል ማስተዳደር የምችለው እኔ ብቻ ነኝ። በዚህ በእኔ ሥልጣን ሙሉ በሙሉ በእኔ ለመኖር የምትተማመነው ወደ እኔ ስትመጣ ብቻ ነው። አሁን እየተዘዋወርክ ቤቴን ተመልከት"።*



ይህን ጊዜ ወደ ኋላዬ ዘወር ብዬ የመጣሁበትን አቅጣጫ ተመለከትኩ። በዙፋኑ ፊት ሆኜ ክፍሉን በሙሉ መቃኘት ችዬ ስለነበር የክፍሉ የክብር ግርማ ከምንም ነገር ጋር የሚነጻጸር አይደለም። ይህን ክፍል በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ባለ ማዕረጎቹ ሞልተውታል። ዝቅተኛው ማዕረግ ላይ የሚገኙት እያንዳንዱ ግለሰብ ከየትኛውም ሠራዊት በበለጠ አስፈሪና የሚበልጥ ኃይል ያላቸው ነበሩ። ለእኔ ይህን የመሰለውን የክብር ትዕይንት መመልከት ከአቅሜ በላይ ሆነብኝ። ይሁንና ማየት የቻልኩት ግን የታላቁን ክፍል በጣም አነስተኛ ውን አካል ብቻ ነበር።

ከዚያም ወደ ኋላዬ ዘወር ብዬ ጌታን ስመለከት ዕንባ ከዓይኖቹ ሲፈስ በማየቴ ደነገጥኩ። ከራሱ በስተቀር እዚህ ክፍል ውስጥ ካለነው ሰዎች ዓይን ላይ እንባችንን አብሶልን ነበር። በጉንጮቹ ላይ ዱብ፣ ዱብ እያለ የወረደውን ዕንባውን በእጆቹ ይዞ *"ይህ ጽዋዬ ነው። ከእኔ ጋር ትጠጣዋለህን?"* አለኝ።

ጌታ ያለ ማቋረጥ ዓይን ዓይኔን ሲመለከተኝ ውስጤን ታላቅ ፍቅሩ ይሰማው ጀመር። እኔም "አልጠጣም" ማለት የምችልበት ምንም ምክንያት አልቀበረኝም። ምንም እንኳን ጥሩ ሰው ባልሆንም አሁንም እንኳን ይወደኝ ነበር። ይህ የማይገባኝ ሰው የነበርኩ እንደ መሆኔ ወደ እርሱ እንድቀርብ ስለፈለገ ግን እንዲህ አለኝ።

*"እዚህ ያሉትን እነዚህን ሁሉ አሁን አንተ ልትረዳው በማትችለው ፍቅር እወዳቸዋለሁ። ያልመጡትን፣ ግን ገና ሊመጡ ያሉትንም እወዳቸዋለሁ። እኔ የመጣሁት የጠፋውን ለማዳን ነው። የጠፋውን አንዱን ፍለጋ፤ ዘጠና ዘጠኙን ትቻቸው ሄጃለሁ። እረኞቼ አሁንም ድረስ ዘጠና ዘጠኙን ለመጠበቅ ሲሉ የጠፋውን አንዱን ከመፈለግ አይቦዝኑም። አንተስ የጠፉትን ለማዳን በመሄድ የልቤን ናፍቆት ልትጋራኝ ትወዳለህን? እነዚህ ዙፋናትና በዚህ አዳራሽ ውስጥ የሚገኙት ሌሎችም መቀመጫዎች እያንዳንዳቸው በሰው ይሞሉ ዘንድ ድርሻህን ትወጣለህን? መንግስተ ሰማይን፣ እኔንና አባቴን ደስ ለማሰኘት ይህን ፍለጋ ትከተላለህን? ይህ ፍርድ ለገዛ ቤቱ ሲሆን ቤቴም ገና በሰው አልሞላም። እስኪሞላ ድረስ ደግሞ የመጨረሻው ትንቅንቅ አያበቃም። ያንጊዜ ብቻ ነው ምድርን የምቤዠውና ክፉውን ከፍጥረቴ ላይ የማስወግደው። ከዚህ ከእኔ ጽዋ ከጠጣህ እኔ የጠፉትን በምወድበት ፍቅር አንተም ትወዳቸዋለህ"።*

ከዚያም ይህን የመሰለ ክብር ባለበት ክፍል ውስጥ መገኘት የማይገባው የሚመስል አንድ በጣም መናኛ ጽዋን አንስቶ እንባውን ጨመረበትና እንድጠጣው ሰጠኝ። ስቀምሰው በጣም ይመር ነበር። እንዲህ ያለ መራራ ነገር ከዚህ በፊት በፍጹም ቀምሼ አላውቅም። ይህን መራራ ዕንባ ሙሉ በሙሉ

ወይም አብዝቼ ልጠጣው ስላልቻልኩም የቻልኩትን ያህል ለመጠጣት ተገደድኩ። በመጨረሻም ጌታ ዕንባዬ እንደ ወንዝ እስኪፈስ ድረስ እስከማለቅስ በትዕግስት ጠበቀኝ። ከዚያም ለጠፋት፣ ይበልጥ ደግሞ ለጌታ አለቀስኩ።

ከዚህ በኋላ እንዲህ ያለውን ታላቅ ስቃይ መቀበል ባለመቻሌ ተስፋ ቆርጬ ወደ እርሱ ተመለከትኩ። ከዚያም ይሰማኝ ከነበረው ፍቅሩ ጋር ሰላሙን በውስጤ ሲሞላው ይሰማኝ ጀመር። ከዚህ በፊት እንዲህ ያለ ድንቅ ስሜት በፍጹም ተሰምቶኝ አያውቅም። ይሄ ለዘላለም ሊፈልቅ የሚችለው የሕይወት ውሃ እንደሆነ አወቅሁ። በመቀጠልም በውስጤ ይፈስ የነበረው ውሃ በእሳት ተያይዞ ሲነድና የክብሩን ልዕልና ማወጅ መጀመር የማልችል ከሆነ ይህ እሳት እኔን እንደሚበላኝ ይሰማኝ ጀመር። ወንጌል ለመስበክ እንዲህ ያለ መነሳሳት በፍጹም ተሰምቶኝ አያውቅም።

በዚያ ስፍራ ላይ ከእርሱ በቀር ሌሎች እንዳሉ በመርሳትም “ጌታ ሆይ! አሁን ይህ የፍርድ ዙፋን የጸጋም ዙፋን መሆኑን አውቄያለሁና እንዳገለግልህና ሥራዬንም ስርቼ እንዳጠናቅቅ ከምንም ነገር በላይ ጸጋህን እንድትሰጠኝ እጠይቅሃለሁ፣ እለምንሃለሁም። እንግዲህ እንድወድህና ሕይወቴንም ካመሰቃቀሉብኝ ከራስ ወዳድነትና አሳች ከሆኑ ሌሎች ስሜቶች ነጻ መውጣት እችል ዘንድ ጸጋህን እንድትሰጠኝ እጠይቃለሁ። ከራሴና ከክፉ ልቤ እድንም ዘንድ አሁን በልቤ ውስጥ ያለ ማቋረጥ እየፈሰሰ እንደሆነ ለተሰማኝ ፍቅር አንተን እጣራለሁ፣ ልብህን፣ ፍቅርህን እንድትሰጠኝም እጠይቅሃለሁ። ስለ ሃጢአቴ እንዲወቅሰኝና ስለ እውነተኛው አንተነትህ እመሰክርም ዘንድ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ እንድትሰጠኝ እጠይቅሃለሁ። የዚህን ፍርድ እውነታ ለመመስከር ጸጋህ በእኔ ላይ እንዲያርፍ እፈልጋለሁ። እነዚህ ባዶ ዙፋናት በተጠሩ ሰዎች እንዲሞሉ፣ በሕይወት መንገድ እንዲጓዙ የሚረዳቸውን የሕይወትንም ቃል ለመስጠትና ይሰሩት ዘንድ የተጠሩለትን ሥራ መስራት እንዲችሉ የሚረዳቸውን እምነት ለማካፈል ጸጋህን እፈልጋለሁና ጌታ ሆይ! ይህንን ጸጋህን እንድትሰጠኝ እለምንሃለሁ” ስል ጮኽኩኝ።

በዚህ ጊዜ ማየት እስከምችለው ርቀት ድረስ ያሉትና በዙፋናቱ ላይ ተቀምጠው የነበሩት በሙሉ ተነስተው ቆሙ። ከዚያም ጌታ ከዚህ በፊት አይቼ በማላውቀው ሁኔታ ዓይኖቹ እንደ እሳት ነበልባል ነደዱ።

*“ጸጋን እንድሰጥህ ለምነኸኛል። ይህን ጥያቄ ደግሞ በፍጹም ቸል የምለው አይደለም። አሁን ወደ መጣህበት መመለስ ይኖርብሃል፣ መንፈስ ቅዱስም ከአንተ ጋር ይሆናል። እዚህ ደግነቴንና ቁጡነቴን ሁለቱንም ቀምሰሃቸዋል። በሕይወት መንገድ የምትቆይ ከሆንክ ሁለቱንም ማስታወስ*



*አለብህ። እውነተኛው የእግዚአብሔር ፍቅር የእግዚአብሔርንም ፍርድ አካትቶ የያዘ ነው። ደግነቴንና ቁጡነቴን ሁለቱንም ማወቅ ይኖርብሃል። አለበለዚያ ትስታለህ። እዚህ የተሰጠህ ጸጋ ሁለቱንም ማወቅ ነው። በዚህ ከወንድሞችህ ጋር አድርገኸው የነበረው ውይይት የእኔ ጸጋ ነውና እንዳትረሳው፤ አስታውሰው”* አለኝ።

ከዚያም በእጁ በያዘው ሰይፍ መጀመሪያ ወደ ልቤ፣ ቀጠለናም ወደ አፌና ወደ እጆቼ አቅጣጫ ጠቆመ። ይህን በሚያደርግበት ጊዜ ከሰይፉ ውስጥ እሳት እየወጣ ያቃጥለኝ ጀመር። በጣም የሚሰማ ህመም ነበረው።

*“ይሄ ጸጋ ነው። ተመልሰህ ወደ ምድር ስትሄድ እዚህ ስላየኸው ነገር በሙሉ ስበክ፣ ጻፍም። የነገርኩህንም ነገር በሙሉ ለወንድሞቼ ንገርልኝ። አንተ ለዚህ ሰዓት ከተዘጋጁት ከብዙዎቹ አንዱ ነህና ሄደህ ለፍጻሜው ጦርነት የተዘጋጁትን የጦር አበጋዞቼን ሰብስብልኝ። ለድሆች፣ ለተጨቆኑ፣ ለመበለቶችና ወላጆቻቸውን በሞት ላጡ ልጆች ተሟገትላቸው። የእኔ ተዋጊዎች ተልዕኮ ይሄ ሲሆን የምታገኛቸውም እንዲህ ባለ ቦታ ነው። ለእኔ በሰማይ ካሉት ከዋክብት ይልቅ ልጆቼ ይበልጡብኛልና በጎቼን መግባቸው፣ ትናንሾቼንም ነቅተህ ጠብቅልኝ። በሕይወትም ይኖሩ ዘንድ የእግዚአብሔርን ቃል መግባቸው። ወደ ጦርነቱ ገስግስ፣ ወደ ፊት ግፋ እንጂ ወደ ኋላ እንዳታፈገፍግ። በቶ፦ እመጣለሁና ፈጥነህ ሂድ። ታዘዘኝ፣ የመምጫዬንም ቀን አፍጥነው”* አለኝ።

ከዚያም የመላዕክቱ ሠራዊት መጡና ከዙፋኑ ፊት አጆበው ወሰዱኝ። መሪያቸውም አጠገቤ ሆኖ እየተራመደ እንዲህ ይለኝ ጀመር።

“የፍጻሜው ጦርነት እስከሚጠናቀቅ ድረስ ጌታ ቆሞ ይጠብቃል እንጂ ተመልሶ ዙፋኑ ላይ አይቀመጥም!። ጠላቶቹ የእግሩ መረገጫ እስኪሆኑ ድረስ ተቀምጦ ነበር። አሁን ግን ጊዜው ደርሷል። ተላልፎ ከተሰጠባት ከዚያች ምሽት አንስቶ በተጠንቀቅ የቆሙት የመላዕክቱ ሌጊዎኖች አሁን በምድር ላይ ተለቀዋል፣ የገሃነም መንጋዎቹም ተለቀዋል። ፍጥረት በሙሉ በናፍቆት የሚጠባበቀው ጊዜ ይህ ነው። ታላቁ የእግዚአብሔር ምስጢር በቅርቡ ይደመደማል። እኛም አሁን ከአንተና ከወንድሞችህ ጋር ሆነን እስከ መጨረሻው አብረን እንዋጋለን”።

# ክፍል አምስት
# ድል ነሺዎቹ



## ክፍል አምስት

## ድል ነሺዎቹ

ከፍርድ ወንበሩ ፊት ወጥቼ ጉዞዬን እንደ ቀጠልኩ አጋጥመውኝ ስለነበሩት አስፈሪና አስደናቂ ተሞክሮዎች ስለ ሁለቱም ማሰላሰል ጀመርኩ:: ተሞክሮዎቹ ልብን የሚመልሱ እንዲሁም የሚገዳደሩ ቢሆኑም ከዚህ በፊት ተሰምቶኝ የማያውቅ ፍጹም ሰላምና ደህንነት ግን ተሰማኝ:: በመጀመሪያ አንዲቷን የልብ ሃሳብ እንኳን መደበቅ በማይቻልበት በብዙዎች ፊት እርቃንን ሆኖ መቆም ቀላል አልነበረም:: ይሁንና ነፍሴን ማንጻት እንደነበር በማወቅ ነገሩን ዘና ብዬ በመቀበሌ ግን ነጻ መውጣት ሆነልኝ:: ምንም የሚደብቀው ነገር አለመኖሩ ከባዱን የእግር ብረት ሰንሰለት እስራት አውልቆ የመጣል ያህል ስለነበር፤ ከዚህ በፊት ተንፍሼ በማላውቀው ሁኔታ መተንፈስ መቻሌ ይሰማኝ ጀመር::

ሁኔታው የበለጠ እየተመቸኝ ሲመጣ አዕምሮዬ የማሰብ አቅሙ ይበልጥ ያደገ ይመስልም ነበር:: ከዚያም የሰው ቋንቋ ሊገልጸው የማይችለው የንግግር ግንኙነት መስማት ጀመርኩ:: በዚህ ጊዜ ሐዋሪያው ጳውሉስ በቃላት መግለጽ የማይችልን ድምጽ ስለሰማበት ስለ ሦስተኛው ሰማይ ጉብኙቱ የተናገረውን ቃል አሰብኩ:: መንፈሳዊ ግንኙነት የትኛውንም ዓይነት የሰው ልጅ ግንኙነትን የሚያስንቅና የሰው ቃላት ሊገልጹት ከሚችሉት በላይ ፍጹም ጥልቅና ትርጉም ያለው ነው:: ይህ ግንኙነት ከንጽህናው የተነሳ አለመግባባት ሊከሰትበት የማይችልበት በጣም ንጹህ የሆነ የልብና የአዕምሮ ግንኙነት ነው::

ከዚያም በዚያ ክፍል ውስጥ አንድ ሰው አየሁ:: ባየሁት ጊዜም ልክ፤ እርሱ በልቤ አስብ የነበረውን ሃሳብ መረዳት እንደቻለው እኔም በልቡ ምን እያሰበ እንዳለ መረዳት ጀመርኩ:: ጌታንም ሳየው በተመሳሳይ መንገድ የእርሱንም ሃሳብ መረዳት ጀመርኩ:: ከዚያም ንግግር መለዋወጥ ስንጀምር የምንጠቀማቸው የእያንዳንዱ ቃል ትርጉም የትኛውም መዝገበ-ቃላት የማያውቀው ጥልቅ ትርጉም ያለው ነበረ:: የአዕምሮዬ የማሰብ ችሎታ በብዙ

እጥፍ ይጨምር ዘንድ በጣም ነጻ ነበር። ይሄ ደግሞ ቀደም ሲል ከነበረው ከማንኛውም ሰው የማሰብ ኃይል ልምምድ ያለፈ ነበር።

ከጌታ ጋር በመገናኘቴ ደስ የተሰኘሁትን ያህል፤ እርሱም ከእኔ ጋር በዚህ መንገድ መገናኘት በመቻሉ መደሰቱ ግልጽ ነበር። የእርሱን የእግዚአብሔር ቃልነት ትርጉም ምን ማለት እንደነበር ከዚህ በፊት እንዲህ በጥልቀት በፍጹም አልተረዳሁትም ነበር። ኢየሱስ እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ጋር የሚገናኝበት ልጁ ነው። ቃሎቹ መንፈስና ሕይወት በመሆናቸው ትርጉማቸውና ኃይላቸው አሁን እኛ ሰዎች ከምንሰጠው ትርጉም በእጅጉ የላቀ ነው። በመንፈስ ግንኙነት ውስጥ የሰው ቃል በጣም ጥልቀት አልባና ጥራዝ ነጠቆች ናቸው። እግዚአብሔር ከሰው ቃላት ይልቅ እጅግ የሚያስንቅ ግንኙነት ማድረግ እንድንችል አድርጎ ፈጥሮን ነበር። ይሁንና ከሰው ልጅና ከባቢሎን ግንብ ድንገተኛ ውድቀት የተነሳ ግን ይህን ሥልጣናችንን አጣነው። ይህንን ሥልጣን መልሰን እስካላገኘነው ጊዜ ድረስ ደግሞ ቀድሞ ለተፈጥረንለት ዓላማ መሆን አንችልም። እናም ይህንን ችሎታችንን መልሰን ማግኘት የምንችለው በእርሱ መገኘት ውስጥ አርነት ስንወጣ ብቻ ነው።

አዳም መተላለፉ ከእግዚአብሔር እንዲሸሽግ ሲያደርገው፤ የሰው ልጅ እንዲሆን የተፈጠረለት እጅግ አስፈሪው የጥፋት ጅማሬ እንደዚሁም በአዕምሮው የማሰብና ከመንፈሳዊ ችሎታዎቹ ኃይል ከፉኛ መውረዱን መረዳት ጀመርኩ። እነዚህን ችሎታዎች መልሰን ማግኘት የምንችለው "ከተሸሸግንበት" ስንወጣና ራሳችንን ለእግዚአብሔርና ለሌላው ሰው ከልባችን ግልጽ ስናደርግ ብቻ ነው። የጌታን መልክ ወደ መምሰል የምንለወጠው የእርሱን ክብር "በማይከደን ፊት" ገልጠን ስናይ ሲሆን፤ ክብሩን እንዳናይ የጋረዱን መጋረጃዎች የመጡት ደግሞ በእኛ መሸሸግ ምክንያት ነው።

አዳም ከበደለ በኋላ ጌታ "ወዴት ነህ?" ብሎ የጠየቀው ጥያቄ ለሰው ልጅ የቀረበ የመጀመሪያው ጥያቄ እንደነበረ ሁሉ እኛም ሙሉ በሙሉ ወደ እርሱ የምንመለስ ከሆነ መልስ ልንሰጥበት የሚገባን የመጀመሪያው ነገር ይህ ነው። እርግጥ ነው ጌታ አዳም የት እንዳለ ሳያውቅ ቀርቶ አይደለም ወዴት ነህ? ያለው። ጥያቄው ግን ለአዳም ከማሰብ የቀረበ ነበር። ያ ጥያቄ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ፍለጋ በወጣ ጊዜ የጠየቀው የመጀመሪያ ጥያቄ



ነው። የመቤዠት ታሪክ እግዚአብሔር ሰውን ለመፈለግ የሰራው እንጂ ሰው እግዚአብሔርን የፈለገበት ታሪክ አይደለም። ከእግዚአብሔር ጋር ካለን ግንኙነት አንጻር ምን ውስጥ እንዳለን በማወቅ ለዚህ ጥያቄ የተሟላ ምላሽ መስጠት ስንችል ወደ እርሱ ሙሉ በሙሉ መመለስ ይሆንልናል። የዚህን ጥያቄ መልሱን ማወቅ የምንችለው በእርሱ መገኘት ውስጥ ስንሆን ብቻ ነው።

በጌታ የፍርድ ዙፋን ፊት በነበርኩበት ጊዜ አጋጥሞኝ የነበረው ተሞክሮ ሙሉ ፍሬ ነገሩ ይሄ ነበረ። ጌታ ስለ እኔ መታወቅ ያለበትን ነገር በሙሉ ያውቃል። ይህንን ያደረገው ደግሞ እኔ የት ቦታ መሆኔን አውቅ ዘንድና ከተደበቅኩበት የጨለማ ስፍራ ወደ ብርሃን እንድወጣ ለማድረግ ነው።

ጌታ ከህዝቡ ጋር አንድ መሆንን ምን ያህል እንደሚሻ መረዳትም ጀመርኩ። ከእርሱ ጋር ባለኝ ኅብረትም በፍርዱ አማካይነት መልካምም ይሁን ክፉ ነገር የማየውን ያህል እንድመለከት እየሞከረ አልነበረም። ጌታ እኔ እርሱን ከምፈልገው በላይ እርሱ እኔን እየፈለገኝ ነበር። ፍርዶቹ እኔን አርነት እንዳወጡኝ፣ በዓለም ላይ የሚፈርደው ፍርድም ዓለምን ነጻ ያወጣታል።

የእግዚአብሔር የፍርድ ቀን ሲመጣ አዳምን ከተሸሸገበት ቦታ ነጻ የሚያወጣበት የመጨረሻው ነጻ መውጣት ይሆናል። ይሄ ለአዳም የመጨረሻ ነጻ መውጣት ሲሆን ከአዳም መተላለፍ የተነሳም በባርነት ስር ወድቆ የነበረው ፍጥረትም የመጨረሻ ነጻ መውጣት ይጀምራል። በዓለም ያለው ጨለማ ትልቁ ፍላጎቱ፤ አዳም ከወደቀ በኋላ በጀመረው መሸሸግ ውስጥ ለዘለቄታው እንዲቆይ ማድረግ ነበር። "በብርሃን መመላለስ" የተወሰኑ እውነቶችን ከማወቅና ከመታዘዝ ያለፈ፣ እውነት መሆንና ከመሸሸግም ነጻ የመሆን ታላቅ ፍላጎትም ነው።

"በብርሃን መመላለስ" ማለት ከዚህ በኋላ ከእግዚአብሔርም ሆነ ከማንም ሰው አለመሸሸግ ማለት ነው። አዳምና ሔዋን ከውድቀት በፊት የነበራቸው ራቁትነት አካላዊ ሳይሆን መንፈሳዊ ሲሆን ይህን ዓይነቱን ነጻነት እንደገና የምናውቀው መዳናችን ሲፈጸም ነው። በእውነቱ ለሌሎች ሰዎች ግልጽ መሆናችን የገዛ ልባችንንና አዕምሯችንን አሁን መኖሩን ለማናውቀው ዓለም እንኳን ክፍት ያደርገዋል። ሰይጣን በአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ (New Age

Movement) አማካይነት ለመስራት እየጣረ ያለው የሃሰት ሥራው ይሄ ነው::

በጉዞዬ ላይ የተማርኳቸውን ነገሮች በሙሉ በአዕምሮዬ እያወጣሁና እያወረድኩ እያለሁ ድንገት ጌታ እንደገና በጥበብ መልክ በአጠገቤ ተገለጠ:: በዚህ ጊዜ ከዚህ በፊት አይቼው በማላውቀውና በፍርድ ወንበር ላይ ተቀምጦ ሳለ ካየሁበት ክብር እጅግ በሚበልጥ ክብር ሲገለጥ ደነገጥኩ፣ ደስም አለኝ:: ሁለቱም ስሜት ተሰማኝ::

የዚህን ጊዜ “ጌታ ሆይ ከእኔ ጋር እንዲሁ ተመልሰህ ትሄዳለህን?” ስል ጠየቅሁት::

እርሱም *“እንዲሁ ሁልጊዜ ከአንተ ጋር እሆናለሁ:: ይሁን እንጂ ለአንተ አሁን ከምታየኝ ከዚህም የበለጠ መሆንን እፈልጋለሁ:: ደግነቴንና ቁጡነቴን እዚህ አይተኸዋል:: ይሁንና ጻድቅ ፈራጅ ስለ መሆኔ ግን አሁንም ሙሉ በሙሉ አላወቅኸኝም”* አለኝ::

*ይህን ያህል ጊዜ ሁሉ አብሬው በፍርድ ወንበሩ ፊት ስቆይና ተምሬው* የነበረው ነገር በሙሉ ስለ ፍርዱ እንደ ነበር ሲሰማኝ ደነገጥኩ:: ይህ እውነት ወደ ውስጤ ዘልቆ ይገባ ዘንድም ንግግሩን እንደገና እንዲህ ሲል ቀጠለ::

*“እውነትን ስታውቅ የሚመጣ ነጻነት አለ:: ይሁንና የመገኘቴ ነጻነት እውነትን ከማወቅ ይበልጣልና እኔ ነጻ ያወጣሁት ሰው፤ እርሱ ነጻ ሰው ነው:: በመገኘቴ ውስጥ ያለውን አርነት ተለማምደኸዋል:: ይሁንና ስለ ፍርዶቼ ግን ልታውቀው የሚገባህ ገና ብዙ የሚበልጥ ነገር አለ:: እኔ በምፈርድበት ጊዜ ጽድቅን ማምጣት እንጂ ማንንም ልኮንን ወይም ላጸድቅ አልፈልግም:: ጽድቅ የሚገኘው ከእኔ ጋር ኅብረት በማድረግ ብቻ ነው:: የጽድቅ ፍርድም ሰዎች ከእኔ ጋር ኅብረት እንዲያደርጉ እነርሱን ማምጣት ነው::*

*“አሁን ቤተ ክርስቲያኔ የሚፈርዱ ፈራጆች ስለሌሏት ሃፍረትን ተከናንባለች:: ፈራጆች የሌሏትም እኔ ፈራጅ መሆኔን ባለማወቋ ነው:: ስለዚህ አሁን ለህዝቤ ፍርዴን የሚያውቁ ፈራጆችን አስነሳለሁ:: ይህም ነገሮች ከእኔ ሃሳብ ጋር እንዲስማሙ በማድረግ ወደ ጽድቅ ለማምጣት እንጂ በሕዝቦችና በጉዳዮች ላይ እንዲፈርዱ አይደለም::*



*“የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ሆኜ ለኢያሱ በተገለጥሁለት ጊዜ የእርሱም ሆነ የጠላቶቹ ወገን አለመሆኔን ገልጬለት ነበር:: እኔ በፍጹም የማንም ወገን ለመሆን አልመጣሁም:: የመጣሁት የማንም ወገን ለመሆን ሳይሆን ለመግዛት ነው:: በእስራኤል ፊት የሠራዊት አለቃ ሆኜ የተገለጥሁት እስራኤል ወደ ተነገረለት የተስፋ ምድሩ መግባት ይችል ዘንድ ነው:: አሁን ቤተ ክርስቲያን ወደ ተስፋ ምድሯ ልትገባ ነው:: እኔም እንደገና የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ሆኜ ልገለጥ ነው:: ስገለጥ ደግሞ በወንድሞቻቸው ላይ በክፉ እንዲነሱባቸው ህዝቤን ጨቁነው አስረውት የነበሩትን በሙሉ አጠፋቸዋለሁ:: ፍርዴ በሰው ልጅ እንዲያውም በህዝቤ መካከል ባሉት አለመግባባቶች ላይ እንኳን ወገንተኛ አይሆንም:: በእስራኤል አማካይነት አደርገው የነበረውን በጠላቶቻቸውም አድርጌዋለሁ:: ፍርዴን የማታዩት እኮ ከምድራዊና ከዓለማዊ ዕይታ አንጻር ብቻ ስለምታዩት ነው:: ጽድቅና ፍርድ የዙፋኔ መሠረት በመሆናቸው በእኔ ሥልጣን ለመመላለስ ፍርዴን ማየት አለባችሁ::*

*“ጽድቅን በመረጥኩት ህዝብ ውስጥ አስቀምጫለሁ:: ይሁንና በምድረ በዳ እንደነበረው እስራኤል የቤተ ክርስቲያን ዘመን ታላላቅ ቅዱሳንም እንኳን ራሳቸውን ለጥቂት ጊዜ ያህል ከመንገዴ ጋር ብቻ አንድ አድርገዋል:: ይሁን እንጂ እኔ ግን ከእነርሱ ጋር አይደለሁም፣ የጠላቶቻቸው ተቃዋሚም አይደለሁም:: እኔ ሰውን ሁሉ እወዳለሁ፣ ሁሉም ሰው እንዲድንም እፈልጋለሁ:: ስለዚህ ህዝቤ ጠላቶቹን ከጥፋት ያድናቸው ዘንድ ልጠቀምበት እመጣለሁ::*

ምርኮኛ አድርጎ በቁጥጥሩ ስር አውሏቸው የነበረውን ክፋውን ለመውጋት ስንል በወነጭፍናቸው ጥሩሮች ብዙዎቹን የገዛ ወንድሞችንን እየወጋን አቁስለናቸው ነበር:: ጠላት አሁንም ድረስ እየተጠቀመባቸው ያሉ ወይም ምርኮኛ አድርጎ በሰፈሩ አስሮ ያስቀመጣቸው ብዙ አሉ:: እነዚህን ወገኖቻችንን በተራራው ላይ ተዋግተነው ስለነበረው ታላቅ ጦርነት እንዲያስቡ ልረዳቸው አልቻልኩም:: እንደገና የምንዋጋው ቀጣዩ ጦርነት ከእነዚህ የገዛ ወንድሞቻችን ጋር የሚደረግ ከሆነ እገረም ጀመር:: ይህንን ሁሉ በሃሳቤ ሳወጣና ሳወርድ ጌታ ተመልክቶኝ እንዲህ አለኝ::

“ጠላት የመጨረሻው ጦርነት እስኪጠናቀቅ ድረስ ምንጊዜም የሚጠቀምባቸው አንዳንድ ወንድሞች ይኖራሉ። ይሁንና አሁን ይህን ልነግርህ የፈለግሁበት ምክንያቱ ግን ያ ሳይሆን ጠላት ወደ ገዛ ልባችሁና አዕምሯችሁ እንዴት እንደሚገባና እንደሚጠቀምባችሁ እንድታዩ ልረዳችሁ ነው። አሁን እንኳን ሁሉንም ነገር እንዴት እየሰራሁ እንዳለሁ አታዩም።

“በዚህ ጊዜ እጅግ ታላላቅ የተባሉት የህዝቤ መሪዎች እንኳን እምብዛም ከእኔ ጋር ተስማምተው እየተጓዙ አይደሉም። ይሄ ደግሞ በህዝቤ መካከል የተለመደ ነገር ሆኗል። ብዙዎቹ መልካም ሥራ እየሰሩ ያሉ ቢሆንም ይሰሩት ዘንድ የሰጠኋቸውን ሥራ እየሰሩ ያሉት ግን በጣም ጥቂቶች ናቸው። ይህ ደግሞ በመካከላችሁ ያለው መለያየት ውጤት ነው። የምመጣው የእኔ ወገን የሚሆኑትን ለመጥራት እንጂ የማንም ወገንተኛ ለመሆን አይደለም።

“አንድ ሰው ስለተያዘበት የሥጋ በሽታ መረዳት የምትችሉበትን የማታውቁትን ‘የጥበብ ቃል’ ወይም ሌላ ዕውቀት ስሰጣችሁ በዚያ ትደነቃላችሁ። ይህ ዕውቀት ወደ እናንተ የሚመጣው ልቤን በአነስተኛ ደረጃ ስትነኩት ነው። እኔ ሁሉን አውቃለሁ። ሙሉ በሙሉ የእኔ ልብ ቢኖራችሁ ልክ እዚህ መለማመድ እንደ ጀመርከው በዚያም ስለ ማንኛውም ሰውና ስለ ማንኛውም ነገር ሁሉን ነገር ማወቅ ትችል ነበር። ሰዎችን ሁሉ እኔ እንደማያቸው ታያቸውም ነበር። ያንጊዜም እንኳን ቢሆን ሙሉ በሙሉ በእኔ ውስጥ በደንብ መኖር አለ። ይህን የመሰለውን ዕውቀት በትክክል እንዴት መጠቀም እንዳለባችሁ ለማወቅ የእኔ ልብ ሊኖራችሁ ይገባል።

“በመለኮታዊ ዕውቀቴ ታምኜ አደራ ልሰጣችሁ የምችለው ልቤን ባወቃችሁት መጠን ብቻ ነው። ለቤተ ክርስቲያኔ የለቀቅኋቸው የመንፈስ ስጦታዎች ሊመጣ ካለው ዘመን ኃይላት ጥቂቶቹ ናቸው። የጠራኋችሁ ለዚያ ዘመን መልዕክተኞች እንድትሆኑ ስለሆነ የዘመኑን ኃይል ማወቅ አለባችሁ። የእኔ አካል እንደ መሆናችሁም ስጦታዎቹን በቅንነት መፈለግ አለባችሁ። እናንተም እንደ እኔ መሆን እንድትችሉ ለእናንተ ሰጥቻችኋለሁ። ሃሳቤን፣ መንገዶቼንና ዓላማዎቼን ማወቅ በመፈለጋችሁ ትክክል ብትሆኑም ልቤንም ለማወቅ በቅንነት መፈለግ አለባችሁ። የልቦናችሁ ዓይኖች የሚከፈቱት ሃሳቤን ስታውቁ ነው። ያንጊዜ እኔ የማየውን ታያላችሁ፣ እኔ የማደርገውንም



ታደርጋላችሁ።

“ሊመጣ ያለውን ዘመን ኃይላትን አብዝቼ ለቤተ ክርስቲያኔ አደራ ልሰጥ ነው። ይሁን እንጂ አብዛኛውን ጊዜ በታላቅ ኃይል በሚያምኑት ላይ የሚደርስ ታላቅ መሳት ግን አለ። አንተም ላሳይህ ያልኩትን ነገር ካልተረዳህ በቀር ከዚህ መሳት አታመልጥም።

“ጸጋዬን እንድሰጥህ ጠይቀኸኛልና ታገኛለህ። በሕይወት መንገድ ላይ እንድትጓዝ የሚረዳህ የመጀመሪያው ጸጋ አሁን ያለህበትን የመሳት ደረጃ ማወቅ ነው። ይህ መሳት እኔ የማውቀውን ማንኛውንም ነገር እንደ እኔ አለማወቅን ያካተተ ነው። አሁን ያለህበትን የመሳት ደረጃ ማወቁ ትሁትነትን ሲያመጣ እኔ ደግሞ ጸጋዬን የምሰጠው ለትሁታን ነው። ለዚህ ነው ‘የእኔ ባሪያ ሆኖ ልቡ የታወረ ማነው?’ ፈሪሳውያኑንም ‘ወደ ዓለም የመጣሁት ልፈርድ ነው. . .ለሚያዩ የዓይን ብርሃንን ለመስጠት፣ የሚያዩትም እንዳያዩ ለማድረግ. . .፣ ዕውሮችስ ብትሆኑ ሃጢአት ባልሆነባችሁ ነበር። ነገር ግን እንደምታዩ ትናገራላችሁ ግን በሃጢአታችሁ አላችሁ’ ያልኳቸው። ባሪያዬ ጳውሎስ የነበረበትን ሁኔታ የሚገልጥለት የእኔ ብርሃን ብቻ ስለነበረ በጠራሁት ጊዜ የዓይኑን ብርሃን ያሳወርኩት ለዚህ ነው። እናንተም እንደ እርሱ በመንፈሴ ማየት ትችሉ ዘንድ በብርሃኔ ተመትታችሁ መታወር አለባችሁ” አለኝ።

ከዚያም አልፈናቸው በመጣናቸው ዙፋናት ላይ ተቀምጠው የነበሩትን ሰዎች ለመመልከት ስለተገደድኩ ወደ እነርሱ አየሁ። በዚህን ጊዜ ዓይኔ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደሆነ ባወቅሁት አንድ ሰው ላይ አረፈና ወደ ኋላዬ ወደ ጌታ ዘወር ብዬ ተመለከትኩ። ጌታም ይህን ሰው እንዳነጋግረው የምልክት ትዕዛዝ ሰጠኝ።

እኔም ሐዋርያው ጳውሎስ ጋር መገናኘቴ ደንቆኝ “ይህን ጊዜ በጣም በናፍቆት ስጠብቀው ኖሬያለሁ። የጻፍካቸው የወንጌል መልክዕታት ቤተ ክርስቲያንን ምን ያህል እንደጠቀሟት፣ ምናልባትም በዚህ ዘመን ያለነውን እኛ ንም እንዴት አንድ ላይ እንዳስተሳሰሩን እንደምትገነዘብ አውቃለሁ። አንተ አሁንም በምድር ላይ ከሚያበሩት ታላላቅ ብርሃናት አንዱ ነህ” አልኩት።

እርሱም ፈገግ ብሎ "አመሰግናለሁ! ከአንተ ጋር ለመገናኘት ይህንን ጊዜ ምን ያህል ስናፍቀው እንደኖርኩ አትረዳልኝም። አንተ በፍጻሜው ጦርነት ላይ የምትጋደል ወታደር ስትሆን በዚህ የሚገኙ ሰዎች ሁሉ ሊያገኟቸው ከሚናፍቋቸው ሰዎችም አንዱ ነህ። እኛ አንተ እዚህ ያየሃቸውን እነዚህን ቀናት ያየናቸው ውስን በሆነ ትንቢታዊ ራዕይ አማካይነት በድንግዝግዝ ብቻ ሲሆን፤ አንተ ግን በእነርሱ ውስጥ ትኖር ዘንድ የተመረጥህ ሰው ነህ። አንተ ለመጨረሻው ፍልሚያ የተዘጋጀህ ወታደር በመሆን ሁላችንም ልናገኛቸው ከምንጠብቃቸው ሰዎች አንዱ ነህ" አለኝ።

እኔም ቀልጠፍ ብዬ "ይሁንና ስለ አንተና ሌሎች በሕይወት ምሳሌነታቸው በጻፏቸው መልዕክታት ሁሉ ትምህርቶችን በማዘጋጀት እገዛ ስላደረጉት በሙሉ የሚሰማኝን አድናቆት መግለጽ የምችልበት ሌላ ምንም መንገድ የለም። አድናቆታችንን ለመለዋወጥ ዘላለም እንደሚኖረን አውቃለሁ። ስለዚህ እባክህ በዚህ እስከተገኘሁ ድረስ 'በዚህ ጦርነት ውስጥ እኛን እያገዘ ላለው ትውልዴ የምትነግረኝ መልዕክት ምንድነው? ብዬ ልጠይቅህ'" ስል ንግግሬን ቀጠልኩ።

ጳውሎስም ዓይን፣ ዓይኔን ትኩር ብሎ እየተመለከተ "አሁንም የምልህ ነገር ቢኖር ቀደም ሲል በመልዕክታቴ የነገርኩህን ብቻ ነው። እሰራው ዘንድ ከተጠራሁለት ነገር መጉደሌን ይህንን በደንብ እንድታውቅ አደርግሃለሁ።

"ሩጫዬን በእግዚአብሔር ጸጋ መጨረስ ብችልም የተመላለስኩት ግን በተጠራሁበት ጥሪ ሁሉ ላይ አይደለም። ከዚህ የተነሳ ልመላለስባቸው እችልባቸው ከነበሩት ከፍተኛ ዓላማዎች ጎድያለሁ። ሁሉም ሰው ጎድሏል። አንዳንዶች የእኔን የክርስትና አገልግሎት ታላቅ ምሳሌነት አሳንሶ ማሰቡ ስድብ እንደሆነ አድርገው እንደሚያስቡ አውቃለሁ። በሕይወቴ ፍጻሜ አካባቢ በመልዕክቴ ላይ ከሃጢአተኞች ዋነኛ መሆኔን ገልጬ ስጽፍ ከልቤ ነበር። ይህም በዚያን ጊዜ ከነበሩት ሃጢአተኞች ዋነኛ ነበርኩ ማለቴ እንጂ ከሃጢአተኞች ዋናው ሆኜ ስኖር ነበር እያልኩ አልነበረም። እውቀው ዘንድ በጣም ብዙ ነገር ቢሰጠኝም እኔ የተመላለስኩት ግን በጣም በጥቂቱ ላይ ነው" አለኝ።



እኔም "ስለ አንተ የማስበው ትሁት እንደሆንክ ነውና ያ እንዴት ሊሆን ቻለ?" ስል ጠየቅኩት።

"እውነተኛ ትህትና ከእውነት ጋር መስማማት ስለሆነ አትፍራ። የጻፍኳቸው መልዕክታት የተጻፉት በመንፈስ ቅዱስ ቅባት ስለሆነ እውነት ነበሩ። ይሁን እንጂ በጣም ብዙ ነገር ተሰጥቶኝ ነበረ፤ እኔ ግን እንደልኩ እንጂ የተሰጠኝን በሙሉ አልተጠቀምኩበትም። ከአንድ ሰው በቀር በዚህ ያለ ሰው ሁሉ ጎድሏል። ብዙዎች ስለ እኔ ያላቸው ግምትና ዕይታ የተሳሳተ በመሆኑ ምክንያት ዛሬም ድረስ ትምህርቶቼን እያጣመሙ ናቸው። አንተ ግን ይህንን ስለ ትምህርቶቼ የሚባለውን በተለየ ሁኔታ ማየት አለብህ።

"መልዕክቶቼን እንዳነበብካቸው ከታላላቆቹ ሐዋርያት ባላንስም፤ ነገር ግን በወቅቱ ከተሰማኝ ስሜት የተነሳ ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ፣ ከዚያም ከቅዱሳን ሁሉ የማንስ በመጨረሻም ከሃጢአተኞች ዋነኛ መሆኔን ወደ መገንዘቡ ደረስኩ። የተናገርኩት እውነት ስለሆነ እንጂ ትሁት ሆኜ አልነበረም። ከተለማመድኩት በላይ ብዙ አደራ ተሰጥቶኝ ነበር። በእዚህ ቦታ ሙሉ በሙሉ ያመነ፣ ሙሉ በሙሉ የታዘዘ፣ ይሰራው ዘንድ የተሰጠውን ሥራም ሙሉ በሙሉ በትክክል ሰርቶ ያጠናቀቀ ሰው አንድ ብቻ ነው። ስለዚህ አንተ ከእኔ በበለጠ በብዙ ብልጫ መመላለስ ትችላለህ" አለኝ።

ለዚህም ንግግሩ "የምትለው ሁሉ እውነት እንደሆነ አውቃለሁ። ይሁንና ስለ መጨረሻው ጦርነት የምትሰጠን እጅግ አስፈላጊው መልዕክት ይሄ ብቻ ስለ መሆኑ እርግጠኛ ነህን?" ስል ጠየቅሁት።

ፍጹም ጽኑ በሆነ እምነት "እርግጠኛ ነኝ! የጌታ ጸጋ መልዕክቶቼን በዚያ ሁኔታ ስለተጠቀመባቸው በጣም አደንቀዋለሁ። ይሁንና አብዛኞቻችሁ በተሳሳተ መንገድ ስለምትጠቀሙባቸው ግን ስጋቱ አለኝ። መልዕክታቱ የመንፈስ ቅዱስ እውነቶችና ቅዱሳት መጻህፍትም ናቸው። ጌታ በታላቅ ተቋሙ በዘላለማዊቱ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ እንዳስቀምጥ ትላልቅ ድንጋዮችን የሰጠኝ ቢሆንም እነዚህ ድንጋዮች ግን መሠረት አልነበሩም። የመሠረት ድንጋዮቹን ያስቀመጠው ኢየሱስ ብቻ በመሆኑ የእኔ ሕይወትና አገልግሎት አንተ እንድትሆን ለተጠራህለት ጥሪ ምሳሌ የሚሆኑ አይደሉም። ምሳሌው ኢየሱስ

ብቻ ነው። እኔ የጻፍኳቸው መልዕክታት መሠረት ተደርገው ጥቅም ላይ ውለው ከሆነ በእነርሱ ላይ መገንባት የሚያስፈልገውን ግንባታ ክብደት መሸከም አይችሉም። ትምህርቶቼን በጌታ ትምህርቶች እያጠራችሁ መመልከት አለባችሁ እንጂ መሠረት አድርጋችሁ መጠቀም የለባችሁም። መሠረቱ የጌታ ቃል በመሆኑ እርሱን ከእኔ ዕይታ አንጻር ለመረዳት አትሞክሩ። እኔ የእርሱን ቃሎች በዝርዝር በማብራራት በእነርሱ ላይ ብቻ ነው የገነባሁት። እጅግ የላቀው ጥበብ፣ ኃይልና እውነቶቹ የእርሱ እንጂ የእኔ ቃሎች አይደሉም።

“በተሰጠኝ መጠን እንዳልተመላለስኩ ይህን ልታውቅ ይገባሃል። ማንኛውም አማኝ እኔ ከተመላለስኩበት በላይ የሚመላለስበት ብዙ ነገር አለው። በውስጣቸውም ፍጥረትን ሁሉ የፈጠረው የእርሱ ኃይል ይኖራል። ከቅዱሳን ሁሉ ከሚያንሱ ከታናናሾች አንዱ ተራሮችን የማናወጥ፣ ገፍቶ የመጣን የጠላት ሠራዊትን የማስቆም ወይም ሙታንን የማስነሳት ሥልጣን አለው። በዘመንህ የተጠራህለትን ጥሪ ሁሉ ለማከናወን የምትፈልግ ከሆነ የእኔን አገልግሎት እንደ መነሻ እንጂ የመጨረሻ አድርገህ ማየት የለብህም። ግብህ የጌታን እንጂ የእኔን ግብ መምሰል የለበትም። በሠርጉ ላይ የወይን ጠጁ ባለቀ ሰዓት እጅግ ምርጡን ወይን ጠጅ የሰጠው እርሱ በመሆኑ አንተም እርሱ የሰራውን ሁሉ መስራት፤ ከዚያም የበለጠ መስራት ትችላለህ” ሲል መለሰልኝ።

በዚህ ቦታ ላይ መናገር የሚቻለው እውነትን ብቻ እንደሆነ ነው የተረዳሁት። ጳውሎስ የተናገረውም ነገር ብዙ ሰዎች በወንጌላቱ መሠረት ላይ ከመገንባት ይልቅ የእርሱን ትምህርቶች በተሳሳተ መንገድ መሠረት አድርገው እንደ ተጠቀሙባቸው የተናገረው እውነት እንደሆነ ነው የማውቀው። ይሁንና ለእኔ ግን ጳውሎስ ከተጠራለት ጥሪ ጎድሎ ነበር ብሎ ለመቀበል ከብዶኛል። ጳውሎስ ተቀምጦበት ወደ ነበረው ዙፋንና ወደ ማንነቱ ክብር ተመለከትኩ። የእርሱ ክብር እጅግ ታላላቅ የተባሉት ቅዱሳን በመንግስተ ሰማይ ይኖራቸዋል ብዬ ከማስበው በብዙ የሚበልጥ ነበር። እርሱም ይሆናል ብዬ እጠብቀው ከነበረው በላይ ቆራጥ ነበር። አሁንም እጅግ የሚያሳስበው የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሸክም እንዳለው ግልጽ በመሆኑ ልቤን ነካው። ጳውሎስ ለእኔ ጣኦት ሆኖብኝ ነበር። ጣኦት የሆነብኝ ጳውሎስ እኔን ከዚህ በደሌ ነጻ ለማውጣት ጥረት ያደርግ የነበረ ቢሆንም እንኳን ለእኔ ግን በብዙ የላቀ ነበር።



ከዚያም በልቤ የማስበውን አውቆብኝ ሁለቱን እጆቹን በትከሻዬ ላይ ጣል አድርጎ ትኩር ብሎ ዓይን ዓይኔን በቆራጥነት እየተመለከተ እንዲህ አለኝ።

“እኔ ወንድምህ ነኝ። እዚህ ያሉት በሙሉ እንደሚወዱህ እኔም እወድሃለሁ። አንተ ግን ማወቅ አለብህ። አሁን እየተወያየንበት ያለው ትምህርት ተጠናቋል። እኛ አሁን በምድር ላይ ሳለን በዘራነው ዘር ላይ መጨመርም ሆነ መቀነስ አንችልም። አንተ ግን ትችላለህ። እኛ ለአንተ ተስፋ አይደለንም፣ አንተ ግን ለእኛ ተስፋችን ነህ። በዚህ ውይይታችን እንኳን ላረጋግጥልህ የምችለው ቀደም ሲል ስለ ጻፍኳቸው መልዕክታት ብቻ ነው። ይሁንና አንተ ግን ገና ብዙ የምትጽፈው መልዕክት አለህ። እግዚአብሔርን ብቻ አምልከው፣ በነገር ሁሉም ወደ እርሱ እደግ። ግብህን እርሱን ብቻ እንጂ በፍጹም የትኛውንም ሰው አታድርግ። በቅርቡ ብዙዎች በምድር ላይ እኛ ከሰራነው የሚበልጥ ሥራ በመስራት ይመላለሳሉ። ፊተኛው ኋለኛ፣ ኋለኛው ፊተኛ ይሆናልና በዚህ ቅር አንሰኝም። ከእናንተ ጋር አንድ በመሆናችን ልባችን ደስተኛ ነው። እኔ የኖርኩበት ትውልድ መሠረትን ማስቀመጥና በመሠረቱም ላይ መገንባትን ጀመረ። እኛም በዚህ ሁልጊዜ ክብር ይሰማናል። ይሁንና በተመሠረተው መሠረት ላይ የሚገነባው እያንዳንዱ ደረጃ ግን ማደግ ይኖርበታል። እያደጋችሁ ካልሄዳችሁ ግን መሆን የሚገባችሁን ህንጻውን አትሆኑም”።

ጳውሎስ የተናገረኝን በሃሳቤ አወጣና አወርድ እንደነበር ተረድቶ ንግግሩን እንዲህ ሲል ቀጠለ። “በዘመናችን ያገኘናቸውን፤ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን በቸልተኝነት የጣለቻቸውና አሁንም ድረስ ያልተመለሱ ሁለት ነገሮች ይቀራሉና እነርሱን ማስመለስ አለብህ”።

ሲገልጻቸው ያለው እነዚህ ሁለት ነገሮች እስካሁን ጽፏቸው ከነበሩት መልዕክታቱ ያለፉ ተጨማሪ ነገሮች ይሆናሉ ብዬ በማሰብ ምን ሲለኝ ነው ብዬ “ምንድን ናቸው እነርሱ?” ስል ጠየቅሁት።

እርሱም “አገልግሎቱንና መልዕክቱን ማስመለስ አለብህ” ሲል በጥብቅ አስገነዘበኝ።

ዘወር ብዬ ጌታን ሳየው ጌታም እውነት መሆኑን ራሱን በመነቅነቅ አረጋገጠልኝና *"ጳውሎስ በእነዚህ ሁለት ነገሮች እስከዚህ ሰዓት ድረስ እጅግ ታማኝ ሰው እንደነበር ይህንን ለአንተ መንገሩ ተገቢ ነው"* አለኝ::

እኔም ጳውሎስን "እባክህ በግልጽ አብራርተህ አስረዳኝ" ብዬ ለመንኩት::

"አስረዳሃለሁ! ዛሬ በዓለም ላይ ታላላቅ የወንጌል ስደት ወይም መከራ ካለባቸው ጥቂት ቦታዎች በቀር እየተሰበከ ያለው የወንጌል መልዕክትና እየተሰጠ ያለው አገልግሎት አንዱንም ማወቅ የሚቻል አይደለም:: ስለዚህም ነው የዚህ ዘመኗ ቤተ ክርስቲያን በእኛ ዘመን ከነበረችው እንኳን ይልቅ ጣዕረ ሞት የመሰለችው:: እኛ እንሆን ዘንድ የተጠራንለትን ጥሪ ሁሉ ከመሆን ርቀን ነበር:: ስናገለግል አንድ ሰው በአገልግሎቱ ሊከፍለው የሚችለው እጅግ ከፍተኛው መስዋትነት በአገልግሎት ውስጥ መቆየትን ነበር:: ይሄ ደግሞ ዋጋ የተከፈለለትን እጅግ የላቀ መስዋትነት ያም የመስቀሉን መልዕክት ያንጸባረቀ ነበር:: መስቀል የእግዚአብሔር ኃይል ሲሆን እንኖርበት ዘንድ የተጠራንለት ሕይወት ማዕከልም ነው:: ዛሬ መስቀሉን ስለማትሰብኩና ስለ መስቀሉ ስለማትኖሩ የደቀ መዛሙርትን ልብና አዕምሮ ለመለወጥ ያላችሁ ኃይል በጣም ደካማ ሆኗል:: ከዚህ የተነሳም በደቀ መዛሙርትና በአህዛብ መካከል ብዙም የሕይወት ልዩነት ለማየት ተቸግረናል:: ስለዚህ በአደራ የተሰጠን ወንጌል ወይም መዳን ያ ባለመሆኑ ወደ መስቀሉ መመለስ አለብህ" አለኝ::

ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን ከተናገረኝና ልክ እንደ አባት ትከሻዬን አቅፎ ከተሰናበተኝ በኋላ ተመልሶ ወደ መቀመጫው ሄደ:: በዚህ ጊዜ በቃላት ሊገለጽ የማይችል በረከትና እጅግ ከባድ ተግሳጽ ሁለቱንም እንደ ተቀበልኩ ተሰማኝ:: ያንን ቦታ ለቅቄ እየሄድኩ እያለሁም ተራራው ላይ ስላሉት የመዳን ደረጃዎችና ተራራው ውስጥ ስላየሁት የመዳን መዝገቦች ማሰብ ጀመርኩ:: ወደዚህ ስፍራ አልፌ የገባሁበትን በር አልፎ ለመግባት የወሰንኩትን ውሳኔ ጨምሮ፤ ብዙዎቹ የገዛ ራሴ ውሳኔዎች የጌታን ፈቃድ በማሰብ የተወሰኑ ሳይሆኑ በአብዛኛው ብዙ ርቀት ይወስደኛል ብዬ ባሰብኩት ሃሳብ ላይ የተመሠረቱ እንደነበሩ ማየት ጀመርኩ:: በዚያ ሁሉ አሁንም ለራሴ እንጂ ለጌታ እየኖርኩ እንዳልሆነ ተገነዘብኩ:: በዚህ ያለውን ፍርድ ለመቀበል ባለኝ ፍላጎት እንኳን፤ ያለ ምንም ውድቀት ወደ ድል ነሺነት የሚመልሰኝን ለማግኘት ይረዳኛል ብዬ



ተነቃቅቼ ነበር:: እስከ አሁን ድረስም ክርስቶስን ማዕከል ከማድረግ ይልቅ ይበልጥ ራስ ወዳድነትን ማዕከል አድርጌ ነበር እመላለስ የነበረው::

ከጳውሎስ ጋር ያደረግሁትን ይህን አጠር ያለ ውይይት ሙሉ ለሙሉ ለመረዳት ረዥም ጊዜ እንደሚወስድብኝ ተረዳሁ:: ከመላዋ ዘላለማዊት ቤተ ክርስቲያን በረከትን በራሴ መንገድ እንደ ተቀበልኩም ተሰማኝ:: በእርግጥ እንደ ደመና የከበቡን እነዚህ ብዙ ታላላቅ ምስክሮች፤ ለልጆቻቸው የተሻለ ነገርን እንደሚፈልጉ ኩሩ ወላጆች አበረታተውናል:: እጅግ የላቀ ደስታቸውም በእነርሱ ዘመን የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ማግኘት ያልቻለቻቸውን ማንኛ ውንም ነገር የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ስታገኝ ማየት ነው:: አሁንም ድረስ እንመላለስበት ዘንድ ባዘጋጁልን ላይ መመላለስ እንደተሳነን አውቄያለሁ::

ጌታም *"የተሰራው ሥራ በሙሉ የተሰራው በእኔ ጸጋ በመሆኑ የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ትልቁን ሥራ ብትሰራም እንኳን ከትውልዷ በላይ አትሆንም:: ይሁንና ይህች የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን በየትኛውም ዘመን የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ካከናወነችው የበለጠ ማከናወን ስላለባት ጸጋዬን ይልቁንም ኃይሌን አበዛላታለሁ:: የመጨረሻው ዘመን አማኞች ከእነርሱ በፊት ለነበሩት አማኞች በሙሉ የመጨረሻዎቹ ተወካዮች ስለሚሆኑ እኔ ለርቼ ባሳየሁበት ኃይል ሁሉ የበለጠ ይመላለሳሉ:: የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን የእኔን ባህርይና መንገድ ከዚህ በፊት በሰዎች በፍጹም ተገልጦ በማያውቅ ሁኔታ ገለጻ ታሳያለች:: ይህ የሚሆንበት ምክንያትም ብዙ ከተሰጠው ብዙ ስለሚጠበቅበትና እኔ የሚበልጥ ጸጋ ስለምሰጣችሁ ነው"* ሲል ሃሳቡን ሰነዘረ::

ይህ የጌታ ንግግር ስለ ጳውሎስ የበለጠ እንዳስብ አደረገኝ:: እርሱ ታማኝና የተሰጠ ሰው እንደነበረ እኛስ እንዴት ነው እንደ እርሱ ታማኝና የተሰጡ ሰዎች የምንሆነው? ብዬም ለራሴ አሰብኩ::

ጌታም *"እኔ የምጠይቃችሁ ያንን ሳይሆን በእኔ እንድትኖሩ ነው:: ራሳችሁን በጳውሎስም ሆነ በሌሎች መመዘን አትችሉም:: ሁልጊዜ ሰውን የምታዩ ከሆነ ትወድቃላችሁ! እኔን የምታዩ ከሆናችሁ ግን መስራት ከምትችሉት በላይም አልፋችሁ ትሰራላችሁ:: አንተው ራስህ ስታስተምር እንደ*

ነበረው በኤማሁስ መንገድ ላይ ይጓዙ የነበሩት ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ዓይኖቻቸው የተከፈቱት ኅብስቱን ቆርሼ በሰጠኋቸውና እኔን ባዩ ጊዜ ነበር:: የጳውሎስንም ሆነ የሌላ የማንንም ሰው መልዕክታት ስታነቡ መስማት ያለባችሁ የእኔን ድምጽ ነው:: ኅብስታችሁን በቀጥታ ከእኔ ስትቀበሉ ያንጊዜ የልቦናችሁ ዓይኖች ይከፈታሉ::

"እኔን በእጅጉ በሚመስሉኝ ሰዎች አማካይነት የማታዩኝ ከሆናችሁ እጅግ በጣም ልትረበሹ ትችላላችሁ:: የእኔን ቅባትና ኃይል ከሌሎች በበለጠ ለማወቅ ወደ እኔ የሚመጡ ሰዎች ተጠምደው የሚያዙበት ሌላም ወጥመድ አለ:: እነዚህ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ ግራ መጋባት ውስጥ የሚወድቁት ወደ ራሳቸው ሲመለከቱ ነው:: ቀደም ሲል ከጳውሎስ ጋር ከመነጋገርህ በፊት እንደነገርኩህ ባሪያዎቼ አጥርተው ማየት ይችሉ ዘንድ አስቀድሞ ዓይናቸው መታወር አለበት:: ጳውሎስ ለዚህ ነገር ምርጥ ከሆኑ ምሳሌዎቼ አንዱ በመሆኑ እርሱን አግኝተህ እንድታነጋግረው አድርጌሃለሁ:: እርሱ ቤተ ክርስቲያኔን እንዲያሳድድ የፈቀድኩለት ከጸጋዬ የተነሳ ነበር:: ብርሃኔን ባየ ጊዜም የገዛ ራሱ ምክንያታዊነት እግዚአብሔርን እያገለገለ ከሚመስለው ከእያንዳንዱ እውነት ጋር ወደ መጋጨት እንደመራው ተረዳ:: ምክንያታችሁ ሁልጊዜ የሚመራችሁ ከፈቃዴ ጋር ፍጹም ተጻራሪ የሆነውን ነገር ታደርጉ ዘንድ ነው:: ከጳውሎስ ተሞክሮ ካልተማርክ እንድሰጥህ የጠየቅከኝ ታላቅ ቅባት ይህን ትልቅ አደጋ ነው የሚያመጣብህ:: እናንተነታችሁንና ያላችሁን ነገር ሁሉ በፊቴ በማስቀመጥ መስቀላችሁን በየዕለቱ ካልተሸከማችሁ በቀር እኔ ከምሰጣችሁ ሥልጣንና ኃይል የተነሳ ትወድቃላችሁ:: ሁሉን ነገር ስለ ወንጌል ብላችሁ ማድረግን እስክትማሩ ድረስም የበለጠ ተጽዕኖ የማሳደር አቅም በኖራችሁ መጠን የሚበልጥ አደጋ ነው የሚገጥማችሁ::

"እኔ በቀባኋቸው ላይ ከሚደርሱት ታላላቅ መሳቶች አንዱ ትንሽ ለማያዊ ዕውቀት ወይም ኃይል ስሰጣቸው፤ መንገዳቸው መንገዴ፣ ሃሳባቸው በሙሉ የእኔ ሃሳብ እንደሆነ አድርገው ማሰብ መጀመራቸው ነው:: ብዙዎቹ ተሰናክለው የወደቁበት ትልቁ ስህተት ይሄ ነው:: ከእኔ ጋር ፍጹም የሆነ ኅብረት ሲኖርህ ግን እኔ እንደማስበው ታስባለህ:: እጅግ ታላቁን ቅባት የተቀባውና በምድር ሁሉ ላይ በዚያ ቅባት የተመላለሰው ሰው ጳውሎስ እንኳን እንዲህ ዓይነቱ ኅብረት የነበረው በከፊልና ለአጭር ጊዜ ያህል ብቻ ነበር::



"ምንም እንኳን ጳውሎስ ማንም ሰው ያልተመላለሰበትን ምልልስ ከእኔ ጋር አብሮ ቢመላለስም ከእኔ ባልሆኑ ፍርሃቶችና ድካሞች ተይዞ ግን ነበር:: እኔም ከእነዚህ ድካሞቹና ፍርሃቶቹ ነጻ ላወጣው እችል ስለነበር ነጻ እንዳወጣው ብዙጊዜ ጠይቆኝ ነበር:: ሆኖም ግን እርሱን ነጻ ላለማውጣት ምክንያት ነበረኝ:: ጳውሎስ ትልቁ ጥበቡ የነበረው ድካሙን አምኖ መቀበሉና ከእነዚህ ችግሮች ነጻ ባወጣው በተገለጥሁበት መገለጥና ኃይል መጠን እርሱን ለማመን እንደምችገር መረዳቱ ነበር:: ጳውሎስ በገዛ ራሱ ድካሞችና በመንፈስ መገለጥ መካከል ያለውን ልዩነት ለይቶ አውቋል:: በድካም ወይም በፍርሃት በተያዘ ጊዜ ነገሮችን ከገዛ ራሱ ዕይታ አንጻር እንጂ ከእኔ ዕይታ አንጻር እንደማያይ ተረድቶታል:: ይሄ ደግሞ እኔን እንዲፈልግ፣ በእኔ ላይ እንዲታመንና ከዚህም በላይ እንዲያደርግ ምክንያት ሆኖታል:: ከገዛ ራሱ ልብ የሚወጣውን ሃሳብ ከእኔ የወጣ ሃሳብ አድርጎ ላለመውሰድም ተጠንቅቋል:: ስለዚህ በመገለጦች ጉዳይ በሌሎች ላይ መተማመን ያልቻልኩትን እርሱን ግን ላምነው ችያለሁ:: ጳውሎስ የገዛ ራሱን ድካሞች፣ የእኔን ቅባትና በእነዚህ በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነትን ለይቶ ስላወቀ ከገዛ ራሱ ሃሳብና ልብ የወጣውን ከእኔ ሃሳብና ልብ ጋር አላምታታምውም" አለኝ::

በዚህ ቦታ ላይ ሁሉም ነገር እንዴት ግልጽ እንደሆነ ማሰብ ጀመርኩ:: ይሁንና ይህን የመሰለ ትልቅ ተሞክሮ ካገኘሁ በኋላ እንኳን አሁንም እንደገና በጣም በቀላሉ ረሳሁት:: በዚህ ስፍራ ያለውን ብርሃን ማወቅና በእርሱም መመላለስ ቀላል ቢሆንም፤ ወደ ጦርነቱ ስንመለስ ግን እንደገና ጭጋጋማ ሆነ:: በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ በመኖራችን ሊኖረን የሚገባውን ዕይታ የተዛባ በሚያደርጉት በቁጠኝነትና በትዕግስት ማጣት የተያዝኩትን ያህል በፍርሃቶች እንዳልተያዝኩ አሰብኩ::

በዚህ ጊዜ ጥበብ ቆም አለና ፊቱን ወደ እኔ በማዞር "አንተ የምድር ዕቃ ነህና በምድር ላይ በምትመላለስበት ዘመን ሁሉ እንደዚያ ነው የምትሆነው:: በዚያ በልቦናህ ዓይኖች የምታየኝ ከሆነ ግን እዚህ በግልጽ እንዳየኸኝ በዚያም ልታየኝ ትችላለህ:: በዚያ ማንም አድርጎት የማያውቀውንም ማድረግና ከዚያም በላይ ወደ እኔ መቅረብ ትችላለህ:: ሰው ሁሉ በትክክል መቅረብ የሚፈልገውን ያህል ወደ እኔ ይቀርብ ዘንድ መንገዱን ያዘጋጀሁለት በመሆኑ ከጳውሎስ

በበለጠ ወደ እኔ መቅረብ ከፈለግህ ትችላለህ:: አንዳንዶች ከእኔ ጋር ባላቸው ግንኙነት ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ እንዳይሰጡ የሚከለክላቸውን ማንኛውንም ነገር ለመተው አጥብቀው ከፈለጉ ያንን የፈለጉትን ያገኛሉ::

“እዚህ ቦታ ላይ ከእኔ ጋር አብረህ መመላለስ እንደምትችለው በዚያም መመላለስ የምትፈልግ ከሆነ አሁን በዚህ በቅርብ እንዳገኘኸኝ ሁሉ በዚያም ከፈለግኸኝ በቅርበት ታገኘኛለህ:: ወደ እኔ የምትቀርብ ከሆነ እኔም ወደ አንተ እቀርባለሁ:: በጠላቶችህ ፊት ለአንተ ገበታን ማዘጋጀት ፈቃዴ ነው:: ይሄ ህዝቤን ለሚመሩ ብቻ ሳይሆን ስሜን ለሚጠሩትም ሁሉ ያለኝ ፈቃዴ ነው:: በሕይወት ያለን የትኛውንም ሰው መቅረብ ከቻልኩት በላይ ለአንተና ስሜንም ለሚጠሩት ሁሉ የበለጠ ቅርብ መሆን እፈልጋለሁ፣ ለሚፈልጉኝም እገኛለሁ:: ይሁንና እንዴት እንደምንቀራረብ የሚወስነው ግን እኔ ሳልሆን አንተ ነህ::

“እዚህ ስፍራ ላይ የተገኘኸው በሕይወትህ እንድፈርድልህ ስለጠየቅኸኝ ነው:: ፈራጅ ዳኛ አድርገህ ስለፈለከኝ አሁን አግኝተኸኛል:: ይሁንና የፍርድ ወንበሬን ስላየህ ግን አሁን የምትፈርዳቸው ፍርዶች በሙሉ የእኔ እንደሆኑ አድርገህ ማሰብ የለብህም:: ፍርዶቼ የሚኖሩህ አንተ ከእኔ ጋር አብረህ በኅብረት እስከተጓዝህና የመንፈሴንም ቅባት እስከፈለግህ ድረስ ብቻ ነው:: ይሄ ደግሞ በየዕለቱ ልታገኘው ወይም ልታጣው የምትችለው ነገር ነው::

“መላዕክቱን እንዳላይህና ሀልምና ራዕዮችንም እንድሰጥህ ያለማቋረጥ ስለጠየቅኸኝም ልጆቼ የሚጠይቁኝን መልካምን ስጦታ መስጠት የምወድ በመሆኔ ሰጥቼሃለሁ፣ እንድታያቸውም አድርጌሃለሁ:: ለብዙ ዓመታት ያህል ጥበብን እንድሰጥህ ስትጠይቀኝ ኖረሃልና አሁን እየተቀበልክ ነው:: እንድፈርድልህ ጠይቀኸኝ ነበር፤ አሁን ፈረድኩልህ:: ይሁንና እነዚህ ተሞክሮዎች ግን ሙሉ ለሙሉ አንተን አስተዋይ ወይም ጻድቅ ፈራጅ አያደርጉህም:: ጥበብና ፈራጅነት የሚኖሩህ አንተ በእኔ ስትኖር ብቻ ነውና በፍጹም እኔን ከመፈለግ አትታቀብ:: የበለጠ እያደግህ በሄድህ መጠን ለእኔ የሚያስፈልግህ ነገር ምን እንደሆነ አብዝተህ ትረዳዋለህ:: ሁልጊዜ በብርሃን መመላለስ ትችል ዘንድ ይበልጥ እየጎለመስህ በሄድህ መጠን ከእኔም ሆነ ከሌሎች ሰዎች መሸሸግህን እየቀነስክ ነው የምትሄደው::



“እኔን እንደ አዳኝ፣ ጌታ፣ ጥበብና ፈራጅ አይተኸኛልና ወደ ጦርነቱ ተመልሰህ በሄድህ ጊዜ የፍርድ ዙፋኔን በልቦናህ ዓይኖች ማየት ትችላለህ:: የምታስባቸውና የምታደርጋቸው ነገሮች በሙሉ እዚህ በደንብ የተገለጡ መሆናቸውን በማወቅ እውነት ውስጥ ስትመላለስ፤ ልክ እዚህ እንደኖርከው በዚያም የመኖር ነጻነቱ ይኖርሃል:: መጋረጃዎቹ እኔን ከአንተ ለመጋረድ የሚመጡት አንተ ራስህን ከእኔም ሆነ ከሌሎች ሰዎች ስትሸሽግ ብቻ ነው:: እኔ እውነት ስለሆንኩ የሚያመልኩኝ በሙሉ በእውነትና በመንፈስ ሊያመልኩኝ ይገባል:: ብርሃን ጨለማውን ስለሚገልጠውና ስለሚያጋልጠውም እውነት ሁልጊዜ በብርሃን ውስጥ መሆንን ትፈልጋለች እንጂ በፍጹም ጨለማ ውስጥ አትደበቅም:: እኔ በብርሃን እንደምመላለሰው አንተም በብርሃን የምትመላለሰው፤ ማንነትህን ከልብህ ገልጠህ ለማሳየትና ራስህን መግለጥ ስትፈልግ ብቻ ነው::

“ከእኔ ጋር እውነተኛ ኅብረት ለማድረግ ራስን ሙሉ በሙሉ መግለጥን ይጠይቃል:: ከህዝቤ ጋር ያለኝ እውነተኛ ኅብረትም የሚፈልገው ይህንኑ ነው::

“ከዚህ በኋላ ራስህን መደበቅ ስለሌለብህ በፍርድ ወንበር ፊት በምትቆም ጊዜ ከዚህ በፊት ተሰምቶህ የማያውቅ ነጻነትና ደህንነት የበለጠ ይሰማሃል:: ፍርዶቼ እውነትና ጻድቅ መሆናቸውን ስለምታውቅ ይበልጥ ደህንነት ይሰማሃል:: እኔ የፈጠርኩት የሕዋው ዓለም ሥነ-ምግባራዊና መንፈሳዊ ሥርዓት በተፈጥሮ ሕግ ላይ እንደተመሠረተው ፍጥረታዊው ሥርዓት እውን ሲሆን፤ በተመሳሳይም እኔ አልለወጥም፣ የጽድቅ መለኪያዎቼም አስተማማኝ ናቸው:: በእምነት መመላለስ ማለት በዚህ እውነት መኖር ማለት ነው:: እውነተኛው እምነት በእኔ ማንነት ላይ መደገፍ ስለሆነ በፍርዶቼ መተማመንን መማር አለብህ::

“በሽተኞችን መፈወስና ተዓምራት ማድረግ ትችል ዘንድ ኃይሌን ማወቅና በዚያም መመላለስ ትፈልጋለህ:: ይሁንና የቃሌን ኃይል ግን ገና ማወቅ እንኳን አልጀመርከም:: ሁሉንም ነገር ደግፌ የያዝኩት በቃሌ ኃይል ስለሆነ በምድር ላይ ይኖሩ የነበሩትንና በሞት የተለዩ ሰዎችን ሁሉ ከሞት ማስነሳት አይሳነኝም:: ፍጥረት የመኖር ሀልውናው ተጠብቆ ያለውና እርስ በርሱ ተደጋግፎ የተያያዘውም በቃሌ ነው::

“በምድር ላይ ሁልጊዜ ስገልጠው የኖርኩት ወይም ወደፊትም የምገልጠው እጅግ ከላቀው ኃይሌ በጣም ትንሹን ቢሆንም እንኳን ይህንን ኃይሌን መጨረሻው ከመምጣቱ በፊት ግን በምድር ላይ በሙላት መግለጥ አለብኝ። ይህን ኃይሌን ደግሞ ሰዎች ፍቅሬን አይተው እንዲያምኑ በሚል አልገልጠውም። በምድር ላይ ስመላለስ ዓለምን በኃይሌ ለማዳን ፈልጌ ቢሆን ኖሮ ተራሮችን በጣቴ ማናወጥ እችል ነበር። ከዚያም ሰው ሁሉ እኔን ወይም እውነትን ወደው ሳይሆን ኃይሌን ፈርተው ይሰግዱልኝ ነበር። እኔ ግን ሰዎች እኔንና እውነትን ወደው እንጂ ኃይሌን ፈርተው እንዲታዘዙኝ አልፈልግም።

“ፍቅሬን የማታውቅ ከሆነ ኃይሌ ያጠፋሃል። ኃይሌን ማወቅ ትችል ዘንድ ደግሞ ፍቅሬን አልሰጥህም። ይሁንና ፍቅሬን ማወቅ ትችል ዘንድ ግን ኃይሌን እሰጥሃለሁ። የሕይወትህ ግብ መሆን ያለበት ፍቅር እንጂ ኃይል አይደለም። ከዚያም የምትወደውን ኃይል እሰጥሃለሁ። በሽተኞችን ስለምትወዳቸው፣ እኔም ስለምወዳቸውና በበሽታ እንዲሰቃዩም ስለማልፈልግ እነርሱን የምትፈውስበትን ኃይል እሰጥሃለሁ።

“ስለዚህ አስቀድመህ ፍቅርን ከዚያም እምነትን መፈለግ አለብህ። ያለ እምነት እኔን ደስ ማሰኘት አትችልም። ይሁንና እምነት ኃይሌን ማወቅ ሳይሆን የፍቅሬን ዕውቀትና የፍቅሬን ኃይል ማወቅ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ እምነት መሆን ያለበት በፍቅር ነው። የበለጠ ለመውደድና በመውደድህ የበለጠ ለመስራትም እምነትን ፈልግ። እምነት የሚሰራው በፍቅር ነውና እምነትን ለመውደድ ስትፈልግ ብቻ ኃይሌን ለመስጠት ልተማመንብህ እችላለሁ።

“ሁሉን ነገር ደግፎ የያዘው ኃይል ቃሌ በመሆኑ ሁሉን ነገር ማድረግ የምትችለው ቃሌ እውነት እንደሆነ አምነህ በተቀበልከው መጠን ነው። እውነት የእኔ ባህርይ በመሆኑ ቃሎቼ እውነት መሆናቸውን ያመኑ ሰዎች እነርሱም በቃላቸው እውነተኛ ይሆናሉ። እኔ በቃሌ ታማኝ በመሆኔ ፍጥረትም በቃሌ ይታመናል። እንደ እኔ የሆኑት ሁሉ ለገዛ ቃሎቻቸው እውነት ሲሆኑ ቃላቸው እርግጠኛ፣ በመስጠታቸውም ታማኞች ናቸው። ነገራቸው ‘አዎን’ ከሆነ ‘አዎን’፣ ‘አይደለም’ ከሆነም ‘አይደለም’ ነው። መሳት ያለው በልብህ ውስጥ በመሆኑ የገዛ ራስህ ቃሎች እውነት ካልሆኑ የእኔን ቃል መጠራጠር ትጀምራለህ። ለገዛ ራስህ ቃል ታማኝ የማትሆነው እኔን በትክክል



ስለማታውቀኝ ነው። እምነትን ለማግኘት ታማኝ መሆን አለብህ። ታማኝነት ባህርዬ በመሆኑና እኔም ታማኝ በመሆኔ የጠራሁህ በእምነት እንድትመላለስ ነው።

“ቃላት ኃይል አላቸው። ስለሆነም ለሚናገሩት ቃል ግድ የሌላቸው ሰዎች የቃሌ ኃይል ሊታመንባቸው የማይችላቸው ናቸው። ለምትናገሬው ቃል ጥንቃቄ ማድረግ ጥበብ ሲሆን እኔ ቃሌን እንደምጠብቅ አንተም የራስህን ቃል ጠብቅ። ግድ የለሽነት ቸልተኝነት በመሆኑ የሚፈረድብህ በግድ የለሽነት ከምትናገራቸው ቃሎች የተነሳ ነው” አለኝ።

ጌታ የተናገረው ይህ ቃል ውስጤን እንደ ታላቅ የባህር ማዕበል አናወጠው። ኢዮብ በአውሎ ነፋስ ፊት ተሰምቶት የነበረውን ዓይነት ስሜትም ተሰማኝ። ለእግዚአብሔር ነገር በጣም ግድ የለሽ መሆን የቻልኩት እንዴት ነበር? ተራራውን ፍዝዝ ብላ እንደምትመለከት ጉንዳን የሆንኩኝ ያህልም ተሰማኝ። ከምድር ትቢያ አነስኩ። ሆኖም ጌታ ግን እኔን ለማናገር ጊዜ እየወሰደ ስለነበር ከዚህ በላይ መቋቋም አልቻልኩምና ፊቴን ዘወር አደረግሁ።

ከጥቂት ቆይታ በኋላም አንድ እጅ ትከሻዬ ላይ ሲያርፍ ተሰማኝ። ይህ እጅ የጥበብ እጅ ነበር። ጥበብ አሁን የተገለጠበት ክብር ታላቅ ሲሆን እርሱ ግን በእኔ መጠን ነበር። ከዚያም ቀጠለና “በዚያን ጊዜ ምን እየተከናወነ እንደሆነ ታውቀሃለን?” ሲል ጠየቀኝ።

ጌታ አንድ ጥያቄ ሲጠይቅ ለማወቅ ብሎ እየጠየቀ እንዳልሆነ አሁን ስለገባኝ ጥያቄውን አውጥቼና አውርጄ አሰላሰልኩ። እውነት እንደ ነበርም አወቅሁ። ከእርሱ ጋር ስተያይ ከምድር ትቢያ የማንስ በመሆኔ ያንን በተወሰነ ምክንያት እንድረዳው ፈልጓል። በልቤ አስበው ለነበረው ሃሳብም እንዲህ ሲል ዝርዝር ማብራሪያ ሰጠኝ።

“በልብህ የምታስበው ሃሳብ እውነት ቢሆንም ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ማስተያየቱ ግን ሚዛናዊ አይሆንም። የቃሌን ኃይል መለማመድ ጀምረሃል። በቃሎቼ መታመን ማለት ዓለማት አንድ ላይ በተያያዙበት ኃይል መታመን ነው። ይህንን ያደረግሁትም ያመንክበትን የእግዚአብሔርን ቃል ኃይልና ከባድነት ታውቀው ዘንድ ልረዳህ እንጂ የታናሽነት ስሜት እንዲሰማህ

አይደለም። በጥረቶችህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ሰው የምትመጣዋ የአንዲቷ ቃል አስፈላጊነት በምድር ላይ ከሚገኘው መዝገብ ሁሉ በላይ የሚበልጥ ዋጋ እንዳላት አስታውስ። የቃሌን ዋጋ ልታውቅና ወንድሞቼም እንዲያከብሩት ልታስተምራቸው ይገባል። እውነትን የሚሸከሙ ሰዎች እውነተኞች መሆን አለባቸውና ቃሌን እንዲሸከሙ እንደተጠሩት ሰዎች አንተም የገዛ ራስህን ቃል ዋጋ ማክበር አለብህ" አለኝ።

ይህንን ስሰማ አጠገባችን ወደነበሩት ዙፋናት ቀና ብዬ ወደ ላይ እንድመለከት የሚያስገድድ አንድ የሆነ ስሜት ተሰማኝ። ወዲያውኑም በምድር ሳለ የማውቀውን አንድ ሰው አየሁ። ይህ ሰው ልጅ እያለሁ የታወቀ ወንጌላዊ የነበረና ከጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ወዲህ ማንም ሰው ባልተገለጠበት መለኮታዊ ኃይል የተመላለሰ ሰው ነበር። ስለዚህ ሰው የተጻፉ ጽሁፎችን አንብቤያለሁ፣ በመቅረጸ ድምጽ የተቀዱ ጥቂት ስብከቶቹንም አዳምጫቸዋለሁ። በእርሱ እውነተኛ ትህትናና ለጌታና ለህዝቡ በነበረው የተገለጠ ፍቅሩ አለመነካት ከባድ ነበር። ይሁን እንጂ ያስተምር የነበረው አንዳንድ ትምህርቶቹ እርስ በርሳቸው የተምታቱ እንደነበሩ ሲሰማኝ ግን ደነገጥኩ። ሆኖም በታላቅ ዙፋን ላይ ተቀምጦ በማየቴ ደግሞ ድንጋጤው ቀለል አለልኝ። ትኩረቴ ሁሉ አሁንም ድረስ ከእርሱ እየተንቆረቆሩ በሚወርዱት ትህትናውና ፍቅሩ ተወሰደ።

ይህንን ሰው ማነጋገር እችል እንደሆነ ጌታን ለመጠየቅ ወደ ጌታ ዘወር ባልኩኝ ጊዜ፣ ጌታ ይህን ሰው ምን ያህል ፍጹም እንደሚወደው ማየት ቻልኩ። ይሁንና ጌታ ግን ጉዞዬን እንድቀጥል ምልክት አሳየኝ እንጂ ይህንን ሰው እንዳነጋግረው አልፈቀደልኝም ።

ጌታም ይህን ለምን እንዳደረገ እንዲህ ሲል አስረዳኝ "እዚህ መሆኑንና በእኔ ዘንድ ያለውን ስፍራ እንድታይ ብቻ ነው የፈለግሁት። ስለ እርሱ ገና ልታውቀው የሚገባህ ብዙ ነገር አለ። እርሱ የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያኔ መልዕክተኛ ነበር። ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያን ግን አንተ ልታውቃቸው ከሚገቡህ ምክንያቶች የተነሳ በጊዜው ልትሰማው አልቻለችም። ስለዚህም ለጊዜው በተስፋ መቁረጥና ግራ መጋባት ውስጥ ወድቆ ስለነበር መልዕክቶቹ የተምታቱ ሆኑ። ስለሆነም ከዚህ በኋላ ግን እነዚህም ሆኑ ሌሎች



የተምታቱ መልዕክቶቹ እንደገና መስተካከል አለባቸው" አለኝ።

በዚህ ቦታ ላይ የሆነው ነገር ሁሉ በሰዓቱ ልማረው የተገባኝ ትምህርት እንዲሆን ስላወቅሁ ይህንን ሰው ማየቴ እስካሁን ስንነጋገርበት ከነበረው ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ማሰብ ጀመርኩ።

ጌታም እንዲህ ሲል መለሰልኝ። "አዎን! በታላቅ ኃይል መመላለስ ትልቅ አደጋ አለው። ይሄ በብዙ መልዕክተኞች ላይ የደረሰ እውነት ሲሆን ለመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያኔ የተሰጡ መልዕክቶች አካልም ነው። አንተ ግን ይህን ታላቅ ኃይል ከተለማመዱት ከእነዚህ መልዕክተኞች በሚበልጥ ኃይሌ መመላለስ አለብህ። ይሁንና ኃይሉ ወይም መልዕክትህ ምንጊዜም የእኔ ማረጋገጫ ፊርማ እንዳለበት አድርገህ ማሰብ ግን የለብህም። እንዲህ ማሰብ ከጀመርክ ግን ለተመሳሳይ ከንቱ ስሜት በርን ትከፍታለህ። መንፈስ ቅዱስ የተሰጠው ስለ እኔ ብቻ እንዲመሰክር ነው። አንተም እንደ ጳውሎስ አስተዋይ ከሆንክ ከብርታቶችህ ይልቅ በድካሞችህ የበለጠ መክበርን ትማራለህ።

"እውነተኛ እምነት የእኔን እውነተኛ ማንነት መገንዘብ ነው። ከዚህ ምንም አይበልጥም፣ አያንስምም። ይሁንና በእኔ ጎልዖት መገኘት ውስጥ ብትኖር፣ እኔንም ብታየኝም ወደ ኋላ ወደ ራስህ ለማየት ፊትህን ከእኔ ላይ የምታነሳ ከሆነ ግን አሁንም ልትወድቅ እንደምትችል ሁልጊዜ ማስታወስ አለብህ። ሉሲፈር የወደቀው ለዚህ ነው። እርሱ በዚህ ክፍል ውስጥ ነበር የሚኖረው። በዚህ የእኔንም ሆነ የአባቴን ክብር አይቷል። ሆኖም ወደ እኔ ከማየት ይልቅ ወደ ራሱ መመልከት በመጀመሩ በተሰጠው ሥልጣንና ስፍራ ይታበይ ጀመር። ይህ እውነት ክብርን ያዩ ዘንድ በተፈቀደላቸውና አመኔታን አግኝተው ኃይል በተሰጣቸው በብዙዎች ባሪያዎቼ ላይ የተከሰተ እውነት ነው። ከአንተ ጥበብ፣ ከአንተ ጽድቅ ወይም ለንፁህ አስተምህሮዎች ካለህ ታማኝነት የተነሳ እንደሆነ አድርገህ ማሰብ ስትጀምር ተሰናክለህ ትወድቃለህ" አለኝ።

ይሄ ከዚህ በፊት ከተቀበልኳቸው ወይም እዚህ ቦታ ላይ ከተነገሩኝ ከምንም ነገር የበለጠ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ እንደሆነ ተረዳሁ። ወደ መጨረሻው ጦርነት ተመልሼ ለመሄድና ለመዋጋት ፈለግሁ። ነገር ግን በየቦታው

የተጠመዱ በሚመስሉ ወጥመዶች ውስጥ ሳይወድቁ ይህንን ማድረግ ይቻል እንደሆነ የሚመለከቱ ከባባድ ጥያቄዎች ስለነበሩኝ ዘወር ብዬ ወደ ጌታ ተመለከትኩ:: ጥበብ ነበር:: ስመለስ እርሱን እንደ ጥበብነቱ ማወቁ በጣም አስፈላጊዬ እንደሆነም አሰብኩ::

*“በራስህ መደገፍን አውልቀህ መጣሉ መልካም ነው:: ይህን እስካላደረግህ ድረስ ሊመጡ ባሉት ኃያላት ልተማመንብህ አልችልም:: በራስህ ላይ ያለህን መደገፍ ይበልጥ አውልቀህ በጣልክ ቁጥርና. . . ካደረግህ ለሚበልጥ ኃይል ልተማመንብህ እችላለሁ”* አለኝ::

ጌታ ንግግሩን ይቀጥላል ብዬ ረዘም ያለ ጊዜ ብጠብቀውም እርሱ ግን ምንም ሳይናገር ቀረ:: በክፍተት የተዋትን ዓረፍተ ነገር እኔ እንደ ምንም እንድሞላው እንደፈለገ ብረዳም ምን መናገር እንዳለብኝ ግን አላወቅሁም ነበር:: ይሁን እንጂ እርሱን ይበልጥ ባየሁት ቁጥር ግን የበለጠ በራስ መተማመን ተሰማኝ:: በመጨረሻም ምን ብዬ እንደምናገር ስላወቅሁ እንዲህ አልኩ::

“እምነቴን በአንተ ላይ ካደረግሁ”::

*“አዎን:: ትሰራው ዘንድ የተጠራህለትን ሥራ ለመስራት እምነት ሊኖርህ ይገባል:: ይሁንና እምነቱ ግን በእኔ መታመን መሆን አለበት:: በራስህ መደገፉን አውልቀህ መጣልህ ብቻውን በቂ ስላይደለ ባዶነትህን በእኔ ላይ ባለህ መታመን ካልሞላኸው የሚወስድህ ወደ ፍራቻና ጥርጣሬ ብቻ ነው:: ብዙዎች የሳቱትና ግራ መጋባት ውስጥ የወደቁት ከዚያ የተነሳ ነው:: እነዚህ የሳቱና ግራ መጋባት ውስጥ የወደቁ ብዙዎቹ ወንዶችና ሴቶች ነቢያት የነበሩ ቢሆኑም፤ አንዳንዶቹ ግን ከፍራቻ የተነሳ ሰዎች ነቢይ ብለው እንዲጠሯቸው የማይፈቅዱ ነበሩ:: ጠላት በትክክል ነቢያት እንዳልነበሩ እንዲያስቡ በማድረግ ሊያስታቸው ከቻለ፤ በራስ መደገፋቸውን በማነሳሳት ከሆኑት በላይ ታላላቅ ነቢያት እንደሆኑ አድርገው እንዲያስቡ በማድረግ ሊያስታቸው ይችላል:: ነቢያት ነበሩ፤ ነገር ግን የውሸት ትህትናም ቢሆን መሳት ነው:: የውሸት ትህትና ጠላት ይጠቀምበት ዘንድ መብት እንዳለው የሚያመለክት ሌላ ዓይነት ራስ ወዳድነት እንጂ ትዕቢትን አውልቆ የጣለ አይደለም::*



*“ውድቀቶችህ በሙሉ የዚህ የአንዱ የራስ ወዳድነት ውጤት ነው የሚሆኑት:: ፍቅር የራሱን የማይፈልግ በመሆኑ ከዚህ ነጻ የሚኮንበት ብቸኛው መንገዱ በፍቅር መመላለስ ነው”* አለኝ::

ስለ እነዚህ ሁሉ ነገሮች እያሰብኩ እያለሁ የሚደንቅ አብርሆት ወደ እኔ ይመጣ ጀመር:: ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻም ሁሉንም ተሞክሮ ማየት በመቻሌም “ለአንተ ያለኝ ቀና ሃሳብና ታማኝነት እንዴት እንዲህ በቀላሉ ተወሰደብኝ” በማለት ትኩረቴን በዚህ አንድና ቀላል መልዕክት ላይ አድርጌ አለቀስሁ::

ከዚያም ጌታ ይህንን ፈጽሜ እንዳልረሳው እንድጸልይ ቆም ብሎ ወደ እኔ እየተመለከተ ፈገግ አለ:: ይህ ዕድል እንዲያልፈኝ አልፈለግሁም:: ነገር ግን እንደዚያ ፈገግ ሲል ምንም ነገር ብጠይቀው እንደሚሰጠኝ ስለተሰማኝ ዕድሉን ተጠቀምኩበት::

“ጌታ ሆይ ‘ብርሃን ይሁን’ ስትል ብርሃን ሆነ:: በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 17 ላይም አብ አንተን እንደሚወድህ እኛም በዚያ ፍቅር እንወድህ ዘንድ ጸልየሃል:: እባክህ አብ አንተን በወደደበት ፍቅር እወድህ ዘንድ ያ ፍቅር አሁን በእኔ ውስጥ ይሆን ዘንድ በል” አልኩት::

አሁንም ፈገግታው አላቋረጠም ነበር:: ከዚያም በላይ እንደ ጓደኛ እጁን ትከሻዬ ላይ ጣል አድርጎ አቀፈኝና *“ያንን ዓለም ሳይፈጠር በፊት ገና ስጠራህ ነግሬህ ነበር:: በመጨረሻው ጦርነት ላይ አብረውህ ለሚዋጉት ወንድሞችህም ነግሬያቸው ነበር:: አባቴ ለእኔ ያለውን ፍቅር ትረዳዋለህ:: ይህ ፍቅር ፍጹምና ፍራቻን በሙሉ አውጥቶ የሚጥል ፍቅር ነው:: ይህ ፍቅር እኔ የሰራሁትን ሥራ መስራት ትችል ዘንድ እንዲያውም አብልጠህ ትሰራ ዘንድ እኔን እንድታምን የሚያስችልህ ነው:: እኔ ከአንተ ጋር በመሆኔ እርሱ ለእኔ ያለውን ፍቅር ትረዳዋለህ፤ እንድትሰራው የሚሰጥህም ሥራ እኔን ያከብረኛል:: አሁን ግን ለአንተ ስል እንደገና እናገራለሁ፤ ‘የአባቴ ፍቅር በአንተም ውስጥ ይሁን’”* አለኝ::

በዚህ ሁሉ ተሞክሮዬ በጣም ተደንቄ ፊቴን ወደ ኋላዬ ወደ ፍርድ ወንበሩ አዙሬ በመመልከት “ፍርዶችህን እወዳቸዋለሁ” ብዬ መናገር ስጀምር ጌታ ንግግሬን አስቆመኝ፡፡

*“ወደ ኋላ አትመልከት፡፡ አሁን እኔ ያለሁት በዚያ ሳይሆን በዚህ ነው፡፡ ከዚህ ክፍል ወደ ጦርነቱ ቦታ እየመራሁ እወስድሃለሁ፡፡ አሁን የፍርድ ወንበሬ የሚገኘው በገዛ ራስህ ልብ ውስጥ ስለሆነ ማየት ያለብህ ልብህን ነው”* አለኝ፡፡

በልቤም “ልክ እንደ ኤደን ገነት፣ እንደ መዳን መዝገቦች. . .” ስል አሰብኩ፡፡

*“አዎን የሕይወት ውሃ የሚወጣው ከልብ ውስጥ ስለሆነ እኔ የማደርገውን ማንኛውንም ነገር የማደርገው በልብህ ውስጥ ነው፣ የምገኘውም በዚያ ነው”* አለኝ፡፡

ከዚያም ጌታ ወደ እኔ ሲቀርብና እኔም ራሴን ስመለከት ባየሁት ነገር ሁሉ ተደነቅሁ፡፡ የጦር ዕቃዎቼ እርሱን የከበበውን ዓይነት ተመሳሳይ ክብር ለብሰው ስመለከት ፈጥኜ የትህትና ካባዬን በማውለቅ በካባው ሸፈንኳቸው፡፡

*“በዚያች ምሽት ተላልፌ ከመሰጠቴ በፊት እናንተ አንድ ትሆኑ ዘንድ፣ ከመጀመሪያ በእርሱ ዘንድ የነበረኝ ክብርም ከህዝቤም ጋር ይሆን ዘንድ ወደ አባቴ ጸልዬ ነበር፡፡ ሰዎችን አንድ የሚያደርጋቸው ክብሬ ሲሆን እኔን የምትወዱ ሁሉ አንድ በምትሆኑ ጊዜ ይህ ክብሬ ጎልቶ ይታያል፡፡ ያንጊዜ ከአብ ተልኬ መምጣቴን ዓለም የበለጠ ያውቀዋል፡፡ አሁን እናንተ ስለምትወዱኝና እርስ በርሳችሁም ስለምትዋደዱ ዓለም የእኔ ደቀ መዛሙርት መሆናችሁን በትክክል ያውቀዋል”* አለኝ፡፡

እርሱን ያለ ማቋረጥ ትኩር ብዬ እያየሁት ሳለሁ በራስ መተማመኔ እየጨመረ መሄዱን ቀጠለ፡፡ በዚህን ጊዜ ውስጤ ታጥቦ የነጻ ያህልና አደርገው ዘንድ የሚጠይቀኝን ማንኛውንም ነገር ቶሎ ለማድረግ ዝግጁ እንደሆንኩ ተሰማኝ፡፡

አብረን እየተራመድን እያለንም *“አሁን ወደ ጦርነቱ ተመልሰህ ከመሄድህ በፊት ልታገኘው የሚገባህ አንድ ሰው አለ”* አለኝ፡፡ እየሄድን እያለንም ከጥቂት



ደቂቃዎች በፊት ከነበረው ክብር የሚበልጥ ክብር እያንጸባረቀ ሲመጣ ስመለከት መደነቅ ሞላኝ፡፡

*“በልቦናህ ዓይኖች ባየኸኝ ጊዜ ሁሉ አዕምሮህ በተወሰነ መጠን የበለጠ ይታደሳል፡፡ አንድ ቀን እኔ በምገኝበት በዚያ ለዘላለም መኖር ትችላለህ፡፡ ያንጊዜ በመንፈሴ የተማርከውን ነገር በሙሉ ወዲያውኑ ታገኘዋለሁ፣ እኔንም ታገኘኛለህ”* አለኝ፡፡

ጌታ የተናገረኝን ነገር ሁሉ መስማትና መረዳት ብችልም በተገለጠው ክብሩ በጣም ስለተማረኩኝ ግን “ጌታ ሆይ! ጥበብን ሆነህ ከተገለጥክልኝ ከመጀመሪያው ጊዜ ይልቅ ለምንድነው ክብርህ እንዲህ በእጅጉ እየጨመረ የሚሄደው?” ብዬ መጠየቅ ስለነበረብኝ ጠየቅሁት፡፡

እርሱም *“የተለወጥከው አንተ እንጂ እኔ በፍጹም ተለውጬ አላውቅም፡፡ ክብሬን ባልተሸፈነ ፊት ስላየህ ተለውጠሃል፡፡ እኔን የበለጠ በግልጽ ማየት ትችል ዘንድ ተለማምደሃቸው የነበሩት ተሞክሮዎች መጋረጃዎቹን ከፊትህ ላይ እያነሱልህ ነው፡፡ ይሁንና ፍቅሬን በምታይ ጊዜ ግን መጋረጃዎቹን ምንም ነገር አያስወግዳቸውም”* አለኝ፡፡

ከዚያም እርሱ ቆም ሲል ከእኛ ቀጥለው ወዳሉትና በዙፋን ላይ ወደ ተቀመጡት ለማየት ዘወር አልኩ፡፡ አሁን ያለነው እጅግ ታላላቆቹ ነገሥታት በተቀመጡበት ቦታ ስለነበር አጠገቤ የነበረውን ሰው ማንነት አወቅሁት፡፡

ከዚያም ይህንን ሰው “ጌታው! የት እንዳየሁህ ቦታውን ማስታወስ አልቻልኩም እንጂ የሆነ ቦታ አውቅሃለሁ” አልኩት፡፡

እርሱም “አንድ ወቅት ላይ በራዕይ አይተኸኛል” ሲል መለሰልኝ፡፡

እኔም ይህን ሲለኝ ወዲያውኑ አይቼ የነበረው ራዕዩ ትዝ አለኝና ደነገጥሁ፡፡ “እውነት ሰው ነበርክ ማለት ነው?” ስል ጠየቅሁት፡፡

“አዎን!” አለኝ፡፡

ከዚያም በክርስትና ሕይወቴ ገና ልጅ በነበርኩበት ጊዜ ላይ በሕይወቴ አጋጥመውኝ ከነበሩ አንዳንድ ጉዳዮች የተነሳ ተስፋ ቆርጬ የነበረበትን ወቅት ማስታወስ ጀመርኩ። በወቅቱ መኖሪያ ቤታችን አጠገብ ወደሚገኘው መናፈሻ ቦታ ሄጄ ጌታ እስከሚናገረኝ ድረስ በዚያ ለመቆየት ወሰንኩ። በዚያ መጽሐፍ ቅዱሴን እያነበብኩ እያለሁ ከዚህ በፊት አይቼ ከማላውቃቸው ራዕዮች አንዱን ተቀበልኩኝ።

በዚህ ራዕይ ውስጥ ጌታን በታላቅ ቅንዓት ያገለግል የነበረ አንድን ሰው አየሁ። ይህ ሰው ያለ መታከት ለሰዎች ስለ ጌታ ይመሰክር፣ ያስተምርና ለታመሙ ሰዎችም በየቤታቸው እየሄደ ይጸልይላቸው ነበር። ይህ ሰው ለጌታ በጣም ቀናዒና ለሰዎችም እውነተኛ ፍቅር የነበረው ሰው ነበር። ከዚያ በመቀጠል ደግሞ ሌላ አንድ በጣም የተጎሳቆለ በረንዳ አዳሪ ሰው አየሁ። ይህ ሰው ደግሞ አንዲት ትንሽ የድመት ግልገል መሃል መኪና መንገድ ላይ አግኝቶ በኃይል ሲመታት፤ ነገር ግን በሰራው በዚህ ስህተቱ ወዲያውኑ በመጸጸት የድመቲቱ ግልገል አደጋ እንዳይደርስባት በማሰብ ፈጥኖ ከመሃል መንገዱ በማውጣት ከመንገዱ ዳር አውጥቶ አስቀመጣት። ከዚያም ጌታ ከእነዚህ ሁለት ሰዎች በየትኛው ይበልጥ ደስ እንደሚለኝ ጠየቀኝ።

እኔም ያለ ምንም ማንገራገር "በመጀመሪያው ሰውዬ" አልኩት።

ጌታ ግን *"አይደለም በሁለተኛው ነው"* አለኝና የሰዎቹን ታሪክ እንዲህ ሲል ይነግረኝ ጀመር።

"የመጀመሪያው ሰው ያደገው እኔን በሚያውቁ መልካም ቤተሰቦችና በአንዲት እያደገች በምትሄድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነበር። ከዚህም በላይ እጅግ ተመራጭ በሚባል የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ገብቶ የተማረም ነበር። ይህ ሰው ግን የፍቅሬን አንድ መቶ ፐርሰንት እጅ ብሰጠውም እርሱ የተጠቀመው ግን ሰባ አምስቱን እጅ ብቻ ነው።

"ሁለተኛው ሰው ግን ደንቆሮ ሆኖ የተወለደ፣ የሚኖርባት ከተማ ባለሥልጣናት ገና ከህጻንነቱ ጀምሮ ስምንት ዓመት እስኪሞላው ድረስ ሜዳ ላይ ተጥሎ እስካገኙት ጊዜ ድረስ ከመንገድ ጥግ ላይ በሚገኝ ታዛ ስር በብርድ ውስጥ በጉስቁልናና በጨለማ ውስጥ ይኖረ የነበረ ሰው ነበር። ይህ ሰው



የጉስቁልና ኑሮ ከማይለያቸው ከአንድ የወጣቶች ማሳደጊያ ተቋም ወደ ሌላው ሲዘዋወር ቆይቶ መጨረሻ ላይ ጎዳና ተዳዳሪ ሆነ። ይህ ሰው እነዚህን ሁሉ ጉስቁልናዎቹን እንዲያሸንፍበት ጌታ የፍቅሩን ሦስቱን እጅ ያህል ብቻ ነበር የሰጠው። ይሁን እንጂ እርሱ ግን ልቡ ውስጥ ከነበረው ቁጣ ጋር በቁርጠኝነት በመዋጋት በግልገል ድመቷ ላይ ጉዳት ላለማድረስ ሲል እያንዳንዷን እጅ ተጠቅሞባታል" አለኝ።

በዚህ ጊዜ ከሰሎሞን እጅግ የሚበልጥ ክብር ባለው ዙፋን ላይ ወደ ተቀመጠው ወደዚያ ሰው ተመለከትኩ። የመላዕክቱ ሠራዊትም እርሱ የሚሰጣቸውን ትዕዛዝ ተግባራዊ ለማድረግ በተጠንቀቅ ተዘጋጅተው ነበር የሚጠብቁት። ይህን በማየቴ ደንቆኝ፤ ወደ ጌታ ዞወር አልኩ። ይህ ሰው ከብዙ ታላላቅ ነገሥታት ከሚያንሱ አንዱ ስለመሆኑ አሁንም ድረስ ማመን አልቻልኩም ነበር።

ይህን ጊዜ "ጌታ ሆይ እባክህ የዚህን ሰው ቀሪ ታሪክ ንገረኝ" ስል ጌታን ለመንኩት። እርሱም ወደ ላይ ቀና ብዬ አንጄሉን እንድመለከት ምልክት አሳየኝ። ለማየት ፊቴን ሳዞር አንጄሎ የዙፋኑን ደረጃዎች ወርዶ ፊቴ መጥቶ ቆመ። ከዚያም እጆቹን ዘርግቶ አቀፈኝና እንደ አባት ግንባሬን ሳመኝ። በዚህን ጊዜ ፍቅር በላዬ ሲፈስና በደም ህዋሳቶቼም ውስጥ ከመጠን ያለፈ ጫና ሲሰማኝ ታወቀኝ። በመጨረሻም ሲለቀኝ ልክ መጠጥ ጠጥቶ እንደ ሰከረ ሰው መንገዳገድ ጀመርኩ። ተሰምቶኝ የነበረው ይህ ልዩ የፍቅር ስሜት አስደናቂ ሲሆን ከዚህ በፊት ተሰምቶኝ የማላውቀው ነበር።

ጌታም *"አንጄሎ ለህዝቤ የሚሰጠው ብዙ ፍቅር የነበረው ሰው ነው። በምድር ላይ ሳለህ ይህን ፍቅር ሊያካፍልህ ይችል ነበር። ይሁንና ማንም ግን እርሱን ሊጠጉት አልወደዱም። ነቢያቶቼ እንኳን ይሸሹት ነበር። አንጄሎ በእምነት ያደገው አንድ መጽሐፍ ቅዱስና ሌሎች ሁለት መጻህፍትን ገዝቶ እነዚያን ደጋግሞ በማንበብ ነበር። ወደ ተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ለመሄድም ሞክሮ ነበር። ሆኖም በፍቅር የሚቀበለውን አንድ ስንኳ ሊያገኝ ግን አልቻለም። በራቸውን በእርሱ አማካይነት ባንኳኳም እነርሱ ግን አልተቀበሉትም። እርሱን ተቀብለውት ቢሆን ኖሮ እኔንም በተቀበሉኝ ነበር"* አለኝ።

በዚህ ጊዜ አዲስ ዓይነት የሃዘን ትርጉም እየተማርኩ ነበር። አንጄሎ ሰማዕት ሆኖ እንደ ሞተ በማሰብና ለዚህም ከፊል ኃላፊነት እንዳለብኝ በመጠበቅ "እንዴት ነበር አሟሟቱ?" ስል ጌታን ጠየቅሁት።

ጌታም *"ሕይወቱ ያለፈው በብርድ ውስጥ መንገድ ሲሻገር የነበረን አንድን ሰካራም ሽማግሌ በበረዶው ቅዝቃዜ እንዳይሞት በሕይወት ለማቆየት ሲል በከፈለው ዋጋ እርሱ ራሱ በበረዶ ቅዝቃዜው በድን ሆኖ ደርቆ ነው"* አለኝ።

አንጄሎን ሳየው ልቤ ምን ያህል ደንዳና እንደነበር ማመን ተሳነኝ። ሰማዕት ስለሚለው ቃል አስብ የነበረው ስለ ምስክርነታቸው ቃል ባለማመቻመቻቸው ለተገደሉ ሰዎች የሚሰጥ ስያሜ እንደሆነ አድርጌ ስለነበር እርሱን ሰማዕት ያሰኘው ምን እንደሆነ አልገባኝም ነበር።

"ጌታ ሆይ! አንጄሎ በዚህ መሆን የተገባው በትክክል ድል ነሺ ሕይወትን በመኖሩ መሆኑን አውቃለሁ። ይሁንና በዚያ ዓይነት መንገድ የሞቱ ሰዎች ሁሉ ግን ሰማዕት ተደርገው ይታያሉን?" ስል አስተያየት መሰል ጥያቄዬን ሰነዘርኩ።

ጌታም *"አንጄሎ በዕድሜ ዘመኑ ሁሉ በየዕለቱ ሰማዕት ሆኖ ያለፈ ሰው ነው። ለራሱም በሕይወት ለመኖር ለሚያስፈልገው ነገር ብቻ ነበር የሚሰራው። የተቸገረ ባልንጀራውን ለማዳን ሲልም ደስ እያለው መስዋዕትነትን ይከፍል ነበር። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ አማኞች 'ሥጋችሁን ለእሳት መቃጠል አሳልፌ ብሰጥ፣ ፍቅር ግን ከሌላችሁ ምንም አይጠቅማችሁም' ብሎ እንደ ጻፈላቸው ራሳችሁን በፍቅር ብትሰጡ ብዙ ይጠቅማችኋል። ጳውሎስ በምድር ይኖር በነበረበት ወቅት ሁልጊዜ ራሱን ከቅዱሳን ሁሉ የሚያንስ አድርጎ ቢቆጥርም እርሱ ግን ከታላላቆቹ አንዱ ነበር። ቀደም ሲል እንደ ተማርከው ራሳቸውን ታላቅ አድርገው የሚቆጥሩ፣ በሌሎች ሰዎችም ዘንድ ታላቅ ተደርገው የሚቆጠሩ ብዙዎች ፍጻሜያቸው ታናሽ መሆን ነው። አንጄሎ የሞተው ስለ ሃይማኖቱ ወይም ከምስክርነቱ ቃል የተነሳ እንኳን አይደለም። እርሱ የሞተው ለእኔ ነው"* አለኝ።



እኔም "ጌታ ሆይ! ተመልሼ ወደ ምድር በምሄድበት ጊዜ በዚህ ያየሁትን ይህን ሁሉ ነገር እንዳልረሳው እባክህ እርዳኝ" ስል ለመንኩት።

*"እዚህ ከአንተ ጋር ያለሁትና ተመልሰህ በምትሄድበትም ጊዜ በዚያ ከአንተ ጋር የምሆነው እኮ ለዚያ ነው። ፊትን አይቶ አለመፍረድና ነገሮችን እኔ በማይበት ዓይን ማየት ጥበብ ነው። ባየኸው ራዕይ ውስጥ መንገድ ላይ በአጠገቡ ስታልፍ ታውቀው ዘንድ አንጄሎን አሳይቼህ ነበር። በዚህ ራዕይ ውስጥ አሳይቼህ የነበረውን ያለፈ ህይወቱን ከእርሱ ጋር ተካፍለኸው ቢሆን ኖሮ ያኔ ህይወቱን ለእኔ ይሰጥ ነበር። አንተም ይህንን ታላቅ ንጉሥ ደቀ መዝሙር ማድረግ በቻልህና እርሱም በቤተ ክርስቲያኔ ላይ ትላቅ ተጽዕኖውን ባሳደረ ነበር። ህዝቤ ሌሎችን እኔ በማይበት ዓይን ቢመለከት፣ አንጄሎና እንደ እርሱ ያሉ ሌሎች ብዙዎች በታወቁ ነበር። የበለጠ ብዙ ፍሬዎችን ማፍራት ትችሉ ዘንድም ሰዎችን እንዴት እንደምትወዱ እንዲሁም የሰጠኋችሁን ስጦታዎችንም እንዴት ሥራ ላይ እንደምታውሉት ባስተማራችሁም ነበር። ህዝቤም እግሮቼ ስር ተቀመጠው ለመማር ከምድር ዳርቻ ሁሉ በመጣና በታላላቅ መድረኮችና ምስባኮችም ላይ ቆመው ህይወትን ሲሰብክ በታየ ነበር"* አለኝ።

ይህንን ስሰማ ጌታን ማየት እስከማልፈልግ ድረስ በጣም ሃፍረት ተሰማኝ። ይሁንና ስቃዩ እንደገና ወደ ራስ ወዳድነት ሊወስደኝ እንደሆነ በተሰማኝ ጊዜ ግን በመጨረሻ ወደ እርሱ ተመለከትኩ። እርሱን ባየሁት ጊዜም ዓይኔ ከክብሩ ነፀብራቅ የተነሳ ሊታወር ምንም አልቀረው ነበር። ጥቂት ጊዜ ቢወስድብኝም ዓይኖቼ ቀስ በቀስ እንደ ቀድሞአቸው እርሱን ማየት ጀመሩ።

*"ይቅር እንደ ተባልክ አትርሳ። እነዚህን ነገሮች የማሳይህ ልኮንንህ ሳይሆን ላስተምርህ ነው። ርህራሄ ከምንም ነገር ይልቅ መጋረጃዎችን ፈጥኖ ከነፍስህ ላይ እንደሚያስወግድልህ ምንጊዜም አትርሳ"* አለኝ።

እንደገና መጓዝ ስንጀምርም አንጄሎ "አንድ ሰው ወደ ጓደኞቹ ሄዶ ስለ አዳኛችን ቢመሰክርላቸው ብዙዎቹ አዳኛችንን ይወዱታልና እባክህ ጓደኞቹን እንዳትረሳቸው" አለኝ።

የተናገራቸው ቃሎች ስሜቴ መልስ ለመስጠት እስኪነካ ድረስ በውስጣቸው ኃይልን የተሞሉ ስለነበሩ ራሴን በእሽታ ነቀነቅሁ። ያ ቃል የታላቅ ንጉሥና የነገሥታቱም ንጉሥ ታላቅ ወዳጅ ከሆነ ሰው የታወጀ አዋጅ እንደሆነ አወቅሁ። በዚህ ጊዜ "ጌታ ሆይ በረንዳ አዳሪዎችን እንድረዳቸው ትረዳኛለህን?" ስል ጠየቅሁት።

*ጌታም "እነርሱን የሚረዳውን ሰው ሁሉ እረዳዋለሁ። ምንጊዜም ቢሆን እኔ የምወዳቸውን ስትወዳቸው ርዳታዬን ታውቀዋለህ። ባላቸው ፍቅር መጠንም ረዳት ይሰጣቸዋል። ቅባቴን አብዝቼ እንድሰጥህ ብዙጊዜ ጠይቀኸኛል የምትቀበለው እንደዚያ ነው። የምወዳቸውን ውደዳቸው፣ እነርሱን ስትወዳቸው እኔን ትወደኛለህ። ለእነርሱ ስትሰጥ ለእኔ ትሰጣለህ፤ እኔም መልሼ አብዝቼ እሰጥሃለሁ"* አለኝ።

በዚህ ጊዜ ሃሳቤ በምድር ላይ አለኝ ወደምለው ወደምወደው ቤቴና ሃብቴ ተወሰደ። በእርግጥ ባለጠጋ አልነበርኩም። ሆኖም በምድራዊ መለኪያ ስታይ ግን ከአንድ ምዕተ ዓመት በፊት በዚህ ምድር ላይ ይኖሩ የነበሩ ነገሥታት ይኖሩት ከነበረው ኑሮ በብዙ የሚሻል ሕይወት እንደምኖር ግን አውቃለሁ። በዚህ የምኖት ኑሮዬ ዙሪያ ከዚህ በፊት የበደለኝነት ስሜት በፍጹም ተሰምቶኝ አያውቅም ነበር። አሁን ግን ተሰማኝ። ስሜቱ ጥሩ ቢሆንም ትክክለኛ ስሜት ግን አይደለም። በዚህ ጊዜ ጌታ እንደሚረዳኝ ሳውቅ እንደገና መልሼ ወደ እርሱ ተመለከትኩ።

*"ፍጹም የሆነው የፍቅር ሕጌ ብርሃንንና ጨለማን እንዴት እንደሚለይ የተናገርኩትን አስታውስ። አሁን እየተሰማህ ያለው ዓይነት ግራ የመጋባት ስሜት ሲሰማህ፤ እየተለማመድከው ያለኸው ነገር ፍጹም የሆነው የፍቅር ሕጌ እንዳልሆነ እወቅ። ልክ አንተ የአንተን እንደምትሰጥ፤ እኔም የአባቴን መልካም ስጦታዎች ስሰጥህ ደስ ይለኛል። እነዚህን ስጦታዎች ደስ እንድትሰኝባቸውና እንድታደንቃቸው እፈልጋለሁ። ለሌሎች እንድታካፍል ስጠራህ በነጻ ማካፈል እንጂ እነርሱን ብቻ ማምለክ የለብህም"። በምድር ላይ ያለውን ድህነት በሙሉ እጄን በማንቀሳቀስ ከመቅጽበት ማጥፋት እችላለሁ። ሆኖም ተራሮችና ከፍታዎች ደልዳላ ሜዳ ሲሆኑ፣ ድሆችና የተጨቆኑ ሰዎች አንገታቸውን ቀና አድርገው ሲሄዱ ያንጊዜ የመታሰብ ቀን ይሆናል። ያንን ደግሞ ማድረግ*



*አለብኝ። ለእኔ ሰብዓዊ ርህራሄ የሰብዓዊ ጭቆና ተጻራሪ ነው። ሰብዓዊ ርህራሄ የመስቀሌ ኃይል ምትክ ሆኖ ጥቅም ላይ ውሏል። አንዳንድ ጊዜ እኔን ለመታዘዝ መስዋዕት ማቅረብ ቢኖርባችሁም እንድትታዘዙኝ እንጂ መስዋዕት እንድታቀርቡልኝ አልጠራኋችሁም። መስዋዕታችሁን ባለመታዘዝ የምታቀርቡ ከሆነ እኔና እናንተ እንለያያለን።*

*"ይህ ታላቅ ንጉሥ በምድር ላይ የእኔ አገልጋይ ሆኖ ሳለ እርሱን ዝቅ አድርገህ በማየትህና የማይረባ ሰው አድርገህ በመቁጠርህም በደል ተገኝቶብሃል። ከዚህ በኋላ ከእኔ ሳታረጋግጥ በማንም ሰው ላይ እንዳትፈርድ። አንተ ለእኔ ነገር ንቁ ስላልነበርክ ለአንተ ያዘጋጀኋቸውንና ከምትገምተው በላይ የሆኑ ብዙ ዕድሎችን ሳታገኛቸው ቀርተሃል። ይህንን የማሳይህ እነዚህን ዕድሎች እንዳታጣቸው ወደ ንስሃ ለማምጣት እንጂ የበደለኝነት ስሜት እንዲሰማህ አይደለም። የበደለኝነት አጻፋዊ ርምጃ የምትወስድ ከሆነ ግን በደልህን ለማካካስ ስትል ለመስቀሌ ውርደት የሚሆኑ ነገሮችን ማድረግ ትጀምራለህ። መስቀሌ ብቻውን የአንተን በደል ማስወገድ ይችላል። እኔ ወደ መስቀሌ ሞት የሄድኩት የአንተን በደል ለማስወገድ በመሆኑ ምንም ዓይነት በበደል የተሰራ ነገር ያ ለእኔ የተሰራ አይደለም"* አለኝ።

ጥበብ ንግግሩን እንዲህ ሲልም ቀጠለ። *"ሰዎች በመከራ ሲጨነቁ ማየት ደስ አይለኝም። ይሁንና ሰብዓዊ ርህራሄም ቢሆን ሰዎችን ካሉበት ጭንቀት ሊያወጣቸው ወደሚችለው ወደ ብቸኛው መፍትሄ ወደ መስቀሉ አያመጣቸውም። ሆኖም በርህራሄ ባለመመላለስህ ምክንያት ግን አንጀሉን ሳታገኘው ቀርተሃል። ተመልሰህ ስትሄድ ግን እንደ አንጀሉ ያሉትን ብዙ ሰዎችን ታገኛለህና ርህራሄህ አሁንም ለመንፈሴ ተገዢ ሊሆን ይገባል። ሆኖም እኔ የምሰራው አባቴ ሲሰራ ያየሁትን ብቻ በመሆኑ የራራሁላቸውን ሰዎች ሁሉ ከበሽታቸው አልፈወስኳቸውም። ስለዚህ ነገሮችን ለመንፈሴ በመታዘዝ ስሩ እንጂ ከርህራሄ ተነስታችሁ መስራት የለባችሁም። ርህራሄያችሁ ሰውን የመቤዠት ኃይል የሚኖረው ያንጊዜ ብቻ ነው።*

*"የመንፈሴን ስጦታዎች የሰጠሁህ ስለተማመንኩብህ ነው። በስበካቸው ስብከቶችና በጻፍካቸው መጽሐፎችህ ቃላቴን አውቀኸዋል። ይሁንና ያወቅኸው ግን ጥቂቱን ነው። በእውነቱ ብዙጊዜ ባይሆንም እኔ በሚገርም ዓይነ*

*ዓይተሃል፣ በምሰማበት ጆሮ አድምጠሃል ወይም በማስተውልበት ልብ አስተውለሃል:: ያለ እኔ ለመንግስቴ የሚጠቅም ወይም ወንጌሉን የሚያስፋፋ ምንም ነገር ልታደርግ አትችልም:: የእኔን ጦርነት በመዋጋትህ የተራራዬን ጫፍ እንኳን አይተኸዋል:: የእውነት ፍላጻዎች እንዴት እንደሚወረወሩና ጠላትን እንደሚመቱም ተምረሃል:: በመጠኑም ቢሆን ሰይፌንም እንዴት አድርገህ መጠቀም እንዳለብህ ተምረሃል:: ይሁንና እጅግ ትልቁ መሳሪያዬ ግን ፍቅር ነው:: ፍቅር ለዘወትር ስለማይወድቅ የዲያቢሎስን ሥራ የሚያፈርስ ኃይል ይሆናል:: መንግስቴን የሚያመጣው ፍቅር ሲሆን ፍቅር የሠራዊቴ መለያ ዓርማም በመሆኑ አሁን በዚህ ዓርማ ስር መዋጋት አለብህ" አለኝ::*

እንዲህ እያለኝም ከታላቁ የፍርድ አዳራሽ ሳንመለስ ወጣንና አንድ መተላለፊያ ኮሪደር ላይ ደረስን:: የጥበብ ክብር ዙሪያዬን ከብቦኝ ስለነበር እርሱን በግልጽ ላየው አልቻልኩም:: ከዚያም ድንገት አንድ በር ደጃፍ ላይ ደረስኩ:: እስካሁን ድረስ የነበርኩበትን ይህንን ቦታ ጥዬ መሄድን ባልፈልግም ተመልሼ ስመጣ ግን ትቼው መሄድ ያለብኝ መሆኔን ወዲያውኑ ተረዳሁኝ:: ይህ በር ጥበብ እየመራኝ ያስገባኝ በር ሲሆን በሩን ማለፍ ነበረብኝና በውስጡ አልፌ ወጣሁ::

*ይቀጥላል. . . .*

መፈለግንም፣ ማድረግንም በሰው ልብ ውስጥ የሚያስቀምጥ ልዑል አምላክ ለዘላለም የተባረከ ይሁን!

# የመጨረሻው ትንቅንቅ



ሐዋርያው ጳውሎስም እንዲህ አለኝ “ዛሬ በዓለም ላይ ታላላቅ የወንጌል ስደት ወይም መከራ ካለባቸው ጥቂት ቦታዎች በቀር እየተሰበከ ያለውን የወንጌል መልዕክትና እየተሰጠ ያለውን አገልግሎት አንዱንም ማወቅ የሚቻል አይደለም። ስለዚህም ነው የዚህ ዘመኗ ቤተ ክርስቲያን በእኛ ዘመን ከነበረችው እንኳን ይልቅ ጣዕረ ሞት የመሰለችው። እንድንሆን የተጠራንለትን ጥሪ ሁሉ ከመሆን ርቀን ነበር። ስናገለግል አንድ ሰው ሊከፍለው የሚችለው እጅግ ከፍተኛው መስዋትነት በአገልግሎት ውስጥ መሆን ነበር። ይሄ ደግሞ ዋጋ የተከፈለለትን እጅግ የላቀ መስዋትነት ያም የመስቀሉን መልዕክት ያንጸባረቀ ነበር።

“መስቀል የእግዚአብሔር ኃይል፣ እንኖርበት ዘንድ የተጠራንለት ሕይወት ማዕከልም ነው። ዛሬ መስቀሉን ስለማትሰብኩና ስለ መስቀሉ ስለማትኖሩ የደቀ መዛሙርትን ልብና አዕምሮ ለመለወጥ ያላችሁ ኃይል በጣም ደካማ ሆኗል። ከዚህ የተነሳ በደቀ መዛሙርትና በአህዛብ መካከል ብዙ የሕይወት ልዩነት ለማየት ተቸግረናል። ስለዚህ በአደራ የተሰጠን ወንጌል ይህ ባለመሆኑ ወደ መስቀሉ መመለስ አለብህ” አለኝ።

*ከመጽሐፉ የውስጥ ክፍል የተቀነጨበ*

**ዋጋው ብር 30.00**

ሕትመት ፋር-ኢስት ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማህ